# የሉቃስ ወንጌል

*አስተዋፅኦ*

I. የሉቃስ ወንጌል መቅድም (1፥1-4)
II. የአዳኙ መምጣት (1፥5—2፥52)
  (ሀ) የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ አስቀድሞ መነገሩ (1፥5-25)
  (ለ) ኢየሱስ እንደሚወለድ አስቀድሞ መነገሩ (1፥26-56)
  (ሐ) የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ (1፥57-80)
  (መ) የኢየሱስ መወለድ (2፥1-20)
  (ሠ) ኢየሱስ በሕፃንነቱ በቤተ መቅደስ መገኘቱ (2፥21-39)
  (ረ) ኢየሱስ ብላቴና እያለ ቤተ መቅደሱን መጐብኘቱ (2፥40-52)
III. ለኢየሱስ አገልግሎት መንገድ ማዘጋጀት (3፥1—4፥13)
  (ሀ) የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት (3፥1-20)
  (ለ) የኢየሱስ መጠመቅ (3፥21-22)
  (ሐ) የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ (3፥23-38)
  (መ) የኢየሱስ መፈተን (4፥1-13)
IV. የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ (4፥14—9፥50)
  (ሀ) ኢየሱስ አገልግሎት መጀመሩ፣ በናዝሬት ተቀባይነት ማጣቱ (4፥14-30)
  (ለ) ቅፍርናሆም፤ የኢየሱስ መለኮታዊ ሥልጣን መገለጡ (4፥31-44)
  (ሐ) ታምራዊ በሆነ መንገድ ዓሣ ማጥመድ (5፥1-11)
  (መ) የለምጻሙ ሰው መፈወስ (5፥12-16)
  (ሠ) በኢየሱስ ሥልጣን ላይ ጥያቄ መቅረቡ (5፥17-26)
  (ረ) ኀጢአተኞችን ወደ ንስሓ የሚመልሰው አዳኝ (5፥27-32)
  (ሰ) አዲስ ሥርዐትን ማስተዋወቅ (5፥33—6፥49)
  (ሸ) መለኮታዊ ኀይል መገለጡ (7፥1—8፥56)
  (ቀ) ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ኀይልን መስጠቱ (9፥1-6)
  (በ) ሄሮድስና መጥምቁ ዮሐንስ (9፥7-9)
  (ተ) አምስት ሺህ ሰዎችን መመገብ (9፥10-17)
  (ቸ) የጴጥሮስ ምስክርነትና የኢየሱስ መልስ (9፥18-27)
  (ኀ) የአዳኙ ክብር መገለጥ (9፥28-50)
V. ወደ ኢየሩሳሌም የመጨረሻ ጉዞ በሚደረግበት ጊዜ ኢየሱስ ያከናወነው አገልግሎት (9፥51—19፥28)
  (ሀ) የአዳኙ ቤዛ የመሆን ተልእኮ (9፥51—10፥37)
  (ለ) ኢየሱስ አገልግሎትንና ጸሎትን በሚመለከት ያስተማረው አስፈላጊ ትምህርት (10፥38—11፥13)
  (ሐ) ኢየሱስ ለተቃዋሚዎቹም ሆነ ለተከታዮቹ የሰጠው ማስጠንቀቂያ (11፥14—14፥35)
  (መ) ጠፍቶ የተገኘ ነገር ምሳሌ (15፥1-32)
  (ሠ) ኢየሱስ ለተከታዮቹ የሰጠው ትእዛዝ (16፥1—17፥10)
  (ረ) ከለምጽ የነጹት ዘጠኝ ሰዎች ምስጋናን ያለማቅረባቸው (17፥11-19)
  (ሰ) የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በድንገት እንደሚሆን ትንቢት መነገሩ (17፥20—18፥14)
  (ሸ) አዳኙ፣ ሕፃናትና ሀብታሙ የአይሁድ አለቃ (18፥15-30)
  (ቀ) ወደ ጉዞው መጨረሻ መዳረስ (18፥31—19፥28)
VI. የሕማማት ሳምንት (19፥29—23፥56)
  (ሀ) ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ (19፥29-48)
  (ለ) ኢየሱስ በየዕለቱ በቤተ መቅደስ ማስተማሩ (20፥1—21፥4)
  (ሐ) ኢየሱስ ቤተ መቅደሱ እንደሚጠፋና እርሱም ዳግመኛ እንደሚመጣ አስቀድሞ ተናገረ (21፥5-38)

(መ) የመጨረሻ ዝግጅትና የመጨረሻው እራት (22፥1-38)
(ሠ) ኢየሱስ በጌቴሴማኒ፣ እርሱም በዚያ አልፎ መሰጠቱ (22፥39-53)
(ረ) ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ለፍርድ መቅረቡ (22፥54-71)
(ሰ) በሮማውያን ፊት ለፍርድ መቅረቡ (23፥1-25)
(ሸ) የኢየሱስ መሰቀል (23፥26-49)
(ቀ) የኢየሱስ መቀበር (23፥50-56)

VII. ከትንሣኤ እስከ ዕርገት (24፥1-53)
(ሀ) የትንሣኤው ዕለት ማለዳ (24፥1-12)
(ለ) ከሞት የተነሣው ጌታ መታየቱ (24፥13-43)
(ሐ) ኢየሱስ በመሰነባበቻ ንግግሩ ላይ የሰጠው ትእዛዝ (24፥44-53)

**ጸሐፊው፤** *ሉቃስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *መለኮትም ሰውም የሆነው አዳኙ ኢየሱስ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *60—63 ዓ.ም.*

### ታሪካዊ ዳራ

የሉቃስ ወንጌል ቴዎፍሎስ ለተባለ ሰው ከተጻፉት ሁለት መጻሕፍት የመጀመሪያው ነው (1፥3፤ ሐሥ 1፥1)። በሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ ጸሐፊው በስም ባይጠቀስም፣ የጥንቱ ክርስትና በአንድ ድምፅ የሚሰጠው ምስክርነትና በሁለቱ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ተጨባጭ ውስጣዊ ማስረጃዎች ጸሐፊው ሉቃስ እንደሆነ ያመለክታሉ።

ሉቃስ ከአሕዛብ ወገን በጌታ ያመነ ክርስቲያን እንደ ሆነ ግልጽ ሲሆን፣ ብቸኛ አይሁዳዊ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊ ነው። ክርስትና እንዴት እንደተጀመረ ማወቅ ለምትፈልግ ከአይሁድ ወገን ያልሆኑ መዕመናን ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ታሪኩን በሚገባ ለመግለጽ ቴዎፍሎስ (የስሙ ትርጒም "እግዚአብሔርን የሚወድ") ለሚባል ሰው ይጽፍ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ሉቃስን አነሣሣው። ይህም ሁለት ክፍል አለው፤ (1) የመጀመሪያው የኢየሱስን ልደት፣ ዕድገት፣ አገልግሎት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት የሚገልጸው የሉቃስ ወንጌል ነው፤ (2) ሁለተኛው መንፈስ ቅዱስ በኢየሩሳሌም እንደወረደና ከዚያም ቀጥሎ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተች የሚገልጸው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ከአንድ አራተኛ በላይ የሚሆነውን የአዲስ ኪዳን ክፍል ይይዛሉ። ሉቃስ የተወደደ ሐኪም (ቈላ 4፥14) ወንድምና ከጳውሎስ ጋር በታማኝነት አብሮ የሚያገለግል እንደነበረ ከጳውሎስ መልእክቶች እንረዳለን (2ጢሞ 4፥11 እና ፊሞ 1፥24 ይመ፤ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ "እኛ" በሚል ከቀረበው ጽሑፍ ጋር ያነጻጽሩ፤ የሐሥ መግቢያ ይመ)። ከራሱ ጽሑፍ እንደምንረዳው ሉቃስ በሚገባ የተማረ፣ ጥሩ የሥነ ጽሑፍ ችሎታ ያለው፣ ታሪክን ጠንቅቆ የሚያውቅና በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የሥነ መለኮት ምሑር ነበር። ሉቃስ ወንጌሉን በጻፈበት ጊዜ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች በሚያመልኩባት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ወንጌል በተሟላ መልኩ ወይም በስፋት እንዳልተሠራጨ ግልጽ ነበር። ማቴዎስ በመጀመሪያ የጻፈው ለአይሁድ ነበር፤ ማርቆስ ደግሞ በሮም ላለችው ቤተ ክርስቲያን እጥር ምጥን ያለ ወንጌል ጽፎአል። የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ አሕዛብ ከዐይን ምስክሮች በቃል የሚነገር እንደዚሁም አጠር ባለ ጽሑፋዊ መግለጫ መልክ የተዘጋጀ የኢየሱስ ታሪክ ቢውቁም የተሟላና በሥርዐት የተጻፈ ወንጌል አልነበራቸውም (1፥1-4 ይመ)። ስለዚህ ጳውሎስ በቂሣሪያ ታስሮ እያለ (ሐሥ 21፥17፤ 23፥23—26፥32) ምናልባት ሉቃስ በፓለስቲና ጥናት በማድረግ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያውን እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄ እየመረመረ በጳውሎስ እስር ማብቂያ ላይ ወይም ከጳውሎስ ጋር ሮም ከደረሱ በኋላ ብዙ ሳይቈይ (ሐሥ 28፥16) ወንጌሉን ጽፎ ሳያጠናቅቅ አልቀረም።

### ዐላማ

ሉቃስ፣ "ኢየሱስ ለማድረግና ለማስተማር የጀመረውን ሁሉ ... እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ" (ሐሥ 1፥1-2) ያለውን ሙሉና ተጨባጭ ታሪክ ለአሕዛብ ለመግለጽ ይህን ወንጌል ጽፎአል። እርሱም በመንፈስ ተመርቶ በመጻፍ ቴዎፍሎስ፣ የሚጠይቁ ሌሎች አሕዛብ እንዲሁም በክርስቶስ ያመኑት ቀደም ሲል በቃል የተማሩት ትምህርት እውነተኛ እንደ ሆነ በርግጠኝነት ያውቁ ዘንድ ይፈልጋል (1፥3-4)። ሉቃስ የጻፈው ለአሕዛብ እንደ ሆነ በወንጌሉ

ሁሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል፤ ለምሳሌ ሉቃስ የኢየሱስን የዘር ሐረግ የሚቈጥረው ማቴዎስ እንዳደረገው እስከ አብርሃም ድረስ (ከማቴ 1፥1-17 ጋር ያነጻጽሩ)ሳይሆን፣ እስከ አዳም ድረስ ያለውን ነው (3፥23-38)። በሉቃስ ላይ፣ ኢየሱስ የአዳም ዘር ሁሉ ድነትን ያገኝ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መለኮትም ሰውም የሆነ አዳኝ እንደ ሆነ በግልጽ ይታያል።

## ቅኝት

የሉቃስ ወንጌል ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን የኢየሱስን የሕፃንነት ታሪክ በመናገር ይጀምራል (1፥5—2፥40)፤ ከሌሎች ወንጌሎች ይልቅ ውልብታም ቢሆን ስለ ልጅነቱ ጊዜ የሚገልጸው ይኸው ወንጌል ነው (2፥41-52)። ሉቃስ የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎትና የኢየሱስን የዘር ሐረግ ከገለጸ በኋላ የኢየሱስን አገልግሎት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይገልጸዋል (1) በገሊላና በዚያ ዙሪያ የሰጠው አገልግሎት (4፥14—9፥50)፤ (2) በመጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም እየተጓዘ ሳለ የሰጠው አገልግሎት (9፥51—19፥27)፤ (3) በኢየሩሳሌም ያሳለፈው የመጨረሻው ሳምንት (19፥28—24፥43)። ሉቃስ በጻፈው የገሊላ አገልግሎት ውስጥ ጐላ ያለ ስፍራ ያላቸው ኢየሱስ ያደረጋቸው ታምራት ናቸው፤ በዚህ ወንጌል ውስጥ ዋና ትኩረት የተደረገው ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርትና ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ በሰጠው ሰፊ አገልግሎት ውስጥ በተናገራቸው ምሳሌዎች ላይ ነው (9፥51—19፥27)። ይህ ክፍል ጣፋጭ የሆኑ ታሪኮችንና ምሳሌዎችን ጨምሮ የሉቃስን ወንጌል ለየት የሚያደርጉ አስፈላጊ የሆኑ ሐሳቦችን በብዛት የያዘ ነው። በዚህ ወንጌል ዋና የሆነው ጥቅስ (9፥51) እና ቁልፍ የሆነው ጥቅስ (19፥10) በዚህ ልዩ የሉቃስ ጽሑፍ መጀመሪያና መጨረሻ አካባቢ ይገኛሉ።

## ልዩ ገጽታ

የሉቃስ ወንጌልን ልዩ የሚያደርጉት ስምንት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ይህ ወንጌል ሰፊ ሲሆን፣ ስለ ኢየሱስ ከልደቱ በፊት ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ ያለውን ሁኔት በውስጡ ይዞአል፤ ይህ መጽሐፍ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ብዙ ገጾች ያሉት ነው፤ (2) ለየት ያለ የአጻጻፍ ስልት፣ ብዙ ቃላት፣ ከፍተኛ የግሪክ ቋንቋ ዕውቀትና አጠቃቀም የሚታይበት በመሆኑ፣ ከወንጌሎች ሁሉ ይልቅ ሥነ ጽሑፋዊ ይዘት ያለው ነው፤ (3) አጠቃላይ የወንጌል ዐሳማን ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድና ለአሕዛብ ሁለ ድነትን ይሰጥ ዘንድ መምጣቱን በአጽንዖት ይገልጻል፤ (4) ሴቶችን፣ ልጆችን፣ ድኾችንና በኅብረተሰቡ የተገለሉትን ጨምሮ ኢየሱስ ለችግረኞች ግድ እንደሚለው አጥብቆ ይገልጻል፤ (5) ስለ ኢየሱስ የጸሎት ሕይወትና ጸሎትንም በሚመለከት ያስተማረውን ነገር በአጽንዖት ይገልጻል፤ (6) በዚህ ወንጌል ላይ ለኢየሱስ የተሰጠው ዋና የማዕረግ ስም፣ "የሰው ልጅ" የሚለው ነው፤ (7) ኢየሱስንና መልእክቱን የሚቀበሉ ሁሉ በሕይወታቸው ታላቅ ደስታ ይታያል፤ (8) መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስና በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነና ከፍተኛ ቦታ እንዳለው ተገልጾአል (ለምሳሌ 1፥15፡41፡67፤ 2፥25-27፤ 4፥1፡14፡18፤ 10፥21፤ 12፥12፤ 24፥49)።

## የሉቃስ ወንጌልን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የሉቃስ ወንጌልን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ49 ቀን መነበብ ይኖርበታል።

❑ 1፥1-25 ❑ 1፥26-56 ❑ 1፥57-80 ❑ 2፥1-20 ❑ 2፥21-52 ❑ 3 ❑ 4፥1-13
❑ 4፥14-44 ❑ 5፥1-16 ❑ 5፥17-39 ❑ 6፥1-16 ❑ 6፥17-49 ❑ 7፥1-35 ❑ 7፥36-50
❑ 8፥1-21 ❑ 8፥22-39 ❑ 8፥40-56 ❑ 9፥1-17 ❑ 9፥18-36 ❑ 9፥37-62 ❑ 10፥1-24
❑ 10፥25-42 ❑ 11፥1-13 ❑ 11፥14-36 ❑ 11፥37-54 ❑ 12፥1-21 ❑ 12፥22-48
❑ 12፥49-59 ❑ 13፥1-21 ❑ 13፥22-35 ❑ 14፥1-24 ❑ 14፥25—15፥10 ❑ 15፥11-32
❑ 16 ❑ 17፥1-19 ❑ 17፥20—18፥14 ❑ 18፥15-43 ❑ 19፥1-27 ❑ 19፥28-48
❑ 20፥1-19 ❑ 20፥20—21፥4 ❑ 21፥5-38 ❑ 22፥1-38 ❑ 22፥39-65 ❑ 22፥66—23፥25
❑ 23፥26-49 ❑ 23፥50—24፥12 ❑ 24፥13-35 ❑ 24፥36-53

*ማስታወሻ*

---

---

---

## መግቢያ

*1፥1-4 ማመ — ሐሥ 1፥1*

1 በእኛ መካከል ስለ ተፈጸሙት[ሀ] ነገሮች
ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸውን
ያህል ጽፈውት ይገኛል፤ 2ይህም ታሪክ
ከመጀመሪያው አንሥቶ የዐይን ምስክሮችና
የቃሉ አገልጋዮች የነበሩት ያስተላለፉልን
ነው። 3ክቡር ቴዎፍሎስ ሆይ፤ እኔም በበኩሌ
ሁሉን ከመሠረቱ በጥንቃቄ ከመረመርሁ
በኋላ፣ ታሪኩን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ
ሁኔታ ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፤
4ይህንንም የማደርገው የተማርኸው ነገር
እውነተኛ መሆኑን እንድታውቅ ነው።

## የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ አስቀድሞ ተነገረ

5በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን፣ ከአብያ
የክህነት ምድብ የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ
ካህን ነበረ፤ ሚስቱ ኤልሳቤጥም ከአሮን ነገድ
ነበረች። 6ሁለቱም የጌታን ትእዛዝና ሥርዐት
ሁሉ ጠብቀው ያለ ነቀፋ የሚኖሩ፣ በእግዚአብሔር
ፊት ጻድቃን ነበሩ፤ 7ይሁን እንጂ ኤልሳቤጥ
መካን በመሆኗ ልጅ አልነበራቸውም፤
ሁለቱም በዕድሜ የገፉ ነበሩ።
8አንድ ቀን ዘካርያስ በምድቡ ተራ፣
በእግዚአብሔርፊት በክህነት በሚያገለግልበት
ጊዜ፣ 9በሥርዐቱ ክህነቱ መሠረት፣ ወደ
ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን በዕጣ
ተመረጠ። 10ዕጣን በሚታጠንበትም ጊዜ
ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ሆኖ ይጸልይ ነበር።
11የጌታም መልአክ ከዕጣን መሠዊያው
በስተቀኝ ቆሞ ታየው። 12ዘካርያስም ባየው
ጊዜ ደነገጠ፤ በፍርሀትም ተዋጠ። 13መልአኩ
ግን እንዲህ አለው፤ "ዘካርያስ ሆይ፤ አትፍራ፤
ጸሎትህ ተሰምቶአል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ
ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም
ዮሐንስ ትለዋለህ። 14በእርሱ ተድላና ደስታ
ታገኛለህ፤ ብዙዎችም እርሱ በመወለዱ ደስ
ይላቸዋል፤ 15በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና።
የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያ ስክር
መጠጥ አይጠጣም፤ በእናቱም ማሕፀን ሳለ ሉቃ
በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል። 16ከእስራኤልም 1፥41
ሰዎች ብዙዎቹን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው
ይመልሳቸዋል፤ 17የአባቶችን ልብ ወደ
ልጆቻቸው፣ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን

1፥2 ማር1፥1፤ 4፥14፤ ሐሥ1፥21፡22፤ ዕብ2፥3፤ 1ጴጥ5፥1፤ 2ጴጥ1፥16፤ 1ዮሐ1፥1 1፥3 ሐሥ1፥1፤ 11፥4፤ 24፥3፤ 26፥25 1፥4 ዮሐ20፥31፤ ሐሥ2፥42 1፥5 1ዜና24፥10፤ ማቴ2፥1 1፥6 ዘፍ6፥9፤ ዘዳ5፥33፤ 1ነገ9፥4፤ ሉቃ2፥25 1፥8 1ዜና24፥19፤ 2ዜና8፥14 1፥9 ዘፀ30፥7፡8፤ 1ዜና23፥13፤ 2ዜና29፥11፤ መዝ141፥2፤ ሐሥ1፥26 1፥10 ዘሌ16፥17 1፥11 ዘፀ30፥1-10፤ ሐሥ5፥19 1፥12 መሳ6፥22፡23፤ 13፥22 1፥13 ቁ30፤ 60፡63፤ ማቴ3፥1፤

1፥13 ቁ14፥27 1፥14 ቁ58 1፥15 ቁ41፡67፤ ዘሌ10፥9፤ ዘኍ6፥3፤ መሳ13፥4፤ ጴጥ1፥5፤ ሉቃ7፥33፤ ሐሥ2፥4፤ 4፥8፡31፤ 6፥3፡5፤ 9፥17፤ 10፥44፤ ገላ1፥15፤ ኤፌ5፥18 1፥17 ቁ76፤ ሚል 4፥5፡6፤ ማቴ3፥3፤ 11፥14

*ሀ1፥1 በርግጥ ስለታመኑት*

**1፥6 ያለ ነቀፋ … በእግዚአብሔር ፊት፤** ሉቃ 2፥25 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**1፥15 በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል፤** በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው የዮሐንስ ሕይወትና አገልግሎት ውጤቱ ምን እንደሆነ ልብ በሉ:: በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ዮሐንስ የሚከተሉትን ውጤቶች ያስገኛል፤ (1) ስብከቱም ሰዎችን ስለ ኀጢአታቸው በመውቀስ ንስሓ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያደርጋል (ቍ 15-17 ይመ፤ ዮሐ 16፥8 እና ማብ ይመ)፤ (2) በኤልያስ መንፈስና ኀይል ይሰብካል (ቍ 17 ይመ፤ ሐሥ 1፥8 እና ማብ ይመ)፤ (3) በቤተ ሰብ ውስጥ ዕርቅ እንዲመጣ ያደርጋል፤ ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ ሕይወት ይመልሳል (ቍ 17)::

**1፥15 የወይን ጠጅ … የሚያስክር መጠጥ፤ በግሪኩ መጽሐፍ ቀጥተኛ ትርጕሙ፣** «የወይን ጠጅ (ኦይኖስ) ወይም የሚያስክር መጠጥ (ሲከራ) ጨርሶ አይጠጣም» ይላል:: «ሌላ» («ሌላ የሚያስክር መጠጥ») የሚለው ቃል በግሪኩ ትርጕም አይገኝም፤ (1) «የሚያስክር መጠጥ» ለሚለው የግሪኩ ቃል «ሲከራ» ይለዋል:: ትክክለኛ ትርጕሙ ምን እንደ ሆነ አልተወሰነም፤ ነገር ግን «ሼካር» ከሚለው ከብሉይ ኪዳኑ ቃል ጋር እንደሚመሳሰል ጥርጥር የለውም (በገጽ 232 ላይ፣ «*የወይን ጠጅ በብሉይ ኪዳን*» በሚል ርእስ እንዲሁም፤ በገጽ 1547 እና 1603 ላይ፣ «*የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1* እና *-2*» በሚሉ ርእሶች የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**1፥17 በኤልያስ መንፈስና ኀይል፤** ዮሐንስ በብዙ መንገድ እንደ ደፋሩ ነቢይ እንደ ኤልያስ ይሆናል (ሚል 4፥5 እና ማብ ይመ)፤ በመንፈስ ቅዱስም የተሞላ ስለ ሆነ (ቍ 15)፣ ስለ ግብረገባዊ ጽድቅ ይሰብካል (3፥7-14፤ ማቴ 3፥1-10):: ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ በመስበክ፣ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት ይገልጻል (ዮሐ 16፥8 እና ማብ ይመ)፤ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ (ማቴ 11፥7 እና ማብ ይመ) ይመልሳል:: ኀሊናው በተረዳው እውነት ላይ አይደራደርም፤ ማዕረግ ለማግኘት ወይም ደኅንነቱን ለመጠበቅ ብሎ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖችን አያጣምም (3፥19-20፤ ማቴ 14፥1-11)፤ እግዚአብሔርን ይታዘዛል፤ በታማኝነት እውነትን ሁሉ ይጠብቃል፤ ባጭሩ ዮሐንስ «የእግዚአብሔር ሰው» ይሆናል::

**1፥17 የአባቶችን … ወደ ልጆቻቸው፤** በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሚፈጽሟቸው የተለያዩ ኀጢአቶች አንዱ ለወንድና ለሴት ልጆቻቸው የእግዚአብሔርን መንገድና ትእዛዞች በማስተማር ፍቅራቸውን ያለመግለጻቸው ነው (ሚል 4፥6 እና ማብ ይመ):: ዮሐንስ ሲመጣና የክርስቶስ ወንጌል ሲነገር የአባቶች ልብ ወደ ልጆቻቸው ይመለሳል::

(1) ቁልፍ ከሆኑ የወንጌል ግቦች ውስጥ አንዱ የሆነው ይህ ሐሳብ በአባቶችና በልጆች መካከል የተስተካከለ ግንኙነት ላላቸው ቤተ ሰቦች የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደገና እንዲፈጸም ማድረግ እንደሆነ የሚያመለክት ግልጽ አነጋገር ነው፤ ስለ ንስሓና ስለ ክርስቶስ ጌትነት በመስበክ ጽድቅን በሚገልጽ ሁኔታ አባቶች ሙሉ በሙሉ ልባቸው ለልጆቻቸው የተሰጠ ይሆናል::

(2) ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ሆና ባትገኝ አንዱ ምክንያት ልጆቻቸውን ባለመውደድ፣ ከእነርሱም ጋር አብሮ ጊዜ ባለማሳለፍ፣ የእግዚአብሔርን ቃልና የጽድቅ መለኪያዎችን ባለማስተማር የአባቶች ልብ ልጆቻቸውን መተዉ ነው:: ከዚህም የተነሣ ልጆች የእግዚአብሔርን መንገድ የማይፈልጉ ይሆናሉ (ሚል 4፥6)::

(3) ቀጥሎ ያሉት ሐሳቦች ከአባቶችና ከልጆች ጋር የተገናኘ ነገር የያዙ አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው፤ (ሀ) ልጆች በእግዚአብሔር መንገድ በታማኝነት ይሄዱ ዘንድ ማስተማር፤ ዘፀ 10፥2፤ 13፥8፤ ዘዳ 4፥9-10፤ 6፥6-25፤ 11፥18-21፤ መዝ 78፥5-8፤ ኢሳ 38፥19፤

ጥበብ ይመልስ ዘንድ፣ ለጌታ የተገባ ሕዝብ
ለማዘጋጀት በኤልያስ መንፈስና ኀይል
በጌታ ፊት ይሄዳል።"
18ዘካርያስም መልአኩን፣ "ይህን በምን
አውቃለሁ? እኔ ሽማግሌ ነኝ፤ ሚስቴም
በዕድሜ ገፋ ታለች" አለው።
19መልአኩም መልሶ እንዲህ አለው፤ "እኔ
በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፤
ይህን እንግርህና ይህን የምሥራች አመጣ
ልህ ዘንድ ተልኬአለሁ፤ 20እነሆ፤ ጊዜውን
ጠብቆ የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፣
ይህም እስከሚፈጸምበት ቀን ድረስ ድዳ
ትሆናለህ፤ መናገርም አትችልም።"
21በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ዘካርያስ ከቤተ
መቅደሱ ሳይወጣ ለምን እንደ ዘገየ በመገረም
ይጠባበቅ ነበር። 22ከወጣ በኋላም ሊያናግ
ራቸው አልቻለም፤ በምልክት ከመጥቀስ
በስተቀር መናገር ባለመቻሉ በቤተ መቅደስ
ውስጥ ራእይ እንዳየ ተገነዘቡ።
23ዘካርያስም የአገልግሎቱ ወቅት
በተፈጸመ ጊዜ ወደ ቤቱ ተመለሰ። 24ከዚህ
በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ፀነሰች፤ አምስት
ወራትም ራሷን ሰወረች፤ 25እርሷም፣ "ጌታ
በምሕረቱ ነቀፌታ ዬን ከሰው መካከል
ሊያስወግድልኝ ተመልክቶ በዚህ ጊዜ ይህን
አድርጎልኛል" አለች።

## የኢየሱስ መወለድ አስቀድሞ ተነገረ

26በስድስተኛው ወር፣ እግዚአብሔር መልአኩ
ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘው ወደ
ናዝሬት ከተማ ላከው፤ 27የተላከውም ከዳዊት
ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች
ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤ የድንግሊቱም
ስም ማርያም ነበረ። 28መልአኩም እርሷ
ወዳለችበት ገብቶ፣ "እጅግ የተወደድሽ
ሆይ፤ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ ጌታ ከአንቺ ጋር

1፥18 ቍ34፤
ዘፍ15፥8፤ 17፥17
1፥19 ቍ26፤
ዳን8፥16፤ 9፥21
1፥20 ዘፀ4፥11፤
ሕዝ3፥26
1፥22 ቍ62
1፥25 ዘፍ30፥23፤
ኢሳ4፥1
1፥26 ቍ19፤
ማቴ2፥23
1፥27
ማቴ1፥16፡18፡20፤
ሉቃ2፥4
1፥30 ቍ13፤
ዘፍ6፥8፤
ማቴ14፥27
1፥31 ኢሳ7፥14፤
ማቴ1፥21፡25፤
ሉቃ2፥21
1፥32 ቍ35፡76፤
ማቴ1፥1ማር5፥7
1፥33
2ሳሙ7፥16፤
መዝ89፥3-4፤
ኤር33፥17፤
ዳን2፥44፤
7፥14ኢሳ9፥7፤
27፤ ሚክ4፥7፤
ማቴ28፥18፤
ዕብ1፥8
1፥35 ቍ32፡76፤
ማቴ1፥18፤ 4፥3፤
ማር1፥24፤ 5፥7
1፥36 ቍ24
1፥37 ማቴ19፥26
1፥39 ቍ65
1፥41 ቍ15

ነው፤ አንቺ የተባረክሽ ነሽ" አላት።
29ማርያምም በንግግሩ እጅግ በጣም
ደንግጣ፣ "ይህ ምን ዐይነት ሰላምታ
ይሆን?" እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር፤
30መልአኩም እንዲህ አላት፤ "ማርያም
ሆይ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና
አትፍሪ። 31እነሆ፤ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ
ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ
ትዪዋለሽ። 32እርሱም ታላቅ ይሆናል፤
የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክ
የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰ ጠዋል፤
33በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሣል፤
ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።"
34ማርያምም መልአኩን፣ "እኔ ወንድ
ስለማላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?"
አለችው።
35መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፤
"መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤
የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ
የሚወለ ደው ቅዱሱ ሕፃን፣ የእግዚአብሔር
ልጅ ይባላል። 36እነሆ፤ ዘመድሽ ኤልሳቤጥም
በስተ እርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ መካን
የተባለችውም ስድስተኛ ወሯን ይዛለች፤
37ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።"
38ማርያምም፣ "እነሆ፤ እኔ የጌታ ባሪያ
ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" አለች።
ከዚያም መልአኩ ተለይቶአት ሄደ።

## ማርያም ኤልሳቤጥን ጥየቃ ሄደች

39ማርያምም በዚያው ሰሞን በፍጥነት
ተነሥታ ወደ ደጋው አገር፣ ወደ አንድ
የይሁዳ ከተማ ሄደች፤ 40ወደ ዘካርያስ ቤትም
ገብታ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ አቀረበች።
41ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች
ጊዜ፣ ፅንሱ በማሕፀኗ ውስጥ ዘለለ፤
ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች፤

ኢል 1፥3፤ ኤፌ 6፥4፤ 1ተሰ 2፥11፤ (ለ) ልጆችን መውደድና ማቅናት፡ መዝ 103፥13፤ ምሳ 3፥12፤ 13፥24፤ 23፥13-14፤ ሚል 4፥6፤ ሉቃ 11፥11-13፤ 2ቆሮ 12፥14፤ ኤፌ 6፥4፤ ቈላ 3፥21፤ 1ተሰ 2፥11፤ 1ጢሞ 3፥4-5፡12፤ 5፥8፤ ቲቶ 2፥4፤ ዕብ 12፥7፤ (ሐ) አባቶች ለልጆቻቸው መጸለይ ይገባቸዋል፤ ዘፍ 17፥18፤ 2ሳሙ 12፥16፤ 1ዜና 22፥11-12፤ 29፥19፤ ኢዮ 1፥5፤ ኤፌ 3፥14-19፤ አባት ለልጆቹ ለሚጸልየው ጸሎት በምሳሌነት በዮሐ 17፥1 ላይ ያለውን ሐሳብ ልብ ይበሉ። በገጽ 1894 ላይ፣ "**ወላጆችና ልጆች**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥28 እጅግ የተወደድሽ ሆይ፤** ማርያም ከሴቶች ሁሉ ሞገስ አግኝታ የኢየሱስ እናት ትሆን ዘንድ ብትመረጥም አምልኮ፥ ሊቀርብላት፣ ወደ እርስዋ ጸሎት ሊደረግና የተለዩ የማዕረግ ስሞች ሊሰጣት እንደሚያስፈልግ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ጨርሶ አላመለከቱም። ማርያምን ልናከብራት ይገባል፤ ነገር ግን አምልኮአችንን ማቅረብ የሚገባን ለልጅዋ ብቻ ነው፤ (1) ማርያም የተመጠረችው በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ስላገኘች እንደሆነ ልብ በሉ (ከዘፍ 6፥8 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በትሕትናዋና ፈሪሀ እግዚአብሔር በተሞላበት ሕይወትዋ ደስ ስለ ተሰኘ ለዚህ ታላቅ ዐላማ እግዚአብሔር መረጣት (ከ2ጢሞ 2፥21 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ማርያም በመባረክዋ ያገኘችው ታላቅ የልብ ደስታ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ልጅዋን ስላልተቀበሉትና በመስቀል ላይ ስለሚሰቅሉት መከራና ሥቃይም አትርፋለች (2፥35)። በዚህ ዓለም ስንኖር የእግዚአብሔር ጥሪ ሁልጊዜ በረከትና ችግር፣ ደስታና ሐዘን፣ ድል ማድረግና ተስፋ መቍረጥ የሚፈራረቅበት ነው።

**1፥35 ቅዱሱ፤** ሉቃስና ማቴዎስ ሁለቱም ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ ያለ ጥርጥር በግልጽ ይናገራሉ (ቍ 27፤ ማቴ 1፥18፡23 እና ማብ ይመ) መንፈስ ቅዱስ በማርያም ላይ ይመጣል፤ ሕፃኑም በእግዚአብሔር ታምራዊ አሠራር ብቻ ይፀነሳል። ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ "ቅዱስ" ነው (የኀጢአት እድፍ የሌለበት ነው)። ስለዚህ ጉዳይ በይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1559 ላይ፣ "**ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥38 እንደ ቃልህ፤** ማርያም ሙሉ በሙሉ ራስዋን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፋ ሰጠች፤ መልእክቱንም አምና ተቀበለች። የቅዱሱ ሕፃን እናት መሆን የሚያመጣውን ክብርም ሆነ ነቀፋ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነች። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጣት ሴቶች በወሲባዊ ግንኙነት ረገድ ቅድስናቸውን በመጠበቅ፣ እግዚአብሔርን በመውደድ፣ በቃሉ በማመንና መንፈስ ቅዱስን በመታዘዝ የማርያምን ምሳሌነት መከተል አለባቸው።

[42]ድምፅዋን ከፍ አድርጋ እንዲህ አለች፤
"አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤
የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። [43]ለመሆኑ
የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ
እኔ ማን ነኝ? [44]እነሆ፤ የሰላምታሽ ድምፅ
ጆሮዬ እንደ ገባ፣ በማሕፀኔ ያለው ፅንስ
በደስታ ዘሎአልና። [45]ጌታ ይፈጽማል ብሎ
የነገራትን ያመነች እርሷ የተባረከች ናት!"

## የማርያም መዝሙር

*1፥46-53 ተጓ ምብ — 1ሳሙ 2፥1-10*

[46]ማርያምም እንዲህ አለች፤
"ነፍሴ ጌታን ከፍ ከፍ
ታደርገዋለች፤
13-14 [47]መንፈሴም በመድኀኒቴ
በእግዚአብሔር ደስ ትሰኛለች፤
[48]እርሱ የባሪያውን መዋረድ
ተመልክቶአልና።
ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት
ይሉኛል፤
[49]ኀያል የሆነው እርሱ ታላቅ
ነገር አድርጎልኛልና፤
ስሙም ቅዱስ ነው፤
[50]ምሕረቱም ለሚፈሩት ከትውልድ
እስከ ትውልድ ይኖራል።
[51]በክንዱ ብርቱ ሥራ ሠርቶአል፤
በልባቸው ሐሳብ የሚታበዩትን
በትኖአቸዋል፤
[52]ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአቸዋል፤
ትሑታንን ግን ከፍ ከፍ
አድርጎአቸዋል፤
[53]የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአቸዋል፤
ሀብታሞችን ግን ባዶአቸውን
ሰዶአቸዋል፤
[54]ምሕረቱን በማስታወስ፣ ባሪያውን
እስራኤልን ረድቶአል፤
[55]ይህም ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፣
ለአብርሃምና ለዘሩ ያለውን
ለዘላለም ለመጠበቅ ነው።"
[56]ማርያምም ሦስት ወር ያህል ኤልሳቤጥ
ዘንድ ከቈየች በኋላ ወደ ቤቷ ተመለሰች።

## የመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ

[57]የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ቀን ደረሰ፤
ወንድ ልጅም ወለደች። [58]ጎረቤቶቿና
ዘመዶቿም ጌታ ታላቅ ምሕረት እንዳደረገላት
ሰሙ፤ የደስታዋም ተካፋዮች ሆኑ።

1፥42 መሳ5፥24
1፥43 ዮሐ13፥13
1፥46 መዝ34፥2:3
1፥47 መዝ18፥46፤ ኢሳ17፥10፤ 61፥10፤ ዕን3፥18፤ 1ጢሞ 1፥1፤ 2፥3፤ 4፥10
1፥48 ቍ38፤ መዝ138፥6፤ ሉቃ11፥27
1፥49 መዝ71፥19፤ 111፥19
1፥50 ዘፀ20፥6፤ መዝ103፥17
1፥51 ዘፍ11፥8፤ ዘፀ 18፥11፤ 2ሳሙ22፥28፤ መዝ98፥1፤ ኢሳ40፥10፤ ጴጥ13፥9፤ 49፥16
1፥52 ማቴ23፥12
1፥53 መዝ107፥9
1፥54 መዝ98፥3
1፥55 ገላ3፥16
1፥59 ዘፍ17፥12፤ ዘሌ12፥3፤ ሉቃ2፥21፤ ፊል3፥5
1፥60 ቍ13:63፤ ማቴ3፥1
1፥62 ቍ22፤
1፥63 ቍ13:60፤ ማቴ3፥1
1፥64 ቍ20፤ ሕዝ24፥27
1፥65 ቍ39
1፥66 ዘፍ39፥2፤ ሐሥ11፥21
1፥67 ቍ15፤ ኢል2፥28
1፥68 ዘፍ24፥27፤ 1ነገ8፥15፤ መዝ72፥18፤ 111፥9፤ ሉቃ7፥16
1፥69 1ሳሙ2፥1:10፤ 2ሳሙ22፥3፤ መዝ18፥2፤ 89፥17፤ 132፥17፤ ሕዝ29፥21፤ ማቴ1፥1
1፥70 ጴጥ23፥5፤ ሐሥ3፥21፤ ሮሜ1፥2

[59]በስምንተኛውም ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት
መጡ፤ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት
ፈለጉ፤ [60]እናቱ ግን፣ "አይሆንም፤ ዮሐንስ
መባል አለበት" አለች።
[61]እነርሱም፣ "ከዘመዶችሽ በዚህ ስም
የተጠራ ማንም የለም" አሏት።
[62]አባቱንም ምን ስም ሊያወጣለት
እንደሚፈልግ በምልክት ጠየቁት።
[63]እርሱም መጻፊያ ሰሌዳ እንዲሰጡት
ለምኖ፣ "ስሙ ዮሐንስ ነው" ብሎ ጻፈ፤
ሁሉም በነገሩ ተደነቁ። [64]ወዲያውም አፉ
ተከፈተ፤ አንደ በቱ ተፈታ፤ እግዚአብሔርንም
እያመሰገነ መናገር ጀመረ። [65]ጎረቤቶቹም
ሁሉ በፍርሀት ተሞሉ፤ ይህም ሁሉ ነገር
በደጋማው የይሁዳ ምድር ሁሉ ተወራ።
[66]ይህንም የሰሙ ሁሉ፣ "ይህ ሕፃን ምን
ሊሆን ይሆን?" እያሉ ነገሩን በልባቸው ያዙ፤
የጌታ እጅ በርግጥ ከእርሱ ጋር ነበርና።

## የዘካርያስ ትንቢት

[67]የሕፃኑም አባት ዘካርያስ በመንፈስ
ቅዱስ ተሞልቶ እንዲህ ሲል ትንቢት ሉቃ 3፥16
ተናገረ፤
[68]"የእስራኤል አምላክ፣ ጌታ ይመስገን፤
መጥቶ ሕዝቡን ተቤዥቶአልና።
[69]በባሪያው በዳዊት ቤት፣
የድነት ቀንድ[^] አስነሥቶልናል፤
[70]ይህም ጥንት በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ
እንደ ተናገረው፣
[71]ማዳኑም ከጠላቶቻችንና፣ ከተፃራሪዎቻ
ችን ሁሉ እጅ ነው፤
[72]ይህንም ያደረገው ለአባቶቻችን
ምሕረቱን ለማሳየት፣
ቅዱስ ኪዳኑን ለማስታወስ፣
[73]ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን
መሐላ ለማሰብ፣
[74]ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶ፣
ያለ ፍርሀት እንድናገለግለው፣
[75]በዘመናችንም ሁሉ በቅድስናና
በጽድቅ በፊቱ ሊያቆመን ነው።
[76]ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፤ የልዑል
ነቢይ ትባላለህ፤

1፥72 መዝ105፥8:9፤ 106፥45፤ ሕዝ16፥60፤ ሚክ7፥20
1፥73 ዘፍ22፥16-18 1፥74 ዕብ9፥14፤ 1ዮሐ4፥18
1፥75 ኤፌ4፥24 1፥76 ቍ17:32:35፤ ማቴ3፥3፤ 11፥9፤ ማር5፥7

^1፥69 *ቀንድ በዚህ ስፍራ ብርታትን በትእምርትነት ያሳያል*

**1፥47 በመድኀኒቴ በእግዚአብሔር፤** ከዚህ ሐረግ ማርያም ድነት እንደሚያስፈልጋት መገንዘቧን እናያለን:: እርሷም የክርስቶስ አዳኝነት የሚያስፈልጋት ኀጢአተኛ ነበረች:: ማርያም ያለ ኀጢአት እንደተፀነሰችና ኀጢአት ሳታደርግ እንደኖረች የሚያስተምር ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጨርሶ የለም (ከሮሜ 3፥9:23 ጋር ያነጻጽሩ)::
**1፥67 በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፤** ከክርስቶስ መወለድ ጋር የተያያዘ ሁኔታ ያላቸው አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች፣ መንፈስ ቅዱስ ብዙዎቹን እንዴት በኀይል እንደሞላቸው ሉቃስ ጽፎአል (ቍ 15:35:41:67፤ 2፥25):: ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ አማኞች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ይቀበሉ ዘንድ መንገዱ ተከፈተ (ሐሥ 1—2)::
**1፥75 በቅድስናና በጽድቅ፤** የቤዛነታችን የመጨረሻ ዐላማ ከሰይጣን መንግሥት ነጻ ወጥተን (ሐሥ 26፥18) በዘመናችን ሁሉ በቅድስናና በጽድቅ እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው (ከኤፌ 1፥4 ጋር ያነጻጽሩ):: የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ማንኛውም ክርስቲያን በዚህ ክፉ ዓለም ውስጥ የቅድስናና የጽድቅ ሕይወት ለመኖር ዐላማው መሆን አለበት:: ይህ ቅዱስ ሕይወት የሚኖረው "በእርሱ ፊት" ማለትም የእግዚአብሔር ህልዎት ባለበት ነው::

የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት በፊቱ
ትሄዳለህና፤
77የኃጢአታቸውን ስርየት ከማግኘታቸው
የተነሣ፤
ለሕዝቡ የመዳንን ዕውቀት ትሰጥ
ዘንድ፣
78ከአምላካችንም በጎ ምሕረት የተነሣ፣
የንጋት ፀሓይ ከሰማይ ወጣችልን፤
79ይኸውም በጨለማ ለሚኖሩት፣
በሞት ጥላ ውስጥም ላሉት
እንዲያበራና፣
እግሮቻችንንም ወደ ሰላም መንገድ
እንዲመራ ነው።" ሉቃ 19፥10
80ሕፃኑም አደገ፤ በመንፈስም ጠነከረ፤
ለእስራኤልም ሕዝብ በይፋ እስከታየበት
ቀን ድረስ በበረሓ ኖረ።

## የኢየሱስ መወለድ

2 በዚያን ዘመን፣ የዓለሙ ሁሉ ሕዝብ
እንዲቈጠርና እንዲመዘገብ ከአውግስጦስ
ቄሳር ትእዛዝ ወጣ። 2ይህም ቄሬኔዎስ የሶርያ
ገዢ በነበረበት ጊዜ የተደረገ የመጀመሪያው
የሕዝብ ቈጠራ ነበር። 3ስለዚህ እያንዳንዱ
ሰው ለመመዝገብ ወደየራሱ ከተማ ሄደ።
4ዮሴፍም ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ፣
በገሊላ አውራጃ ከምትገኘው ከናዝሬት
ከተማ ተነሥቶ የዳዊት ከተማ ወደሆነችው፣
ቤተ ልሔም ወደምትባል ከተማ ወደ ይሁዳ
ወጣ። 5ወደዚያም ለመመዝገብ የተጓዘው፣
የመውለጃ ጊዜዋ ከተቃረበው ከእጮኛው
ከማርያም ጋር ነበር። 6በዚያም እንዳሉ
የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ፤ 7የበኵር ልጇ
የሆነውን ወንድ ልጅ ወለደች፤ በጨርቅም
ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማረፊያ ቦታ
ስላላገኙ በግርግም አስተኛችው።

## እረኞችና መላእክት

8በዚያው አገር በሌሊት መንጋቸውን
ሲጠብቁ በሜዳ የሚያድሩ እረኞች
ነበሩ። 9የጌታም መልአክ ድንገት መጥቶ
በአጠገባቸው ቆመ፤ የጌታም ክብር
በዙሪያቸው አበራ፤ ታላቅም ፍርሀት
ያዛቸው። 10መልአኩ ግን እንዲህ አላቸው፤
"አትፍሩ፤ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ
ደስታ የምሥራች እምጣቼላችኋለሁና። 11ዛሬ
በዳዊት ከተማ መድኅን ተወልዶላችኋልና፤
እርሱም ጌታ ክርስቶስ[ሀ] ነው። 12ይህ ምልክት
ይሁናችሁ፤ ሕፃን ልጅ በጨርቅ ተጠቅልሎ
በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ።"
13ድንገትም ብዙ የሰማይ ሰራዊት
ከመልአኩ ጋር ታዩ፤ እግዚአብሔርንም
እያመሰገኑ፣ እንዲህ አሉ፤
14"ክብር በእግዚአብሔር በአርያም፣ ሰላምም
እርሱ ለሚወዳቸው ሰዎች በምድር ይሁን!"
15መላእክቱ ከእነርሱ ተለይተው
ወደ ሰማይ ከወጡ በኋላ እረኞቹ፣ "ጌታ
የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንድናይ
ወደ ቤተ ልሔም እንሂድ" ተባባሉ።
16እነርሱም ፈጥነው ሄዱ፤ ማርያምንና
ዮሴፍን፣ ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ።
17ካዩም በኋላ፣ ስለ ሕፃኑ የተነገራቸውን
ገልጠው አወሩ። 18ይህንንም የሰሙ
ሁሉ እረኞቹ በነገሯቸው ነገር ተደነቁ፤
19ማርያም ግን ይህንን ሁሉ በልቧ ይዛ
ታሰላስል ነበር። 20እረኞቹም ሁሉም ነገር
እንደ ተነገራቸው ሆኖ በማግኘታቸው፣
ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን
እያከበሩና እያመሰገኑ ተመለሱ።

## ሕፃኑን ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት

21ስምንት ቀን ሆኖት የመገረዝ ጊዜው
ሲደርስ፣ ከመፀነሱ በፊት መልአኩ ባወጣለት
ስም ኢየሱስ ተባለ።
22በሙሴ ሕግ መሠረት፣ የመንጻታቸው
ወቅት በተፈፀመ ጊዜ፣ ዮሴፍና ማርያም
ሕፃኑን **ለጌታ** ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም
ይዘው ወጡ፤ 23ይኸውም **በጌታ** ሕግ፣
"ተባዕት የሆነ በኵር ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ
ይሆናል" ተብሎ እንደ ተጻፈ ለመፈጸምና
24ደግ ሞም **በጌታ** ሕግ፣ "ሁለት ዋኖሶች

1፥77 ኢዮ31፥34፤ ማቴ1፥21፤ ማር1፥4
1፥78 ሚል4፥2
1፥79 መዝ107፥14፤ ኢሳ9፥2፤ 59፥9፤ ማቴ4፥16፤ ሉቃ2፥14፤ ሐሥ26፥18
1፥80 ሉቃ2፥40:52
2፥1 ማቴ22፥17፤ 24፥14፤ ሉቃ3፥1
2፥2 ማቴ4፥24፤ ሐሥ15፥23:41፤ 21፥3፤ ገላ1፥21
2፥4 ዮሐ7፥42
2፥5 ሉቃ1፥27
2፥9 ሐሥ5፥19
2፥11 ማቴ1፥16:21፤ 16፥16:20፤ ዮሐ3፥17፤ 4፥42፤ 11፥27፤ 3፥13፤ ሐሥ2፥36፤ 3፥20፤ 5፥31፤ 9፥22፤ 13፥23፤ ሮሜ1፥14፤ 1ጢሞ4፥10፤ 1ዮሐ4፥14
2፥12 1ሳሙ2፥34፤ 10፥7፤ 1ነገ19፥29፤ መዝ86፥17፤ ኢሳ7፥14
2፥14 ኢሳ9፥6፤ 52፥7፤ 53፥5፤ ሚክ5፥5፤ ሉቃ1፥79፤ ዮሐ14፥27፤ ሮሜ5፥1፤ ኤፌ2፥14:17
2፥16 ቍ 7
2፥19 ቍ 51
2፥20 ማቴ9፥8
2፥21 ሉቃ1፥31፤ 59
2፥22 ዘሌ12፥2-8
2፥23 ዘፀ13፥2:12:15፤
2፥23 ዘኍ3፥13 2፥24 ዘሌ12፥8

[ሀ]2፥11 ወይም መሲሕ፡ ክርስቶስ (በግሪክ) መሲሕ (በዕብራይስጥ) ማለት ሲሆን የሁለቱም ትርጕም የተቀባ ማለት ነው፡ እንዲሁም ቍ 26 ይመ

**2፥7 በግርግም፤** ኢየሱስ የተወለደው ከብቶች በሚያድሩበት ጋጣ ነው:: ጋጣው ምናልባት ዋሻ ሲሆን፣ ግርግሙ ደግሞ ከብቶች የሚመገቡበት ገንዳ ሊሆን ይችላል:: በታሪክ ከተደረገው ሁሉ የሚበልጠው ሁነት የአዳኙ መወለድ ሲሆን፣ ይህም የተፈጸመው እጅግ ዝቅ ባለ ሁኔታ ነው:: ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥ ቢሆንም፣ በዚህ ምድር ልደቱም ሆነ ኑሮው ለንጉሥ እንደሚሆን አልነበረም:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ነገሥታትና ካህናት እንዲሆኑ ተጠርተዋል፡ ነገር ግን በዚህ ምድር እያለን እንደ እርሱ ትሑት መሆንና በልክ መኖር ይገባናል::

**2፥11 መድኅን ... ጌታ ክርስቶስ፤** አስቀድሞ እንደተነገረው፣ ኢየሱስ ከመወለዱ ጀምሮ "አዳኝ" ተብሎ ተጠርቶአል፡ (1) እርሱ አዳኝ እንደመሆኑ ከኃጢአት፣ ከሰይጣን አገዛዝ፣ ከፍርሃት፣ ከሞት፣ ከመተላለፋችን የተነሣ ከሚመጣብን ፍርድ ነጻ ሊያወጣን ወደዚህ ምድር መጣ (ማቴ 1፥21 እና ማብ ይመ)፡ (2) አዳኙ "ጌታ ክርስቶስ" ነው:: የእግዚአብሔር መሲሕና በሕዝቡ ላይ የሚገዛ ጌታ ሆኖ ተቀብቶአል (ማቴ 1፥1 እና የክርስቶስን ስም በሚመለከት የተሰጠውን ማብ ይመ):: ማንም ሰው በኢየሱስ ጌትነት ሳያምንና ራሱን ለእርሱ አሳልፎ ሳይሰጥ ክርስቶስ አዳኙ ሊሆን አይችልም::

**2፥22 ሕፃኑን ለጌታ ለማቅረብ፤** ዮሐንስና ማርያም ኢየሱስን ለጌታ እንዳቀረቡ፣ ወላጆች ሁሉ ልጆቻቸውን በፍጹም ልብ ለእግዚአብሔር አሳልፈው መስጠት አለባቸው:: እያንዳንዱ ልጅ ከመጀመሪያ አንሥቶ እስከ መጨረሻ ድረስ ባለው የሕይወት ዘመኑ በፍጹም ልብ የጌታን ፈቃድ በማድረግ፣ እግዚአብሔርን በማገልገልና እርሱን በማክበር እንዲኖር ወላጆች ያለማቋረጥ ሊጸልዩለት ይገባል::

**2፥24 ሁለት ዋኖሶች፤** ዮሴፍና ማርያም ሁለት ዋኖሶችን ለመሥዋዕት ማቅረባቸው፣ ድኾች እንደነበሩ

ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች እንደ
ተባለ፣" መሥዋዕት ለማቅረብ ነበር።
25በዚያን ጊዜ ጻድቅና ትጉሕ የሆነ
ስምዖን የሚባል አንድ ሰው በኢየሩሳሌም
ይኖር ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን
መጽናናት የሚጠባበቅና መንፈስ ቅዱስ
በላዩ ያደረሰው ነበር። 26ደግሞም የጌታን
መሲሕ ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ
ቅዱስ ተገልጦለት ነበር፤ 27እርሱም በዚህ
ጊዜ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ቤተ መቅደስ
ገባ፤ የልጁም ወላጆች በሕጉ ልማድ
መሠረት ተገቢውን ሊፈጽሙለት ሕፃኑን
ኢየሱስን ይዘው በገቡ ጊዜ፣ 28ስምዖን
ተቀብሎ ዐቀፈው፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ
እንዲህ አለ፤

29"ጌታ ሆይ፤ ቃል በገባኸው መሠረት፣
አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተው፤
30ዐይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት
ያዘጋጀኸውን፣
31ማዳንህን አይተዋልና።
32ይህም ለአሕዛብ መገለጥን የሚሰጥ
ብርሃን፣
ለሕዝብህ ለእስራኤልም ክብር
ነው።"

33አባቱና እናቱም ስለ እርሱ በተነገረው
ነገር ተገረሙ። 34ስምዖንም ባረካቸው፤
እናቱን ማርያምንም እንዲህ አላት፤ "ይህ
ሕፃን በእስራኤል ለብዙዎች መነሣትና
መውደቅ ምክንያት እንዲሆን፣ ደግሞም
ክፉ ለሚያስወሩበት ምልክት እንዲሆን
ተወስኖአል፤ 35የብዙዎችም የልብ ሐሳብ
የተገለጠ እንዲሆን፣ የአንቺም ነፍስ ደግሞ
በሰይፍ ይወጋል።"

36ደግሞም ከአሴር ወገን የሆነች
የፋኑኤል ልጅ፣ ሐና የምትባል ነቢይት
በዚያ ነበረች፤ እርሷም በጣም አርጅታ
ነበር፤ በድንግልናዋ ካገባችው ባሏም ጋር
ሰባት ዓመት የኖረች ነበረች፤ 37ዕድሜዋም
ሰማንያ አራት ዓመት″ እስኪሆናት ድረስ
ቀንና ሌሊት ከቤተ መቅደስ ሳትለይ፣
በጾምና በጸሎት የምታገለግል መበለት ሆና
ቈየች። 38በዚያኑም ጊዜ ቀርባ እግዚአብሔርን
አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም መቤዠት
ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ ሕፃኑ ተናገረች።

39ዮሴፍና ማርያም በጌታ ሕግ
የታዘዘውን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላ፣ በገሊላ
አውራጃ ወዳለችው ከተማቸው ወደ ናዝሬት
ተመለሱ። 40ሕፃኑም እያደገና እየጠነከረ
ሄደ፤ በጥበብ ተሞላ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ
በእርሱ ላይ ነበረ።

## ኢየሱስ በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ

41ወላጆቹም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ

2፥25 ቍ38፤ ኢሳ52፥9፤ ሉቃ1፥6፤ 23፥5
2፥27 ቍ22
2፥29 ቍ26፤ ሐሥ2፥24
2፥30 ኢሳ40፥5፤ 52፥10፤ ሉቃ3፥6
2፥32 ኢሳ42፥6፤ 49፥6፤ ሐሥ13፥47፤ 26፥23
2፥34 ኢሳ8፥14፤ ማቴ12፥46፤ 21፥44፤ 1ቆሮ1፥23፤ 2ቆሮ2፥16፤ ገላ5፥11፤ 1ጴጥ2፥7፡8
2፥36 ሐሥ21፥9
2፥37 ሐሥ13፥3፤ 14፥23፤ 1ጢሞ5፥5፡9
2፥38 ቍ25፤ ኢሳ40፥2፤ 52፥9፤ ሉቃ1፥68፤ 24፥21
2፥39 ቍ51፤ ማቴ2፥23
2፥40 ቍ52፤ ሉቃ1፥80
2፥41 ዘፀ23፥15፤ ዘዳ16፥1-8፤ ሉቃ22፥8

*″2፥37 ወይም ለሰማንያ አራት ዓመት መበለት የነበረች*

ያመለክታል (ዘሌ 12፥8)። ከመጀመሪያው ጀምሮ ክርስቶስ እንደ ድኻ ተቈጥሯል (9፥58፤ ማቴ 8፥20፤ ራእ 2፥9 እና ማብ ይመ)።

**2፥25 ጻድቅና ትጉሕ፤** "ጻድቅ" ወይም "ነቀፋ የሌለበት" የሚለው (ከ1፥6 ጋር ያነጻጽሩ) በግሪኩ "ዲካዮስ"፣ በዕብራይስጡ ደግሞ "ያሼር" ለሚለው ቃል ትርጒም ይሰጣል፤ ይህም "ቅን" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው ከትእዛዛቱ ጋር መስማማቱን ብቻ ሳይሆን፣ በሐሳብና በተግባር ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ይዞ መገኘቱን ነው (መዝ 32፥2 እና ማብ ይመ)፤ (1) በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር የሚፈልገው ጽድቅ እርሱን በእውነት በማመን፣ እርሱን በመውደድና በመፍራት (ዘዳ 4፥10፡29፤ 5፥29) ላይ ከተመሠረተ ልብ የሚመነጨውን ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ልብ የነበራቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ሥርዐት ሁሉ በመጠበቅ ያለነቀፋ የነበሩት የዮሐንስ መጥምቁ ወላጆች ናቸው (1፥6፤ ዘፍ 7፥1፤ 17፥1፤ 1ነገ 9፥4 ይመ፤ በዚህ ስፍራ ይህ ቃል "የልብ እውነተኛነትንም" ጭምር የሚያመለክት ነው)። ስምዖንም በሕይወቱ ተመሳሳይ ባሕርያትን አሳይቷል፤ (2) የብሉይ ኪዳን ጻድቅ ሰዎች ፍጹማን አልነበሩም፤ ኀጢአት በሚሠሩበት ጊዜ በእውነተኛ ንስሓና በእምነት እንስሳን መሥዋዕት አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት በማቅረብ ለኀጢአታቸው ይቅርታን ያገኙ ነበር (ዘሌ 4፥27-35፤ እንዲሁም በገጽ 202 ላይ፣ "*የስርየት ቀን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥25 መጽናናት የሚጠባበቅ፤** በጊዜው የነበረው መንፈሳዊ ሁኔታ አሳዛኝ በነበረበት ጊዜ ጻድቁ ስምዖን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በእምነት፣ በትዕግሥትና በታላቅ ናፍቆት የመሲሑን መምጣት በመጠባበቅ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሰው ነበር። እንደዚሁም ብዙ ሰዎች የአዲስ ኪዳንን የሐዋርያት አስተምህሮና የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የክርስቶስን መምጣት (ቲቶ 2፥13) ችላ ብለው የራሳቸውን ፈቃድ እያደረጉ በሚመላለሱበት በዚህ ዘመን የመጨረሻዎቹ ቀናት እንደ ስምዖን ያሉ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎች ይኖራሉ። ሌሎች ተስፋ የሚያደርጉት ምድራዊ ሕይወትንና ይህን ዓለም ነው። ነገር ግን ታማኝ ክርስቲያኖች፣ ረጅምና ድቅድቅ ጨለማ በሆነው ሌሊት የጌታውን መመለስ በትዕግሥት እንደሚጠብቀው ታማኝ ባሪያ (ማቴ 24፥45-47) ይሆናሉ። ታላቅ በረከት የሚሆንልን "የጌታን መሲሕ" ፊት ለፊት ስናይ (ቍ 26 ይመ፤ ከራእ 22፥4 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በሚመጣበት ጊዜ ዝግጁ ሆነን ስንገኝና የእርሱ ህልዎት ባለበት ለዘላለም ስንኖር ነው (ራእ 21—22)።

**2፥36-37 ሐና ... የምታገለግል፤** ሐና በፍጹም ልብ የክርስቶስን መምጣት በተስፋ የምትጠባበቅ ነቢይት ነበረች። መልሳ ባል ሳታገባ ለብዙ ዓመት ብቻዋን በመኖር ሌትና ቀን "በጾምና በጸሎት" እየተጋች ሙሉ በሙሉ ራስዋን ለጌታ አሳልፋ የሰጠች ሴት ነበረች። ከማግባት ይልቅ አለማግባት የበለጠ በረከት እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ያላገቡ ሰዎች ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለጌታ እንዴት እንደሚያስገዙና ጌታን እንዴት ደስ እንደሚያሰኙ ስለ ጌታ ነገር አብዝተው ለማሰብ አመቺ ሁኔታ እንዳላቸው ጳውሎስ ይናገራል (1ቆሮ 7፥32-35 ይመ)።

**2፥40 ሕፃኑም እያደገ፤** እንደማንኛውም ሕፃን ኢየሱስ በአካልና በመንፈስ እያደገ ሄደ። የእግዚአብሔር ጸጋ በእርሱ ላይ ስለነበር በጥበብም እየተሞላ መጣ። እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ደረጃ በማደግ በሰብአዊ ባሕርዩም ፍጹም ነበር።

ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። 42ልጁም ዐሥራ
ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ፣ እንደ ተለመ ደው
ወደ በዓሉ ወጡ። 43በዓሉን ከፈጸሙ በኋላ፣
ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ ብላቴናው ኢየሱስ
በኢየሩሳሌም ቀረ፤ ወላጆቹ ግን መቅረቱን
አላወቁም ነበር። 44አብሮአቸው ያለ
መስሎአቸው፣ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዙ፤
በኋላ ግን ከዘመዶቻቸውና ከወዳጆቻቸው
ዘንድ ይፈልጉት ጀመር፤ 45ባጡትም
ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
46ከሦስት ቀንም በኋላ፣ በመምህራን
መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸውና ጥያቄ
ሲያቀርብላቸው በቤተ መቅደስ ውስጥ
አገኙት፤ 47የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና
በመልሱ ይደነቁ ነበር። 48ወላጆቹም ባዩት
ጊዜ ተገረሙ፤ እናቱም፣ "ልጄ ሆይ፤
ለምን እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔኮ
ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር" አለችው።
49እርሱም፣ "ለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ
ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁ
ምን?" አላቸው። 50እነርሱ ግን የተናገራ
ቸው ነገር አልገባቸውም።
51ከዚያም አብሮአቸው ወደ ናዝሬት
ወረደ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም
ይህን ሁሉ ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበር።
52ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም
በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ።

### የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

*3፥2-10 ተጓ ምብ — ማቴ 3፥1-10፤*
*ማር 1፥3-5*
*3፥16-17 ተጓ ምብ — ማቴ 3፥11፡12፤*
*ማር. 1፥7፡8*

3 ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ በዐሥራ
አምስተኛው ዓመት፣ ይኸውም ጳንጥዮስ
ጲላጦስ የይሁዳ ገዥ፣ ሄሮድስ የገሊላ
አራተኛው ክፍል ገዥ፣ ወንድሙ ፊልጶስ
የኢጡርያስና የጥራኮኒዶስ የአራተኛው
ክፍል ገዥ ሊሳኒዮስም የሳቢላኒስ
አራተኛው ክፍል ገዥ በነበሩበት ጊዜ፣
2ሐናና ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፣
የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ
ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ። 3እርሱም
ለኀጢአት ስርየት የሚሆን የንስሓን
ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ

2፥47 ማቴ7፥28
2፥48
ማቴ12፥46፤
ሉቃ3፥23፤ 4፥22
2፥49 ዮሐ2፥16
2፥50 ማር9፥32
2፥51 ቍ19፡39፤
ማቴ2፥23
2፥52 ቍ40፤
1ሳሙ2፥26፤
ምሳ3፥4፤
ሉቃ1፥80
3፥1 ማቴ14፥1፤
27፥2
3፥2 ማቴ3፥1፤
26፥3፤ ሉቃ1፥13
3፥3 ቍ16፤
ማር1፥4
3፥6 መዝ98፥2፤
ኢሳ40፥3-5፤
42፥16፤ 52፥10፤
ሉቃ2፥30
3፥7 ማቴ12፥34፤
23፥33፤
ሮሜ1፥18
3፥8 ኢሳ51፥2፤
ሉቃ19፥9፤
ዮሐ8፥33፡39፤
ሐዋ13፥26፤
ሮሜ4፥1፡11፡12፡
16፡17፤ 9፥7፡8፤
ገላ3፥7
3፥9 ማቴ3፥10
3፥10 ቍ12፡14፤
ሐሥ2፥37፤
16፥30
3፥11 ኢሳ58፥7፤
ሕዝ18፥7
3፥12 ሉቃ7፥29
3፥13 ሉቃ19፥8
3፥14 ዘፀ23፥1፤
ዘሌ19፥11
3፥15 ማቴ3፥1፤
ዮሐ1፥19፡20፤
ሐሥ13፥25
3፥16 ቍ3፤
ማር 1፥4፤
ዮሐ1፥26፡33፤
11፥16፤ 19፥4

ወዳሉት ስፍራዎች ሁሉ መጣ፤ 4ይኸውም
ነቢዩ ኢሳይያስ በመጽሐፉ እንዲህ ሲል
በጻፈው ቃል መሠረት ነበር፤
"በበረሓ እንዲህ ብሎ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፤
'የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤
ጐዳናውንም አቅኑ፤
5ሸለቆው ሁሉ ይሞላል፤
ተራራውና ኰረብታው ሁሉ ዝቅ
ይላል፤
ጠማማው መንገድ ቀና፣
ሸካራውም ጐዳና ትክክል ይሆናል፤
6የሰውም ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን
ማዳን ያያል።' "
7ዮሐንስም በእርሱ እጅ ሊጠመቁ
የወጡትን ሰዎች እንዲህ ይላቸው ነበር፤
"እናንት የእፉኝት ልጆች፣ ከሚመጣው ቍጣ
እንድትሸሹ ማን መከራችሁ? 8እንግዲህ
ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤ ደግሞም
በልባችሁ፣ 'አብርሃም አባታችን አለን'
ማለትን አትጀምሩ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ
ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ማስነሣት
እንደሚችል እነግራችኋለሁና። 9አሁን እንኳ
ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ መልካም
ፍሬ የማያፈራም ዛፍ ሁሉ ተቈርጦ ወደ
እሳት ይጣላል።"
10ሕዝቡም፣ "ታዲያ፣ ምን እናድርግ?"
ብለው ጠየቁት።
11ዮሐንስም፣ "ሁለት ልብስ ያለው ምንም
ለሌለው ያካፍል፤ ምግብ ያለውም እንዲሁ
ያድርግ" ብሎ መለሰላቸው።
12ቀረጥ ሰብሳቢዎችም ሊጠመቁ ወደ
እርሱ መጥተው፣ "መምህር ሆይ፤ እኛስ
ምን እናድርግ?" አሉት።
13እርሱም፣ "ከታዘዛችሁት በላይ ቀረጥ
አትሰብስቡ" አላቸው።
14ወታደሮች ደግሞ፣ "እኛስ ምን
እናድርግ?" ብለው ጠየቁት።
እርሱም፣ "የማንንም ገንዘብ በግፍ
አትንጠቁ፤ ሰውንም በሐሰት አትክሰሱ፤
ደመወዛችሁ ይብቃችሁ" አላቸው።
15ሕዝቡ በጕጕት እየተጠባበቁ ሳሉ፣
"እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?" እያሉ ሁሉም
በልባቸው ስለ ዮሐንስ ያሰላስሉ ነበር።
16ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ከእኔ
የሚበረታ ይመጣል፤ እኔም የእርሱን የጫማ

**2፥52፤ ኢየሱስም በጥበብ ... አደገ፤** በ2፥52 እና በ3፥1 መካከል የኢየሱስን ሕይወት በሚመለከት ምንም ነገር ሳይነገር በግምት ዐሥራ ስምንት ዓመት ቆይቷል። በእነዚያ ዓመታት የኢየሱስ ሕይወት ምን ይመስል ነበር? በማቴ 13፥55 እና በማር 6፥3 ላይ ከተጻፈው ሐሳብ ኢየሱስ በሰፊ ቤተ ሰብ ውስጥ እንዳደገ፣ አባቱ አናጢ እንደሆነና የአናጢነትንም ሥራ እንደተማረ እንረዳለን። ከዚህ በኋላ በወንጌሎች ውስጥ ስለ ዮሴፍ ምንም ነገር ስለማይነሣ፣ ኢየሱስ አገልግሎቱን በይፋ ከመጀመሩ በፊት ሞቶ ሊሆን ይችላል፤ ኢየሱስም እናቱን፣ ታናናሽ ወንድሞቹንና እኅቶቹን እየሠራ መርዳት ጀምሮ ይሆናል። የአናጢ ሥራ ቤት መጠገንን፣ የቤት ዕቃና ቀንበር የመሳሰሉትን የእርሻ መሣሪያዎች መሥራትን ያካትታል። በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በአካሉም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤ እግዚአብሔርም አባቱ እንደ ሆነ በሚገባ ያውቅ ነበር (ቍ 49)።
**3፥8 ለንስሓ የሚገባ ፍሬ፤** ማቴ 3፥8 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
**3፥16 በመንፈስ ቅዱስ ... ያጠምቃችኋል፤** ክርስቶስ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቁ (ከማቴ 3፥11 ጋር ያነጻጽሩ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ተለይተው የሚታወቁበት አዲሱ ምልክት ነው፤ (1) ይህ ተስፋ የተሰጠው በኢዩኤል 2፥28 ላይ ሲሆን፣ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ እውን ሆኖአል (24፥49፤ ሐሥ 1፥4-8)። ይህ ትንቢት በመጀመሪያ የተፈጸመው በበዓለ ኀምሳ

ማሰሪያ መፍታት የሚገባኝ አይደለሁም፤
እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት
ያጠምቃችኋል፤ [17]ዐውድማውን ፈጽሞ
ለማጥራትና ስንዴውንም ወደ ጐተራው
ለመክተት መንሹ በእጁ ነው፤ ገለባውን ግን
በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።" [18]ዮሐንስም
በብዙ ሌሎች የምክር ቃላት ሕዝቡን
እያስጠነቀቀ ወንጌልን ሰበከላቸው።
[19]ነገር ግን ዮሐንስ፣ የአራተኛውን ክፍል
ገዥ ሄሮድስን የወንድሙ ሚስት በነበረችው
በሄሮድያዳ ምክንያትና ስለ ሌሎች ሥራዎቹ
በገሠጸው ጊዜ፣ [20]ሄሮድስ ይህን በሌላው
ሁሉ ላይ በመጨመር፣ ዮሐንስን ወህኒ ቤት
አስገባው።

## የኢየሱስ መጠመቅና የትውልድ ሐረጉ

*3፥21፡22 ተጓ ምብ — ማቴ 3፥13-17*
*ማር 1፥9-11*
*3፥23-38 ተጓ ምብ — ማቴ 1፥1-17*

[21]ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቀ በኋላ ኢየሱስም
ተጠመቀ፤ እየጸለየም ሳለ ሰማይ ተከፈተ፤
[22]መንፈስ ቅዱስም በአካላዊ ቅርጽ እንደ
ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ ከሰማይም፣
"የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ
ይለኛል" የሚል ድምፅ መጣ።
[23]ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር ዕድሜው
ሠላሳ ዓመት ያህል ነበር፤ ሕዝቡም እንደ
መሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ፣
የኤሊ ልጅ፣ [24]የማቲ ልጅ፣
የሌዊ ልጅ፣ የሚልኪ ልጅ፣
የዮና ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣
[25]የማታትዩ ልጅ፣ የአሞጽ ልጅ፣
የናሆም ልጅ፣ የኤሲሊም ልጅ፣
የናጌ ልጅ፣ [26]የማአት ልጅ፣
የማታትዩ ልጅ፣ የሴሜይ ልጅ፣
የዮሴፍ ልጅ፣ የዮዳ ልጅ፣
[27]የዮናን ልጅ፣ የሬስ ልጅ፣
የዘሩባቤል ልጅ፣ የሰላትያል ልጅ፣
የኔሪ ልጅ፣ [28]የሚልኪ ልጅ፣
የሐዲ ልጅ፣ የዮሳስ ልጅ፣ የቆሳም
ልጅ፣
የኤልሞዳም ልጅ፣ የኤር ልጅ፣
[29]የዮሴዕ ልጅ፣ የኤልዓዘር ልጅ፣
የዮራም ልጅ፣ የማጣት ልጅ፣
የሌዊ ልጅ፣ [30]የስምዖን ልጅ፣
የይሁዳ ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ፣
የዮናም ልጅ፣ የኤልያቄም ልጅ፣
[31]የሜልያ ልጅ፣ የማይናን ልጅ፣
የማጣት ልጅ፣ የናታን ልጅ፣
የዳዊት ልጅ፣ [32]የእሴይ ልጅ፣
የኢዮቤድ ልጅ፣ የቦዔዝ ልጅ፣
የሰልሞን[a] ልጅ፣ የነአሶን ልጅ፣
[33]የአሚናዳብ ልጅ፣ የአራም[b] ልጅ፣
የአሮኒ ልጅ፣ የኤስሮም ልጅ፣
የፋሬስ ልጅ፣
የይሁዳ ልጅ፣ [34]የያዕቆብ ልጅ፣
የይስሐቅ ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣
የታራ ልጅ፣ የናኮር ልጅ፣
[35]የሴሮህ ልጅ፣ የራጋው[c] ልጅ፣
የፋሌቅ ልጅ፣ የአቤር ልጅ፣
የሳላ ልጅ፣ [36]የቃይንም ልጅ፣
የአርፋክስድ ልጅ፣ የሴም ልጅ፣
የኖኅ ልጅ፣ የላሜህ ልጅ፣
[37]የማቱሳላ ልጅ፣ የሄኖክ ልጅ፣
የያሬድ ልጅ፣ የመላልኤል ልጅ፣
የቃይናን ልጅ፣ [38]የሄኖስ ልጅ፣
የሤት ልጅ፣ የአዳም ልጅ፣
የእግዚአብሔር ልጅ።

## የኢየሱስ መፈተን

*4፥1-13 ተጓ ምብ — ማቴ 4፥1-11፤*
*ማር 1፥12፡13*

4 ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮ
ርዳኖስ እንደ ተመለሰ መንፈስ ወደ

3፥17 ኢሳ30፥24፤ ማቴ13፥30፤ 25፥41
3፥19 ቀላ፥1፤ ማቴ14፥1
3፥20 ማቴ14፥3፡4
3፥21 ማቴ14፥23፤ ማር1፥35፤ 6፥46፤ ሉቃ5፥16፤ 6፥12፤ 9፥18፡28፤ 11፥1
3፥22 ኢሳ42፥1፤ ማቴ3፥17፤ ዮሐ1፥32፡33፤ ሐሥ10፥38
3፥23 ማቴ4፥17፤ ሉቃ1፥27፤ ሐሥ1፥1
3፥27 ማቴ1፥12
3፥31 2ሳሙ5፥14፤ 1ዜና3፥5
3፥33 ሩት4፥18-22፤ 1ዜና2፥10-12
3፥34 ዘፍ11፥24፡26
3፥36 ዘፍ5፥28-32፤ 11፥12
3፥37 ዘፍ5፥12-25
3፥38 ዘፍ5፥1፡2፡6-9
4፥1 ቀላ14፥18፤ ሕዝ37፥1፤ ሉቃ1፥15፡35፤ 2፥27፤ 3፥3፡16፡21፡22፤ 10፥21

*[a]3፥32* አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሳላ ይላሉ ሌሎች ቅጆች ይለያያሉ
*[b]3፥33* አንዳንድ ቅጆች የአሚናዳብ ልጅ የአዲም ልጅ የአርኒ ልጅ ይላሉ፤
*[c]3፥35* የግሪኩ ቅጅ ‹የራጋው›

ቀን ነው (ሐሥ 2፥4 እና ማብ ይመ)።

(2) የክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ አገልግሎት በቀጣይነት በአሁኑም ዘመን ያለ አገልግሎት ነው (በገጽ 1664 ላይ፣ «*በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህም በግሪኩ መጽሐፍ በዮሐ 1፥33 ላይ፣ «በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው» በማለት የተጠቀሰውን ሐሳብ ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል። ይህ ሐረግ የአሁን ጊዜን የሚያመለክት «ሆ. ባፕቲዞ» የሚል ቦዝ አንቀጽ የያዘ ሲሆን፣ ትርጕሙም «ዛሬም የሚያጠምቀው» ማለት ነው። ስለዚህ በሉቃስና በዮሐንስ ወንጌል ላይ የተጻፉት ጥቅሶች በበዓለ ኀምሳ ቀን የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ብቻ የሚያመለክቱ ሳይሆን፣ በአሁኑ ዘመንም ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሚናውና አገልግሎቱ መቀጠሉን የሚያመለክቱ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ... በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና» (ሐሥ 2፥39) ይላል።

**3፥17 ገለባውን ግን ... እሳት ያቃጥለዋል፤** ለሠሩት ኀጢአት ንስሓ ገብተው ክርስቶስንና ቃሉን የሚቀበሉ ሰዎች፣ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ። በሕይወታቸው ኀጢአት የነገሠባቸው ሰዎች ግን በማይጠፋ እሳት ይቀጣሉ (ማቴ 10፥28 እና ማብ ይመ)።

**3፥22 መንፈስ ቅዱስም ... በእርሱ ላይ ወረደ፤** በመጀመሪያም በመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰውና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሰው ያደረው ኢየሱስ (1፥35) አሁንም ለአገልግሎቱ የተቀባውና ኀይልን የተቀበለው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቁ ምን ያህል የጐላ ስፍራ እንዳለው ይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1559 ላይ፣ «*ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥23-37 ይህ ክፍል የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ የሚያመለክት ነው፤** ማቴ 1፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**4፥1 ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፤** ኢየሱስ የሰይጣንን ፈተና ለመጋፈጥ የሄደው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተሞልቶና በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ነው። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ሕይወት ላይ የነበረውን ጉልህ ሚና በሚመለከት በገጽ 1559 ላይ፣ «*ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

ሉቃ 24፥49 በረሓ ወሰደው፤ 2በዚያም አርባ ቀን በዲያ
ብሎስ ተፈተነ፤ በእነዚያም ቀናት ምንም
ሳይበላ ቈይቶ በመጨረሻ ተራበ።
3ዲያብሎስም፣ "የእግዚአብሔር ልጅ
ከሆንህ፣ እስቲ ይህ ድንጋይ እንጀራ
እንዲሆን እዘዘው" አለው።
4ኢየሱስም፣ " 'ሰው በእንጀራ ብቻ
አይኖርም' ተብሎ ተጽፎአል" ብሎ
መለሰለት።
5ከዚያም ዲያብሎስ ወደ አንድ ከፍታ
ቦታ አውጥቶት የዓለምን መንግሥታት
ሁሉ በቅጽበት አሳየው፤ 6እንዲህም አለው፤
"የእነዚህ መንግሥታት ሥልጣንና ክብር
ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶአል፤ እኔም ለምወደው
ስለምሰጥ፣ ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ 7ስለዚህ
ብትሰግድልኝ ይህ ሁሉ የአንተ ይሆናል።"
8ኢየሱስም መልሶ፣ " 'ለጌታ ለአምላክህ
ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ' ተብሎ
ተጽፎአል" አለው።
9ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ
በቤተ መቅደስ ጕልላት ላይ አቆመውና
እንዲህ አለው፤ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣
እስቲ ራስህን ከዚህ ወደ ታች ወርውር፤
10ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤
" 'ይጠብቁህ ዘንድ፣

4፥2 ዘፀ34፥28፤ 1ነገ19፥8፤ ዕብ4፥15
4፥3 ማቴ4፥3
4፥4 ዘዳ8፥3
4፥5 ማቴ24፥14
4፥6 ዮሐ12፥31፤ 14፥30፤ 1ዮሐ5፥19
4፥8 ዘዳ6፥13
4፥11 መዝ91፥11:12
4፥12 ዘዳ6፥16
4፥13 ዮሐ14፥30፤ ዕብ4፥15
4፥14 ማቴ4፥12፤ 9፥26
4፥15 ማቴ4፥23
4፥16 ማቴ2፥23፤ 13፥54፤ 1ጢሞ4፥13
4፥18 ማር16፥15፤ ዮሐ3፥34

መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋል፤
11እግርህም ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ፣
በእጆቻቸው ወደ ላይ አንሥተው
ይይዙሃል።' "
12ኢየሱስም፣ " 'ጌታ አምላክህን
አትፈታተነው' ተብሎአል" ብሎ
መለሰለት።
13ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ
በኋላ ሌላ አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ሉቃ 4፥36
ከእርሱ ተለየ።

## ኢየሱስ በናዝሬት ተቀባይነት ማጣቱ

14ኢየሱስም በመንፈስ ኀይል ወደ ገሊላ
ተመለሰ፤ ዝናውም በአካባቢው ባለው አገር
ሁሉ ወጣ። 15እርሱም በምኵራባቸው ያስተምር
ነበር፤ ሰውም ሁሉ ያመሰግነው ነበር።
16ከዚያም ወዳደገበት ከተማ ወደ ናዝሬት
መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ወደ ምኵራብ
ገባ፤ ሊያነብም ተነሥቶ ቆመ። 17የነቢዩ
ኢሳይያስ ጥቅልል መጽሐፍም ተሰጠው፤
ጥቅልሉንም መጽሐፍ በተረተረው ጊዜ
እንዲህ ተብሎ የተጻፈበትን ክፍል አገኘ፤
18"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤
ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣
እርሱ ቀብቶኛልና፤

**4፥2 በዲያብሎስ ተፈተነ፤** የኢየሱስ መፈተን አንዱና ዋና ገጽታ እርሱ ምን ዐይነት መሲሕ ይሆናል፣ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ቅባቱንስ እንዴት ይጠቀምበታል? በሚለው ሐሳብ ዙሪያ ላይ ያተኮረ ነው፤ (1) ኢየሱስ መስቀሉንና የሥቃዩን መንገድ ከመምረጥ ይልቅ (ቍ 5-8) አስገራሚ መሲሕ (ቍ 9-11) መሆኑን ይገልጽ ዘንድ ሕዝቡ የነበረውን ከፍተኛ ግምት ተቀብሎ በመንግሥታት ላይ ክብርንና ኀይልን በመቀዳጀት፣ ቅባቱንና ሥልጣኑን ለራሱ ጥቅም እንዲያውል በሚያደርግ ሁኔታ ተፈተነ (ቍ 3-4)፤ (2) የተሰጣቸውን ቅባት፣ ሥልጣንና ችሎታ ለራሳቸው ጥቅም በማዋል የራሳቸውን ክብርና መንግሥት ይመሠርቱ ዘንድ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ደስ ያሰኙ ዘንድ ዛሬም ሰይጣን ክርስቲያን መሪዎችን ከመፈተን ወደ ኋላ አይልም:: የራስን ጥቅም በመፈለግ ከሰይጣን ጋር የሚደራደሩ ሰዎች በመሠረቱ የሰይጣንን ጌትነት አሜን ብለው የተቀበሉ ናቸው::

**4፥2 ምንም ሳይበላ፤** ማቴ 4፥2 እና ጾምን በሚመለከት የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**4፥4 በእንጀራ ብቻ አይኖርም፤** ኢየሱስ ከሁሉም ነገር በላይ በእግዚአብሔር ቃል እንደሚኖር በመናገር የሰይጣንን ፈተና አሸነፈ (ከዘዳ 8፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (1) ኢየሱስ ለሕይወት አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔርና በእርሱ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይገልጻል (ዮሐ 4፥34):: ከእግዚአብሔር መንገድና ዐላማ ውጭ ድል ለማድረግ፣ ደስታን ወይም ሀብትን ለማግኘት መጣር ወደ ከፋ ሐዘንና ውድቀት ያደርሳል፤ (2) ኢየሱስ ይህን እውነት የገለጸው፣ ከሁሉ አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥት ይኸውም የእግዚአብሔር ሕግ፣ የእግዚአብሔር ሥራና ኀይል በሕይወታችን ይገለጽ ዘንድ መፈለግ እንዳለብን በሚያስተምርበት ጊዜ ነው:: ይህ ሲሆን ብቻ ነው ሌሎች ለሕይወታችን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች እንደ ፈቃዱና እንደ መንገዱ የሚሰጡን (ማቴ 5፥6 እና ማብ፤ 6፥33 እና ማብ ይመ)::

**4፥5 የዓለምን መንግሥታት፤** ሰይጣን በዓለም መንግሥታት ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደሚሰጠው በመግለጽ፣ ኢየሱስን ፈተነው፤ ይህንንም ሐሳብ ኢየሱስ ውድቅ አደረገው፤ (1) በዚህ ዘመን ያለው የኢየሱስ መንግሥት ከዚህ ዓለም አይደለም (ዮሐ 18፥36-37):: ኢየሱስ የዓለምን ስልት ተከትሎ በመደራደር፣ ምድራዊ ኀይልን በመጠቀም፣ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ፣ ዐመፅን በማነሣሣት፣ ታዋቂነትንና ክብርን እንዲሁም ዝናን ያተርፍ ዘንድ በማሰብ ለራሱ መንግሥት ለመመሥረት አልፈለም:: (2) የኢየሱስ መንግሥት፣ ከዓለም መንግሥት ውስጥ የእርሱ እንዲሆኑና ለእርሱ እንዲኖሩ በወሰኑ ሕዝብ ልብ ውስጥ የሚገዛ መንግሥት ነው፤ ሰማያዊ መንግሥትም እንደመሆኑ፣ (ሀ) መከራ መቀበልን፣ ራስን መካድን፣ በትሕትናና በታዛዥነት መመላለስን የሚጠይቅ ነው፤ (ለ) ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ በመስጠትና እርሱን በመታዘዝ፣ ሰውነታችንን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ ይኖርብናል (ሮሜ 12፥1)፤ (ሐ) ሙሉ መንፈሳዊ የጦር ዕቃ በመልበስ ኀጢአትን፣ ሰይጣንንና እርሱም የሚያመጣውን ፈተና መቃወም ያስፈልጋል (ኤፌ 6፥10-12)፤ (መ) ዓለምን ከመምሰል መራቅን ይጠይቃል (ሮሜ 12፥2):: በገጽ 1443 ላይ፣ *“የእግዚአብሔር መንግሥት”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**4፥9፤** ማቴ 4፥10 እና ኋሰይጣንኝ በሚለው ርእስ ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**4፥10 በዚህ ስፍራ ዲያብሎስ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል መጠቀሙን እንመለከታለን፤** ማቴ 4፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**4፥18 የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤** በገጽ 1559 ላይ፣ *“ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**4፥18 እርሱ ቀብቶኛልና፤** ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ የሚሰጠው አገልግሎት ዐላማው

ለታሰሩት መፈታትን፣
ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣
የተጨቈኑትን ነጻ እንዳወጣ፣
19የተወደደችውንም የጌታን ዓመት
እንዳውጅ ልኮኛል።"
20ከዚያም መጽሐፉን ጠቅልሎ ለአገል ጋዩ
መልሶ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኵራብ
የነበሩትም ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱት
ነበር። 21እርሱም፣ "ይህ በጆሮአችሁ
የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ"
ይላቸው ጀመር።
22ሁሉም ስለ እርሱ በበጎ ይናገሩ ነበር፤
ደግሞም ከአንደበቱ በሚወጣ የጸጋ ቃል
እየተገረሙ፣ "ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለ
ምን?" ይሉ ነበር።
23እርሱም፣ " 'ባለ መድኀኒት ሆይ፤
ራስህን ፈውስ፤ በቅፍርናሆም ስታደርግ
የሰማነውን ነገር እዚህ በራስህ ከተማ
ደግሞ አድ ርግ' የሚለውን ምሳሌ
እንደምትጠቅሱብኝ ጥርጥር የለውም"
አላቸው።
24ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ነቢይ በገዛ አገሩ አይከበርም።
25ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይ ሦስት
ዓመት ከመንፈቅ ተዘግቶ ጽኑ ራብ በምድሪቱ
ሁሉ ላይ በነበረበት በኤልያስ ዘመን፣ ብዙ
መበለቶች በእስራኤል ነበሩ፤ 26ኤልያስ
ከእነዚህ መካከል ወደ አንዱም አልተላከም፤
ነገር ግን በሲዶና አገር በሰራፕታ ወደ
ነበረችው መበለት ተላከ። 27በነ ቢዩ በኤልሳዕ
ዘመንም በእስራኤል ብዙ ለምጻሞች*
ነበሩ፤ ነገር ግን ከሶርያዊው ከንዕማን በቀር
ከእነዚያ መካከል ማንም አልነጻም።"
28በምኵራብ የነበሩ ሰዎች ሁሉ
ይህን በሰሙ ጊዜ በቍጣ ገነፈሉ፤
29ከተቀመጡበትም ተነሥተው ከከተማው
አስወጡት፤ ቍል ቍል ሊጥሉትም
ከተማቸው ወደ ተሠራችበት ኰረብታ
አፋፍ ወሰዱት፤ 30እርሱ ግን በመካከላቸው
ሰንጥቆ ሄደ።

4፥19 ዘሌ25፥10፤ መዝ102፥20፤ 103፥6፤ ኢሳ42፥7፤ 49፥8፡9፤ 58፥6፤ 61፥1፡2
4፥20 ቍ17፤ ማቴ26፥55
4፥21 ማቴ1፥22
4፥22 ማቴ13፥54፡55፤ ዮሐ6፥42፤ 7፥15
4፥23 ቍ16፤ ማቴ2፥23፤ ማር1፥21-28፤ 2፥1-12
4፥24 ማቴ13፥57፤ ዮሐ4፥44
4፥25 1ነገ17፥1፤ 18፥1፤ ያዕ5፥17፡18፤ ራእ11፥6
4፥26 1ነገ17፥8-16፤ ማቴ11፥21
4፥27 2ነገ5፥1-14
4፥29 ዘኍ15፥35፤ ሐሥ7፥58፤ ዕብ13፥12
4፥30 ዮሐ8፥59፤ 10፥39
4፥31 ቍ23፤ ማቴ4፥13
4፥32 ቍ36፤ ማቴ7፥28፡29
4፥34 ቍ41፤ ማቴ8፥29፤ ማር1፥24፤ ያዕ2፥19
4፥35 ቍ39፡41፤ ማቴ8፥26፤ ሉቃ8፥24
4፥36 ቍ32፤ ማቴ7፥28፡29፤ 10፥1
4፥37 ቍ14፤ ማቴ9፥26
4፥39 ቍ35፡41
4፥40 ማቴ4፥23፤ ማር5፥23

## ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ አስወጣ

*4፥31-37 ተጓ ምብ — ማር 1፥21-28*

31ከዚያም በገሊላ አውራጃ ወደምትገኘው
ከተማ ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፤ በዚያም
በሰንበት ዕለት ሕዝቡን ያስተምር
ጀመር፤ 32የሚናገረው በሥልጣን ስለ ነበር
በትምህርቱ ተደነቁ።
33በምኵራብም የርኩስ ጋኔን መንፈስ
ያደረበት ሰው ነበረ፤ እርሱም ከፍ ባለ ድምፅ
ጮኸ፣ 34"ወ×! የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፤
ምን የሚያገናኘን ጉዳይ አለ? የመጣኸው
ልታጠፋን ነውን? አንተ ማን እንደ ሆንህ
ዐውቃለሁ፤ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ!"
አለው።
35ኢየሱስም፣ "ጸጥ ብለህ ከዚህ ሰው
ውጣ!" ብሎ ገሠጸው። ጋኔኑም ሰውየውን
በሕዝቡ ሁሉ ፊት ጣለውና ምንም ጕዳት
ሳያደርስበት ለቅቶ ወጣ።
36ሰዎቹም ሁሉ ተገረሙ፤ እርስ
በእርሳቸውም፣ "ለመሆኑ ይህ ትምህርት
ምንድን ነው? በሥልጣንና በኀይል ርኩሳን
መናፍ ስትን ያዛል፤ እነርሱም ይወጣሉ" ሉቃ
ተባባሉ። 37የእርሱም ዝና በአካባቢው 10፥17-19
ወዳለው ስፍራ ሁሉ ወጣ።

## ኢየሱስ ብዙ በሽተኞችን ፈወሰ

*4፥38-41 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥14-17*
*4፥38-43 ተጓ ምብ — ማር 1፥29-38*

38ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከምኵራብ ወጥቶ
ወደ ስምዖን ቤት ገባ። የስምዖንም አማት
ኀይለኛ ትኵሳት ይዞአት ታማ ነበር፤ እን
ዲፈውሳትም ስለ እርሷ ለመኑት። 39 እርሱም
ወደ ተኛችበት ጠጋ ብሎ በማጐንበስ
ትኵሳቱን ገሠጸው፤ ትኵሳቱም ለቀቃትና
ወዲያው ተነሥታ አስተናገደቻቸው።
40ፀሓይ መጥለቂያ ላይም፣ የተለያየ

*4፥27 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያየ የቈዳ በሽታዎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል

ምን እንደሆን እዚህ ላይ ይገልጻል፡ (1) ለድኾች፣ ለምስኪኖች፣ በመከራ ውስጥ ላሉት፣ ለትሑታን፣ መንፈሳቸው ለተሰበረ፣ ልባቸው ላዘነና «በቃሉም ለሚንቀጠቀጡት» ወንጌልን መስበክ (ኢሳ 61፥1-3 እናማብ እንዲሁም ኢሳ 66፥2 እና ማብ ይመ)፤ (2) የተቀጠቀጡትንና የተጨቈኑትን ለማዳን ሲሆን፣ ይህም የሰውን ሁለንተና ይኸውም አካላዊና መንፈሳዊ ፈውስን ያካተተ ነው፤ (3) የእግዚአብሔርን ወንጌል እውነት ማየት ይችሉ ዘንድ በዓለምና በሰይጣን የታወሩትን ሰዎች መንፈሳዊ ዐይን መክፈት (ከዮሐ 9፥39 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (4) ከሰይጣን ሥልጣን፣ ከኀጢአት፣ ከፍርሃትና ከኀሊና ወቀሳ ተላቀው እውነተኛ ነጻነትና ድነት የሚያገኙበትን ጊዜ ማወጅ (ከዮሐ 8፥36፤ ከሐሥ 26፥18 ጋር ያነጻጽሩ)።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሁሉ በዚህ ሁኔታ የክርስቶስ አገልግሎት ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ተጠርተዋል። ይህም ይሆን ዘንድ ከኀጢአትና ከሰይጣን ኀይል የተነሣ የተፈጠረውን ይኸውም ለክፉ ነገር ባሪያ መሆንን፣ የልብ ስብራትን፣ መንፈሳዊ ዕውርነትን፣ የአእምሮ ጭንቀትንና ሐዘንን የመሳሰሉትን ከባድ ሥቃይና ሐዘን በጥልቀት መረዳት አስፈላጊ ነው።

**4፥33 የርኩስ ... መንፈስ፤** መሲሕነቱን ካስታወቀ በኋላ ኢየሱስ በቀዳሚነት ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ የአጋንንትን አሠራር ፊት ለፊት መቃወም እንደነበር ሉቃስ በጽሑፉ ይገልጻል፤ (1) ኢየሱስ፣ በአገልግሎቱ ውስጥ ዋነኛ ትኵረቱ የሰይጣንን ሥራ ማፍረስ ነበር (1ዮሐ 3፥8)። የሰይጣንን መንግሥት ፊት ለፊት ሳንቃወም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ሊሰፋና ሊታወቅ አይችልም (ማቴ 12፥28 ይመ፤ በገጽ 1443 ላይ፣ «*የእግዚአብሔር መንግሥት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ (2) ኀጢአተኞችን ከኀጢአት ባርነትና ከአጋንንት አሠራር ነጻ በማውጣት የከፋውን ኀይል ፊት ለፊት አለመቃወም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሕዝቡ መካከል መገለጡ እንዳቆመ የሚያሳይ ትክክለኛ ምልክት ነው (በገጽ 1499 ላይ፣ «*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥40 ፈወሳቸው፤** ማቴ 4፥23 እና ማብራሪያውን

ሕመም ያደረባቸውን ሰዎች ሁሉ ወደ
እርሱ አመጡ፤ እርሱም በእያንዳንዳቸው
ላይ እጁን ጭኖ ፈወሳቸው። 41አጋንንትም
ደግሞ፣ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!"
እያሉና እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ወጡ።
እርሱ ግን ገሠጻቸው፤ ክርስቶስ[*] መሆኑንም
ያውቁ ስለ ነበር፣ እንዳች እንዲናገሩ
አልፈቀደላቸውም።
42ሲነጋም ኢየሱስ ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ ሄደ፤ ሕዝቡም ይፈልጉት ነበር፤ እርሱ
ወዳለበትም ቦታ መጡ፤ ከእነርሱ ተለይቶ
እንዳይሄድ ሊከለክሉት ሞከሩ። 43እርሱ ግን፣
"ወደ ሌሎቹም ከተሞች ሄጄ የእግዚአብሔርን
መንግሥት ወንጌል መስበክ ይገባኛል፤
የተላክሁት ለዚሁ ዐላማ ነውና" አላቸው።
44በይሁዳ ምኵራቦችም መስበኩን ቀጠለ።

## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ተጠሩ

*5፥1-11 ተጓ ምብ — ማቴ 4፥18-22፤ ማር 1፥16-20፡ ዮሐ 1፥40-42*

5 ሕዝቡ ዙሪያውን እያጨናነቁት
የሚያስተምረውን የእግዚአብሔርን ቃል
ሲሰሙ፣ ኢየሱስ በጌንሳሬጥ ሐይቅ[†] አጠገብ
ቆሞ ነበር፤ 2በዚህ ጊዜ ሁለት ጀልባዎች
በሐይቁ ዳርቻ ቆመው አየ፤ ዓሣ አጥማጆቹ
ግን ከጀልባዎቹ ወርደው መረባቸውን ያጥቡ
ነበር። 3ከጀልባዎቹም መካከል የስምዖን ወደ
ነበረችው ገብቶ፣ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ
እንዲያደርጋት ለመነው፤ ከዚያም ጀልባዋ
ላይ ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ጀመር።
4ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ስምዖንን፤ "ወደ
ጥልቁ ውሃ ፈቀቅ በልና ዓሣ ለመያዝ
መረባችሁን ጣሉ" አለው።
5ስምዖንም መልሶ፣ "መምህር ሆይ፤
ሌሊቱን ሙሉ ስንደክም አድረን ምንም
አልያዝንም፤ አንተ ካልህ ግን መረቦቹን
እጥላለሁ" አለው።
6እንደዚያም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ
ያዙ፤ መረባቸውም ይበጣጠስ ጀመር። 7በሌላ
ጀልባ የነበሩት ባልንጀሮቻቸው መጥተው
እንዲያግዟቸውም በምልክት ጠሯቸው፤
እነርሱም መጥተው ሁለቱን ጀልባዎች በዓሣ
ሞሏቸው፣ ጀልባዎቹም መስመጥ ጀመሩ።
8ስምዖን ጴጥሮስም ይህን ባየ ጊዜ
በኢየሱስ ጕልበት ላይ ወድቆ፣ "ጌታ ሆይ፤
እኔ ኀጢአተኛ ሰው ነኝና ከእኔ ተለይ"
አለው። 9ይህንን ያለው እርሱና ከእርሱ ጋር
የነበሩት በያዙት ዓሣ ብዛት ስለ ተደነቁ
ነው፤ 10ደግሞም የስምዖን ባልንጀሮች
የነበሩት የዘብዴዎስ ልጆች፣ ያዕቆብና
ዮሐንስም ተደነቁ።
ኢየሱስም ስምዖንን፣ "አትፍራ፤
ከእንግዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ"
አለው። 11እነርሱም ጀልባዎቹን ወደ ምድር
ካስጠጉ በኋላ ሁሉን ትተው ተከተሉት።

## ለምጻሙ ሰው

*5፥12-14 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥2-4፤ ማር 1፥40-44*

12ኢየሱስ ከከተሞች በአንዱ በነበረበት
ጊዜ፣ አንድ ለምጽ የወረሰው[‡] ሰው በዚያው
ከተማ ነበር፤ ይህ ሰው ኢየሱስን ባየው ጊዜ
በፊቱ ተደፋና፣ "ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድ እኮ
ልታነጻኝ ትችላለህ" ብሎ ለመነው።
13ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣
"እፈቅዳለሁ፤ ንጻ!" አለው፤ ወዲያውም
ለምጹ ጠፋለት።
14ኢየሱስም፣ "ይህን ለማንም አትናገር፤
ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤
ለእነርሱ ምስክር እንዲሆንም ስለ መንጻትህ
ሙሴ ያዘዘውን መሥዋዕት አቅርብ" ሲል
አዘዘው።
15ይሁን እንጂ ስለ እርሱ የሚወራው ወሬ
ይበልጥ እየሰፋ ሄደ፤ እጅግ ብዙ ሰዎችም
እርሱ የሚናገረውን ለመስማትና ካለባቸው
ደዌ ለመፈወስ ይሰበሰቡ ነበር። 16ኢየሱስ

4፥41 ቍ35፡ ማቴ4፥3፡ 8፥4
4፥43 ማቴ3፥2
4፥44 ማቴ4፥23
5፥1 ማር4፥14፡ ዕብ4፥12
5፥3 ማቴ13፥2
5፥4 ዮሐ21፥6
5፥5 ሉቃ8፥24፡45፡ 9፥33፡49፡ 17፥13፡ ዮሐ21፥3
5፥6 ዮሐ21፥11
5፥8 ዘፍ18፥27፡ ኢዮ42፥6፡ ኢሳ6፥5
5፥10 ማቴ14፥27
5፥11 ቍ28፡ ማቴ4፥19
5፥12 ማቴ8፥2
5፥14 ዘሌ14፥2-32፡ ማቴ8፥4
5፥15 ማቴ9፥26
5፥16 ሉቃ3፥21

*[*] 4፥41 ወይም መሲሕ*
*[†] 5፥1 የገሊላ ባሕር ነው*
*[‡] 5፥12 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቈዳ በሽታዎችንም ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል።*

ይመልከቱ፤ በገጽ 1433 ላይ፣ *«መለኮታዊ ፈውስ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።
**5፥10 ሰውን የምታጠምድ፤** ማቴ 4፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
**5፥16 ኢየሱስ ... ይጸልይ ነበር፤** (1) በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ጸሎት ምን ያህል ወሳኝ ሥፍራ እንደነበረው፣ ከሌሎች የወንጌል ጸሐፊዎች ይልቅ ሉቃስ በአጽንዖት ይገልጻል። በዮርዳኖስ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ በወረደ ጊዜ እርሱ እየጸለየ ነበር (3፥21)፤ አንዳንድ ጊዜ ከሕዝቡ ገለል ብሎ ይጸልይ ነበር (5፥16)፤ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ከመምረጡ በፊት ሌሊቱን ሁሉ ሲጸልይ አድሮአል (6፥12)፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን አንድ አስፈላጊ ጥያቄ ከመጠየቁ በፊት ብቻውን ሲጸልይ ነበር (9፥18)። ኢየሱስ ከዉላጤ ራእዩ በፊት ማለትም መልኩ ከመለወጡ ቀደም ብሎ «ሊጸልይ» ወደ ተራራው ወጣ (9፥28)፤ የፊቱም መልክ የተለወጠው «በመጸለይ ላይ እንዳለ» ነው (9፥29)። ደቀ መዛሙርቱ ጠይቀው ጌታ ካስተማረው ጸሎት በፊትም እየጸለየ ነበር (11፥1)። በጌቴሴማኒም እጅግ አጥብቆ ጸልዮአል (22፥24)፤ በመስቀል ላይ ሆኖ ስለ ሌሎች ጸልዮአል (23፥34)። ከመሞቱ በፊት በመጨረሻ የተናገረውም የጸሎት ቃል ነበር (23፥46)። ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ እንደ ጸለየ ሉቃስ ጽፎአል (24፥30)፤ (2) በሌሎች ወንጌሎች ውስጥ የኢየሱስ ሕይወት ምን እንደሚመስል በምንመረምርበት ጊዜ፣ ኢየሱስ «እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤» (ማቴ 11፥25-28) ብሎ ለሰዎች ጥሪ ከማድረጉ በፊት እንደ ጸለየ እናያለን (ማቴ 11፥25-28)። ኢየሱስ በአልዓዛር መቃብር ላይ (ዮሐ 11፥41-42) እንዲሁም የጌታን እራት የመውሰድ ሥርዐት በተጀመረበት ጊዜ (ዮሐ 13፣ ሉቃ 22) ጸልዮአል (ዮሐ 17)። ስለ ኢየሱስ የጸሎት ሕይወት በተጨማሪ ለመረዳት ማቴ 14፥23 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ግን ብዙ ጊዜ ወደ ገለልተኛ ስፍራ ወጥቶ
ይጸልይ ነበር።

## ኢየሱስ ሽባውን ሰው ፈወሰ

*5፥18-26 ተጓ ምብ — ማቴ 9፥2-8፤*
*ማር 2፥3-12*

17አንድ ቀን ኢየሱስ እያስተማረ ነበር፤
በዚያም ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮች ሁሉ
እንዲሁም ከኢየሩሳሌም የመጡ ፈሪሳው
ያንና የሕግ መምህራን ተቀምጠው ነበር፤
ይፈውስም ዘንድ የጌታ ኀይል ከእርሱ ጋር
ነበረ። 18በዚያን ጊዜም፣ ሰዎች አንድ ሽባ
በዐልጋ ተሸክመው አመጡ፤ ኢየሱስ ፊት
ለማኖርም ወደ ቤት ሊያስገቡት ሞከሩ፤
19ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ቤቱ ውስጥ ማስ
ገባት ስላቃታቸው፣ ጣሪው ላይ ወጥተው
የቤቱን ክዳን በመንደል በሽተኛውን
ከነዐልጋው በሕዝቡ መካከል ቀጥታ ኢየሱስ
ፊት አወረዱት።
20ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ፣ "አንተ
ሰው፤ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል" አለው።
21ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም፣ "ይህ
አምላክን በመዳፈር እንዲህ የሚናገር
ማን ነው? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር
ኀጢአትን ሊያ ስተስረይ ማን ይችላል?"
ብለው ያስቡ ጀመር።
22ኢየሱስም ሐሳባቸውን ስለ ተረዳ
እንዲህ አላቸው፤ "ለምን በልባችሁ እንዲህ
ታስ ባላችሁ? 23'ኀጢአትህ ተሰረየችልህ'
ከማለትና 'ተነሥተህ ሂድ' ከማለት የትኛው
ይቀላል? 24ነገር ግን ይህን ያልሁት የሰው
ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ለማስተስረይ
ሥል ጣን እንዳለው ታውቁ ዘንድ ነው።"
ከዚያም ሽባውን ሰው፣ "ተነሥተህ ዐልጋህን
ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ እልሃለሁ" አለው።
25እርሱም ወዲያው ተነሥቶ በፊታቸው
ቆመ፤ ተኝቶበት የነበረውንም ተሸክሞ፣
እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ ሄደ።

5፥17 ማቴ15፥1፡ ማር5፥30፤ ሉቃ2፥46፤ 6፥19
5፥20 ሉቃ7፥48፡49
5፥21 ኢሳ43፥25
5፥24 ማቴ8፥20
5፥26 ማቴ9፥8
5፥27 ማቴ4፥19
5፥28 ቍ11፤ ማቴ4፥19
5፥29 ሉቃ15፥1
5፥30 ማቴ9፥11፤ ሐሥ23፥9
5፥32 ዮሐ3፥17
5፥33 ሉቃ7፥18፤ ዮሐ1፥35፤ 3፥25፡26
5፥34 ዮሐ3፥29
5፥35 ሉቃ9፥22፤ 17፥22፤ ዮሐ16፥5-7

26በዚህ ጊዜ ሁሉንም መገረም ያዛቸው፤
እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ "ዛሬስ ድንቅ
ነገር አየን" እያሉ በፍርሀት ተዋጡ።

## የሌዊ መጠራት

*5፥27-32 ተጓ ምብ — ማቴ 9፥9-13፤*
*ማር 2፥14-17*

27ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ
ሄደ፤ ሌዊ የተባለ አንድ ቀረጥ ሰብሳቢም
በቀረጥ መቀበያው ቦታ ተቀምጦ አየውና፣
"ተከተለኝ" አለው፤ 28እርሱም ሁሉን ትቶ
ተነሥቶ ተከተለው።
29ሌዊም ለኢየሱስ በቤቱ ትልቅ ግብዣ
አደረገ፤ ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ሌሎች
ሰዎችም ከእነርሱ ጋር በማእድ ተቀምጠው
ነበር። 30ፈሪሳውያንና ጸሐፍታቸውም
"ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና 'ከኀጢአተኞች' ጋር
የምትበሉትና የምትጠጡት ለምንድን ነው?"
እያሉ በደቀ መዛሙርቱ ላይ አጕረመረሙ።
31ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም
አያስፈልጋቸውም፤ 32እኔም ኀጢአተኞችን
ወደ ንስሓ ልመልስ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ
አልመጣሁም።"

## ኢየሱስ ስለ ጾም ተጠየቀ

*5፥33-39 ተጓ ምብ — ማቴ 9፥14-17፤*
*ማር 2፥18-22*

33እነርሱም፣ "የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት
አብዛኛውን ጊዜ ይጾማሉ፤ ይጸልያሉ፤
የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርትም እንደዚሁ
ያደርጋሉ፤ የአንተዎቹ ግን ዘወትር
ይበላሉ፤ ይጠጣሉ" አሉት።
34ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ሙሽራው
አብሮአቸው እያለ ዕድምተኞቹ እንዲጾሙ
ማድረግ ይቻላልን? 35ነገር ግን ሙሽራው
ከእነርሱ የሚወሰድበት ቀን ይመጣል፤
በዚያን ጊዜ ይጾማሉ።"

---

**5፥18 አንድ ሽባ ... ተሸክመው፤** ሽባውን ወደ ኢየሱስ ለማምጣት ካደረጉት ውሳኔ እንደምንረዳው፣ የሽባው ጓደኞች ኢየሱስ ሽባውን እንዲፈውሰው የሚያስችል ጠንካራ እምነት ነበራቸው:: ዛሬም እኛ የምናውቃቸውን የብዙ ሰዎች ችግር ኢየሱስ መፍታት እንደሚችል ማመን አለብን:: የተከፈተውን በር ሁሉ በመጠቀም ሰዎች ወደ ኢየሱስ እንዲመጡ ማድረግ ይጠበቅብናል:: ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ምሪት የመስጠት ምኞት በልባችን ውስጥ ካለ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ለዚህ በር ይከፍትልናል::

**5፥22 ኢየሱስም ሐሳባቸውን ስለ ተረዳ፤** ክርስቲያኖች እያንዳንዱን ሐሳባችንን፣ ምኞታችንና ስሜታችንን እግዚአብሔር እንደሚመዝን መዘንጋት የለብንም (መዝ 139፤ ማቴ 17፥25፤ ዮሐ 1፥48፤ 2፥25፤ 21፥17፤ ዕብ 4፥13 ይመ)::

**5፥24 የሰው ልጅ፤** ይህስም ኢየሱስ ራሱ እንዲጠራበት የሚወደው ስያሜ ነው፤ ኢየሱስ ይህን አባባል ለመጠቀም መሠረት ያደረገው በዳንኤል 7፥13 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ ይመስላል:: ዳንኤል በራእይ ያየውን ሰው ለመግለጽ ይህን ማዕረግ ተጠቅሞአል፤ ያየውም፣ "የሰውን ልጅ የሚመስል"፣ ከሰማይ ደመና ጋር ሲመጣ ሲሆን፣ የማያልፍም የዘላለም ግዛት የተሰጠው ነው (ዳን 7፥13 እና ማብራሪውን ይመ):: ኢየሱስ በትንቢት የተነገረለትና በእግዚአብሔር የተላከው መሲሕ ራሱ እንደ ሆነ እውነቱን ገልጾ ይናገራል:: ኢየሱስ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ይህን ቃል ይጠቀማል፤ (1) "እኔ" በሚለው ቃል ምትክ (ማቴ 11፥19)፣ (2) እንዲፈጸም የሚፈልገውን ዐቢይ ጉዳይ በሚያነሣበት ጊዜ (ማቴ 20፥28፤ ማር 10፥45)፣ (3) በመስቀል ላይ እንደሚሰቀል አስቀድሞ በሚናገርበት ጊዜ (9፥44፤ ማቴ 17፥22፤ ማር 8፥31)፣ (4) ስለ ትንሣኤው በተናገረበት ጊዜ (ማቴ 17፥9)፣ (5) በታላቅ ክብር ወደ ምድር እንደሚመጣ በጠቀሰበት ጊዜ (ማቴ 24፥27፤ ማር 13፥26፤ 14፥62)፣ (6) በፍርድ ጊዜ ስላለው ሥልጣን በሚናገርበት ጊዜ (ማቴ 13፥41)::

**5፥30 ከኀጢአተኞች ጋር የምትበሉትና የምትጠጡት፤** ማቴ 9፥11 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**5፥35 በዚያን ጊዜ ይጾማሉ፤** ማቴ 9፥15 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

36ደግሞም እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራቸው፤
"ከአዲስ ልብስ ላይ እራፊ ቀዶ በአሮጌ ልብስ
ላይ የሚጥፍ ማንም የለም፤ እንዲህ ቢያደርግ
አዲሱን ልብስ ይቀደዋል፤ አዲሱም እራፊ
ለአሮጌው ልብስ አይስማማውም። 37አዲስ
የወይን ጠጅም በአሮጌ አቍማዳ ጨምሮ
የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤ እንዲህ
ቢያደርግ አዲሱ የወይን ጠጅ አቍማዳውን
ያፈነዳዋል፤ የወይን ጠጁም ይፈስሳል፤
አቍማዳውም ከጥቅም ውጭ ይሆናል።
38ስለዚህ አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ
አቍማዳ መጨመር አለበት፤ 39እንግዲህ፣
አሮጌ የወይን ጠጅ ከጠጣ በኋላ፣ አዲሱን
የሚሻ ማንም የለም፤ ምክንያቱም፣
'አሮጌው የተሻለ ነው' ስለሚል ነው።"

## የሰንበት ጌታ

*6፥1-11 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥1-14፤*
*ማር 2፥23-36*

6 በአንድ የሰንበት ቀን ኢየሱስ በዕርሻ
መካከል ያልፍ ነበር፤ ደቀ መዛሙር
ቱም እሸት ቀጥፈው በእጃቸው እያሹ ይበሉ
ነበር። 2ከፈሪሳውያን መካከል አንዳንዶቹ
ግን፣ "በሰንበት ቀን ሊደረግ ያልተፈቀደውን
ለምን ታደርጋላችሁ?" አሏቸው።
3ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"ዳዊት በተራበ ጊዜ ከባልንጀሮቹ ጋር ያደረ
ገውን ከቶ አላነበባችሁምን? 4ወደ እግዚአብሔር
ቤት ገብቶ ለካህናት ብቻ የተፈቀደውን
ኅብስተ ገጽ ወስዶ በላ፤ አብረውት
ለነበሩትም ሰጣቸው።" 5ደግሞም፣ "የሰው
ልጅ ለሰንበት ጌታዋ ነው" አላቸው።
6በሌላ ሰንበት ቀንም ወደ ምኵራብ ገብቶ
ያስተምር ነበር፤ በዚያም ቀኝ እጁ የሰለለ
አንድ ሰው ነበረ። 7ጸሐፍትና ፈሪሳውያ
ንም ሊከሱት ምክንያት በመፈለግ፣ ይፈው
ሰው እንደ ሆነ ለማየት ይጠባበቁት ነበር።
8ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ እጁ የሰለለ
ውን ሰው፣ "ተነሥተህ በመካከል ቁም"
አለው፤ ሰውየውም ተነሥቶ ቆመ።
9ኢየሱስም፣ "እስቲ አንድ ነገር
ልጠይቃችሁ፤ በሰንበት ቀን የተፈቀደው
በጎ ማድረግ ነው ወይስ ክፉ ማድረግ? ነፍስ
ማዳን ነው ወይስ ማጥፋት?" አላቸው።
10ደግሞም ኢየሱስ በዙሪያው ያሉትን
ሁሉ ከተመለከተ በኋላ ሰውየውን፣ "እጅህን
ዘርጋ" አለው። ሰውየውም እንደ ተባለው
አደረገ፤ እጁም ፈጽሞ ዳነለት። 11ሰዎቹ ግን
በቍጣ ተሞሉ፤ በኢየሱስ ላይ ምን ማድረግ
እንዳለባቸውም እርስ በርስ ተወያዩ።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥ

*6፥13-16 ተጓ ምብ — ማቴ 10፥2-4፤*
*ማር 3፥16-19፤ ሐሥ 1፥13*

12ከእነዚያም ቀናት በአንዱ ኢየሱስ
ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም
ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።

6፥1 ዘዳ23፥25
6፥2 ማቴ12፥2
6፥3 ኢሳ21፥6
6፥4 ዘሌ24፥5፡9
6፥5 ማቴ8፥20
6፥6 ቍ1
6፥7 ማቴ12፥2፡10
6፥8 ማቴ9፥4
6፥11 ዮሐ5፥18
6፥12 ሉቃ3፥21

5፥37 **አዲስ የወይን ጠጅም በአሮጌ አቍማዳ፤** ማቴ 9፥17 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

5፥39 **አሮጌው የተሻለ ነው፤** በወንጌል ውስጥ ከተጠቀሰው ከ"አዲሱ የወይን ጠጅ" ይልቅ፣ "አሮጌው የወይን ጠጅ" (የመጀመሪያው ምእተ ዓመት የአይሁድ እምነት) የተሻለ እንደ ሆነ ስለሚያስቡት አይሁድ የተሰጠ ምጸት አዘል አስተያየት ነው:: እዚህ ላይ ኢየሱስ ያቀረበው ሐሳብ፣ የፈላውን የወይን ጠጅ የመጠጣት ልምድ ያላቸው ሰዎች የሚመኙት ያንኑ ለመጠጣት እንጂ ያልፈላውን ለማግኘት እንዳልሆነ ያመለክታል (በገጽ 232 ላይ፣ "*የወይን ጠጅ በብሉይ ኪዳን*" እንደዚሁም በገጽ 1547 ላይ "*የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -I*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ኢየሱስ የአልኮል መጠጥ ለመጥፎ ልማድና ሱስ እንደሚዳርግ ያውቃል:: "አሮጌው የወይን ጠጅ" ይሻላል ብሎ የሚያስበው ኢየሱስ ሳይሆን፣ አሮጌውን የወይን ጠጅ የመጠጣት ልምድ ያለው ሰው ነው::

(1) ይህን ጥቅስ ስንተረጉም፣ አሮጌው የወይን ጠጅ (የአይሁድ ሃይማኖት) ከአዲሱ የወይን ጠጅ (ከክርስቶስ ወንጌል) ይሻላል ብለን መተርጐም አንችልም፤ እንደዚያ ከተተረጐመ የዚህን ምሳሌ ትክክለኛ ትርጕም ያዛባዋል:: የኢየሱስ ንግግር፣ ፈሪሳዊያንና ተከታዮቻቸው አዲሱ የወይን ጠጅ ብልጫ እንዳለው አለማወቃቸውን የሚያሳይ ነው፤ እነርሱ አሮጌው ጥሩ ነው ብለው ያስባሉና:: ፈሪሳዊያን ንጹሕ፣ አዲስና ጣፋጭ ከሆነው የወይን ጠጅ ይኸውም ከክርስቶስ ወንጌል ይልቅ የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ለሕጉ የሚሰጡትን ትርጕም ይመርጣሉ::

(2) ፈሪሳዊያን ምርጥ የሆነውን የወይን ጠጅ ለማግኘትና ለመጠጣት ፍላጎት የላቸውም፤ ከእግዚአብሔር የሆነውን አዲስ ራእይ መቀበልን ትተው ሰው ያዘጋጀውን ይመርጣሉ:: ነገር ግን ኢየሱስን የሚቀበሉ ሰዎች ከሚያሰክረው ከአሮጌው የወይን ጠጅ ይኸውም ከፈሪሳዊያን ሃይማኖት ይልቅ፣ ንጹሕና አዲስ የሆነውን የወይን ፍሬ ጭማቂ ይኸውም ወንጌልን ይመርጣሉ::

6፥1 **ሰንበት፤** ማቴ 12፥1 እና በሰንበት ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

6፥2-10 **በዚህ ክፍል ስለ ኢየሱስና ስለ ሰንበት ተጠቅሶአል፤** ፈሪሳውያን ኢየሱስ ሰንበትን ሽሯል ብለው ቢከሱትም፣ በመሠረቱ ግን ኢየሱስ የሻረው እነርሱ ለሰንበት የሰጡትን ከትክክለኛው ሐሳብ የራቀውን ትርጕም ነው:: ሰንበትን ማክበር ትክክለኛው ትርጕም ለቆ የሰውን መሠረታዊ ፍላጎት በሚነሣ ሥርዐት አከባበር መለወጥ እንደሌለበት ኢየሱስ ይናገራል:: ክርስቶስ የሰንበት ጌታ ነው (ቍ 5)፤ ሰንበት ከየዕለቱ ሥራችንና ሥጋዊ ጥቅምን ለማግኘት ከምናደርገው ሩጫ ጋር ከመያያዝ ተላቆ እግዚአብሔር በሕይወት ሁሉ ላይ ጌታ ስለ ሆነ፣ እርሱን ሊያስከብር በሚችል መልኩ እንዲውል ስጦታ አድርገን ማቅረብ አለብን:: በተጨማሪም ኢየሱስ የተናገረውና ያደረገው (ቍ 6-10) ነገር ለእግዚአብሔር የሰጠነው የጌታ ቀን በአንድ በኩል ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ለመርዳት ልናውለው እንደምንችል ያስተምረናል::

6፥12 **ሌሊቱንም ሁሉ ... ሲጸልይ አደረ፤** ኢየሱስ በተደጋጋሚ በተለይም ዐቢይ ውሳኔ ማድረግ በሚያስፈልገው ጊዜ ብቻውን በጸሎት በአባቱ ፊት መሆን ይፈልግ ነበር (5፥16 እና ማብ ይመ)፤ (1) ሌሊቱን ሁሉ አጥብቆ ሲጸልይ ማደሩ፣ እጅግ ከፍተኛ ውጤት አስገኝቶአል (ያዕ 5፥16 እና ማብ

13 ሲነጋም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ከእነርሱ
ዐሥራ ሁለቱን መረጠ፤ እነዚህንም
ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤ 14 እነርሱም፣
ጴጥሮስ ብሎ የጠራው ስምዖንና ወንድሙ
እንድርያስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ፊልጶስ፣
በርተሎሜዎስ፣ 15 ማቴዎስ፣ ቶማስ፣
የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ቀናተኛ የተባለው
ስምዖን፤ 16 የያዕቆብ ልጅ ይሁዳና ኋላ
አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነበሩ።

## የቡራኬና የወዮታ ስብከት

*6፥20-23 ተጓ ምብ — ማቴ 5፥3-12*

17 ኢየሱስም አብሮአቸው ከተራራው
ወርዶ ደልዳላ ቦታ ላይ ቆመ፤ ከደቀ
መዛሙር ቱም እጅግ ብዙ ሰዎች በዚያ ነበሩ፤
ከይሁዳ ሁሉና ከኢየሩሳሌም እንዲሁም
ከጢሮስና ከሲዶና ባሕር ጠረፍ የመጣ ብዙ
ሕዝብም በዚያ ነበረ፣ 18 እነዚህም የመጡት
ሊሰሙትና ካለባቸው ደዌ ሊፈወሱ ነበር።
በርኩሳን[a] መናፍስት ይሠቃዩ የነበሩትም
ተፈወሱ፤ 19 ኀይል ከእርሱ እየወጣ ሁሉንም
ይፈውስ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ ሁሉ እርሱን
ለመንካት ይፈልጉ ነበር።
20 ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመመልከት
እንዲህ አለ፤
"እናንት ድኾች ብፁዓን ናችሁ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ
ናትና፤
21 እናንት አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፤
ኋላ ትጠግባላችሁና፤
እናንት አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፤
ኋላ ትሥቃላችሁና፤
22 ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሲጠሏችሁ፣
ከመካከላቸው ሲለዩአችሁና
ሲነቅፏችሁ፣
ክፉ ስምም ሲሰጧችሁ ብፁዓን
ናችሁ።
23 "እነሆ፤ ወሮታችሁ በሰማይ ታላቅ
ነውና፣ በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ፤ ፈንድቁም፤
የቀድሞ አባቶቻቸውም በነቢያት ላይ ያደረ
ጉት ይህንኑ ነበርና።

24 "ነገር ግን እናንት ሀብታሞች ወዮላችሁ፤
መጽናናታችሁን አሁኑኑ
ተቀብላችኋልና።
25 እናንት አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፤
ኋላ ትራባላችሁና።
እናንት አሁን የምትሥቁ ወዮላችሁ፤
ኋላ ታዝናላችሁ፤ ታለቅሳላችሁም።
26 ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካም
ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤

6፥13 ማር6፥30
6፥15 ማቴ9፥9
6፥17 ማቴ4፥25፤ 11፥21፤ ማር3፥7-8
6፥19 ማቴ9፥20፤ ማር 5፥30፤ ሉቃ5፥17
6፥20 ማቴ25፥34
6፥21 ኢሳ55፥1:2፤ 61፥2:3፤ ማቴ5፥46፤ ራእ7፥17
6፥22 ኢሳ51፥7፤ ዮሐ9፥22፤ 16፥2፤ 15፥21
6፥23 ማቴ5፥12
6፥24 ሉቃ16፥25፤ ያዕ5፥1
6፥25 ምሳ14፥13፤ ኢሳ65፥13
6፥26 ማቴ7፥15

[a] 6፥18 ወይም ክፉ

ይመ):: ከዚህ የሌሊት ጸሎት ቀጥሎ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን መረጠ (ቍ 13-16)፤ የታመሙ ብዙ ሰዎችን ፈወሰ (ቍ 17-19)፤ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚጠቀሰውን ስብከቱን ሰበከ (ቍ 20-49)፤ (2) ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ዐቢይ ውሳኔ ለመወሰን ሌሊቱን ሁሉ በአባቱ ፊት መጸለይ ካስፈለገው፣ ድካምና ውድቀት ያለብን እኛማ ምን ያህል አብዝተን በጸሎትና ከሰማዩ አባታችን ጋር ኅብረት በመፍጠር ጊዜ ማጥፋት ይኖርብናል.

**6፥17፤ በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የተራራው ስብከት ነው፤** ማቴ 5—7 እና በተራራው ስብከት ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**6፥20 ብፁዓን፤** ማቴ 5፥3 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**6፥20 እናንት ድኾች፤** በገጽ 1577 ላይ፣ *"ብልጽግናና ድህነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**6፥21 እናንት አሁን የምታለቅሱ፤** ማቴ 5፥4 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**6፥22 ሰዎች ... ሲጠሏችሁ፤** የኢየሱስ ተከታዮች ለክርስቶስና ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ታማኝ በመሆናቸው ሰዎች በሚነቅፏቸውና በሚያሬዙባቸው ጊዜ ደስ ሊላቸውና ሊፈነድቁ ይገባል (ቍ 23):: ኢየሱስም በዓለም የተንገላታና የተጠላ በመሆኑ (ዮሐ 15፥18-21፤ ማቴ 5፥10 እና ማብ ይመ)፣ አማኞች ስለ ጽድቅ በሚሰደዱበት ጊዜ ከጌታ ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ነው::

**6፥23 የቀድሞ አባቶቻቸውም በነቢያት ላይ ያደረጉት ይህንኑ ነበርና፤** በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ ለብዙ ጊዜ ነቢያትንና መልእክቶቻቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም (1ነገ 19፥10፤ ማቴ 5፥12፤ 23፥31፡37፤ ሐሥ 7፥51-52)፤ (1) መሪዎቹና ሕዝቡ የጽድቅ ሕይወት እንዲኖሩ፣ ለቃሉ ታማኝ እንዲሆኑና ከዓለም እንዲለዩ (ራእ 2—3) ጥሪ ለማድረግ እግዚአብሔር ነቢያትን እንደሚልክላቸው (1ቆሮ 12፥28፤ ኤፌ 4፥11) ዛሬም አብያተ ክርስቲያናት ማስታወስ ይገባቸዋል::

(2) ጥንት እስራኤል እንዳደረገችው ሁሉ ዛሬም አብያተ ክርስቲያናት የነቢያቶቻቸውን ቃል ሳይቀበሉና ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር የሚመጣውን በረከትና ድነት ሊያጡ ይችላሉ:: በሌላ አንጻር የእግዚአብሔርን መልእክት ሊቀበሉ፣ ከኀጢአት ሊርቁ፣ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ የበለጠ ታማኞች ሊሆኑና የእግዚአብሔር በመሆን ሊቀጥሉ ይችላሉ:: እውነተኛ የሆኑትን ነቢያት የማይቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት በመጨረሻ እነርሱንም ራሳቸው እግዚአብሔር አይቀበላቸውም (13፥34-35፤ ራእ 2—3)::

(3) ሰይጣን ሆን ብሎ የሐሰት ነቢያትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይልካል (ማቴ 13፥24-30:36-43)፤ እነዚህም ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ሥልጣን እንዳለው የማይቀበሉ፣ ከእግዚአብሔር ቃል እኩል ሥልጣን እንዳላቸው የሚናገሩ፣ ከእነርሱ የሚመጣው መገለጥ እንከን የለሽ እንደ ሆነ የሚያስቡና ቃላቸውም ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጠው ፍርድ ነጻ እንደ ሆነ የሚናገሩ ናቸው (በገጽ 1519 ላይ፣ *"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: እነዚህን ሐሰተኛ ነቢያት በጥብቅ መቃወም ይገባል::

**6፥24 እናንት ሀብታሞች ወዮላችሁ፤** ኢየሱስ ይህን የሚናገረው ኑሮአቸው፣ ዐላማቸው፣ ደስታቸው ወይም ግባቸው ሥጋዊ ነገር ላይ ወይም ሀብት ማካበት ላይ ለሚያተኩር ሰዎች ነው (በገጽ 1577 ላይ፣ *"ብልጽግናና ድህነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**6፥26 ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ፤** ከማያምነው ዓለም

የቀድሞ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች
ነቢያት ያደረጉላቸው ይህንኑ
ነበርና።

## ጠላትን መውደድ

*6፥29፡30 ተጓ ምብ — ማቴ 5፥39-42*

27 "ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ
እላችኋለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤
ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፤
28 የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚበድሏችሁም
ጸልዩ። 29 አንዱን ጉንጭህን ለሚመታህ
ሌላውን ጉንጭህን ደግሞ ስጠው፤
መጎናጸፊያህን ለሚወስድብህ እጀ
ጠባብህን አትከልክለው። 30 ለሚለምንህ
ሁሉ ስጥ፤ ንብረትህን የሚወስድ
እንዲመልስልህ አትጠይቀው። 31 ሰዎች
እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን
እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው።
32 "የሚወዱችሁን ብትወዱ ምን የተለየ
ዋጋ ታገኛላችሁ? ኀጢአተኞችም እንኳ
የሚ ወዷቸውን ይወዳሉና። 33 መልካም
ላደረጉ ላችሁ መልካም ብታደርጉ ምን
የተለየ ዋጋ ታገኛላችሁ? ኀጢአተኞችም
እንኳ እንደ ዚያ ያደርጋሉና። 34 ብድር
ይመልሳሉ ለምትሉት ብታበድሩ ምን
የተለየ ዋጋ ታገኛላችሁ? ኀጢአተኞችም
እንኳ ያበደሩትን ያህል መልሰው ለመቀበል
'ለኀጢአተኞች' ያበድራሉ። 35 ነገር ግን
ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤
መልሳችሁ ለመቀበል ተስፋ ሳታደርጉም
አበድሩ፤ በዚህም ወሮታችሁ ታላቅ
ይሆናል፤ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፤
እርሱ ለማያመሰግኑና ለክፉ ዎች ቸር
ነውና። 36 አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ
እናንተም ርኅሩኆች ሁኑ።

6፥27 ቀኍ35፤ ማቴ5፥44፤ ሮሜ12፥20
6፥28 ማቴ5፥44
6፥30 ዘዳ15፥7፡8፡10፤ ምሳ21፥26
6፥31 ማቴ7፥12
6፥32 ማቴ5፥46
6፥34 ማቴ5፥42
6፥35 ቀኍ27፤ ማር5፥7፤ ሮሜ8፥14
6፥36 ማቴ5፥48፤ 6፥1፤ ሉቃ11፥2፤ 12፥32፤ ሮሜ8፥15፤ ኤፌ4፥6፤ ያዕ2፥13፤ 1ጴጥ1፥17፤ 1ዮሐ1፥3፤ 3፥1
6፥37 ማቴ6፥14፤ 7፥1
6፥38 መዝ79፥12፤ ኢሳ65፥6፡7፤ ማቴ7፥2
6፥39 ማቴ15፥14
6፥40 ዮሐ13፥16
6፥44 ማቴ12፥33
6፥45 ምሳ4፥23፤ ማቴ12፥34፡35፤ ማር7፥20

## በሌሎች አለመፍረድ

*6፥37-42 ተጓ ምብ — ማቴ 7፥1-5*

37 "አትፍረዱ፤ አይፈረድባችሁም፤
አትኰንኑ፤ አትኰነኑም። ይቅር
በሉ፤ ይቅር ትባላላችሁ። 38 ስጡ፤
ይሰጣችኋል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ
ተመልሶ ስለሚሰፈርላችሁ፣ ጫን
በተደረገ፣ በተነቀነቀና በተትረፈረፈ
መልካም መስፈሪያ ተሰፍሮ በዕቅፋችሁ
ይሰጣችኋል።"
39 ደግሞም ይህን ምሳሌ እንዲህ
ሲል ነገራቸው፤ "ዕውር ዕውርን ሊመራ
ይችላልን? ሁለቱ ተያይዘው ጕድጓድ
አይገቡምን? 40 ደቀ መዝሙር ከመምህሩ
አይበልጥም፤ ነገር ግን በሚገባ የተማረ ሰው
ሁሉ እንደ መምህሩ ይሆናል።
41 "በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን
ጕድፍ ለምን ታያለህ? በራስህ ዐይን ውስጥ
የተጋደመውን ግንድ አትመለከትምን?
42 በራስህ ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ
ሳታይ ወንድምህን፣ 'ወንድሜ ሆይ፤
በዐይንህ ውስጥ ያለውን ጕድፍ ላውጣልህ'
እንዴት ልትለው ትችላለህ? አንተ ግብዝ፤
በመጀመሪያ በዐይ ንህ ውስጥ የተጋደመውን
ግንድ አውጣ፤ ከዚያ በኋላ በወንድምህ
ዐይን ውስጥ ያለውን ጕድፍ ለማውጣት
አጥርተህ ታያለህ።

## ዛፍና ፍሬው

*6፥43፡44 ተጓ ምብ — ማቴ 7፥16፡18፡20*

43 "መልካም ዛፍ ሆኖ ሳለ መጥፎ ፍሬ
የሚያፈራ የለም፤ እንዲሁም መጥፎ ዛፍ
ሆኖ መልካም ፍሬ የሚያፈራ የለም።
44 ዛፍ ሁሉ በፍሬው ይታወቃል፤ ከእሾኽ
የበለስ ፍሬ አይለቀምም፤ ከቀጋ ቊጥቋጦ
የወይን ፍሬ አይቈረጥም። 45 መልካም ሰው

ከፍተኛ ቍጥር ያለው ሕዝብ ስለ አንድ አማኝ ወይም የታወቀ የእግዚአብሔር አገልጋይ መልካምነት በሚናገርበት ጊዜ፣ ያ ሰው እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ እንዳልሆነ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም የሐሰት ትምህርት ነቢያትም ብዙውን ጊዜ ክብርና ዝናን የሚያገኙት ለክርስቶስ ታማኝ ባልሆኑት ሰዎች ዘንድ ነው። እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ነቢያት ወይም አገልጋዮች በክርስቶስ ላይ የደረሰው መከራ ሊደርስባቸው ይችላል፤ ሕይወታቸውና መልእክታቸው እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች የሚሠሩትን ኀጢአት የሚቃወም በመሆኑ፣ በእነርሱ ዘንድ የተጠሉና የተገለሉ ይሆናሉ።

**6፥27 ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤** በቍ 27-42 ላይ ኢየሱስ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት መኖር እንዳለብን ይነግረናል። የአዲስ ኪዳን አባላት እንደ መሆናችን በዚህ ውስጥ የተሰጠውን ትእዛዝ የማክበር ግዴታ አለብን፤ (1) ጠላቶቻችንን መውደድ ማለት ስሜታዊ ፍቅርን መግለጽ ሳይሆን፣ መልካም እንዲሆንላቸውና የዘላለም ሕይወት እንዲያገኙ ስለ እነርሱ ከልብ ማሰብ ማለት ነው። የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ጠላቶች የሆኑ ሰዎች በመጨረሻ የሚቆያቸው ሰጣ ፈንታ እጅግ አሳዛኝና አስፈሪ መሆኑን ስለምናውቅ ልንጸልይላቸው፣ በክፉ ፈንታ መልካም በመመለስ ወደ ክርስቶስና ወደ ወንጌል እምነት ይመጡ ዘንድ ልናደርግ ይገባል (ከምሳ 20፥22፤ 24፥29፤ ከማቴ 5፥39-45፤ ከሮሜ 12፥17፤ ከ1ተሰ 5፥15፤ ከ1ጴጥ 3፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ጠላቶቻችንን መውደድ ማለት ክፉዎች ክፉት የሞላበት ድርጊታቸውን ያለማቋረጥ ሲፈጽሙ ከጻር ሆነን መመልከት ማለት አይደለም። ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሌሎች በጎነትና ደኅንነት ወይም ክፉ አድራጊው ራሱ መጨረሻው ያምር ዘንድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክፋትን ለማስቆም ጥብቅ እርምጃ መወሰድ አለበት (ማር 11፥15፤ ዮሐ 2፥13-17 ይመ)።

**6፥29 እጀ ጠባብህን አትከልክለው፤** ማቴ 5፥39 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥37 አትፍረዱ፤** ማቴ 7፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**6፥38 ስጡ፤** የፍቅርን ሕግ በመከተል ለችግረኞች መስጠት ይገባናል (2ቆሮ 8፥2 እና ማብራሪያውን ይመ፤ በገጽ 1327 ላይ፣ «ድኾችንና ችግረኞችን መርዳት» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። እግዚአብሔር ራሱ ስጦታችንን ይመዝናል፤ ብድራታችንንም ይሰጠናል። የምንቀበለው በረከትና ሽልማት መጠን የሌሎች ችግር ግድ ብሎን ባደረግነው መልካም ነገርና በሰጠነው እርዳታ ልክ ይወሰናል (2ቆሮ 9፥6 ይመ)።

በልቡ ከሞላው መልካም ነገር መልካሙን ያወጣል፤ ክፉ ሰውም በልቡ ከሞላው ክፉ ነገር ክፉ ውን ያወጣል፤ ሰው በልቡ ሞልቶ የተረፈ ውን በአፉ ይናገራልና።

## ልባምና ሰነፍ ቤተ ሠሪዎች

*6፥47-49 ተጓ ምብ — ማቴ 7፥24-27*

46 "እኔ የምለውን አታደርጉም፤ ታዲያ ለምን፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ' ትሉኛላችሁ? 47 ወደ እኔ የሚመጣ፣ ቃሌንም ሰምቶ የሚፈጽም ሁሉ ማንን እንደሚመስል ላሳያችሁ፤ 48 ቤት ለመሥራት አጥልቆ የቈፈረና በዐለት ላይ መሠረቱን የመሠረተ ሰው ይመስላል፤ ጐርፍ በመጣ ጊዜ የውሃው ሙላት ያን ቤት ገፋው፤ በሚገባ ስለ ታነጸም ሊያነቃንቀው አልቻለም። 49 ቃሌን ሰምቶ የማይፈጽም ግን ቤቱን ያለ መሠረት በዐፈር ላይ የሠራን ሰው ይመስላል፤ የወንዝ ሙትም ቤቱን በመታው ጊዜ ወዲያው ወደቀ፤ ክፉኛም ፈራረሰ።"

ሉቃ 25-37

## የመቶ አለቃው እምነት

*7፥1-10 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥5-13*

7 ኢየሱስ ይህን ሁሉ በሕዝቡ ፊት ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ገባ። 2 በዚያም አንድ የመቶ አለቃ ነበረ፤ እጅግ የሚወደው አገልጋዩም ታሞበት ለሞት ተቃርቦ ነበር። 3 እርሱም ስለ ኢየሱስ በሰማ ጊዜ አገልጋዩን እንዲፈውስለት ይለምኑት ዘንድ አንዳንድ የአይሁድ ሽማግሌዎችን ላከበት። 4 መልእክተኞቹም ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ እንዲህ ብለው አጥብቀው ለመኑት፤ "ይህን ሊታደርግለት ይገባዋል፤ 5 ምክንያቱም ይህ ሰው ሕዝባችንን ይወዳል፤ ምኵራባችንንም የሠራልን እርሱ ነው።" 6 ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሄደ።

እርሱም ወደ ቤቱ በተቃረበ ጊዜ፣ የመቶ አለቃው ወዳጆቹን ልኮ እንዲህ አለው፤ "ጌታ ሆይ፤ ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ የሚገባኝ ሰው አይደለሁምና አትድከም፤ 7 ከዚህም የተነሣ በአንተ ፊት ለመቅረብ እንኳ እንደሚገባኝ ራሴን አልቈጠርሁም፤ ብቻ አንድ ቃል ተናገር፤ አገልጋዩ ይፈወሳል። 8 እኔ ራሴ የበላይ አለቃ አለኝ፤ ከበታቼም የማዛቸው ወታደሮች አሉኝ፤ አንዱን፣ 'ሂድ' ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን፣ 'ና' ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬንም፣ 'ይህን አድርግ' ስለው የታዘዘውን ያደርጋል።"

9 ኢየሱስም ይህን ሲሰማ በእርሱ ተደነቀ፤ ዘወር ብሎም ይከተለው ለነበረው ሕዝብ፣ "እላችኋለሁ፤ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት በእስራኤል እንኳ አላገኘሁም" አላቸው። 10 የተላኩት ሰዎችም ወደ ቤት በተመለሱ ጊዜ፣ አገልጋዩን ድኖ አገኙት።

## ኢየሱስ የመበለቲቱን ልጅ ከሞት አስነሣው

*7፥11-16 ሣጠ — 1ነገ 17፥17-24፤ 2ነገ 4፥32-37፤ ማር 5፥21-24:35-43፤ ዮሐ 11፥1-44*

11 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ብዙ ሳይቈይ፣ ናይን ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱና ብዙ ሕዝብም አብረውት ሄዱ። 12 ወደ ከተማዋ መግቢያ በር ሲደርስም፣ እነሆ፤ ሰዎች የአንድ ሰው አስከሬን ተሸክመው ከከተማዋ ወጡ፤ ሟቹም ለእናቱ አንድ ልጅ ብቻ ነበር፤ እናቱም መበለት ነበረች፤ ብዙ የከተማውም ሕዝብ ከእርሷ ጋር ነበረ። 13 ጌታም ባያት ጊዜ ራራላትና፣ "አይዞሽ፤ አታልቅሺ" አላት።

14 ቀረብ ብሎም ቃሬዛውን ነካ፤ የተሸከሙትም ሰዎች ቀጥ ብለው ቆሙ፤ ኢየሱስም፣ "አንተ ጐበዝ፤ ተነሥ እልሃለሁ" አለው። 15 የሞተውም ሰው ቀና ብሎ ተቀመጠ፤ መናገርም ጀመረ። ኢየሱስም ወስዶ ለእናቱ ሰጣት።

6፥46 ሚል1፥6፤ ማቴ7፥21፤ ዮሐ13፥13፤
6፥47 ሉቃ8፥21፤ 11፥28፤ ያዕ1፥22-25
7፥1 ማቴ7፥28
7፥7 መዝ107፥20
7፥13 ቍ19፤ ሉቃ10፥1፤ 13፥15፤ 17፥5፤ 22፥61፤ 24፥34፤ ዮሐ11፥2
7፥14 ማቴ9፥25፤ ማር 1፥31፤ ሉቃ8፥54፤ ዮሐ11፥43፤ ሐሥ9፥40

---

**6፥45 በልቡ፤** በማንነታችን ውስጥ ማዕከላዊ ስፍራ የያዘው ልብ፣ ውጫዊ ጠባያችንንም ስለሚወስን መለወጥ ይገባዋል (ማር 7፥20-23 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 932 ላይ፣ *"ልብ"* በሚል ርእስና በገጽ 1606 ላይ፣ ደግሞ *"ዳግም ልደት"* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)። ማንም ሰው ውስጣዊ ሕይወቱ ሳይለወጥ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ አይችልም (ከኤር 24፥7፤ 31፥33፤ 32፥39፤ ከሕዝ 36፥23:27፤ ከማቴ 7፥16-20፤ 12፥33-35፤ 15፥18-19፤ 21፥43፤ ከሉቃ 1፥17፤ ከሮሜ 6፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

**6፥46 እኔ የምለውን አታደርጉም፤** ማቴ 7፥21 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**7፥9 እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት፤** ማቴ 8፥10 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**7፥13 ራራላት፤** ኢየሱስ ለዚህች መበለት ያሳየው ርኅራኄ፣ እግዚአብሔር ለመበለቶች ወይም በዓለም ላይ ብቸኛ ለሆነ ማንኛውም ሰው የተለየ ፍቅር እንዳለውና ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ ያለውን አስፈላጊ ነገር ያስተምረናል፤ (1) እግዚአብሔር ለድኻ አደጉ አባት ለባልቴቱም ተሟጋች ነው (መዝ 68፥5 እና ማብ ይመ)፤ እንደዚህ ያሉ ሰዎች በእርሱ ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ሥር ናቸው (ዘፀ 22፥22-23፤ ዘዳ 10፥18፤ መዝ 146፥9፤ ምሳ 15፥25)፤ (2) ለቤተ ክርስቲያን ከሚሰጠው ዐሥራትና ከሕዝቡ ብልጽግና እግዚአብሔር አባት የሌላቸውን ልጆችና መበለቶችን ይመግባል (ዘዳ 14፥28-29፤ 24፥19-21፤ 26፥12-13)፤ (3) ባል የሌላቸውንና መበለቶችን የሚረዱና የሚያከብሩ ሰዎችን እግዚአብሔር ይባርካቸዋል (ኢሳ 1፥17:19፤ ኤር 7፥6-7፤ 22፥3-4)፤ (4) የመበለቶችንና ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ጉዳይ ለራሳቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቃወማቸዋል (ዘፀ 22፥22-24፤ ዘዳ 24፥17፤ 27፥19፤ ኢዮ 24፥3፤ መዝ94፥6:16፤ ዘካ7፥10)፤ (5) መበለቶች የእግዚአብሔርን ፍቅርና ርኅራኄ በመቀበል የሚኖሩ ናቸው (ቍ 11፥17፤ 18፥2-8፤ 21፥2-4፤ ማር 12፥42-43)፤ (6) የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መበለቶችን መርዳት ቀዳሚ ተግባርዋ ነበር (ሐሥ 6፥1-6)፤ (7) ወላጆች የሌላቸውን ልጆችንና መበለቶችን በችግራቸው መርዳት እውነተኛ እምነት የሚገለጽበት አንዱ አቅጣጫ ነው (ያዕ 1፥27 ይመ፤ ከ1ጢሞ 5፥3-8 ጋር ያነጻጽሩ)።

16ሁሉም በፍርሀት ተውጠው
እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፣ "ታላቅ ነቢይ
በመካከላችን ተነሥቶአል"፤ "እግዚአብሔርም
ሕዝቡን ጐብኝቶአል" አሉ። 17ይህም
የኢየሱስ ዝና በመላው ይሁዳና’ በአካባቢው
ባለው አገር ሁሉ ወጣ።

## ኢየሱስና መጥምቁ ዮሐንስ

*7፥18-35 ተጓ ምብ — ማቴ 11፥2-19*

18የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም
ይህንን ሁሉ ለዮሐንስ ነገሩት። እርሱም
ከመካከላቸው ሁለቱን ጠርቶ፣ 19"ይመጣል
የተባለልህ አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ?
በሉት" ብሎ ወደ ጌታ ላካቸው።
20ሰዎቹም ወደ ኢየሱስ መጥተው፣
"መጥምቁ ዮሐንስ፣ 'ይመጣል የተባለልህ
አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? ብሎ ወደ
አንተ ልኮናል' አሉት።
21በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን
ከበሽታ፣ ከደዌና ከርኩሳን መናፍስት
ፈወሳቸው፤ የብዙ ዐይነ ስውራንንም ዐይን
አበራ። 22ከዮሐንስ ተልከው የመጡትንም
እንዲህ አላቸው፤ "ሂዳችሁ ያያችሁትንና
የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዐይነ
ስውራን ያያሉ፤ ዐንካሶች በትክክል
ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች’ ነጽተዋል፤
ደንቈሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ተነሥተዋል፤
ለድኾችም ወንጌል ይሰበካል፤ 23በእኔ
የማይሰናከል ሰው ሁሉ የተባረከ ነው።"
24የዮሐንስ መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ፣
ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ይናገር ጀመር፤
እንዲህም አለ፤ "ወደ በረሓ የወጣችሁት
ምን ልታዩ ነው? ነፋስ የሚያወዛውዘውን
ሸምበቆ? 25እኮ! ምን ልታዩ ወጣችሁ?
ያማረ ልብስ የለበሰውን ሰው ነውን? ባማረ
ልብስ የሚሽሞነሞኑና በድሎት የሚኖሩ
በቤተ መንግሥት አሉላችሁ። 26እ÷! ምን
ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን ለማየት ይሆን?
አዎን፣ እላችኋለሁ፤ ለማየት የወጣችሁት
ከነቢይም የሚበልጠውን ነው። 27እንዲህ

7፥16 ቀ፡39፤ ማቴ9፥8፤ 21፥11፤ ሉቃ1፥65፤ 1፥68
7፥17 ማቴ9፥26
7፥18 ማቴ3፥1፤ ሉቃ5፥33
7፥21 ማቴ4፥23
7፥22 ኢሳ29፥18፡19፤ 35፥5፡6፤ 61፥1፡2፤ ሉቃ4፥18
7፥26 ማቴ11፥9
7፥27 ሚል3፥1፤ ማቴ11፥10፤ ማር1፥2
7፥28 ማቴ3፥2
7፥29 ማቴ21፥32፤ ማር1፥5፤ ሉቃ3፥12
7፥30 ማቴ22፥35
7፥33 ሉቃ1፥15
7፥34 ሉቃ5፥29፡30፤ 15፥1፡2

ተብሎ የተጻፈለትም እርሱ ነው፤
" 'መንገድህን በፊትህ የሚያስተካክል፣
መልእክተኛዬን ከአንተ አስቀድሜ
እልካለሁ።'
28እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት
መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም፤
በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ
የሚያንሰው ይበልጠዋል።"
29ቀረጥ ሰብሳቢዎች እንኳ ሳይቀሩ፣
ይህን የሰሙ ሁሉ፣ የዮሐንስን ጥምቀት
በመጠመቅ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ክብር
ሰጡት፤ 30ፈሪሳውያንና ሕግ ዐዋቂዎች ግን
በዮሐንስ እጅ ባለ መጠመቃቸው፣ እግዚአብሔር
ለእነርሱ ያለውን ዐላማ አቃለሉ።
31ኢየሱስ በመቀጠል እንዲህ አለ፤
"እንግዲህ የዚህን ትውልድ ሰዎች በምን
ልመስላቸው? ምንስ ይመስላሉ? 32በገበያ
ቦታ ተቀምጠው እርስ በርሳቸው እየተጠራሩ
እንዲህ የሚባባሉ ልጆችን ይመስላሉ፤
"ዋሽንት ነፋንላችሁ፤
አልጨፈራችሁም፤
ሙሾ አወረድንላችሁ፤
አላለቀሳችሁም።"
33ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ እህል
ሳይበላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ፣
'ጋኔን አለበት' አላችሁት፤ 34የሰው ልጅ
ደግሞ እየ በላና እየጠጣ ቢመጣ፣
'በላተኛና ጠጪ፣ የቀረጥ ሰብሳቢዎችና
"የኀጢአተኞች" ወዳጅ' አላችሁት።
35እንግዲህ የጥበብ ትክክለኛነት በልጆቿ
ሁሉ ዘንድ ተረጋገጠ።"

## አንዲት ሴት ኢየሱስን ሽቶ ቀባች

*7፥37-39 ማመ — ማቴ 26፥6-13፤*
*ማር 14፥3-9፤ ዮሐ 12፥1-8*
*7፥41፡42 ማመ — ማቴ 18፥23-34*

36ከዚህ በኋላ ከፈሪሳውያን አንዱ ምግብ

’7፥17 ወይም *በአይሁድ ምድር*
’7፥22 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቈዳ በሽታዎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል

7፥24 **ነፋስ የሚያወዛውዘውን ሸምበቆ፤** ማቴ 11፥7 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::
7፥28 **ዮሐንስ፤** ማቴ 11፥11 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::
7፥33 **የወይን ጠጅ፤** የወይን ጠጅ መጠሪያ የሆኑ የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃሎችን ለመመርመርና በአዲስ ኪዳን ጥቅሙ ምን እንደ ሆነ ለመረዳት 1፥15 እና ማብራሪያውን ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1547 ላይ፣ "***የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1***" በሚል ርእስና በገጽ 1603 ላይ፣ "***የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2***" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመልከቱ::
7፥34 **በላተኛና ጠጪ፤** የወይን ጠጅ (በግሪክ "አይኖስ") በአዲስ ኪዳን ላይ የፈላውንም ሆነ ያልፈላውን የወይን ጠጅ ሁሉ የሚያመለክት ነው (በገጽ 1547 ላይ፣ "***የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: እርሱ የወይን ጠጅ እንደጠጣ፣ ዮሐንስ ግን እንዳልጠጣ የኢየሱስ ንግግር ያመለክታል:: ኢየሱስ ምን ዐይነት የወይን ጠጅ እንደጠጣ ከዚህ ክፍል መረዳት ባይቻልም፣ የኢየሱስን ባሕርይ በሚመለከት ፈሪሳውያን ያቀረቡት ክስ ግን ውሸት መሆኑ ጥርጥር የለውም:: ኢየሱስን፣ "በላተኛና ጠጪ ነው" በማለት ይከሱታል፤ ነገር ግን ይህ ክስ፣ ኢየሱስ የጽድቅ አስተማሪ በመሆኑ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ የታቀደና ስም የሚያጠፋ ዐይነተኛ ውሸት ነበር (ማቴ 12፥24፤ ዮሐ 7፥20፤ 8፥48 ይመ):: ከሰካራሞች ጋር የሚበሉና የሚጠጡ ሁሉ የጌታቸውን መምጣት በሚገባ ተዘጋጅተው የማይጠብቁ ክፉ አገልጋዮች እንደ ሆኑ (ማቴ 24፥48-49) ጌታ ኢየሱስ ራሱ ይናገራል:: ስለዚህ በምንም ዐይነት መንገድ ኢየሱስ የሚያሰክር የወይን ጠጅ እንደጠጣ ከዚህ ክፍል እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: ኢየሱስ የጠጣው የወይን ጠጅ ዐይነት በሚመለከት ለመወያየት በገጽ 1547 ላይ፣ "***የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1***" በሚል ርእስና በገጽ 1603 ላይ፤ "***የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2***" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመልከቱ::

# የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1

*ሉቃ 7፥33-34 "ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ እህል ሳይበላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ፣ ጋኔን አለበት አላችሁት፤ የሰው ልጅ ደግሞ እየበላና እየጠጣ ቢመጣ፣ በላተኛና ጠጪ፣ የቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኃየጋጢአተኞችኝ ወዳጅ አላችሁ።"*

**የወይን ጠጅ፤ የፈላውን ነው ወይስ ያልፈላውን?** ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የወይን ጠጅ የሚጠራበት የተለመደው ቃል ምን እንደ ሆነ ቀጥሎ እንመለከታለን። በሉቃስ 7፥33 ላይ የተጠቀሰው "የወይን ጠጅ" የሚለው ቃል በግሪኩ "ኦይኖስ" ተብሎ ይጠራል። ኦይኖስ ሁለት የተለያዩ ዐይነት የወይን ጭማቂዎችን የሚያመለክት ነው፤ እነዚህም (1) ያልፈላ የወይን ጭማቂ እንዲሁም (2) የፈላ ወይም የሚያሰክር የወይን ጠጅ ናቸው። ይህም ቀጥሎ ባለው መረጃ የተደገፈ ነው፣

(1) "ኦይኖስ" የሚለው የግሪኩ ቃል ከክርስትና በፊት ባለው ጊዜና በጥንት የቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ ዓለማውያንና ሃይማኖታውያን ጸሓፊዎች አዲስ የተጨመቀውን የወይን ጭማቂ ለማመልከት አውለውታል (በአርስቶትል የተጻፈው፣ "ሜቲሪዮሎጂካ" የተባለውን መጽሐፍ 387.ቢ.9-13 ይመ)፤ (ሀ) በ500 ዓ.ቅ.ክ ገደማ አናክሪዮን የተባለው የግሪክ ገጣሚ፣ "ወይኑን ጭመቀው፤ የወይን ጠጅም እንዲወጣው አድርግ (ኦይኖስ)" በማለት ጽፎአል (ኦዴ 5)። (ለ) በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ይኖር የነበረው ኒካንደር ወይንን ስለ መጭመቅ ጽፎአል፤ የተዘጋጀውም ጭማቂ ኦይኖስ እንደ ሆነ ያመለክታል (ጂኦርጂካ፡ፍራግመንት 86)፤ (ሐ) በ60—130 ዓመተ ምሕረት ይኖር የነበረው ፓፒያስ የተባለው የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባት ወይንን በመጭመቅ "ብዙ ገንቦ የወይን ጠጅ (ኦይኖስ)" ማግኘት እንደሚቻል ይገልጻል (በዩራኑስ ተጠቅሶአል፤ አጌንስት ሄረሲስ፣ 5.33.3-4)፤ (መ) በ137 ዓ.ም. በፒረስ ላይ የተጻፈው የግሪክ ደብዳቤ "ከመጭመቂያው ጋን የወጣውን ኋትክጽስ የወይን "ጅኝ (ኦይኖስ) በሚመለከት ይናገራል፤ ሙልተን እና ሚሊጋን የተባሉት የጻፉት፣ ዘ ቮካቡላሪ ኦፍ ዘ ግሪክ ቴስታመንት ገጽ 10)፤ (ሠ) በ200 ዓመተ ምሕረት ይኖር የነበረው አቴናኦስ ኋራስን ስለማያሳምመጥኝ ጣፋጭ ስለሆነው የወይን ጠጅ (ኦይኖስ) ይናገራል (አቴናኦስ፣ ባንኩዌት 1.54)፤ በሌላ ስፍራ፣ "በየቦታው እየሄደ ከእርሻ ላይ የወይን ፍሬ ስለሚሰበስበውና ከዚያም የወይን ጠጅ (ኦይኖስ) ስለሚጠጣው ሰው ጽፎአል (1.54)። በጥንት ጸሓፊዎች ዘንድ የኦይኖስ ጥቅም ምን ይመስል እንደነበረ በይበልጥ ለመረዳት፣ "ዘ ዩዝ ኦፍ ዋይን ኢን ዘ ኦልድ ቴስታመንት" በሚል ርእስ ሮበርት ፒ. ቲችአውት የዶክተርነት ዲግሪያቸውን ለማግኘት የጻፉትን ጽሑፍ ይመልከቱ (ዳላስ ቲኦሎጂካል ሰሚናሪ 1979)።

(2) በ200 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ የተረጐሙ የአይሁድ ምሁራን፣ የወይን ጠጅን የሚያመለክቱ የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት ለመተርጐም ኦይኖስን ተጠቅመዋል (በገጽ 232 ላይ፣ "የወይን ጠጅ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በሌላ አባባል የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ኦይኖስ የፈላ ወይም ያልፈላ የወይን ጭማቂ ሊሆን እንደሚችል ያለ ጥርጥር ዐውቀዋል።

(3) መንፈሳዊ ያልሆኑና መንፈሳዊ የሆኑ የግሪክ ጽሑፎች እንደሚያመለክቱት ሁሉ፣ የአዲስ ኪዳን የተለያዩ ክፍሎችም ሲመረመሩ "ኦይኖስ" የሚለው ቃል የፈላ ወይም ያልፈላ የወይን ጠጅ ሊሆን እንደሚችል ይገልጻሉ። በኤፌ 5፥18 ላይ "በወይን ጠጅ (ኦይኖስ) አትስከሩ" የሚለው ትእዛዝ የፈላውንና የሚያሰክረውን የወይን ጠጅ ያመለክታል። በሌላ በኩል በራእ 19፥15 ላይ ክርስቶስ የወይን መጭመቂያውን እንደሚረግጥ ያሳያል። በግሪኩ መጽሐፍ ላይ የተጻፈው "የወይን ጠጁን (ኦይኖስ) የወይን መጭመቂያ ይረግጣል" የሚል ነው። ከወይን መጭመቂያው የሚወጣው ኦይኖስ፣ የወይን ጭማቂ ይሆናል (ኢሳ 16፥10 እና ማብራሪያውን እንዲሁም ኤር 48፥32-33 እና ማብ ይመ)። በራእ 6፥6 ላይ የተጠቀሰው ኦይኖስ፣ በሰብል ደረጃ በወይኑ ተክል ላይ ያለውን መጉዳት የሌለበትን ወይን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን ለሚገኙ አማኞች፣ የወይን ጠጅ (ኦይኖስ) ሁለት የተለያዩ ከወይን የተዘጋጁ መጠጦችን ይኸውም የፈላውንና ያልፈላውን የወይን ጠጅ ለማመልከት የሚጠቅም አጠቃላይ ቃል ነው።

(4) በመጨረሻም የጥንት ሮማውያን ጸሓፊዎች ትኩስ የወይን ጭማቂን በማዘጋጀት ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ሂደቶች ምን እንደ ሆኑ በሰፊው አብራርተዋል፤ እንዳይፈላ ለማድረግም

የተለያየ መንገድ መጠቀም እንደሚቻል ገልጸዋል። (ሀ) ኮሉሜላ (ኦን አግሪካልቸር 12.29) የተባለ ሰው፣ የወይን ጭማቂ አምሳ ዲግሪ ቀዝቃዛና ከኦክስጂን ነጻ በሆነ ቦታ ከተቀመጠ ሊፈላ እንደማይችል በመረዳት የሚከተለውን ጽፎአል፣ “የወይን ጭማቂህ አዲስ እንደተጨመቀ ጭማቂ ሁል ጊዜ ጣፋጭ ሆኖ ሊቆይ ይችላል፤ በመቀጠልም ወይኑን ከጨመቅህ በኋላ ትኩሱን ጭማቂ አውጥተህ በአንድ አዲስ ዕቃ ውስጥ ጨምረው፤ ከዚያም በኋላ የዕቃውን አፍ በሚገባ ወትፈው፤ ምንም ውሃ እንዳያስገባ በሙጫ በጥንቃቄ አጣብቀው፤ በመቀጠልም በውሃ ማጠራቀሚያ ወይም ቀዝቃዛ የኩሬ ውሃ ውስጥ አስቀምጠው፣ ሽጣጣው እንስራ ምንም ከውጭ እንዳይታይ አድርግ። ከአርባ ቀንም በኋላ አውጣው። ጣፋጭነቱንና ጣዕሙን ጠብቆ ለዓመት ያህል ይቆያል።” (ኮሉሜላ፣ አግሪካልቸር ኤድን ትሪስ፤ ካቶ፡ ኦን አግሪካልቸር) በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረው ፕሊኒ የተባው ሮማዊ ጸሐፊ እንደሚከተለው ጽፎአል፤ “የወይኑ ጭማቂ ከጋኑ እንደወጣ፣ እንጨት በርሜል ውስጥ በማድረግ የክረምቱ አጋማሽ እስከሚያልፍና መደበኛው ቀዝቃዛ አየር እስከሚጀምር ድረስ በውሃ ውስጥ ያስቀምጡታል (ፕሊኒ፣ ናቹራል ሂስተሪ 14.11.83 ይመ)። ይህ ዘዴ በእስራኤል አገር በሚገባ ሥራ ላይ ውሎአል (ዘዳ 8፥7፤ 11፥11-12፤ መዝ 65፥9-13)፤

(ለ) የወይኑ ጭማቂ እንዳይፈላ ለማድረግ ሌላው ዘዴ በእሳት አፍልቶ ጣፋጭ መጠጥ እንዲሆን ማድረግ ነው (ስለዚህ ይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1603 ላይ፣ “የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በመሠረቱ የጥንት የታሪክ ምሑራን ይህ ጭማቂ የወይን ጠጅ (ኦይኖስ) እንደሆነ ይናገራሉ። ካነን ፋረር (እስሚዝስ ባይብል ዲክሽነሪ ገጽ 747)፣ “በጥንት ዘመን የነበረው የወይን ጠጅ ጣፋጭ መጠጥ ነበር፤ እንደዚህ ያሉት ብዙዎቹ አስካሪ መጠጦች አልነበሩም” በማለት ይናገራል። ዘ ኒው ባይብል ዲክሽኔሪ በገጽ 1332 ላይ፣ “የወይን ጠጅ ዓመቱን ሁሉ ጣፋጭ እንደሆነና ጣዕሙን ጠብቆ እንዲቆይ ማድረጊያ ዘዴ እንዳለ” ይገልጻል።

በጌታ እራት ጊዜ የወይን ጠጅን ስለ መጠቀም፤ ኢየሱስ የጌታ እራትን ሥርዐት በደነገገ ጊዜ የተጠቀመው የፈላ የወይን መጠጥ ነው ወይስ ያልፈላ (ማቴ 26፥26-29፤ ማር 14፥22-25፤ ሉቃ 22፥17-20፤ 1ቆሮ 11፥23-26)? ቀጥሎ ያለው መረጃ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የጠጡት ያልፈላ የወይን ጠጅ ነበር ብለን ለመደምደም ያስችለናል፤

(1) ሉቃስም ሆነ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የጌታ እራትን በሚመለከት “የወይን ጠጅ” (በግሪክ ኦይኖስ) የሚለውን ቃል አይጠቀሙም። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ወንጌል ጸሓፊዎች በዚህ ፈንታ “የወይን ፍሬ” በማለት ጽፈዋል (ማቴ 26፥29፤ ማር 14፥25፤ ሉቃ 22፥18)። ያልፈላ የወይን ጠጅ፣ የወይን ተክል የተፈጥሮ ፍሬ ጭማቂ ሲሆን፣ አልኮል የሌለበትና በግምት ከመቶ ሃያ እጅ ስኳር ነው። መፍላት፣ ብዙ ስኳር እንዲጠፋ ከማድረጉም በላይ የወይን ተክሉ በተፈጥሮ የሚያዘጋጀውንም ነገር ይለውጣል፤ የፈላ የወይን ጠጅ በወይን ተክሉ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ውጤት አይደለም።

(2) የጌታ እራት ሥርዐት የተደነገገው፣ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የፋሲካን እራት እየበሉ በነበረበት ጊዜ ነው። በፋሲካ ሳምንት፣ እርሾን ወይም እንዲፈላ የሚያደርግ ነገርን መጨመር፣ በዘፀ 12፥14-20 ላይ የተጠቀሰው የፋሲካ ሕግ ይከለክላል። “ሲኦር” እርሾን የሚያመለክት ቃል ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ በጥንቱ ዓለም እየፈላ ካለ የወይን ጠጅ ላይ ከሚገኘው ወፍራም አሰር የሚወጣ ነው። በተጨማሪም ማንኛውንም እርሾ ያለበትን ነገር መጠቀም የተከለከለ ነበር (ዘፀ 12፥19፤ 13፥7 ይመ፤ 13፥7 እና ማብ ይመ)። እርሾ የመበላሸትንና ኀጢአት የማድረግን ሁኔታ የሚገልጽ ምሳሌ ስለሆነ (ከማቴ 16፥6፡12፤ ከ1ቆሮ 5፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ)፣ እግዚአብሔር ይህን ሕግ ሰጥቶአል። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ፣ ማንኛውም ሕጉ የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ ፈጽሞአል (ማቴ 5፥17)። ስለዚህ ኢየሱስ ፋሲካን በሚመለከት እግዚአብሔር የሰጠውን ሕግ ጠብቆአል፤ የፈላ የወይን ጠጅንም አልተጠቀመም።

(3) ፋሲካ በሚከበርበት ጊዜ የፈላውን የወይን ተክል ፍሬ ጭማቂ መጠጣት ተፈቅዶአል ወይስ አልተፈቀደም በሚል በአይሁድ ረበናትና ምሑራን መካከል ለዘመናት ሞቅ ያለ ክርክር ሲካሄድ ቆይቶአል። ጠንካራ አቋም ያላቸውና የዕብራይስጡን ቅዱሳት መጻሕፍት ሐሳብ በተለይም በዘፀ 13፥7 ላይ የተጠቀሰውን ትርጕሙን ቃል በቃል የሚወስዱ ሰዎች ፋሲካ በሚከበርበት ጊዜ የፈላ የወይን ጠጅ ጨርሶ መጠጣት እንደሌለበት በአጽንዖት ይናገራሉ።

(4) በአዲስ ኪዳን ዘመን ፋሲካ በሚከበርበት ጊዜ ያልፈላ የወይን ጠጅ መጠጣት የተለመደ እንደነበር አንዳንድ የአይሁድ የመረጃ ምንጮች ያረጋግጣሉ። ለምሳሌ፣ በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ጸጻፍ መሠረት፣ ኢየሱስ አልፎ በሚሰጥበት በመጨረሻው ሳምንት ባለው ሐሙስ ምሽት ...ዶስችው ከተማ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት ይበላ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም

የመጣ ይመስላል:: ይህም ከሆነ፣ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ እርሱ በደነገገው የቅዱስ ቍርባን ሥርዐት ላይ የሚቀርበው እርሾ የሌለበት ኅብስትና ያልፈላ የወይን ፍሬ ጭማቂ መሆን አለበት ("ጂሰስ" ዘ ጂውስ ኢንሳይክሎፒድያ፣ 1904 እትም፤ ቅጽ 165 ይመ)::

(5) በብሉይ ኪዳን ዘመን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የፈላ መጠጥ መጠጣት ፈጽሞ አይቻልም ነበር፤ ካህናትም የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተው እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ ወደ እርሱ እንዲቀርቡ አይፈቀድላቸውም ነበር (ዘሌ 10፥9 እና ማብራሪያውን ይመ):: ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሊቀ ካህናት ነው (ዕብ 3፥1፤ 5፥1-10)::

(6) የአንድ ትእምርት ፋይዳ ወይም አስፈላጊነት የሚወሰነው፣ የአንድን መንፈሳዊ እውነታ ሐሳብ በሚገባ ሊገልጽ ከመቻሉ አንጻር ነው:: ስለዚህ ኅብስቱ የክርስቶስን ንጹሕና እድፈት የሌለበት ሥጋ የሚያሳይ ትእምርት ስለ ሆነ፣ በክቶ እንዳይበላሽ ከእርሾ ነጻ መሆን እንዳለበት ሁሉ፣ እድፈት የሌለበት የክርስቶስ ደም ምሳሌ የሆነው ከወይን ተክል ፍሬም የሚገኘው ጭማቂ ያልፈላ መሆን አለበት (ከ1ጴጥ 1፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ):: የመበስበስና የመበላሸት ሂደት በክርስቶስ ሥጋ ወይም ደም ላይ ይሠራ ዘንድ እንዳልተፈቀደ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ስለሚናገር (መዝ 16፥10፤ ሐሥ 2፥27፤ 13፥37)፣ እርሾ የሌለበት ኅብስትና ያልፈላ የወይን ፍሬ ጭማቂ ለክርስቶስ ሥጋና ደም ትእምርት በመሆን ያገለግላሉ::

(7) መንፈሳዊ እርሾን ከሕይወታቸው ያስወግዱ ዘንድ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ይመክራል፤ ይኸውም ክርስቶስ ፋሲካችን በመሆኑ (1ቆሮ 5፥6-8)፣ እንደ እርሾ ሆኖ "ግፍና ክፋትን" የሚያነሣሣውን ነገር እንዲያስወግዱ ነው:: የክፉ ነገር ምሳሌ የሆነውን መጠቀም፣ በጌታ እራት ጊዜ የሚያስፈልጉ መንፈሳዊ ነገሮችና ግቡን በተመለከተ ያለን ሐሳብ ተለዋዋጭ ያደርገዋል:: በአዲስ ኪዳን ዘመን የወይን ጠጅን በሚመለከት ይበልጥ ለመረዳት፣ በገጽ 1603 ላይ፣ "የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

አብሮት እንዲበላ ኢየሱስን ጋበዘው፤
እርሱም ወደ ፈሪሳዊው ቤት ሄዶ በማእድ
ተቀ መጠ። 37በዚያ ከተማ የምትኖር አንዲት
ኀጢአተኛ ሴት፣ ኢየሱስ በፈሪሳዊው
ቤት በማእድ መቀመጡን በሰማች ጊዜ
አንድ የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቶ ይዛ
መጣች፤ 38ከበስተ ኋላው እግሩ አጠገብ
ቆማ እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ ታርስ፣
በራሷም ጠጕር ታብሰው ጀመር፤ እግሩንም
እየሳመች ሽቱውን ቀባችው።
39የጋበዘውም ፈሪሳዊ ይህን ባየ ጊዜ፣
"ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ኖሮ፣ የነካችው ሴት
ማን እንደ ሆነች፣ ደግሞም ምን ዐይነት
ሰው እንደ ሆነች ባወቀ ነበር፤ ኀጢአተኛ
ናትና" ብሎ በልቡ አሰበ።
40ኢየሱስም፣ "ስምዖን ሆይ፤ የምነግርህ
ነገር አለኝ" አለው።
እርሱም፣ "መምህር ሆይ፤ ንገረኝ"
አለው።
41ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "ከአንድ
አበዳሪ ገንዘብ የተበደሩ ሁለት ሰዎች
ነበሩ፤ አንደኛው አምስት መቶ ዲናር፣
ሁለተኛው ደግሞ አምሳ ዲናር ነበረበት።
42የሚከፍሉትም ቢያጡ ዕዳቸውን ለሁለቱም
ተወላቸው። እንግዲህ ከሁለቱ አበዳሪውን
አብልጦ የሚወደው የትኛው ነው? "
43ስምዖንም፣ "ብዙው ዕዳ የተተወለት
ይመስለኛል" ሲል መለሰ።
ኢየሱስም፣ "ትክክል ፈርደሃል" አለው።
44ወደ ሴቲቱም ዞወር ብሎ ስምዖንን
እንዲህ አለው፤ "ይህቺን ሴት ታያታለህን?
እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ፤ አንተ ለእግሬ ውሃ
እንኳ አላቀረብህልኝም፤ እርሷ ግን እግሬን
በእንባዋ እያራሰች በጠጕሯ አበሰች። 45አንተ
ከቶ አልሳምኸኝም፤ እርሷ ግን ከገባሁ
ጀምራ እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም።
46አንተ ራሴን ዘይት አልቀባህም፤ እርሷ ግን
እግሬን ሽቶ ቀባች። 47ስለዚህ እልሃለሁ፤ እጅግ
ወዳለችና ብዙው ኀጢአቷ ተሰርዮላታል፤

7፥39 ቍ16፤
ማቴ21፥11
7፥44 ዘፍ18፥4፤
19፥2፤ 43፥24፤
መሳ19፥21፤
ዮሐ13፥4-14፤
1ጢሞ5፥10
7፥45
ሉቃ22፥47፡48፤
ሮሜ16፥16
7፥46 መዝ23፥5፤
መክ9፥8
7፥48 ማቴ9፥2
7፥50 ማቴ9፥22፤
ሐሥ15፥33
8፥1 ማቴ4፥23
8፥2
ማቴ27፥55፡56
8፥3 ማቴ14፥1
8፥8 ማቴ11፥15

በትንሹ የተሰረየለት ግን የሚወደው
በትንሹ ነው።" 48ኢየሱስም ሴቲቱን፣
"ኀጢአትሽ ተሰርዮልሻል" አላት።
49አብረውት በማእድ ተቀምጠው የነበሩ
እንግዶችም፣ "ይህ ኀጢአትን እንኳ
የሚያስተሰርይ እርሱ ማን ነው?" ብለው
በል ባቸው አሰቡ።
50ኢየሱስም ሴቲቱን፣ "እምነትሽ
አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ" አላት።

### የዘሪው ምሳሌ

*8፥4-15 ተጓ ምብ — ማቴ 13፥2-23፤*
*ማር 4፥1-20*

8 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን
መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ
በየከተማውና በየመንደሩ አለፈ። ዐሥራ
ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፤ 2እንዲሁም
ከርኩሳን መናፍስትና ከደዌ የተፈወሱ
አንዳንድ ሴቶች አብረውት ነበሩ፤ እነርሱም
ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት
የተባለችው ማርያም፣ 3የሄሮድስ ቤት
ኀላፊ የነበረው የኩዛ ሚስት ዮሐና፣ ሶስና፣
ደግሞም ሌሎች ብዙዎች ነበሩ፤ እነዚህም
በግል ንብረታቸው የሚያገለግሉት ነበሩ።
4ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰብስቦ ሳለ፣
ደግሞም ሰዎች ከተለያዩ ከተሞች ወደ
እርሱ በሚጐርፉበት ጊዜ፣ ይህን ምሳሌ
እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ 5"አንድ ዐራሽ
ዘሩን ሊዘራ ወጣ፤ ሲዘራም፣ አንዳንዱ ዘር
መንገድ ዳር፤ ወደቀ በእግርም ተረገጠ፤
የሰማይ ወፎችም በሉት። 6አንዳንዱም ዘር
በድንጋያማ ቦታ ላይ ወደቀ፤ እንደ በቀለም
ርጥበት አል ነበረውምና ደረቀ። 7ሌላው
ዘር ደግሞ እሾኽ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም
አብሮት አደገና አንቆ አስቀረው። 8ሌላውም
ዘር በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፤ በበቀለም
ጊዜ መቶ ዕጥፍም አፈራ።"

7፥38 **እያለቀሰች፤** ይህች ሴት ለኢየሱስ ካላት ፍቅር የተነሣ እግሮቹ በእምባዋ ርሰው ነበር። ልቅሶ፣ የሐዘን ወይም የክርስቶስን ውለታ በማሰብ የሚያደረግ የፍቅር መግለጫ ነው፤ (1) እያለቀሱ በመጸለይና በማመን ክርስቲያኖች በልባቸው ያለውን ነገር ለእግዚአብሔር ይገልጻሉ፤ እንደዚህ ዐይነቱ እንባ ለእርሱ መሥዋዕት እንደማቅረብና እርሱንም እንደማገልገል ነው (ቍ 37-50፤ መዝ 126፥5-6፤ ኤር 9፥1፤ 14፥17፤ 31፥15-16፤ ሐሥ 20፥19፡31፤ 2ቆሮ 2፥4፤ ነህ 8፥9 እና ማብ ይመ)። በዚህ ሁኔታ አማኞች የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች ይሆናሉ (2ቆሮ 1፥5፤ ፊል 3፥10፤ 1ጴጥ 4፥13)።

(2) ክርስቶስ ራሱ እያለቀሰ ጸልዮአል፤ ጸሎቱም ተሰምቶለት (ዕብ 5፥7)፤ እንደዚሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በብዙ እንባ ጌታን አገልግሎአል (ሐሥ 20፥19 2ቆሮ 2፥4)። ዛሬም በክርስቶስ ሆነው የሚያለቅሱ ብፁዓን ናቸው (ሉቃ 6፥21)። ወደ ፊት በሚመጣው በክርስቶስ መንግሥት፣ እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከሕዝቡ ዐይን ያብሳል (ራእ 7፥17፤ 21፥4፤ ጸሎትንና እንባን በሚመለከት 2ነገ 20፥5፤ መዝ 39፥12 እንደዚሁም መዝ 56፥8 እና ማብ ይመ)።

7፥47 **እጅግ ወዳለችና፤** ለኢየሱስ የምንገልጸው እውነተኛ ፍቅርና መሰጠት ቀደም ሲል በኀጢአት የነበርንበትን ሁኔታ፣ ክርስቶስ ለመስቀል ሞት ራሱን አሳልፎ በመስጠት ለእኛ የገለጸውን ፍቅር፣ አሁን የኀጢአት ይቅርታን እንዳገኘንና እንክብካቤም እንደሚደረግልን የሚመሰክር ውስጣዊ ማረጋገጫን በሚገባ ከመረዳት የተነሣ የመጣ መሆን አለበት። በእነዚህ መሠረቶች ላይ ያልተገነባ እምነት ዘላቂነት አይኖረውም።

8፥3 **እነዚህም … የሚያገለግሉት፤** ከኢየሱስ ፈውስንና የተለየ መልካም ነገርን የተቀበሉ እነዚህ ሴቶች፣ እርሱንና ደቀ መዛሙርቱን በግል ንብረታቸው ታማኝ ሆነው በማገልገል ጌታን ያከብሩ ነበር። አገልግሎታቸውና ከልብ የሆነው መሰጠታቸው፣ በእርሱ ለምታምን ማንኛዋም ሴት መልካም ምሳሌ በመሆን ወደ ፊትም ይቀጥላል። እርሱን እስካገለገልን ድረስ፣ በማቴ 25፥34-40 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ እኛንም የሚመለከት ይሆናል።

8፥4 **ምሳሌ፤** ማቴ 13፥3 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

8፥5 **ይህ ክፍል ስለ ዘሪው ምሳሌ የሚናገር ነው፤** ማር 4፥3 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ይህን ብሎ ሲያበቃም ድምፁን ከፍ
አድርጎ፣ "ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ" አለ።
9ደቀ መዛሙርቱም የዚህን ምሳሌ
ትርጕም ጠየቁት። 10እርሱም እንዲህ
አለ፤ "የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር
ማወቅ ለእናንተ ተሰጥቶአል፤ ለሌሎች ግን
በምሳሌ እናገራለሁ፤ ይኸውም፣
" 'እያዩ ልብ እንዳይሉ፣
እየሰሙም እንዳያስተውሉ ነው።'
11"እንግዲህ የምሳሌው ትርጕም ይህ
ነው፤ ዘር የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ነው።
12በመንገድ ዳር የወደቀው ቃሉን የሚሰሙ፣
ነገር ግን አምነው እንዳይድኑ ዲያብሎስ
መጥቶ ቃሉን ከልባቸው የሚወስድባቸው
ናቸው። 13በድንጋያማ ቦታ ላይ የወደቀውም
ቃሉን ሲሰሙ በደስታ የሚቀበሉ ናቸው፤
እነዚህ ለጊዜው ያምናሉ እንጂ ሥር
ስለሌላቸው በፈተና ጊዜ ፈጥነው የሚክዱ
ናቸው። 14በእሾኽ መካከል የወደቀውም
ቃሉን የሚሰሙት ናቸው፤ እነዚህም ውለው
አድረው በምድራዊ ሕይወት ጭንቀት፣
በባለጠግነትና ተድላ ደስታ ታንቀው
በሚገባ አያፈሩም። 15በመልካም መሬት
ላይ የወደቀውም ቃሉን ቅንና በጎ በሆነ
ልብ ሰምተው የሚጠብቁ፣ ታግሠውም
በመጽናት ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።

## በመቅረዝ ላይ ያለ መብራት

16"መብራትን አብርቶ ጋን ውስጥ ወይም
በዐልጋ ሥር የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤
ይልቁንም ወደ ቤት የሚገቡ ብርሃኑን
እን ዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጠዋል።
17የማ ይገለጥ የተሰወረ፣ የማይታወቅ
ወደ ብርሃን የማይወጣ፣ የተደበቀ ነገር
የለምና። 18እንግዲህ እንዴት እንደምትሰሙ
ተጠንቀቁ፤ ላለው ይጨመርለታልና፤
ከሌለው ሁሉ ግን ያው ያለው የሚመስለው
እንኳ ይወሰድበታል።"

8፥10 ኢሳ6፥9፤
ማቴ13፥11፡13፡14
8፥11 ዕብ4፥12
8፥13 ማቴ11፥6
8፥14
ማቴ19፥23፤
1ጢሞ6፥9፡10፡17
8፥16 ማቴ5፥15
8፥17
ማቴ10፥26፤
ማር4፥22፤
ሉቃ12፥2
8፥18 ማቴ25፥29
8፥20 ዮሐ7፥5
8፥21 ሉቃ6፥47፤
11፥28፤
ዮሐ14፥21
8፥24
መዝ107፥29፤
ሉቃ4፥35፤ 5፥5፤
ሉቃ39፥41፤
ዮሐ1፥15

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞች

*8፥19-21 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥46-50፤*
*ማር 3፥31-35*

19ከዚህ በኋላ የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ
እርሱ ወዳለበት መጡ፤ እነርሱም ከሕዝቡ
ብዛት የተነሣ ወደ እርሱ ሊቀርቡ አልቻሉም።
20በዚህ ጊዜ፣ "እናትህና ወንድሞችህ ሊያዩህ
ፈልገው በውጭ ቆመዋል" የሚል ወሬ
ደረሰው።
21እርሱም መልሶ፣ "እናቴና ወንድሞቼስ
የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት
ናቸው" አላቸው።

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

*8፥22-25 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥23-27፤*
*ማር 4፥36-41*
*8፥22-25 ማመ — ማር 6፥47-52፤*
*ዮሐ 6፥16-21*

22ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ጀልባ ላይ ወጣ፤ ኢየሱስም፤
"ወደ ባሕሩ ማዶ እንሻገር" አላቸው፤ ከዚ
ያም ጕዞ ቀጠሉ። 23እየተጓዙ ሳሉም ኢየሱስ
እንቅልፍ ወስዶት ተኛ፤ በዚህ ጊዜ በባሕሩ
ላይ ማዕበል ተነሣ፤ ውሃውም ጀልባዋን
ዘልቆ ስለ ገባ፣ አደጋ አፋፍ ላይ ደረሱ።
24ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፣ "ጌታ
ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ ማለቃችን እኮ ነው!"
እያሉ ቀሰቀሱት።
እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና፣ የውሃውን
መናወጥ ገሠጸ፤ በዚህ ጊዜ ነፋሱም፣
ነውጡም ተወ፤ ጸጥታም ሆነ። 25እርሱም
ደቀ መዛሙ ርቱን፣ "እምነታችሁ የት
አለ?" አላቸው።
እነርሱም በፍርሀትና በመደነቅ፣
"ይህ ነፋስንና ውሃን የሚያዝ፣ እነርሱም
የሚታዘዙለት ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?"
ተባባሉ።

**8፥12 ቃሉን ... የሚወስድባቸው፤** ማር 4፥15 እና ሙሉ ያልሆነ መለወጥ በሚለው ሐሳብ ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**8፥13 ለጊዜው ያምናሉ ... ፈጥነው የሚክዱ፤** ክርስቶስ የዚህን ምሳሌ ትርጒም ሲያስረዳ፣ አንድ ሰው ጥሩ የእምነት ሕይወት ይጀምርና ነገር ግን ፈተና በሚመጣበት ጊዜ ጸንቶ ባለመቆሙ ሊወድቅ እንደሚችል በግልጽ ይናገራል:: በአንጻሩ ፍሬ የሚያፈሩት ቃሉን የሚሰሙት፣ የሚጠብቁትና በዛም ጸንተው የሚኖሩት ናቸው (ቊ 15):: ኢየሱስ ቃሉን የሰሙት አጥብቀው መያዝ እንደሚያስፈልጋቸው ያስተምራል (11፥28፤ ዮሐ 8፥51፤ 1ቆሮ 15፥1-2፤ ቈላ 1፥21-23፤ 1ጢሞ 4፥1፡16፤ 2ጢሞ 3፥13-15፤ 1ዮሐ 2፥24-25 ይመ፤ ዮሐ 15፥6 እና በክርስቶስ መኖር በሚለው ሐሳብ ላይ የተሰጠውን የግብ ይመ)::

**8፥14 በምድራዊ ሕይወት ጭንቀት ... ታንቀው፤** እኛ በኢየሱስ የምናምን ክርስቲያኖች የመንፈሳዊ ሕይወታችን ጸጋ ተሚጥጦ እስከሚጠፋ ድረስ በምድራዊ ኑሮ ኀላፊነት፣ ብልጽግና ወይም ተድላ ሐሳብ እንዳንወሰድ ሁል ጊዜ መጠንቀቅ ይኖርብናል:: እንደ እነዚህ ያሉ እሾኾችና አረሞች ቃሉ በሕይወታችን ፍሬ እንዳያፈራ ሊያንቁ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም:: «በሕይወቴ ውስጥ ምን እየተፈጸመ ነው ያለው? አብዛኛውን ጊዜዬን የማጠፋው ጊዜያዊ በሆኑ የኑሮ ጉዳይ ላይ ነውን? ወይስ ከዕለት ወደ ዕለት በሕይወቴ የጐላ ስፍራ እያገኘ ያለው የእግዚአብሔር ቃልና መንፈሳዊ ነገር ነው?» በማለት እያንዳንዳችን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል::

**8፥18 ላለው ይጨመርለታልና፤** ማቴ 25፥29 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**8፥21 እናቴና ወንድሞቼስ፤** የኢየሱስ ዘመድና የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል ሊሆኑ የሚችሉት፣ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙና ሰምተውም የሚታዘዙ ብቻ ናቸው:: በእግዚአብሔር መንፈሳዊ ቤተ ሰብ ውስጥ እምነትና መታዘዝ ፍጹም የማይነጣጠሉ ስለ ሆነ፣ እምነትን ከመታዘዝ ነጥለን ለመውሰድ ምርጫ አልተሰጠንም::

## አጋንንት ያደረበት ሰው መፈወሱ

*8፥26-37 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥28-34*
*8፥26-39 ተጓ ምብ — ማር 5፥1-20*

26ከዚህ በኋላ ከገሊላ ባሻገር ወዳለው
ወደ ጌርጌሴኖን[ሀ] አገር በጀልባ ተሻገሩ።
27ኢየሱስ ከጀልባዋ ወደ ምድር በወረደ
ጊዜ፣ አጋንንት ያደረበት አንድ ሰው ከከተማ
ወጥቶ አገኘው፤ ይህ ሰው ለብዙ ጊዜ ልብስ
ሳይለብስ፣ በቤትም ሳይኖር የመቃብርን
ስፍራ ቤቱ ያደረገ ነበር። 28ኢየሱስንም ባየው
ጊዜ እየጮኸ ፊቱ ተደፋ፤ በታላቅ ድምፅም፣
"የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፤
ከእኔ ጋር ምን ጉዳይ አለህ? እንዳታሠቃየኝ
እለምንሃለሁ" አለ። 29ርኩሱ[ለ] መንፈስ ይህን
ያለው ከሰውየው እንዲወጣ ኢየሱስ አዞት
ስለ ነበር ነው። ርኩሱ መንፈስ በየጊዜው
ስለሚነሣበት ሰውየው በሰንሰለትና በእግር
ብረት እየታሰረ ቢጠበቅም የታሰረበትን
ሰንሰለት እየበጣጠሰ ያደረበት ጋኔን ወደ
በረሓ ይነዳው ነበር።
30ኢየሱስም፣ "ስምህ ማን ነው?" ብሎ
ጠየቀው።
እርሱም ብዙ አጋንንት ገብተውበት ስለ
ነበር፣ "ሌጌዎን" አለው። 31አጋንንቱም
እንጦርጦስ ግቡ ብሎ እንዳያዛቸውም
አጥብቀው ለመኑት።
32በዚያም አካባቢ በተራራ ወገብ ላይ
የብዙ ዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር፤
አጋንንቱም ወደ ዐሣማው መንጋ ግቡ
ብሎ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት፤ እርሱም
ፈቀደላቸው። 33አጋንንቱም ከሰውየው
ወጥተው ወደ ዐሣማዎቹ ገቡ፤ የዐሣማውም
መንጋ በገደሉ አፋፍ ቍልቍል በመንደርደር
ባሕሩ ውስጥ ገብቶ ሰጠመ።
34እረኞቹም የሆነውን ነገር ባዩ ጊዜ፣
ሸሽተው በመሄድ በከተማውና በገጠሩ
አወሩ። 35ሕዝቡም የተደረገውን ነገር
ለማየት ካሉበት ወጥተው ወደ ኢየሱስ
መጡ። አጋንንት የወጡለትም ሰው ልብስ
ለብሶ፣ ወደ ልቦናው ተመልሶ፣ በኢየሱስም
እግር ሥር ተቀምጦ ባዩት ጊዜ ፈሩ።
36በአጋንንት የተያዘው ሰው ሲድን ያዩትም፣
እንዴት እንደ ዳነ ለሕዝቡ አወሩላቸው።
37የጌርጌሴኖን አካባቢ ሰዎችም ሁሉ ታላቅ
ፍርሀት ስላደረባቸው፣ ከዚያ እንዲሄድላቸው
ኢየሱስን ለመኑት፤ እርሱም ወደ ጀልባው
ገብቶ ተመልሶ ሄደ።
38አጋንንት የወጡለትም ሰው አብሮት
ለመሆን ኢየሱስን ለመነው፤ እርሱ ግን
እንዲህ ሲል አሰናበተው፤ 39"ወደ ቤትህ
ተመልሰህ፣ እግዚአብሔር ያደረገልህን
ታላቅ ነገር ተናገር።" ሰውየውም ኢየሱስ
ያደረገለትን ታላቅ ነገር በከተማው ሁሉ
በይፋ እየተናገረ ሄደ።

8፥28 ማቴ8፥29፤ ማር5፥7
8፥31 ራእ9፥1፡2፡11፤ 11፥7፤ 17፥8፤ 20፥1፡3
8፥33 ቍ22፡23
8፥35 ሉቃ10፥39
8፥36 ማቴ4፥24
8፥37 ሐሥ16፥39

## የሞተችው ልጅና የታመመችው ሴት

*8፥40-56 ተጓ ምብ — ማቴ 9፥18-26፤ ማር 5፥22-43*

40ሕዝቡ ሁሉ መምጣቱን ይጠባበቁ
ስለ ነበር፣ ኢየሱስ በተመለሰ ጊዜ በደስታ
ተቀበሉት። 41በዚህ ጊዜ ኢያኢሮስ የተባለ
የምኵራብ አለቃ መጥቶ፣ በኢየሱስ እግር
ላይ በመውደቅ ወደ ቤቱ እንዲሄድለት
ለመነው፤ 42ይህን ልመና ያቀረበው ዕድሜዋ
ዐሥራ ሁለት ዓመት የሆነ አንዲት ልጅ ስለ
ነበረችው ነው፤ እርሷ በሞት አፋፍ ላይ
ነበረች። ወደዚያው እየመራ ሳለ፣ ሕዝቡ
በመጋፋት እጅግ ያጨናንቀው ነበር።
43ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የኖረች
አንዲት ሴት ነበረች፤ ያላትን ሁሉ ለባለ
መድኀኒቶች ጨርሳ[ሐ] ሊፈውሳትም የቻለ
ማንም አልነበረም። 44እርሷም ከበስተ ኋላው
ተጠግታ የልብሱን ጫፍ ነካች፤ ይፈስ
የነበረው ደሟም ወዲያው ቆመ።
45ኢየሱስም፣ "የነካኝ ማነው?" አለ።
ሁሉም መንካታቸውን በካዱ ጊዜ
ጴጥሮስ፣ "ጌታ ሆይ፤ ሕዝቡ ሁሉ ከቦህ
በግፊያ እያስጨነቀህ ነው" አለው።
46ኢየሱስ ግን፣ "አንድ ሰው ነክቶኛል፤
ኀይል ከእኔ እንደ ወጣ ዐውቃለሁና" አለ።
47ሴትዮዋም ሳትታወቅ መሄድ
እንዳልቻለች በተረዳች ጊዜ፣
እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ ተደፋች፤
ለምን እንደ ነካች ውና እንዴት ወዲያው
እንደ ተፈወሰች በሕዝቡ ሁሉ ፊት
ተናገረች። 48እርሱም፣ "ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ
ፈውሶሻል፤ በሰላም ሂጂ" አላት።
49ኢየሱስ ገና እየተናገረ ሳለ፣ አንድ
ሰው ከምኵራብ አለቃው ከኢያኢሮስ ቤት
መጥቶ፣ "ልጅህ ሞታለች፤ ከዚህ በኋላ
መምህሩን አታድክመው" አለው።
50ኢየሱስም ይህን ሰምቶ ኢያኢሮስን፣
"አይዞህ አትፍራ፤ እመን ብቻ፤ ልጅህ ትድ
ናለች" አለው።
51ወደ ኢያኢሮስ ቤት ሲገባም ከጴጥሮስ፣
ከዮሐንስና ከያዕቆብ እንዲሁም ከልጅቱ
አባትና እናት በቀር ማንም አብሮት እንዲ
ገባ አልፈቀደም። 52በዚህ ጊዜ ሰዎቹ
ሁሉ እያለቀሱላት ዋይ ዋይ ይሉ ነበር።
እርሱ ግን፣ "አታልቅሱ፤ ተኝታለች እንጂ

8፥41 ቍ49፤ ማር5፥22
8፥43 ዘሌ15፥25-30
8፥44 ማቴ9፥20
8፥45 ሉቃ5፥5
8፥46 ማቴ14፥36፤ ማር3፥10፤ ሉቃ5፥17፤ 6፥19
8፥48 ማቴ9፥22፤ ሐሥ15፥33
8፥49 ቍ41
8፥51 ማቴ4፥21
8፥52 ማቴ9፥24፤ ሉቃ23፥27

*[ሀ]8፥26 አንዳንድ ቅጆች ጋድሬኔስ፣ ሌሎች ቅጆች ደግሞ ጌርጌ ሴኔስ ይላሉ፤ ቍ 37 ይመ*
*[ለ]8፥29 ወይም ክፉ*
*[ሐ]8፥43 አያሌ ቅጆች ያላትን ሁሉ ለባለ መድኃኒቶች ጨርሳ የሚለው የላቸውም*

---

8፥27 **አጋንንት ያደሩበት አንድ ሰው፤** ከቍ. 27-33 ይመልከቱ:: ሰይጣንና በክፋት ሥር ያለው መንግሥት፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመቃወም ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ አጋንንት በሰዎች ውስጥ እንዲያድሩ ማድረግ ነው:: ይህን ጉዳይ ይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

8፥44 **የልብሱን ጫፍ ነካች፤** ማር 5፥28 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

8፥50 **አትፍራ፤ እመን ብቻ፤** ማር 5፥36 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

አልሞተችም" አላቸው።
53ሰዎቹም መሞቷን ስላወቁ ሣቁበት።
54እርሱ ግን እጇን ይዞ፣ "ልጄ ሆይ፤ ተነሺ"
አላት። 55የልጅቷም መንፈስ ተመለሰ፤ ወዲ
ያውም ተነሥታ ቆመች፤ ኢየሱስም የሚበላ
ነገር እንዲሰጧት አዘዛቸው። 56ወላጆቿም
ተደነቁ፤ እርሱ ግን የሆነውን ነገር ለማንም
እንዳያወሩ አዘዛቸው።

## የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መላክ

*9፥3-5 ተጓ ምብ — ማቴ 10፥9-15፤*
*ማር 6፥8-11*
*9፥7-9፤ ተጓ ምብ — ማቴ 14፥1፡2፤*
*ማር 6፥14-16*

9ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት
በአንድነት ጠርቶ አጋንንትን ሁሉ
እንዲያወጡ፣ ደዌንም እንዲፈውሱ
ኀይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤ 2ደግሞም
የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩና
የታመሙትን እንዲፈውሱ ላካቸው፤
3እንዲህም አላቸው፤ "ለመንገዳችሁ በትር
ቢሆን፣ ከረጢትም ቢሆን፣ እንጀራም
ቢሆን፣ ገንዘብም ቢሆን፣ ሁለት ሁለት እጀ
ጠባብም መያዝ አያስፈልጋችሁም። 4ከዚያ
ከተማ እስከምትወጡ ድረስ መጀመሪያ
በገባችሁበት በማንኛውም ቤት ቈዩ።
5የከተማው ሰዎች ሳይቀበሏችሁ ቀርተው
ከተማቸውን ለቃችሁ ስትሄዱ፣ ምስክር
እንዲሆንባቸው የእግራችሁን ትቢያ
አራግፉችሁ ውጡ።" 6እነርሱም በዚሁ
መሠረት ወጥተው ወንጌልን እየሰበኩ
በየቦታው ሁሉ ሕመምተኞችን እየፈወሱ
በየመንደሩ ያልፉ ነበር።
7የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስም፣ በዚህ
ጊዜ የሆነውን ነገር ሁሉ ሰምቶ በሁኔታው
ተደናገረ፤ ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች
ዮሐንስ ከሙታን እንደ ተነሣ ያወሩ ነበር፤

8፥54 ሉቃ7፥14
8፥56 ማቴ8፥4
9፥1 ማቴ4፥23፤ 10፥1፤ ሉቃ5፥17
9፥2 ማቴ3፥2
9፥3 ሉቃ10፥4፤ 22፥35
9፥5 ማቴ10፥14
9፥7 ማቴ3፥1፤ 14፥1
9፥8 ቍ19፤ ማቴ11፥14፤ ዮሐ1፥21
9፥9 ሉቃ23፥8
9፥10 ማቴ11፥21፤ ማር6፥30
9፥11 ቍ2፤ ማቴ3፥2
9፥16 ማቴ14፥19

8ሌሎች ኤልያስ እንደ ተገለጠ፣ ሌሎች
ደግሞ ከቀድሞዎቹ ነቢያት አንዱ ከሙታን
እንደ ተነሣ ይናገሩ ነበር። 9ሄሮድስም፣
"መጥምቁ ዮሐንስን እኔው ራሱ ዐንገቱን
አስቈርጬው ሞቶአል፤ ታዲያ፣ ስለ እርሱ
እንዲህ ሲወራ የምሰማው ይህ ሰው ማነው?"
አለ፤ በዐይኑም ሊያየው ይሻ ነበር።

## ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን መገበ

*9፥10-17 ተጓ ምብ — ማቴ14፥13-21፤*
*ማር 6፥32-44፤ ዮሐ 6፥5-13*
*9፥13-17 ማመ — 2ነገ 4፥42-44*

10ሐዋርያትም ተመልሰው በመጡ ጊዜ
ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት፤ እርሱም ይዞአቸው
ቤተ ሳይዳ ወደምትባል ከተማ በመሄድ
ለብቻው ገለል አለ። 11ሕዝቡም ይህንኑ
ዐውቀው ተከተሉት፤ እርሱም ተቀብሎአቸው
ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ይነግራ ቸው
ነበር፤ ፈውስ የሚያስፈልጋቸውንም
ፈወሳቸው።
12ቀኑም ሊመሽ ሲል፣ ዐሥራ ሁለቱ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ "ያለነው በምድረ በዳ
ስለ ሆነ፣ ሕዝቡ ወደ አካባቢው መንደርና
ገጠር ሄደው ማደሪያና ምግብ እንዲፈልጉ
አሰናብታቸው" አሉት።
13እርሱ ግን፣ "የሚበሉትን እናንተው
ስጧቸው" አላቸው።
እነርሱም፣ "ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚበቃ
ምግብ ሄደን ካልገዛን በስተቀር፣ እኛ ያለን
ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ አይበል
ጥም" አሉት፤ 14አምስት ሺህ ያህል ወንዶች
በዚያ ነበሩና።
ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን፣
"ሕዝቡን በአምሳ በአምሳ ሰው መድቡችሁ
አስቀምጧቸው" አላቸው። 15ደቀ
መዛሙርቱም በታዘዙት መሠረት ሰዎቹ
እንዲቀመጡ አደረጉ። 16እርሱም አምስቱን
እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ

**9፥1 አጋንንትን ሁሉ እንዲያወጡ ... ሥልጣን ሰጣቸው፤** ማቴ 10፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**9፥2 የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰብኩና የታመሙትን እንዲፈውሱ፤** (1) ይህ ወቅት እርሱን ወክለው ቃሉን እንዲናገሩና በተግባርም እንዲገልጹት፣ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለመጀመሪያ ጊዜ የላከበት ነው:: በማቴዎስ ውስጥ በተጻፈው ተጓዳኝ ክፍል መሠረት፣ ለዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የተሰጠው ትእዛዝ፣ «የእስራኤል ቤት ወደ ሆኑት ወደ ጠፉት በጎች» እንዲሄዱ ነው (ማቴ 10፥6):: ይሁን እንጂ ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ሕዝቦች ሁሉ «እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ» በሚዘልቀው ታላቁ ተልእኮ ውስጥ እንዲታቀፉ የመጀመሪያውን ዕቅድ በመለወጥ ይዘቱን ሰፋ አድርጐታል (ማቴ 28፥18-20፤ ማር 16፥15-20)::

(2) የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰበክ ኢየሱስ የሰጠው ትእዛዝ (በገጽ 1443 ላይ፣ «*የእግዚአብሔር መንግሥት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፣ «የታመሙትን ፈውሱ፤ አጋንንትን አስወጡ» የሚለውን ትእዛዝ ሳይጨምር የተነገረው አልፎ አልፎ እንደ ሆነ የወንጌል ጸሓፊዎች ግልጽ ያደርጉታል (ማቴ 9፥35-38፤ 10፥7-8፤ ማር 3፥14-15፤ 6፥7-13፤ 16፥15፡17፤ ሉቃ 9፥2፡6፤ 10፥1፡9 ይመ፤ ከ4፥17-19 ጋር ያነጻጽሩ):: በእነዚህ የመጨረሻዎቹ ቀናት የሰይጣንን ፈተና ለመቋቋም (1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ 3፥1-5) ዛሬም ቢሆን የወንጌል አገልግሎት እንደ ድሮው ዘመን በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና በታምራት የተደገፈ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል (ማቴ 10፥1 እና ማብ ይመ፤ ማር 16፥15-18፤ ሐሥ 1፥8፤ ሮሜ 15፥18-19፤ 1ቆሮ 2፥4-5፤ 4፥20 ይመ፤ በገጽ 1527 ላይ፣ «*አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

(3) በአሁኑ ዘመን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን ማወዳደር ያለባቸው አንዱ ከሌላው ጋር ሳይሆን በአዲስ ኪዳን ከተሰጠው መልእክትና ምሳሌነት ጋር ነው:: የጥንት ቤተ ክርስቲያን እንዳደረገችው የእግዚአብሔርን መንግሥት እያየንና በሕይወታችንም እየገለጽን ነውን? የእግዚአብሔር መንግሥት ለእኛ ቅርብ ነውን? ቅርብ ካልሆነም ያልሆነው ለምንድነው?

**9፥12-17 በዚህ ክፍል አምስቱን ሺህ ሕዝብ ስለ መመገብ ተጠቅሶአል::** ማቴ 14፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

አሻቅቦ እያየ ባረካቸው፤ ቈርሶም ለሕዝቡ
እንዲያቀርቡ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ።
17ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ከእነርሱ የተረፈውን ቍርስራሽ እንጀራ
ዐሥራ ሁለት መሶብ አነሡ።

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት መሰከረ

*9፥18-20 ተጓ ምብ — ማቴ 16፥13-16፤ ማር 8፥27-29*
*9፥22-27፤ ተጓ ምብ — ማቴ 16፥21-28፤ ማር 8፥31—9፥1*

18ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ብቻውን ይጸልይ
ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱም ከእርሱ ጋር
ነበሩ፤ እርሱም፣ "ሕዝቡ እኔን ማን ነው
ይሉኛል?" ብሎ ጠየቃቸው።
19እነርሱም፣ "አንዳንዶች መጥምቁ
ዮሐንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች
ደግሞ ከቀድሞ ነቢያት አንዱ ከሙታን
ተነሥቶአል ይላሉ" አሉት።
20እርሱም፣ "እናንተስ ማን ነው
ትሉኛላችሁ?" አላቸው።
ጴጥሮስም፣ "አንተ የእግዚአብሔር መሲሕ[a]
ነህ" ሲል መለሰለት።
21ኢየሱስም ይህን ለማንም እንዳይናገሩ
አጥብቆ አስጠነቀቃቸው፤ 22ደግሞም፣
"የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀበል
ይገባዋል፤ እንዲሁም በሽማግሌዎች፣
በካህናት አለቆችና በጸሐፍት ዘንድ መናቅ፣
መገደልና በሦስተኛውም ቀን ከሙታን
መነሣት አለበት" አላቸው።
23ከዚያም ለሁሉም እንዲህ አላቸው፤
"በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር
ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ
ይከተለኝ፤ 24ምክንያቱም ነፍሱን ሊያድናት
የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱን ስለ እኔ
ብሎ የሚያጠፋት ግን ያድናታል። 25ሰው
ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጠፋ
ወይም ቢያጐድል ጥቅሙ ምንድን ነው?

9፥18 ሉቃ3፥21
9፥19 ቍ7፡8፤ ማቴ3፥1
9፥20 ዮሐ1፥49፤ 6፥66-69፤ 11፥27
9፥21 ማር8፥30
9፥22 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ 27፥1፡2፤ ሐሥ2፥23፤ 3፥13
9፥23 ማቴ10፥38፤ ሉቃ14፥27
9፥24 ዮሐ12፥25
9፥26 ማቴ10፥33፤ 1ዮ፥27፤ ሉቃ12፥9፤ 2ጢሞ2፥12
9፥28 ማቴ4፥21፤ ሉቃ3፥21
9፥31 2ጴጥ1፥15
9፥32 ማቴ26፥43
9፥33 ሉቃ5፥5
9፥35 ኢሳ42፥1፤ ማቴ3፥17
9፥36 ማቴ17፥9

26ማንም በእኔና በቃሌ ቢያፍር፣ የሰው ልጅ
በራሱ ክብር እንዲሁም በአብና በቅዱሳን
መላእክት ክብር ሲመጣ ያፍርበታል፡
፡ 27እውነት እላችኋለሁ፤ እዚህ ከቆሙት
መካከል የእግዚአብሔርን መንግሥት ሳያዩ
ሞትን የማይቀምሱ ሰዎች አሉ።"

## የኢየሱስ መልክ መለወጥ

*9፥28-36 ተጓ ምብ — ማቴ 17፥1-8፤ ማር 9፥2-8*

28ኢየሱስ ይህን ከተናገረ ከስምንት
ቀን ያህል በኋላ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና
ያዕቆብን ይዞ ሊጸልይ ወደ አንድ ተራራ
ወጣ። 29በመጸለይ ላይ እንዳለም የፊቱ
መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም እንደ መብረቅ
የሚያንጸባርቅ ነጭ ሆነ። 30እነሆ፤ ሁለት
ሰዎች ፣ እነርሱም ሙሴና ኤልያስ
ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ 31በክብርም
ተገልጠው፣ በኢየሩሳሌም ይፈጸም ዘንድ
ስላለው ከዚህ ዓለም ስለ መለየቱ ይናገሩ
ነበር። 32ጴጥሮስና አብረውት የነበሩት ግን
እንቅልፍ ተጭኖአቸው ነበር፤ ሲነቁ ግን
ክብሩንና ከእርሱ ጋር የቆሙትን ሁለት
ሰዎች አዩ። 33ሰዎቹም ከኢየሱስ ተለይተው
ሲሄዱ፣ ጴጥሮስ፣ "ጌታ ሆይ፤ እዚህ ብንሆን
ለእኛ መልካም ነው፤ ስለዚህ ሦስት ዳስ
እንሥራ፤ አንዱ ለአንተ፣ አንዱ ለሙሴ፣
አንዱም ለኤልያስ ይሆናል" አለው፤
የሚናገረውንም አያውቅም ነበር።
34ይህንም እየተናገረ ሳለ ደመና መጥቶ
ጋረዳቸው፤ ወደ ደመናውም ሲገቡ ፈሩ።
35ከደመናውም ውስጥ፣ "የመረጥሁት ልጄ
ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" የሚል ድምፅ
መጣ። 36ድምፁም በተሰማ ጊዜ ኢየሱስ
ብቻውን ሆኖ ተገኘ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ነገሩን በልባቸው ያዙ እንጂ ስላዩት ነገር
በዚያን ወቅት ለማንም አልተናገሩም።

*[a]9፥20 ወይም ክርስቶስ*

**9፥23 መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ፤** ኢየሱስን ጌታና አዳኝ አድርጎ መቀበል የወንጌልን እውነት ማመን ብቻ ሳይሆን፣ ራሳችንንም መሥዋዕት አድርገን ሰጥተን እንድንከተለው የሚጠይቅ ነው (ማር 8፥34 እና ማብ ይመ)። ራሳችንን በመካድና ሥጋዊ ምኞታችንን በመከተል መካከል ምርጫችን የቱ እንደሆነ በየዕለቱ መታወቅ አለበት። ይህ ምርጫ ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታችንን የሚወስን ነው።

**9፥24 ነፍሱን … የሚያጠፋት፤** በእግዚአብሔር ፈቃድና በእርሱ ሕግ መሠረት በመኖር ፈንታ በሕይወት ውስጥ ደስታንና ተድላን ማግኘት ዐላማችን አድርገን የምንኖር ከሆነ፣ መጨረሻችን ተስፋ መቍረጥና ነፍሳችንን ማጣት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ነገር ግን ሕይወታችንን በቃሉ ትምህርት ላይ መሥርተን የራሳችንን መንገድ ንቀን በመተው ከኢየሱስ ጋር ኅብረት አድርገን መኖር፣ በዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም እውነተኛ ሕይወትና ደስታን ማግኘት ነው።

**9፥26 በእኔ … ቢያፍር፤** በኢየሱስ ማፈር ማለት፣ ኢየሱስ ባስተማረው መሠረት መንገዱን፣ ሕጉንና ዐላማውን ይዘን ለመቆም ኀፍረት ወይም ፍርሀት ሲሰማን ማለት ነው። በቃሉ ማፈር፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ምሪት ለመናገር ማፈር፣ በእርሱ ለመኖርና ከእርሱም ጋር ተስማምቶ ለመቆም ማፈር ማለት ነው። እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ክርስቶስ ይክዳቸዋል፣ ይፈርድባቸዋልም (ማቴ 10፥33 ይመ፤ ማር 8፥34 እና ማብ፤ ሮሜ 1፥16፤ 2ጢሞ 1፥8፡12፡16፤ ራእ 3፥14-16 ይመ)።

**9፥27 የእግዚአብሔርን መንግሥት ሳያዩ፤** ማቴ 16፥28 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**9፥29 የፊቱ መልክ ተለወጠ፤** በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የፊቱ መልክ የተለወጠው ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ባሉበት ነው፤ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ እንዳለ በሰማያዊ ክብሩ ተመለከቱት። የኢየሱስ መልክ የተለወጠበት ይህ ሁኔታ አስፈላጊነቱን የሚያመለክቱ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፤ (1) ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሚሰቀልበት ጊዜ ብርታትንና መጽናናትን የሚሰጥ ነበር (ከማቴ 16፥21 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ኢየሱስ በመስቀል ላይ መከራ ሊቀበል እንዳለው ለደቀ መዛሙርት ፍንጭ የሚሰጥ ነበር (ቍ 31)፤ (3) ኢየሱስ እውነተኛ ልጁ እንደሆነና የሰውንም ዘር ለመቤዠት ብቃት ያለው እርሱ ብቻ እንደ ሆነ ለማመልከት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ማረጋገጫ ነው።

## ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ ያለበትን ልጅ ፈወሰ

*9፥37-42፡43-45 ተጓ ምብ — ማቴ17፥14-18፡22፡23፤ ማር 9፥14-27፡30-32*

37በማግሥቱ ከተራራው ከወረዱ በኋላ፣
ብዙ ሕዝብ መጥቶ ኢየሱስን አገኘው።
38በዚህ ጊዜ ከሕዝቡ መካከል አንድ
ሰው ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤
"መምህር ሆይ፤ ያለኝ ልጅ እርሱ ብቻ
ስለሆነ ልጄን እንድታይልኝ እለምንሃለሁ።
39መንፈስ ሲይዘው በድንገት ይጮኻል፤
አረፋ እያስደፈቀው ያንፈራግጠዋል፤
ጕዳትም ካደረሰበት በኋላ በስንት
መከራ ይተወዋል፤ 40ደቀ መዛሙርትህ
እንዲያወጡለት ለመንኋቸው፤ ነገር ግን
አልቻሉም።"
41ኢየሱስም "እምነት የለሽ ጠማማ
ትውልድ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር
እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ?
ልጅህን ወደዚህ አምጣው" አለ።
42ልጁ በመምጣት ላይ ሳለም ጋኔኑ
መሬት ላይ ጥሎ አንፈራገጠው፤ ኢየሱስ
ግን ርኩሱን[ሀ] መንፈስ ገሥጾ ልጁን ፈወሰው፤
ለአባቱም መልሶ ሰጠው። 43ሰዎቹም ሁሉ
በእግዚአብሔር ታላቅነት ተገረሙ።
እርሱ ባደረገው ሁሉ ሰዎች
ሁሉ እየተገረሙ ሳሉ፣ ኢየሱስ ደቀ
መዛሙርቱን፣ 44"ይህን የምነግራችሁን
ነገር ከቶ እንዳትዘነጉ፤ የሰው ልጅ አልፎ
በሰዎች እጅ ይሰጣልና" አለ። 45እነርሱ ግን
ይህን አባባል አልተረዱም፤ እንዳያስተውሉ
ነገሩ ተሰውሮባቸው ነበር፤ መልሰው
እንዳይጠይቁትም ፈሩ።

## ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?

*9፥46-48 ተጓ ምብ — ማቴ 18፥1-5*
*9፥46-50 ተጓ ምብ — ማቴ 9፡33-40*

46ከእነርሱ ማን እንደሚበልጥ በደቀ
መዛሙርቱ መካከል ክርክር ተነሣ። 47ኢየሱ
ስም የልባቸውን ሐሳብ ተረድቶ፣ አንድ ሕፃን
ይዞ በአጠገቡ አቆመ፤ 48እንዲህም አላቸው፤
"ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል ማንም ቢኖር
እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል ደግሞ
የላከኝን ይቀበላል፤ ከሁላችሁ የሚያንስ
እርሱ ከሁሉ ይበልጣልና።"
49ዮሐንስም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንድ ሰው
በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየን፤ ከእኛ ጋር
ሆኖ ስለ ማይከተል ልንከለክለው ሞከርን"
አለው።
50ኢየሱስም፣ አትከልክሉት
"የማይቃወማችሁ ሁሉ እርሱ ከእናንተ ጋር
ነውና" አለው።

## የሰማርያ ሰዎች ተቃውሞ

51ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሚያርግበት ጊዜ

9፥41 ዘዳ32፥5
9፥44 ቍ22
9፥45 ማር9፥32
9፥46 ሉቃ22፥24
9፥47 ማቴ9፥4
9፥48 ማቴ10፥40፤ ማር9፥35
9፥49 ሉቃ5፥5
9፥50 ማቴ12፥30፤ ሉቃ11፥23
9፥51 ማር16፥19፤ ሉቃ13፥22፤ 17፥11፤ 18፥31፤ 19፥28
9፥52 ማቴ10፥5
9፥54 2ነገ1፥10፡12፤ ማቴ4፥21
9፥58 ማቴ8፥20
9፥59 ማቴ4፥19
9፥60 ማቴ3፥2
9፥61 1ነገ19፥20

በመቃረቡ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቈርጦ
ተነሣ፤ 52አስቀድሞም መልእክተኞችን
ወደዚያ ላከ። እነርሱም ሁኔታዎችን
አስቀድመው ሊያመቻቹለት ወደ አንድ
የሳምራውያን መንደር ገቡ። 53ሕዝቡ ግን
ወደ ኢየሩሳሌም እያመራ መሆኑን ስላወቁ
አልተቀበሉትም። 54ደቀ መዛሙርቱም
ያዕቆብና ዮሐንስ ይህን ሲያዩ፣ "ጌታ
ሆይ፤ ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ[ለ] እሳት
ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው እንድናዝ
ትፈቅዳለህን?" አሉት። 55ኢየሱስ ግን ዘወር
ብሎ ገሠጻቸውና[ሐ] "እናንተ ከምን ዐይነት
መንፈስ እንደ ሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው
ልጅ የመጣው የሰውን ሕይወት ለማዳን ነው
እንጂ ለማጥፋት አይደለምና" አላቸው፤
56ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ።

## ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ

*9፥57-60 ተጓ ምብ — ማቴ 8፥19-22*

57በመንገድ ሲሄዱም አንድ ሰው ቀርቦ፣
"ወደ ምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ"
አለው።
58ኢየሱስም፣ "ቀበሮዎች ጕድጓድ፣
የሰማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ
ግን ራሱን እንኳ የሚያስገባበት የለውም"
አለው።
59ሌላውን ሰው ግን፣ "ተከተለኝ"
አለው።
ሰውየውም፣ "ጌታ ሆይ፤ አስቀድሜ
ልሂድና አባቴን ልቅበር" አለው።
60ኢየሱስም፣ "ሙታን ሙታናቸውን
እንዲቀብሩ ተዋቸው፤ አንተ ግን ሂደህ
የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ" አለው።
61ሌላ ሰው ደግሞ፣ "ጌታ ሆይ፤
መከተልስ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን ልመለስና
መጀመሪያ የቤቴን ሰዎች እንድሰናበት
ፍቀድልኝ" አለ።
62ኢየሱስ ግን፣ "ዕርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ
የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት
የተገባ አይደለም" አለው።

*ሀ9፥42 ወይም ክፉ*
*ለ9፥54 አንዳንድ ቅጆች ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ የሚለው የላቸውም*
*ሐ9፥55፡56 አንዳንድ ቅጆች ገሠጻቸው፤ 56ከዚያም ወደ ሌላ መንደር ሄዱ ይላሉ:: በቍ 55ላይ በትእምርተ ጥቅሱ ውስጥ የሚገኘው ዐረፍተ ነገር ተአማኒ በሆኑ ብዙ የጥንት ቅጆች ላይ አይገኝም::*

**9፥41 እምነት የለሽ ጠማማ ትውልድ፤** ማቴ 17፥17 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**9፥55 ገሠጻቸው፤** ለክርስቶስ ያለን ታማኝነትና ቅናት ባልጸኑት፣ በጨለማና በኀጢአት ውስጥ ባሉት ላይ ለመበቀልና ዐመፃን ለመፈጸም ድብቅ ሐሳብ የያዘ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል::

## ኢየሱስ ሰባ ሁለቱን ላካቸው

*10፥4-12 ትን ምብ — ሉቃ 9፥3-5*
*10፥13-15፡21፡22 ተን ምብ — ማቴ 11፥21-23፡25-27*
*10፥23፡24 ተን ምብ — ማቴ 13፥16፡17*

10 ከዚህ በኋላ ጌታ ሌሎች ሰባ
ሁለት ሰዎችን መርጦ ሾመ፤
ወደሚሄድበትም ከተማና ቦታ ሁሉ
እንዲቀድሙት፣ ሁለት ሁለት አድርጎ
ላካቸው፤ 2እንዲህም አላቸው፤ "መከሩ ብዙ
ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂት ናቸው፤ ስለዚህ
የመከሩ ጌታ ሠራተ ኞችን ወደ መከሩ ቦታ
እንዲልክ ለምኑት። 3እንግዲህ ሂዱ፤ እንደ
በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፡
፡ 4ኰረጆ ወይም ከረጢት፣ ወይም ጫማ
አትያዙ፤ በመንገድ ላይም ለማንም ሰላምታ
አትስጡ።
5"ወደ ማንኛውም ቤት ስትገቡ
አስቀድማችሁ፣ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን
በሉ፤ 6የሰላም ሰው በዚያ ካለ፣ ሰላማችሁ
ያርፍበታል፤ አለዚያም ሰላማችሁ
ለእናንተው ይመለሳል። 7የቀረቡላችሁን
ሁሉ እየበላችሁና እየጠጣችሁ በዚያ ቤት
ተቀመጡ፤ የሚሠራ ደመወዝ ማግኘት
ይገባዋልና። ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት
አትዘዋወሩ።
8"ወደ ማንኛውም ከተማ ስትገቡ ሰዎቹ
ከተቀበሏችሁ፣ ያቀረቡላችሁን ብሉ። 9በዚያ
ሉቃ 13፥10-17 የሚገኙትን በሽተኞች እየፈወሳችሁ፣
'የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ
ቀርባለች' በሏቸው። 10ነገር ግን ወደ አንድ
ከተማ ገብታችሁ ካልተቀበሏችሁ፣ ወደ
አደባባዩ ውጡና እንዲህ በሉ፤ 11'በእግራችን
ላይ ያለውን የከተማችሁን ትቢያ እንኳ
እናራግፍላችኋለን፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር
መንግሥት እንደ ቀረበች ይህን ዕወቁ።'
12እላችኋለሁ፤ በዚያን ዕለት ከዚያች ከተማ
ይልቅ ለሰዶም ቀላል ይሆንላታል።
13"ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ
በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና
በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ዱሮ ማቅ
ለብሰው፣ ዐመድ ነስንሰው ንስሓ በገቡ
ነበር። 14ነገር ግን በፍርድ ጊዜ ከእናንተ
ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል።
15አንቺም ቅፍርናሆም፣ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ
አልሽን? ወደ ሲኦል[a] ትወርጃለሽ።
16"እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤
እናንተን የማይቀበል እኔን አይቀበልም፤ እኔ
ንም የማይቀበል የላከኝን አይቀበልም።"
17ሰባ ሁለቱም ደስ እያላቸው ተመልሰው፣
"ጌታ ሆይ፤ አጋንንት እንኳ በስምህ
ተገዙልን" አሉት።
18እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ሰይጣን
እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ
አየሁ። 19እንግዲህ እባቡንና ጊንጡን
እንድትረግጡ፣ በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ
ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም
አንዳች ነገር አይኖርም። 20ይሁን እንጂ
መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚያ ደስ
አይበላችሁ፤ ስማችሁ ግን በሰማይ ስለ
ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።"
21በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ
ሐሤት አድርጎ እንዲህ አለ፤ "የሰማይና
የምድር ጌታ፤ አባት ሆይ፤ ይህን ሁሉ ከጥ
በበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ
ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ አዎን፣ አባት

10፥1 ማቴ10፥1፤ ማር6፥7፤ ሉቃ7፥13፤ 9፥1፡2፡51፡52
10፥2 ማቴ9፥37፡38፤ ዮሐ4፥35
10፥3 ማቴ10፥16
10፥7 1ጢሞ5፥18
10፥8 1ቆሮ10፥27
10፥9 ማቴ3፥2
10፥11 ቁ9፤ ማቴ10፥14
10፥12 ማቴ10፥15፤ ማቴ11፥24
10፥13 ሉቃ6፥24-26፤ ራእ11፥3
10፥15 ማቴ4፥13
10፥16 ማቴ10፥40
10፥17 ቁ1፤ ማር16፥17
10፥18 ኢሳ14፥12፤ ማቴ4፥10፤ ራእ9፥1፤ 12፥8፡9
10፥19 ማር16፥18፤ ሐሥ28፥3-5
10፥20 ራእ20፥12
10፥21 1ቆሮ1፥26-29

[a] *10፥15 ወይም ወደ ጥልቁ*

---

**10፥1 ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው፤** አገልጋዮችን ሁለት ሁለት አድርጎ የመላክ መርሕ ለእያንዳንዱ አገልጋይ እምነትንና ጥበብን ስለሚጨምር፣ በጌታ ሥራ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ከዚህም በላይ ሁለት ሁለት አድርጎ መላክ፣ በአገልግሎት ውስጥ ድፍረትን ይሰጣል:: ሁለት ሁለት አድርጎ ስለመላክ የሚናገሩ ሌሎች ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፤ መክ 4፥9-12፤ ማቴ 18፥16፤ ማር 6፥7፤ 14፥13፤ ሉቃ 7፥19፤ ዮሐ 1፥35-41፤ 8፥17፤ ሐሥ 9፥38፤ 10፥7፤ 15፥36-41፤ 19፥22፤ 2ቆሮ 13፥1፤ 1ጢሞ 5፥19፤ ዕብ 10፥28፤ ራእ 11፥3-6፡10-12::

**10፥2 መከሩ ብዙ ነው፤** ማቴ 9፥37 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**10፥3 እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል፤** የእግዚአብሔርን ፈቃድ በታማኝነትና የሚከተሉ አማኞች ብዙ አስፈሪ ችግር ሊደርስባቸው ይችላል:: በተኩላዎች መካከል እንዳሉና ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህንንም በመረዳት የእግዚአብሔር ሀልዎት፣ ጥበቃና መግቦት እንዳይለየን ዘወትር አጥብቀን መጸለይ አለብን::

**10፥9 በሽተኞች እየፈወሳችሁ፣** የእግዚአብሔር መንግሥት፤ «የእግዚአብሔርን መንግሥት» መስበክ በሽተኞችን ከመፈወስ ጋር የተያያዘ እንደ ሆነ እዚህም ላይ ኢየሱስ በአጽንኦት ይናገራል:: ይህንንም በይበልጥ ለመረዳት 9፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**10፥19 እባቡንና ጊንጡን፤** «እባብና ጊንጥ» እጅግ አደገኛ የሆኑ የክፉት መንፈሳዊ ኀይላትን የሚያመለክቱ ቃሎች ናቸው:: ክርስቶስ በሰይጣን ላይ ሥልጣኑን ስለ ሰጠን፣ ክርስቲያኖች በክፉ መንፈስ ላይ ኀይል አላቸው (በገጽ 1499 ላይ፣ *«በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**10፥20 በዚያ ደስ አይበላችሁ፤** አጋንንት ስለተገዙላቸውና በአገልግሎት ድል ስላገኙ የደስታቸው ምንጭ በዚያ ላይ የተመሠረተ እንዳይሆን ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ያስጠነቅቃል:: የደስታቸው ምንጭ መሆን ያለበት ከኀጢአት መቤዠታቸውና የዘላለም ሕይወት ማግኘታቸው ነው (ማቴ 7፥22-23 እና ማብ ይመ)::

**10፥21 ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ... ለሕፃናት፤** ሰማያዊ አባቱ ስለ መንፈሳዊ እውነት መረዳትን የሚሰጠው፣ በራሳቸው ዐይን ዐዋቂዎችና ጥበበኞች ነን ለሚሉት ሳይሆን በቃሉ የተገለጠውን እውነት እንደ ሕፃን ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በትሕትና ለሚቀበሉ በመሆኑ ኢየሱስ ደስ ይለዋል:: በራሳቸው ከፍተኛ ተብዬ ዕውቀት ላይ በመደገፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት ለመመርመር ራሳቸውን ዐዋቂዎች አድርገው የሚቈጥሩ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል ዕውቀታቸውን መሠረት የሚያደርጉ ከልጁ ኅብረትና እርሱ ከሚገልጠው ዕውቀት የራቁ ናቸው (ቍ 22)::

ሆይ፤ ይህ የአንተ በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።

22"ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ደግሞም ወልድ ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፤ አብ ማን እንደ ሆነም ከወልድ በቀር፣ ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅደው በቀር የሚያውቅ የለም።"

23ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ ለብቻቸው እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዐይኖች ብፁዓን ናቸው፤ 24እላ ችኋለሁና፤ ብዙ ነቢያትና ነገሥታት እናንተ የምታዩትን ለማየት ፈልገው አላዩም፤ የምትሰሙትንም ለመስማት ፈልገው አልሰሙም።"

## ደጉ ሳምራዊ

*10፥25-28 ተጓ ምብ — ማቴ 23፥34-40፤ ማር 12፥28-31*

25እነሆም አንድ ቀን፣ አንድ ሕግ ዐዋቂ ኢየሱስን ሊፈትነው ተነሥቶ፣ "መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?" አለው።

26ኢየሱስም፣ "በሕግ የተጻፈው ምንድን ነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?" ሲል መለሰለት።

27ሰውየውም መልሶ፣ "'ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህና በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ' ይላል" አለው።

28ኢየሱስም፣ "በትክክል መልሰሃል፤ አንተም እንደዚሁ አድርግ፤ በሕይወት ትኖራለህ" አለው።

29ሰውየውም ራሱን ጻድቅ ለማድረግ ፈልጎ፣ "ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?" አለው።

30ኢየሱስም እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው፤ "አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ በወንበዴዎች እጅ ወደቀ፤ ልብሱንም ገፈው ደበደቡት፤ በሞት አፋፍ ላይ ጥለውት ሄዱ። 31አንድ ካህን በአጋጣሚ በዚያው መንገድ ቍልቍል ሲወርድ አየውና ገለል ብሎ አለፈ። 32ደግሞም አንድ ሌዋዊ እዚያ ቦታ ሲደርስ አየውና እርሱም ገለል ብሎ አለፈ። 33አንድ ሳምራዊ ግን እግረ መንገዱን ሲሄድ ሰውየው ወዳለበት ቦታ ደረሰ፤ ባየውም ጊዜ ዐዘነለት፤ 34ቀርቦም ቍስሎቹ ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ አፍስሶ አሰረለት፤ በራሱም አህያ ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማረፊያ ቤት ወሰደው፤ በዚያም ተንከባከበው። 35በማግሥቱም ሁለት ዲናር[x] አውጥቶ ለማረፊያ ቤቱ ባለቤት ሰጠና፣ 'ይህን ሰው ዐደራ አስታመው፤ ከዚህ በላይ የምታወጣውንም ወጪ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ' አለው።

36"እንግዲህ፣ ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ሰው ባልንጀራ የሆነው የትኛው ይመስልሃል?"

37ሕግ ዐዋቂውም፣ "የራራለት ነው" አለ።

ኢየሱስም፣ "አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ" አለው። *ሉቃ 12፥42-48*

## ኢየሱስ በማርታና በማርያም ቤት

38ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መንገድ ሲሄዱ፣ ኢየሱስ ወደ አንድ መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤቷ ተቀበለችው። 39እርሷም ማርያም የተባለች እኅት ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ነበር። 40ማርታ ግን በሥራ ብዛት ትባክን ነበርና ወደ እርሱ ቀርባ፣ "ጌታ ሆይ፤ እኅቴ ሥራውን ለእኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን? እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ" አለችው።

41ጌታ ግን እንዲህ ሲል መለሰላት፤ "ማርታ፣ ማርታ፤ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፤ ትዋከቢአለሽም፤ 42የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው[y]፤ ማርያም እኮ የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወሰድም።"

10፥22 ማቴ28፥18፤ ዮሐ1፥18
10፥24 1ጴጥ1፥10-12
10፥25 ማቴ19፥16፤ ሉቃ18፥18
10፥27 ዘሌ19፥18፤ ዘዳ6፥5፤ ማቴ5፥43
10፥28 ሮሜ7፥10
10፥29 ሉቃ16፥15
10፥31 ዘሌ21፥1-3
10፥33 ማቴ10፥5
10፥38 ዮሐ11፥1፤ 12፥2
10፥39 ሉቃ8፥35፤ ዮሐ11፥1፤ 12፥3
10፥40 ማር4፥38
10፥41 ማቴ6፥25-34፤ ሉቃ12፥11፡22
10፥42 መዝ27፥4

*[x]10፥35 ወይም ሁለት የናስ ሳንቲሞች*
*[y]10፥42 አንዳንድ ቅጆች የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ብቻ ነው ይላሉ*

**10፥27 ጌታ አምላክህን … ውደድ፤ ባልንጀራህንም … ውደድ፤** ማቴ 22፥37፡39 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።።

**10፥30-35 በዚህ ክፍል የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ ተጠቅሶአል፤** በውስጣችን ለድነት የሚያበቃ እውነተኛ እምነትና መታዘዝ ካለ ለተቸገሩት በመራራት ሊታይ እንደሚገባው ይህ ምሳሌ ይገልጻል። እግዚአብሔርን እንድንወድ የሚደረግ ጥሪ ሌሎችን እንድንወድ የሚጠይቅ ነው፤ (1) ክርስቶስ፣ እርሱን ለሚቀበሉ የሚሰጠው አዲስ ሕይወትና ጸጋ በችግርና በጭንቀት ውስጥ ላሉት እናስብ ዘንድ ፍቅርን፣ ምሕረትንና ርኅራኄን በልባችን የሚፈጥር ነው። ልብን ከሚያደነድን ርቀው፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በሚያፈስው ፍቅር መሠረት መኖርና በተግባር መግለጽ የአማኞች ሁሉ ኀላፊነት ነው። (2) ክርስቲያን በመባል በግልጽ የሚታወቁ ሰዎች፣ ነገር ግን በመከራና በችግር ውስጥ ላሉት የሚራራ ልብ የሌላቸው በውስጣቸው የዘላለም ሕይወት እንደሌላቸው ማለትም እምነታቸው በተግባር የማይታይና ሊያድን የማይችል ሙት እንደ ሆነ ይህ ተጨባጭ ማስረጃ ነው (ቍ 25-28፡31-37 ይመ፤ ከማቴ 25፥41-46፤ ከ1ዮሐ 3፥16-20 ጋር ያነጻጽሩ)።።

**10፥42 የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው፤** ትጋት በታከለበትና በተግባር በሚታይ ሁኔታ እግዚአብሔርን ማገልገል አስፈላጊና ጥሩ ቢሆንም፣ ከሁሉ ይበልጥ አስፈላጊና ቀዳሚ የሆነው ተግባራችን በጸጥታ እግዚአብሔርን በማምለክ፣ በመጸለይና ከጌታ ጋር ኅብረት በመፍጠር የሚገለጽ ፍቅርና የተሰጠ ልብ እንዲኖረን መትጋት ነው (ማቴ 26፥13 እና ማብ ይመ)።። ከአዳኛችን ጋር ላለን መንፈሳዊ ግንኙነት ጊዜ እስከምናጣ ድረስ የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራት፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመካፈልና ለተቸገሩት መልካም ነገር በማድረግ ጉዳይ የተጠመድን ነን?

## ኢየሱስ ያስተማረው ጸሎት

*11፥2-4 ተጓ ምብ — ማቴ 6፥9-13*
*11፥9-13 ተጓ ምብ — ማቴ 7፥7-11*

11 አንድ ቀን ኢየሱስ በአንድ ስፍራ
ይጸልይ ነበር፤ ጸሎቱንም እንደ
ጨረሰ፣ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ "ጌታ
ሆይ፤ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ጸሎት
እንዳስተማራቸው አንተም መጸለይን
አስተምረን" አለው።
[2]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ስትጸልዩ
እንዲህ በሉ፤
"'አባታችን[ሠ] ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
መንግሥትህ ትምጣ፤[ሡ]
[3]የዕለት እንጀራችንን በየዕለቱ ስጠን፤
[4]በደላችንን ይቅር በለን፤
እኛም የበደሉንን[ሢ] ሁሉ
ይቅር ብለናልና።
ወደ ፈተናም አታግባን፤
ከክፉው አድነን እንጂ።'"[ሣ]
[5]ደግሞም እንዲህ አላቸው፤ "ከእናንተ
አንዱ ወዳጅ ቢኖረውና በእኩለ ሌሊት ወደ
እርሱ ሄዶ፣ 'ወዳጄ ሆይ፤ ሦስት እንጀራ
አበድረኝ፤ [6]አንድ ባልንጀራዬ ከመንገድ
መጥቶብኝ የማቀርብለት ምንም ነገር
የለኝምና' ብሎ ለመነው እንበል።
[7]"በቤት ውስጥ ያለውም፣ 'አታስቸግረኝ፤
በሩ ተቈልፎአል፤ ልጆቼም አብረውኝ
ተኝተዋል፤ ከእንግዲህ ተነሥቼ ልሰጥህ
አልችልም' ይለዋልን? [8]እላችኋለሁ፤
ወዳጁ በመሆኑ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፣
ስለ ንዝነዛው[ሤ] ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ
ይሰጠዋል።
[9]"ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለምኑ
ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ
ይከፈትላችኋል፤ [10]ምክንያቱም የሚለምን
ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ በር
ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል።
[11]"ከእናንተ መካከል አባት ሆኖ ሳለ
ልጁ[ሥ] ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው
ይኖራልን? [12]ወይስ ዕንቍላል ቢለምነው
ጊንጥ ይሰጠዋልን? [13]እናንተ ክፉዎች
ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም
ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት፣ የሰማዩ
አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ
ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ!"

## ጌታ ኢየሱስና ብዔል ዜቡል

*11፥14:15:17-22:24-26 ተጓ ምብ —*
*ማቴ12፥22:24-29:43-45*
*11፥17-22 ተጓ ምብ — ማር 3፥23-37*

[14]አንድ ቀን ኢየሱስ ድዳ ጋኔን ያወጣ
ነበር፤ ጋኔኑም ከወጣለት በኋላ ድዳው ሰው
ተናገረ፤ ሕዝቡም ተገረመ። [15]አንዳንዶቹ
ግን፣ "በአጋንንት አለቃ፣ በብዔል ዜቡል[ሦ]፣
አጋንንትን ያወጣል" አሉ፤ [16]አንዳንዶቹ
ደግሞ ሊፈታተኑት ከሰማይ ምልክት
እንዲያሳያቸው ከእርሱ ይፈልጉ ነበር።
[17]ኢየሱስ ግን ሐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ "እርስ በርሱ የሚከፋፈል
መንግሥት ሁሉ ይጠፋል፤ የሚለያይ
ቤትም ይወድቃል። [18]ሰይጣንም እርስ
በርሱ ከተከፋፈለ፣ መንግሥቱ እንዴት
ይጸናል? አጋንንትን በብዔል ዜቡል
እንደማወጣ ትናገራላችሁና። [19]እንግዲህ
እኔ አጋንንትን የማወጣው በብዔል ዜቡል
ከሆነ፣ ልጆቻችሁ በማን ያወጧቸው ይሆን?

*[ሠ]11፥2 አንዳንድ ቅጆች በሰማይ የምትኖር አባታችን ይላሉ*
*[ሡ]11፥2 አንዳንድ ቅጆች ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ይላሉ*
*[ሢ]11፥4 አንዳንድ ቅጆች በእኛ ላይ ኀጢአት የሠሩትን ይላሉ።*
*[ሣ]11፥4 አንዳንድ ቅጆች ከክፉው አድነን እንጂ የሚለው የላቸውም።*
*[ሤ]11፥8 ወይም ስለ ብዙ ልመናው*
*[ሥ]11፥11 አንዳንድ ቅጆች ዳቦ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው አለን? የሚል አላቸው።*
*[ሦ]11፥15 ግሪኩ ብዔኤዜቡል ወይም ብዔል ዜብል ይላል፤ እንዲሁም ቍ 18፡19 ይመ*

11፥1 ሉቃ3፥21፤ ዮሐ13፥13
11፥2 ማቴ3፥2
11፥4 ማቴ18፥35፤ 26፥41፤ ማር11፥25፤ ያዕ1፥13
11፥8 ሉቃ18፥1-6
11፥9 ማቴ7፥7
11፥14ማቴ፥32:33
11፥15 ማቴ9፥34፤ ማር3፥22
11፥16 ማቴ12፥38
11፥17 ማቴ9፥4
11፥18 ማቴ4፥10

**11፥2-4 በዚህ ክፍል ኢየሱስ ያስተማረው ጸሎት ተገልጾአል፤** ማቴ 6፥9-15 እና ጌታ ባስተማረው ጸሎት ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**11፥3 የዕለት እንጀራችንን፤** አማኞች በሚከተሉት አራት መርሖች ላይ በመመሥረት በየቀኑ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ጸሎት መጸለይን መማር አለባቸው (ከማቴ 6፥11 ጋር ያነጻጽሩ) (1) እንደዚህ ዐይነቱን ጥያቄ በጸሎት ማቅረብ ያለብን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ለእግዚአብሔር ክብር መሆን አለበት (ማቴ 6፥10:33፤ 1ቆሮ 10፥31፤ 1ዮሐ 5፥14-15)፤ (2) እግዚአብሔር የአባትነት ፍቅሩን እንዲገልጽልን በመሻት በእርሱ ፊት በጸሎት መቅረብ አለብን (ማቴ 6፥9:25-34)፤ (3) እንዲሰጡን በጸሎት የምንለምናቸው ነገሮች መሠረታዊ ፍላጐታችንን የሚያሟሉና ክርስቲያናዊ አገልግሎት ለመፈጸም የሚያስችሉን መሆን አለባቸው (2ቆሮ 9፥8፤ 1ጢሞ 6፥8፤ ዕብ 13፥5)፤ (4) እግዚአብሔር አንድን ነገር እንዲሰጠን መጠየቅ የምንችለው፣ በመጀመሪያ የሰጠንን ነገር በታማኝነት ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ከሰጠን በኋላ ነው (2ቆሮ 9፥6 ይመ፤ 8፥2 እና ማብራሪያውን ይመ)።

**11፥9 ለምኑ ... ፈልጉ ... በር አንኳኩ** ማቴ 7፥7 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**11፥11 እባብ የሚሰጠው ይኖራልን?** ማቴ 7፥11 እና እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያደርገው ጥንቃቄ በሚለው ሐሳብ ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**11፥13 ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ፤** ክርስቶስን አምነው በሚለወጡበት ጊዜ አማኞች ሁሉ ወዲያውኑ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ይኖር ዘንድ ስለሚሰጣቸው (ሮሜ 8፥9-10፤ 1ቆሮ 6፥19-20 ይመ፤ በገጽ 1646 ላይ፣ *"የደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን መቀበል"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፣ ምናልባት ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው በአዲስ ልደት ጊዜ የሚሆነውን መንፈስ ቅዱስን መቀበል ላይሆን ይችላል (ዮሐ 3፥3)። ነገር ግን ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ተስፋ የሰጠውን በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን ነው (በገጽ 1559 ላይ፣ *"ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

# ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ

*ሉቃ 11፥13 "እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት፣ የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ!"*

---

ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተለየ ግንኙነት ነበረው፤ ይህ ግንኙነት ዛሬም በግል ሕይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህ የትኩረት ጽሑፍ ያንን ግንኙነትና ተጨባጭ የሆኑ እንድምታዎችን ምን እንደሆኑ ይገልጻል።

**የብሉይ ኪዳን ትንቢት፤** የመሲሑን መምጣት አስመልክቶ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶች ብዙዎቹ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል በእርሱ ላይ እንደሚሆን አስቀድመው በግልጽ ተናግረዋል (ኢሳ 11፥2 እና ማብራሪያውን፣ 61፥1-3 እና ማብራሪያውን ይመ)። ኢየሱስ በናዝሬት በአይሁድ ምኩራብ ውስጥ ሆኖ ከኢሳ 61፥1-2 ጠቅሶ ባነበበት ጊዜ፣ "ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ" ብሎ ተናገራቸው (ሉቃ 4፥18-21)።

**የኢየሱስ መወለድ፤** ኢየሱስ በእግዚአብሔር ታምራዊ አሠራር ወደዚህ ምድር እንደመጣ ማቴዎስና ሉቃስ ሁለቱም ያለምንም ማዛባት ግልጽ አድርገው ይናገራሉ። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ፣ ከድንግል ማርያምም ተወለደ (ማቴ 1፥18፡23፤ ሉቃ 1፥27)። ታምራዊ በሆነ አሠራር በመፀነሱ ኢየሱስ ጨርሶ የኀጢአት እድፈት የሌለበት "ቅዱስ" ነበር (ሉቃ 1፥35)። ከዚህም የተነሣ አበሳችንን ለመሸከምና ኀጢአታችንን ለማስተሰረይ ብቁ ሆነ (ማቴ 1፥23 እና ማብ ይመ)። ፍጹም የሆነና ኀጢአት የሌለበት አዳኝ ሳይኖረን፣ ድነትን ማግኘት አንችልም ነበር።

**የኢየሱስ መጠመቅ፤** በኋላ በበዓለ ኀምሳ ቀንና በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ (ሉቃ 3፥16፣ ሐሥ1፥4-5፤ 2፥33፡38-39) ደቀ መዛሙርቱን በመንፈስ ቅዱስ ያጠመቀው ኢየሱስ፣ በዮሐንስ መጥምቁ በተጠመቀበት ጊዜ ራሱ በግሉ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶአል (ማቴ 3፥16-17፤ ሉቃ 3፥21-22)። መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የድነት ሥራውን ጨምሮ አገልግሎቱን ያከናወን ዘንድ በታላቅ ኀይል ሞላው። ጌታችን የውሃ ጥምቀት ከወሰደ በኋላ ወደ በረሐ በሚሄድበት ጊዜ፣ "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ" ነበር (ሉቃ 4፥1)። መለኮታዊ በሆነ አሠራር በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ያገኙ ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ሕይወት ላይ እንደታየው፣ በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው ኀይልን ይቀበሉ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አለባቸው (ሐሥ 1፥8 እና ማብ ይመ)።

**የኢየሱስ በሰይጣን መፈተን፤** ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው መንፈስ ቅዱስ ወደ በረሐ ወሰደው፣ በዚያም ለአርባ ቀናት በዲያብሎስ ተፈተነ (ሉቃ 4፥1-2)። ኢየሱስ ሰይጣንን ፊት ለፊት ለመግጠምና በጉዞውም ላይ ያመጣበትን ፈተና ለመቋቋም የቻለው በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞላ ብቻ ነበር። እንደዚሁም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ሳንሞላ የክፋትን መንፈሳውያን ሰራዊት ኀይልና ኀጢአትን ለመግጠም እንወጣ ዘንድ የእግዚአብሔር ፍላጎት አይደለም። በሰይጣን ላይ ድል ለመቀዳጀት በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መታጠቅና የእርሱን ምሪት መከተል አለብን። በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞላንና በኀይሉም ካልኖርን፣ በእግዚአብሔር እይታ "ጤናማ" ልጆቹ አይደለንም።

**የኢየሱስ አገልግሎት፤** ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ እንደሚወርድ በኢሳይያስ ላይ የተጻፈውን ትንቢት ጠቅሶ እንደተናገረ ሁሉ፣ የአገልግሎቱም ዐይነት ወንጌልን መስበክ፣ የታመሙትን መፈወስና በአጋንንት የተያዙትን ነጻ ማውጣትን እንደሚያካትት ለመግለጽ ይህንኑ ክፍል ተጠቅሞአል (ኢሳ 61፥1-2፤ ሉቃ 4፥16-19 ይመ)፤ (1) መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ቀባው፤ ለተልእኮውም ለማዘጋጀት በኀይል ሞላው። ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ 1፥1)፤ ደግሞም ሰው (1ጢሞ 2፥5) ነበረ። ሰው እንደ መሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ኀላፊነቱን ለመወጣት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታና ኀይል መደገፍ ያስፈልገው ነበር (ከማቴ 12፥28፤ ከሉቃ 4፥1፡14፤

ከሮሜ 8፥11፤ ከዕብ 9፥14 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ኢየሱስ መኖር፣ ማገልገልና ወንጌልን መስበክ የቻለው እንደ አንድ በመንፈስ ቅዱስ እንደተቀባ ሰው በመሆን ብቻ ነበር (ሐሥ 10፥38)። በዚህ አቅጣጫ ኢየሱስ ለአንድ ክርስቲያን ፍጹም የሆነ ምሳሌ ነው፤ እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መቀበል አለበት (ሐሥ 1፥8 እና ማብ፤ 2፥4 እና ማብ ይመ)።

**መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት ኢየሱስ የሰጠው ተስፋ፤** ኢየሱስ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ፣ ዮሐንስ መጥምቁ ትንቢት ተናግሮአል (ማቴ 3፥11፤ ማር 1፥8፤ ሉቃ 3፥16 እና ማብ፤ ዮሐ 1፥33 ይመ)፤ ስለዚህም ጉዳይ ኢየሱስ ራሱ ደጋግሞ ትንቢት ተናግሮአል (ሐሥ 1፥5፣ 11፥16)። በሉቃ 11፥13 ላይ ኢየሱስ ለሚለምኑት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ ተስፋ ሰጥቶአል (በዚያ ጥቅስ ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)። እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች ክርስቶስ፣ የሰማያዊ አባት ልጆች ለሆኑት የሰጠውን በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ተስፋን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህም ተስፋ በበዓለ ኀምሳ ቀን የተፈጸመ ከመሆኑም ባሻገር (ሐሥ 2፥4 እና ማብ ይመ) ዛሬም ደቀ መዛሙርቱ ለሆኑትና በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ ለሚጸልዩት ሁሉ እውን የሚሆን ነው (ሐሥ 1፥5፤ 2፥39 እና ማብ ይመ)።

**የኢየሱስ ትንሣኤ፤** በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶአል፤ ይህም እውነተኛው መሲሕና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያረጋግጣል። በሮሜ 1፥3-4 ላይ በቅድስና መንፈስ ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተገለጠው" በማለት ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጽፎ እናነባለን፤ በሮሜ 8፥11 ላይ ደግሞ፣ ኢየሱስ ከሞት ለመነሣት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መደገፍ እንዳስፈለገው ሁሉ፣ ዛሬም አማኞች ምሳሌነት ያለው መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖርና ወደፊትም የአካል ትንሣኤን ለማግኘት (ሮሜ 8፥10-11) በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ ያስፈልጋቸዋል።

**የኢየሱስ ወደ ሰማይ ማረግ፤** ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም መንግሥት እኩል ኀላፊነት ያለው ገዥ በመሆን፣ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ (ማር 16፥19፤ ሉቃ 24፥51፤ ሐሥ 1፥9-11፤ ኤፌ 4፥8-10)። ኢየሱስ በዚህ እጅግ ከፍ ባለ ስፍራ ከተቀመጠ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ከአባቱ ተቀብሎ በበዓለ ኀምሳ ቀን በሕዝቡ ላይ አፈሰሰው (ሐሥ 2፥33 ይመ፤ ከዮሐ 16፥5-14 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም የነቢይነት፣ የካህንነትና የንጉሥነት ሥልጣኑን ያረጋግጣል። በበዓለ ኀምሳ ቀን እንደዚሁም በዚህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የከበረው አዳኝ ህልዎትና ሥልጣን የማያቋርጥ መሆኑን ይገልጻል።

**የኢየሱስ ለሕዝቡ ቅርብ መሆን፤** አሁን የመንፈስ ቅዱስ አንዱ ሥራ፣ የክርስቶስ ከሆነው ወስዶ ለአማኞች ማግለጽ ነው (ዮሐ 16፥14-15)። ይኸውም በክርስቶስ የሆነልን ድነት ያስገኘልን ጠቀሜታ ወደ እኛ የሚመጣውና የምንረዳው በመንፈስ ቅዱስ ነው (ከሮሜ 8፥14-16፤ ከገላ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። ከሁሉም የሚበልጠው ነገር፣ ኢየሱስ ለእኛ ቅርብ የመሆኑ ጉዳይ ነው (ዮሐ 14፥18)። መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ህልዎት፣ ፍቅር፣ በረከት፣ እርዳታ፣ ምሕረት፣ ፈውስ እንደዚሁም በእምነት የእኛ የሆነው ሁሉ ለመረዳት ያስችለናል። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ በፍቅር፣ በጸሎትና በአምልኮ ጌታን እንድንፈልግ ልባችንን ያነሣሣል (ዮሐ 4፥23-24፤ 16፥14 እና ማብ ይመ)።

**የኢየሱስ ሕዝቡን ለመውሰድ ተመልሶ መምጣት፤** ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር ይኖሩ ዘንድ ኢየሱስ ለእርሱ ታማኝ የሆኑትን ለመውሰድ ተመልሶ እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶአል (ዮሐ 14፥3 እና ማብራሪያውን፤ 1ተሰ 4፥13-18 ይመ)። ይህ ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ የተባረከ ተስፋ ሲሆን (ቲቶ 2፥13)፣ ሁላችንም የምንጸልይበትና የምንናፍቀው ጉዳይ ነው (2ጢሞ 4፥8)። የጌታችንን መመለስ አስመልክቶ ወደ እግዚአብሔር እንጮህ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ልባችንን እንደሚያነሣሣ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል። ከኀጢአት ፍጹም ነጻ የምንሆነው ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ እንደሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልናል (ከሮሜ 8፥23 ጋር ያነጻጽሩ)። በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ላይ መንፈስ ቅዱስ፣ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ና" የሚለው ሐረግ እንዲጻፍ አድርጐአል (ራእ 22፥20)።

ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባች ኋል።
20እኔ ግን አጋንንትን የማወጣው በእግዚአብሔር
ጣት ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ
እናንተ እንደ መጣች ዕወቁ።
21"ብርቱ ሰው በሚገባ ታጥቆ ቤቱን
ከጠበቀ፣ ንብረቱ በሰላም ይቀመጣል።
22ነገር ግን ይበልጥ ብርቱ የሆነ ሰው መጥቶ
ካጠቃ ውና ካሸነፈው ታምኖበት የነበረውን
ትጥቁን ያስፈታዋል፤ ምርኮውንም ወስዶ
ለሌሎች ያካፍላል።
23"ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፤
ከእኔ ጋር የማይሰበስብም ይበትናል።
24"ርኩስᵘ መንፈስ ከሰው ሲወጣ ዕረፍት
ፍለጋ ውሃ በሌለበት ስፍራ ይንከራተታል፤
ሳያገኝም ሲቀር፣ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመ
ለሳለሁ ይላል፤ 25ሲመለስም ቤቱ ተጠራርጎና
ተስተካክሎ ያገኘዋል። 26ከዚያም በኋላ ሄዶ
ሌሎች ከእርሱ የከፉ ሰባት አጋንንት ይዞ
ይመጣል፤ ገብተውበትም በዚያ ይኖራሉ፤
ለዚያ ሰው ከመጀመሪያው ይልቅ የኋለኛው
ሁኔታ የከፋ ይሆንበታል።
27ኢየሱስ ይህን እየተናገረ እያለ፣ ከሕዝቡ
መካከል አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፣
"የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባሃቸው
ጡቶች ብፁዓን ናቸው" አለችው።
28እርሱ ግን፣ "ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን
ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው" አለ።

11፥20 ዘፀ8፥19፤ ማቴ3፥2
11፥23 ማቴ12፥30፤ ማር9፥40፤ ሉቃ9፥50
11፥26 2ጴጥ2፥20
11፥27 ሉቃ23፥29
11፥28 ምሳ8፥32፤ ሉቃ6፥47፤ 8፥21፤ ዮሐ14፥21፤ ዕብ4፥12
11፥29 ቍ16፤ ዮና1፥17፤ ማቴ12፥38፤ 16፥4
11፥31 1ነገ10፥1፤ 2ዜና9፥1
11፥32 ዮና3፥5
11፥33 ማቴ5፥15

## የዮናስ ምልክትነት

*11፥29-32 ተጓ ምብ — ማቴ 12፥39-42*

29ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ በሄደ ጊዜ
ኢየሱስ እንዲህ ይል ጀመር፤ "ይህ ትውልድ
ክፉ ነው፤ ታምራዊ ምልክት ይፈልጋል፤
ነገር ግን ከዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ
አይሰጠውም። 30ምክንያቱም ዮናስ ለነነዌ
ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው የሰው
ልጅም ለዚህ ትውልድ ምልክት ይሆናል።
31የደቡብ ንግሥት በፍርድ ጊዜ ከዚህ
ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድባቸዋለች፤
እርሷ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር
ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ፤ ከሰሎሞን
የሚበልጥ እዚህ አለ። 32የነነዌ ሰዎችም
በፍርድ ጊዜ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው
ይፈርዱበታል፤ እነርሱ የዮናስን ስብከት
ሰምተው ንስሓ ገብተዋልና፤ እነሆ፣ ከዮናስ
የሚበልጥ እዚህ አለ።

## የሰውነት መብራት

*11፥34-35 ተጓ ምብ — ማቴ 6፥22-23*

33"መብራት አብርቶ በስውር ቦታ ወይም
ከእንቅብ በታች የሚያስቀምጥ ማንም
የለም፤ ይልቁን የሚገቡ ሰዎች ብርሃኑን
እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጠዋል።
34የሰውነትህ ብርሃን ዐይንህ ናት፤ ዐይንህ
ጤናማ ስትሆን መላ ሰውነትህ ብሩህ ይሆ

*ᵘ11፥24 ወይም ክፉ*

**11፥20 አጋንንትን ... የእግዚአብሔር መንግሥት፤** ይህ ክፍል የሚከተሉትን ሦስት ነገሮች ይገልጻል፤ (1) የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ የሚያገኘው ድል፣ ከሚጠፋው የዲያብሎስ ሥራ፣ ከኀጢአትና ከአጋንንት አሠራር ነጻ ከመውጣት ጋር በቀጥታ የሚመጣጠን ነው፤ (2) ሰይጣን የክርስቶስን መንግሥት ወደ ምድር መምጣት ይቃወማል (ቍ 24-26 ይመ፤ ከማቴ 13፥18-30፤ ከራእ 12፥12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) ኢየሱስ አጋንንትን በማስወጣት፣ ሰይጣንን አሸንፎ ንብረቱን በመንጠቅ (ቍ 20-22)፣ መለኮታዊ ኀይሉንና ሥልጣኑን ይገልጻል፤ ስለዚህ የበለጠ ለመረዳት በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስና በገጽ 1499 ላይ፣ ደግሞ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመልከቱ።

**11፥23 ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፤** በክርስቶስ መንግሥትና በክፋው ኀይል መካከል ጦርነት ሲደረግ ገለልተኛ ሆኖ መቆመጥ በፍጹም አይቻልም፤ (1) ክርስቶስን የማይቃወሙትና ከክርስቶስ ጋር የሚተባበሩት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በግልጽ የሚያሴሩትን ሰይጣንንና ክፉ መናፍስትን ይቃወማሉ። እያንዳንዱ ሰው ወይ የክርስቶስና የጽድቅ ወገን በመሆን፣ አሊያም ሰይጣንና ተከታዮቹን በመደገፍ በውጊያ ላይ ይገኛል፤ (2) የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ገለልተኛነትን፣ ከዐመፅ ሥጋ ጋር መተባበርን ወይም ከፊል የሆነ መታዘዝን ያወግዛል።

**11፥26 ሌሎች ... ሰባት አጋንንት ... በዚያ ይኖራሉ፤** በዚህ ክፍል ያለው ሐሳብ በማቴ 12፥43-45 ላይ በተጠቀሰው ቤቱ ባዶ እንደሆነና ጽድቅም እንደሚገኝ በሚናገረው ተመሳሳይ ሐሳብ ግልጽ ተደርጎአል፤ (1) የሕይወት ለውጥና ድነት በሚሆንበት ጊዜ (ዮሐ 3፥3) አማኞች ከኀጢአት ነጻ መውጣት ብቻ ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ፣ ለጸሎት፣ ለጽድቅ፣ ለቃሉና ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት (ሐሥ 2፥4፤ ሮሜ 8) ራሳቸውን አሳልፈው መስጠት አለባቸው፤ (2) ከሕይወት መለወጥ በኋላ የሰይጣን ኀይል መሥራት ያቆማል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ጨርሶ የማያቋርጥ ሥጋት ፈጣሪ ሆኖ ይቀጥላል (22፥31፤ ማቴ 6፥13 እና ማብ ይመ)። ከኀጢአትና ከሰይጣን መጠበቅ የሚቻለው፣ ሕይወትን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ አሳልፎ በመስጠትና ክርስቶስ ከሚሰጠው ጸጋ የሚገኘውን ብልኀትና ጥበብ በመጠቀም ብቻ ነው (ኤፌ 6፥11 እና ማብ ይመ)፤ (3) ከአጋንንት እስራት ነጻ እንዲወጡ የተደረጉ፣ ነገር ግን አሁንም ኀጢአትን ሙሉ በሙሉ የማያወግዙ ወይም ለእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን የማይከፍቱ ከሆነ፣ ክፉ መንፈስ ወደ እነርሱ ተመልሶ በአዲስ ኀይል እንዲኖር መጋበዛቸው ነው።

**11፥34 የሰውነትህ ብርሃን ዐይንህ ናት፤** ሰውነት ብርሃን የሚቀበለው በዐይን አማካይነት ነው። አንድ ሰው ዐይኑ ጤናማ ከሆነች በሚገባ ብርሃን መቀበልና በብርሃንም መጠቀም ይችላል። ዐይኑ ታማሚ ከሆነች ግን ሰውነቱ ጨለማ ይወርሰዋል፤ መራመድም ሆነ መሥራት አይችልም፤ (1) የሰዎች መንፈሳዊ ዐይን የሚሠራውም እንደዚሁ ነው፤ አመለካከታቸው፣ ስሜታቸውና ፍላጎታቸው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሚሆንበት ጊዜ የእግዚአብሔር ብርሃን ወደ ልባቸው ይገባል፤ ከዚህም በረከት፣ ፍሬና ድነት ይገኛል (ገላ 5፥22-23)፤ ነገር ግን ምኞታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሆኑ ነገሮች

ናል፤ ዐይንህ ታማሚ ከሆነች ግን መላ
ሰውነትህ የጨለመ ይሆናል። 35ስለዚህ
በውስጥህ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን
ተጠንቀቅ። 36እንግዲህ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ
ከሆነና የጨለመ የሰውነት ክፍል ከሌለበት፣
የሰውነትህ ሁለንተና መብራት በወገግታው
ያበራልህ ያህል ይደምቃል።"

## ስድስት ዐይነት ወዮታ

37ኢየሱስ ንግግሩን እንደ ጨረሰ፣ አንድ
ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምግብ እንዲበላ ጋበዘው፤
እርሱም አብሮት ገብቶ በማእድ ተቀመጠ።
38ፈሪሳዊውም ኢየሱስ ከምግብ በፊት እጁን
እንዳልታጠበ ባየ ጊዜ ተደነቀ።
39ጌታም እንዲህ አለው፤ "አሁን እናንተ
ፈሪሳውያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጫዊ
ክፍል ታጸዳላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን
በስስትና በክፋት የተሞላ ነው። 40እናንት
ሞኞች፤ የውጪውን የፈጠረ የውስጡንም
አልፈጠረምን? 41ነገር ግን በውስጥ ያለውን
ምጽዋት^ አድርጋችሁ ስጡ፤ በዚህ ጊዜ
ሁሉም ንጹሕ ይሆንላችኋል።
42"እናንት ፈሪሳውያን ግን ወዮላችሁ፤
ከአዝሙድና ከጤና አዳም እንዲሁም
ከአትክልት ሁሉ ዐሥራት ታወጣላችሁ፤
ሆኖም ፍትሕንና እግዚአብሔርን መውደድ
ቸል ትላላችሁ፤ ነገር ግን ያንን ሳትተዉ
ይኸኛውን ማድረግ በተገባችሁ ነበር።
43"እናንት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፤
በምኵራብ የክብር መቀመጫ፣ በገበያ
መካከልም እጅ መነሣትን ትወዳላችሁና።
44"ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበትን
የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ፣
ወዮላችሁ።"
45ከሕግ ዐዋቂዎች አንዱ መልሶ
"መምህር ሆይ፤ እንዲህ ስትናገር እኮ
እኛንም መስደብህ ነው" ሲል መለሰለት።
46ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "እናንት
ሕግ ዐዋቂዎችም ደግሞ ወዮላችሁ፤ ሰዎች
ሊሸከሙ የማይችሉትን ከባድ ሸክም ታሸክማ
ላችሁ፤ እናንተ ራሳችሁ ግን በጣታችሁ
እንኳ አትነኩትም።
47"አባቶቻችሁ የገደሏቸውን የነቢያትን
መቃብር ስለምታበጁ፣ ወዮላችሁ፤
48እንግዲህ የአባቶቻችሁን ሥራ የምታጸኑ
ምስክሮች ናችሁ፤ እነርሱ ነቢያትን ገደሉ፣
እናንተም መቃብራቸውን ታበጃጃላችሁ።
49ስለዚህም የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች፤
'ነቢያትንና ሐዋርያትን እልክላቸዋለሁ፤
እነርሱ አንዳንዶቹን ይገድላሉ፤ ሌሎችንም
ያሳድዳሉ።' 50ስለዚህ ይህ ትውልድ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ስለፈሰሰው፣ ስለ ነቢያት
ሁሉ ደም ተጠያቂ ነው፤ 51ከአቤል ደም
ጀምሮ፣ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ
መካከል እስከ ፈሰሰው እስከ ዘካርያስ ደም
ድረስ ይፈለግበታል፤ አዎን፣ እላችኋለሁ፤
ይህ ትውልድ ለዚህ ተጠያቂ ነው።
52"እናንት ሕግ ዐዋቂዎች ወዮላችሁ፤
የዕውቀትን መክፈቻ ነጥቃችሁ
ወስዳችኋልና፤ እናንተ ራሳችሁ
አልገባችሁበትም፤ የሚገቡትንም
ከልክላችኋል።"
53ኢየሱስ ከዚያ ከወጣ በኋላ፣ ጸሐፍትና
ፈሪሳውያን ክፉኛ ይቃወሙትና በጥያቄም
ያዋክቡት ጀመር፤ 54ከአፉ በሚወጣውም
ቃል ሊያጠምዱት ያደቡ ነበር።

## የማስጠንቀቂያና የማበረታቻ ቃላት

*12፥2-9 ተዛ ምብ — ማቴ 10፥26-33*

12 በዚያን ጊዜ፣ በብዙ ሺህ የሚቈጠር
ሕዝብ እርስ በርስ እስኪረጋገጥ
ድረስ ተሰብስቦ ሳለ፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙ
ርቱ እንዲህ ይል ጀመር፤ "ከፈሪሳውያን

11፥37
ሉቃ7፥36፤ 14፥1
11፥38 ማር7፥3፡4
11፥39
ማቴ23፥25፡26፤
ማር7፥20-23፤
ሉቃ7፥13
11፥40
ሉቃ12፥20፤
1ቆሮ15፥36
11፥41
ሉቃ12፥33፤
ሐሥ10፥15
11፥42 ዘዳ6፥5፤
ሚክ6፥8፤
ማቴ23፥23፤
ሉቃ18፥12
11፥43
ማቴ23፥6፤
ሉቃ14፥7፤
20፥46
11፥44
ማቴ23፥27
11፥45
ማቴ22፥35
11፥46 ማቴ23፥4
11፥48
ማቴ23፥29-32፤
ሐሥ7፥51-53
11፥49
ማቴ23፥24፤
1ቆሮ1፥24፡30፤
ቈላ2፥3
11፥52
ማቴ23፥13
11፥54
ማቴ12፥10
12፥1
ማቴ16፥6፡11፡12

*^11፥41 ወይም ያላችሁን*

ላይ ያተኰረ ካልሆነ ከእግዚአብሔር የሆነው መገለጥና እውነት በሕይወታቸው ምንም ፍሬ አያፈሩም።

(2) ወንጌል በእርግጥ እኛን መቀደስና ውስጣዊ ሕይወታችንን መለወጥ ይችል ዘንድ፣ መንፈሳዊ ዐይናችን ጤናማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሕይወታችንን መመርመር አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ በምንማርበትና በምናጠናበት ጊዜ ለእግዚአብሔር፣ ለክርስቶስና ለቃሉ ያለን ፍቅር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመሄድ ሁኔታ አለው ወይስ ይህን ሁሉ የወንጌል መልእክት የተቀበልንና መጽሐፍ ቅዱስ የተማርን ቢሆንም በውስጣችን ባዶነት ይሰማናል? አሁንም የኀጢአት ባሪያዎች ነን? መንፈሳዊ ሕይወታችን በመጨረሻ በተጠቀሰው ሁኔታ የሚገኝ ከሆነ፣ መንፈሳዊ ዐይናችን ትክክል አይደለም፤ አሁንም ሰውነታችን ያለው በጨለማ ውስጥ ነው ማለት ነው። ኀጢአታችንን መናዘዝና ሕይወታችንን ወደ ጨለማ ሊመራ ከሚችል ከማንኛውም ነገር ጋር ተደራድረን ከመሄድ መራቅ አለብን።

**11፥42 እናንተ … ወዮላችሁ፤** ማቴ 23፥13 እና ክርስቶስ ፈሪሳውያንን መንቀፉን አስመልክቶ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**12፥1 ግብዝነት፤** ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ስለ ግብዝነታቸው ይነቅፋቸዋል፤ ይህም ኀጢአት በደቀ መዛሙርቱ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ እንዳይኖር ይጠንቀቁ ዘንድ ያሳስባቸዋል፤ (1) ግብዝነት ማለት ያልሆንከውን መሆን ማለት ነው፤ ለምሳሌ በውስጥህ ድብቅ ኀጢአት፣ ኢግብረገባዊነት፣ ስግብግብነት፣ ቅናትና ሌሎችም ጽድቅ ያልሆኑ ነገሮች ተሸክመህ እያለ፣ በሕዝቡ ፊት ግን እግዚአብሔርን የምትፈራ ታማኝ ክርስቲያን መምሰል ግብዝነት ነው። ግብዝ ሰው ውጫዊ የሆነ ጽድቅን በመፈጸም በብዙ መልኩ አታላይ ነው (በገጽ 1519 ላይ፣ *"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ግብዝነት እየዋሸህ የምትኖርበት ሕይወት ስለሆነ፣ የውሸት አባት ከሆነው ከሰይጣን ጋር አብረህ እንድትሠራና ኅብረት እንድትፈጥር ያደርግሃል (ዮሐ 8፥44)።

(3) ግብዝነትና የተደበቀ ኀጢአት ሁሉ በዚህ ዓለም በሕይወት እያለን ባይሆንም ነገር ግን በፍርድ ቀን መገለጡ እንደማይቀር (ሮሜ 2፥16፤ 1ቆሮ 3፥13፤ 4፥5፤ ራእ 20፥12)፣ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ያስጠነቅቃቸዋል፤ ከመጋረጃ በስተጀርባ በድብቅ የተሠራው ሁሉ አንድ ቀን ይፋ ይወጣል (ቍ 2-3)፤

እርሾ ተጠንቀቁ፤ ይህም ግብዝነት ነው።
2የማይገለጥ የተሸፈነ፣ የማይታወቅ
የተሰወረ ምንም የለም። 3ስለዚህ በጨለማ
ያወራችሁት ሁሉ በብርሃን ይሰማል፤
በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ ያንሾካሾካችሁት
በሰገነት በይፋ ይነገራል።
4"ወዳጆቼ ሆይ፤ እላችኋለሁ ሥጋን
የሚገድሉትን፣ ከዚያ ወዲያ ግን ምንም
ማድረግ የማይችሉትን አትፍሩ። 5ነገር
ግን መፍራት የሚገባችሁን አሳያችኋለሁ፤
ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን
ያለውን እርሱን ፍሩት፤ አዎን፤ እርሱን
ፍሩት እላችኋለሁ። 6አምስት ድንቢጦች
በዐሥር ሳንቲም* ይሸጡ የለምን? ይሁን
እንጂ ከእነርሱ አንዷ እንኳ በእግዚአብሔር ዘንድ
አትዘነጋም። 7የእናንተ የራሳችሁ ጠጕር ሁሉ
እንኳ የተቈጠረ ነው፤ እንግዲህ አትፍሩ፤
ከብዙ ድንቢጦች የበለጠ ዋጋ አላችሁ።
8"እላችኋለሁ፤ በሰው ፊት
ለሚመሰክርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ
በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል።
9በሰው ፊት የሚክደኝም በእግዚአብሔር
መላእክት ፊት ይካዳል። 10በሰው ልጅ
ላይ የማቃለል ቃል የሚሰነዝር ሁሉ
ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ
ግን አይሰረይለትም።
11"ሰዎች ይዘው ወደ ምኵራብ፣ ወደ
ገዥዎችና ወደ ባለ ሥልጣናት ባቀረቧችሁ
ጊዜ፣ እንዴት ወይም ምን እንደምትመልሱ
አትጨነቁ፤ 12በዚያ ሰዓት መንፈስ ቅዱስ
መናገር የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና።"

## የሀብታሙ ሰው ሞኞነት

13ከሕዝቡም መካከል አንድ ሰው፣
"መምህር ሆይ፤ ወንድሜ ውርስ
እንዲያካፍለኝ ንገረው" አለው።
14ኢየሱስም፣ "አንተ ሰው፤ በእናንተ
ላይ ፈራጅ ወይም ዳኛ ያደረገኝ ማነው?"
አለው። 15ደግሞም፣ "የሰው ሕይወቱ በሀብቱ
ብዛት የተመሠረተ ስላልሆነ፣ ተጠንቀቁ፤
ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁንም ጠብቁ"
አላቸው።
16ቀጥሎም እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራቸው፤
"ዕርሻው እጅግ ፍሬያማ የሆነችለት አንድ
ሀብታም ነበረ፤
17ይህም ሰው፣ ምርቴን የማከማችበት
ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ
አሰበ።
18"እንዲህም አለ፤ 'እንደዚህ አደርጋለሁ፤
ያሉኝን ጐተራዎች አፈርስና ሌሎች ሰፋ ያሉ
ጐተራዎች እሠራለሁ፤ በዚያም ምርቴ ንና
ንብረቴንም ሁሉ አከማቻለሁ፤ 19ነፍሴንም፣
"ነፍሴ ሆይ፤ ለብዙ ዘመን የሚበቃሽ ሀብት
አከማችቼልሻለሁ፤ እንግዲህ ዕረፊ፤ ብዪ፤
ጠጪ፤ ደስም ይበልሽ" እላታለሁ።'
20"እግዚአብሔር ግን፣ 'አንተ ሞኝ፤
ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሊወስዱ
ይፈልጓታል፤ እንግዲህ፣ ለራስህ
ያከማቸኸው ለማን ይሆናል?' አለው።
21"ስለዚህ ለራሱ ሀብት የሚያከማች፣
ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሀብታም ያልሆነ
ሰው መጨረሻው ይኸው ነው።"

## አትጨነቁ

*12፥23-31 ተጓ ምብ — ማቴ 6፥25-33*

22ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ
እንዲህ አለ፤ "ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ
ሕይወታችሁ ምን እንደምትበሉ፣ ወይም
ስለ ሰው ነታችሁ ምን እንደምትለብሱ
አትጨነቁ፤ 23ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትም
ከልብስ ይበልጣልና። 24ቁራዎችን
ተመልከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤

12፥2 ማር4፥22
12፥4 ዮሐ15፥14፡15
12፥5 ዕብ10፥31
12፥7 ማቴ10፥30፤
12፥12
12፥8 ሉቃ15፥10
12፥10 ማቴ8፥20፤
12፥31፡32፤
1ዮሐ5፥16
12፥11 ማቴ10፥17፡19፤
ሉቃ21፥12፡14
12፥12 ዘፀ4፥12፤
ማቴ10፥20፤
13፥11፤
ሉቃ21፥15
12፥15 ኢዮ20፥20፤
31፥24፤
መዝ62፥10
12፥20 ኢዮ27፥8፤
መዝ39፥6፤
49፥10፤
ኤር17፥11፤
ሉቃ11፥40
12፥21 ቍ33
12፥24 ኢዮ38፥41፤
መዝ147፥9

*12፥6 ግሪኩ ሁለት አሳሪያ ይላል

(4) ግብዝነት፣ አንድ ሰው እግዚአብሔርን እንደማይፈራ (ቍ 5)፣ ለዳግም ልደት የሚያበቃው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በውስጡ እንደሌለ ያመለክታል (ሮሜ 8፥5-14፤ 1ቆሮ 6፥9-10፤ ገላ 5፥19-21፤ ኤፌ 5፥5)። በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታ የሚኖር ሰው፣ ከገሃነም ፍርድ ሊያመልጥ አይችልም (ማቴ 23፥33)።

**12፥5 እርሱን ፍሩት፤** የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የእግዚአብሔር ግርማ፣ ቅድስናና በነጢአት ላይ የሚገለጸው ቍጣው ሊያስፈራቸውና ሊያከብሩት ይገባል (ከኢሳ 6፥1-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

**12፥8 በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፤** ማቴ 10፥32 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**12፥9 በሰው ፊት የሚክደኝም፤** የሚከተሉትን ነገሮች ያለማድረጋችን ክርስቶስን መካዳችን ነው፤ (1) በማያምኑ ሰዎች ፊት የክርስቶስ ተከታዮች መሆናችንን አለመግለጽ፣ (2) ክርስቲያናዊ ያልሆኑ የኅብረተ ሰብ ሥርዐቶች በሚካሄዱበት ቦታ ለወንጌልና ለክርስቶስ የጽድቅ ሕጎች ጸንቶ ያለመቆም።

**12፥10 መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ፤** ማቴ 12፥31 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**12፥15 ከስግብግብነትም ሁሉ ... ጠብቁ፤** ምድራዊ ጥቅም ወይም ሀብት ማግኘትን የሕይወት ዐላማ አድርጎ መያዝ፣ ወደ ዘላለም ጥፋት የሚመራ ከባድ ስሕተት ነው (ቍ 20-21)፤ (1) ስግብግብነት የሚለው ቃል በግሪኩ (ፕሌኔክስያ) ቃል በቃል ሲተረጎም ይበልጥ ለማግኘት አብዝቶ መጠማትን ወይም መፈለግን ያመለክታል፤ (2) ቅናት፣ አንድ ሰው በግሉም ሆነ በቤተ ሰብ ደረጃ የሚያስፈልገውን ነገር ስለማድረግ የሚገልጽ (የሚናገር) አይደለም (ከምሳ 6፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። ፍላጎታችንን ለማሟላት በምንሠራበት ጊዜ በቀዳሚነት ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን በመፈለግ በእግዚአብሔር ዘንድ ሀብታሞች ልንሆን ይገባል (ቍ 31 ይመ፤ ከማቴ 6፥33 እና ማብራሪያው ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) እያንዳንዳችን ኢየሱስ የተናገረውን ነገር ማስተዋል እንዲሁም በልባችን ውስጥ ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት መኖሩንና ያለመኖሩን መመርመር ይገባናል። ስለዚህ ጉዳይ ይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1577 ላይ፣ «ብልጽግናና ድህነት» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**12፥22 ስለ ሕይወታችሁ ... አትጨነቁ፤** ማቴ 6፥25 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**12፥24 እጅግ ትበልጡ የለምን?** ማቴ 6፥25፡30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ማከማቻ ወይም ጐተራ የላቸውም፤ እግዚአብሔር
ግን ይመግባቸዋል። እናንተማ ከወፎች እጅግ
ትበልጡ የለምን? [25]ለመሆኑ፣ ከእናንተ
ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንድ ሰዓት
መጨመር የሚችል ማነው?[a] [26]እንግዲህ
ቀላሉን ነገር እንኳ ማድረግ የማትችሉ ከሆነ፣
ስለ ሌላው ነገር ለምን ትጨነቃላችሁ?
[27]"እስቲ አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ
ተመልከቱ፤ አይለፉም፤ አይፈትሉም፤
ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰሎሞን እንኳ
በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ አንዱ
አልለበሰም። [28]እንግዲህ እግዚአብሔር ዛሬ
ታይቶ ነገ ወደ እሳት የሚጣለውን የሜዳ
ሣር እንዲህ የሚያለብስ ከሆነ፣ እናንተ
እምነት የጐደላችሁ፣ እናንተንማ እንዴት
ሉቃ 17፥5-6 አብልጦ አያለብሳችሁም? [29]ስለዚህ ምን
እንደምትበሉና ምን እንደምትጠጡ በመሻት
ልባችሁ አይጨነቅ፤ [30]ይህንማ በዓለም ያለ
ሕዝብ ሁሉ ይፈልጋል፤ አባታችሁ እኮ
ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃል።
[31]ይልቁንስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤
ይህም ሁሉ በተጨማሪ ይሰጣችኋል።
[32]"እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ
መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ መልካም
ፈቃድ ነውና አትፍሩ፤ [33]ያላችሁን ሽጡና
ለድኾች ስጡ፤ ሌባ በማይሰርቅበት፣ ብል
በማይበላበት፣ በማያረጅ ከረጢት የማያልቅ
ንብረት በሰማይ አከማቹ፤ [34]ልባችሁ፣
ንብረታችሁ ባለበት ቦታ ይሆናልና።

12፥27 1ነገ10፥4-7
12፥28 ማቴ6፥30
12፥30 ማቴ6፥8፤ ሉቃ6፥36
12፥31 ማቴ3፥2፤ 19፥29
12፥32 ማቴ14፥27፤ 25፥34
12፥33 ማቴ6፥20፤ ሐሥ2፥45፤ ያዕ5፥2
12፥34 ማቴ6፥21
12፥37 ማቴ20፥28፤ 24፥42:46፤ 25፥13
12፥39 ማቴ6፥19፤ 1ተሰ5፥2፤ 2ጴጥ3፥10፤ ራእ3፥3፤ 16፥15
12፥40 ማር13፥33፤ ሉቃ21፥36
12፥42 ሉቃ7፥13

## ንቅቶ መጠበቅ

*12፥35፡36 ተጓ ምብ — ማቴ 25፥1-13፤ ማር 13፥33-37*
*12፥39፡40፡42-46 ተጓ ምብ — ማቴ 24፥43-51*

[35]"በአጭር ታጥቃችሁ ተዘጋጁ፤
መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ [36]ጌታቸው
ከሰርግ ግብዣ እስኪመለስ እንደሚጠባበቁና
መጥቶም በር ሲያንኳኳ ወዲያው ለመክፈት
ዝግጁ የሆኑ ሰዎችም ምሰሉ። [37]ጌታቸው
በሚመጣበት ጊዜ ነቅተው የሚያገኛቸው
አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት
እላችኋለሁ፤ ጌታቸውም በአጭር
ይታጠቃል፤ በማእድ ያስቀምጣቸዋል፤
ቀርቦም ያስተናግዳቸዋል። [38]ከሌሊቱ
በሁለተኛውም ሆነ በሦስተኛው ክፍል
መጥቶ እንደዚያው ነቅተው ቢያገኛቸው፣
እነዚያ አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው።
[39]ይህን ግን ዕወቁ፤ ሌባ በምን ሰዓት
እንደሚመጣ የቤቱ ባለቤት ቢያውቅ
ኖሮ፣ ቤቱ ሲቈፈር ዝም ብሎ ባላየ ነበር።
[40]እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ፤ የሰው
ልጅ ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና።
[41]ጴጥሮስም፣ "ጌታ ሆይ፤ ይህን ምሳሌ
የምትናገረው ለእኛ ብቻ ነው ወይስ ለሁሉም
ጭምር ነው?" አለው።
[42]ጌታም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "እንግዲህ፣
ምግባቸውን በተገቢው ጊዜ እንዲሰጣቸው
ጌታው በቤቱ ሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማ

[a]12፥25 ወይም በቁመቱ ላይ አንድ ስንዝር

**12፥31 የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤** ማቴ 6፥33 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**12፥33 ያላችሁን ሽጡ፤** እዚህ ላይ ኢየሱስ የተናገረው ነገር ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት፣ ማቴ 19፥21 እና ማብ፣ 1ቆሮ 16፥2፤ 2ቆሮ 8፥1-5 ይመልከቱ::

**12፥34 ልባችሁ፣** ንብረታችሁ ባለበት፣ የሰው ልብ ይኸውም ስሜቱ፣ ሐሳቡ፣ ምኞቱ፣ ፋይዳው፣ ፈቃዱና ውሳኔው ለእርሱ አስፈላጊ በሆነ ነገር ላይ ያረፈ ነው (በገጽ 932 ላይ፣ *"ልብ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (1) ምድራዊ ነገርን ሀብትህ ካደረግህ፣ ልብህ ለእንደዚህ ዐይነት ነገር የተገዛ ይሆናል፤ (2) ሀብትህ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ሰማያዊ ነገር፣ ቃሉ፣ ህልዎቱ፣ ቅድስናውና ከእርሱ ጋር ያለህ ግንኙነት ከሆነ፣ ልብህ የመንግሥቱን ነገር የሚናፍቅና የሕይወትህም አቅጣጫ ወደ ሰማይ ያቀና እንደዚሁም የጌታህን መምጣት የሚጠባበቅ ይሆናል (ቍ 35-40)::

**12፥35 በአጭር ታጥቃችሁ ተዘጋጁ፤** ከቍ 35-40 ይመልከቱ:: የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የጌታ ወደ ሕዝቡ መምጣት በሚመለከት በቅርብ እንደሚሆንና በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት እንደሚችል ከመረዳት በስተቀር ሌላ የተለየ ሐሳብ አልነበራትም (ማር 13፥35 እና ማብራሪያውን ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንጥቀት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሁልጊዜ ተዘጋጅቶ የጌታን ዳግም ምጽአት እንዲጠብቅ ይደረግ ነበር:: ይህ የአዲስ ኪዳን ሕግ በክርስቶስ የሚያምኑ እውነተኛ አማኞች ሁሉ እንዲቀበሉት የሚያስገድድ ነው፤ (1) አማኞች ተስፋ የሚያደርጉትና የሚናፍቁት ከሁሉ የሚበልጥ ሀብታቸው (ቍ 34) የኢየሱስ ዳግም ምጽአት (ቍ 35-37) በመሆኑ፣ ከጌታ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው፤ (2) አማኞች ሁሉ ልብሳቸውን ለብሰውና ተዘጋጅተው ድንገት የሚሆነውን የክርስቶስ መምጣት መጠባበቅ አለባቸው (ቍ 38፡40 እና ማብ ይመ)፤ (3) ክርስቶስ የሚመጣበት ጊዜ ቅርብ ነው፤ ይህም በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል ያመለክታል (ቍ 38):: አማኝ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰቱ በሚችሉ ውስብስብ ጉዳዮች ሐሳቡ ሳይያዝ፣ ክርስቶስን መጠበቅና ተስፋ ማድረግ አለበት (ማቴ 24፥42፡44 እና ማብራሪያውን፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ 1ቆሮ 15፥51 እና ማብ ይመ)::

**12፥36 ጌታቸው ... እንደሚጠባበቁ፤** ማቴ 25፥1፡4 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**12፥38 እነዚያ አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው፤** በሰርጉና በዳግም ምጽአቱ መካከል ባለው ጊዜ የጌታቸውን መመለስ በአጭር ታጥቀው በታማኝነት ለሚጠብቁ (ቍ 36) እና ተስፋ ለሚያደርጉ (ቍ 37)፣ የክርስቶስ ህልዎት የሚሰጠው የተለየ በረከትና እንክብካቤ ተጠብቆላቸዋል::

**12፥40 ባላሰባችሁት ሰዓት፤** የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሁል ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ዝግጁና ታዛዥ ሆነው (ቍ 35) መጠበቅ አለባቸው፤ ምክንያቱም ጌታ የሚመጣው በድንገት ነው:: ስለዚሁ እውነት የሚገልጹ ሌሎች ክፍሎች ማቴ 24፥36፡42-44፤ ሉቃ 21፥34፤ 1ተሰ 5፥2-4 ናቸው::

**12፥42-48 ይህ ክፍል ታማኝ ስለሆነና ታማኝ ስላልሆነ አገልጋይ ይናገራል፤** በዚህ ምድር የማይኖርበትን ጊዜና ተመልሶ የመምጣቱን ተስፋ ግምት

ኝና ብልህ መጋቢ ማነው? 43ጌታው ሲመ
ለስ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው አገልጋይ
እርሱ ብፁዕ ነው። 44እውነት እላችኋ ለሁ፤
ባለው ንብረት ሁሉ ላይ ይሾመዋል። 45ዳሩ
ግን ያ አገልጋይ፣ ጌታዬ ቶሎ አይመጣም፤
ይዘገያል፤ ብሎ ቢያስብና ወንድና ሴት
አገልጋዮችን ቢደበድብ፣ ደግሞም እን
ዳሻው መብላት፣ መጠጣትና መስከር
ቢጀምር፣ 46የዚያ አገልጋይ ጌታ ባላሰበው
ቀንና ባልጠረጠረው ሰዓት ይመጣበታል፤
ስለዚህ ይቈራርጠዋል፤ ዕድል ፈንታውንም
ከማያምኑ ጋር ያደርጋል።
47"የጌታውን ፍላጎት እያወቀ
የማይዘጋጅና ፈቃዱን የማያደርግ አገልጋይ
እርሱ ክፉኛ ይገረፋል፤ 48ነገር ግን ይህን
ሳያውቅ ቀርቶ መገረፍ የሚገባውን ያህል
ያደረገ አገልጋይ በጥቂቱ ይገረፋል። ብዙ
ዮሐ ከተሰጠው ሁሉ ብዙ ይፈለግበታል፤ ብዙ
31 ዐደራም ከተቀበለም ብዙ ይጠበቅበታል።

## ሰላም ሳይሆን መለያየት

*12፥51-53 ተጓ ምብ — ማቴ 10፥34-36*

49"እኔ የመጣሁት በምድር ላይ እሳት
ለመለኰስ ነው፤ አሁኑኑ ቢቀጣጠል
ምንኛ ደስ ባለኝ! 50ነገር ግን የምጠመቀው
ጥምቀት አለኝ፤ እስኪፈጸምም ድረስ
እንዴት ተጨንቄአለሁ? 51በምድር ላይ
ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋል?
አይደለም፤ እላችኋለሁ፤ እኔ የመጣሁት
ለመለያየት ነው። 52ከአሁን ጀምሮ እርስ
በርሱ የተለያዩ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ
አምስት ሰዎች ይኖ ራሉ፤ ሁለቱ በሦስቱ
ላይ፣ ሦስቱም በሁለቱ ላይ ተነሥተው
ይለያያሉ፤ 53አባት በወንድ ልጁ ላይ፣
ወንድ ልጅም በአባቱ ላይ፣ እናት በሴት
ልጇ ላይ፣ ሴት ልጅም በእናቷ ላይ፣
አማት በምራቷ ላይ፣ ምራትም በአማቷ ላይ
ተነሥተው ይለያያሉ።"

12፥46 ቍ40
12፥47 ዘዳ25፥2
12፥48 ዘሌ5፥17፤
ዘኍ15፥27-30
12፥50
ማር10፥38፤
ዮሐ19፥30
12፥53 ሚክ7፥6፤
ማቴ10፥21

12፥54 ማቴ16፥3
12፥58 ማቴ5፥25
12፥59
ማቴ5፥26፤
ማር12፥42
13፥1 ማቴ27፥2
13፥2 ዮሐ9፥2:3
13፥4 ዮሐ9፥7:11
13፥5 ማቴ3፥2፤
ሐሥ2፥38

## ዘመናትን መመርመር

54ደግሞም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ "ደመና
በምዕራብ በኩል ሲወጣ ስታዩ ወዲያው፣
ዝናብ ሊመጣ ነው ትላላችሁ፤ እንደዚያም
ይሆናል፤ 55የደቡብ ነፋስም ከደቡብ በኩል
ሲነፍስ፣ ቀኑ ሞቃት ይሆናል ትላላችሁ፤
እንደዚያም ይሆናል። 56እናንተ ግብዞች፤
የም ድሩንና የሰማዩን መልክ መመርመር
ታውቁበታላችሁ፤ ታዲያ ይህን የአሁኑን
ዘመን መመርመር እንዴት ተሳናችሁ?
57"ታዲያ ራሳችሁ ትክክለኛ የሆነውን
ነገር ለምን አትፈርዱም? 58ከባላጋራህ
ጋር ወደ ዳኛ ፊት ለመቅረብ ስትሄድ፣
ገና በመንገድ ላይ ሳለህ ለመታረቅ ጥረት
አድርግ፤ አለበለዚያ ጐትቶ ወደ ዳኛው
ይወስድሃል፤ ዳኛውም ለመኰንኑ አሳልፎ
ይሰጥሃል፤ መኰንኑም ወደ ወህኒ ይጥልሃል፤
59እልሃለሁ፤ የመጨረሻዋን ሳንቲም[ሉ]
እስክትከፍል ድረስ ከዚያ አትወጣም።

## የንስሓ ጥሪ

13 በዚህ ጊዜ መጥተው፣ ጲላጦስ
ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር
ስለ ደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች ያወሩለት
ሰዎች በዚያ ነበሩ። 2እርሱም እንዲህ
መለሰላቸው፤ "ታዲያ እነዚህ የገሊላ ሰዎች
ይህ ሥቃይ የደረሰባቸው ከሌሎቹ የገሊላ
ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኀጢአተኞች ስለ ነበሩ
ይመስላችኋል? 3አይደለም እላችኋለሁ፤
ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ
ትጠፋላችሁ። 4ወይም ደግሞ በሰሊሆም
ግንብ ተንዶባቸው የሞቱት ዐሥራ ስምንት
ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ
ይልቅ በደለኞች ስለ ነበሩ ይመስላችኋል?
5አይደለም፤ እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ
ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።"

[ሉ] 12፥59 ግሪኩ ሌፕቶን ይላል

ውስጥ በማስገባት፣ በደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ሕይወት ውስጥ ሁለት ዐይነት የአኗኗር ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ለመግለጽ ጌታ ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ተናግሮአል፤ ይህም (1) ታማኞች፣ ታዛዦች፣ ተግተው የሚጠብቁ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ተዘጋጅተው በማንኛውም ሰዓት የጌታቸውን መመለስ ተስፋ የሚያደርጉና የጌታቸውን በረከት የሚቀበሉ ሆነው በመገኘት የሚመላለሱ (ቍ 35 እና ማብ፤ ማር 13፥35 እና ማብ፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)፤ (2) ወይም ግዴለሾች፣ ዓለማዊ አስተሳሰብ ያላቸው፣ የጌታ ተመልሶ መምጣት የሚዘገይ የሚመስላቸው፣ ኀጢአትን የማይቃወሙ፣ ታማኝ ሆኖ መገኘት ከሕይወታቸው የራቀ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እነዚህም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላሉ፤ ጌታም በሚመጣበት ጊዜ ዕድል ፈንታቸው የዘላለም ኀፍረትና ጥፋት መውረስ ይሆናል (ቍ 45-46 ይመ፤ ማቴ 24፥44 እና ማብ፤ ዮሐ 5፥24 እና ማብ፤ 15፥6 እና ማብ ይመ)።

**12፥45 ጌታዬ ቶሎ አይመጣም፤ ይዘገያል፤** በግድየለሾች ላይ ለመፍረድ ክርስቶስ በማንኛውም ሰዓት ሊመጣ እንደሚችል ባለመቀበል፣ ግድየለሽ ደቀ መዝሙር ጌታ ድንገት እንደሚመጣ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁል ጊዜ በእምነት ጸንተው ይኖሩ ዘንድ ለተናገረው ልባዊ ምክር ክብደት አይሰጠውም (ቍ 35:37-38:40)። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ለመንፈሳዊ ንስሓ ሌላ ዕድል ስለሌለ፣ መምጣቱ እምነታቸውን ለጣሉ ሰዎች እጅግ አደገኛ ነው፤ በሌላ አነጋገር የክርስቶስ መምጣት ልክ እንደ ሞት ነው፤ የመጨረሻና በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችል ነው (ማቴ 24፥42: 44 እና ማብ፤ ማር 13፥35 እና ማብ፤ 2ተሰ 2፥11 እና ማብ ይመ)።

**12፥48 በጥቂቱ ይገረፋል፤** በመንግሥተ ሰማይ የተለያዩ የሽልማት ደረጃዎች እንዳሉ ሁሉ (1ቆሮ 15፥41-42)፣ በገሃነምም የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች ይኖራሉ። ወደ ዘላለም ጥፋት የሚሄዱት እንደተቀበሉት መብትና ኀላፊነት መጠን የተለያየ የቅጣት ደረጃ ይጠብቃቸዋል (ሉቃ 10፥15፤ 11፥24 ይመ ከማቴ 23፥14፤ ከዕብ 10፥29 ጋር ያነጻጽሩ)።

**12፥51 እኔ የመጣሁት ለመለያየት ነው፤** ማቴ 10፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

6ደግሞምእንዲህሲል ይህንምሳሌ ተናገረ፤
"አንድ ሰው በወይኑ ዕርሻ ቦታ የተተከለች
አንዲት የበለስ ተክል ነበረችው፤ እርሱም
ፍሬ ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም።
7የወይን አትክልት ሠራተኛውንም፣ 'እነሆ፤
ፍሬ ለማግኘት ልፈልግባት ሦስት ዓመት
ወደዚህች በለስ መጥቼ ምንም አላገኘሁም፤
ስለዚህ ቍረጣት፤ ለምን ዐፈሩን በከንቱ
ታሟጥጣለች?' አለው።
8"እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት፤
'ጌታ ሆይ፤ ዙሪያዋን እስክኰተኵትላትና
ፍግ እስከማደርግላት ድረስ ለዘንድሮ ብቻ
ተዋት፤ 9ለከርሞ ካፈራች መልካም ነው፤
አለበለዚያ ትቈርጣታለህ።'"

13፥6 ኢሳ5፥2፤ ኤቄ8፥13፤ ማቴ21፥19
13፥7 ማቴ3፥10
13፥10 ማቴ4፥23
13፥11 ቍ16
13፥13 ማር5፥23
13፥14 ዘፀ20፥9፤ ማቴ12፥2፤ ማር5፥22

## አንዲት ጐባጣ ሴት በሰንበት ቀን ተፈወሰች

10ኢየሱስ በሰንበት ቀን በአንድ ምኵራብ
ያስተምር ነበር። 11በዚያም የድካም መን
ፈስ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ አካለ
ስን ኩል ያደረጋት አንዲት ሴት ነበረች፤
እርሷም ከመጕበጧ የተነሣ ፈጽሞ ቀና
ማለት አትችልም ነበር። 12ኢየሱስም ባያት
ጊዜ ጠራትና፣ "አንቺ ሴት፤ ከሕመምሽ
ነጻ ወጥተሻል" አላት፤ 13እጁንም በላይዋ
ጫነ፤ እርሷም ወዲያው ቀጥ ብላ ቆመች፤
እግዚአብሔርንም አመሰገነች።
14የምኵራቡ አለቃ ግን፣ ኢየሱስ በሰንበት
ቀን ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ ሕዝቡን፤ "ሥራ
ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤
ስለዚህ በእነዚያ ቀኖች እየመጣችሁ ተፈወሱ
እንጂ በሰንበት ቀን አይደለም" አላቸው።
15ጌታም መልሶ እንዲህ አለው፤ "እናንት
ግብዞች፤ ከእናንተ መካከል አንድ ሰው
በሬውን ወይም አህያውን በሰንበት ቀን
ከማደ ሪያው ፈትቶ ውሃ ሊያጠጣ ይወስደው
የለምን? 16ታዲያ፣ ይህች ሴት የአብርሃም
ልጅ ሆና ሳለች ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ
በሰይጣን ታስራ ስትኖር፣ ከዚህ እስራት
በሰንበት ቀን መፈታት አይገባትምን?"
17ይህን በተናገረ ጊዜ ተቃዋሚዎቹ ሁሉ
ዐፈሩ፤ ሕዝቡ ሁሉ ግን እርሱ ባደረገው
ድንቅ ሥራ ሁሉ ደስ አላቸው።

13፥15 ሉቃ14፥5
13፥16 ማቴ4፥10፤ ሉቃ3፥8
13፥17 ኢሳ66፥5
13፥18 ማቴ3፥2፤ 13፥24
13፥19 ማቴ13፥32፤ ሉቃ17፥6

## የሰናፍጭ ቅንጣትና የእርሾ ምሳሌ

*13፥18፡19 ተጓ ምብ — ማር 4፥30-32*
*13፥18-21 ተጓ ምብ — ማቴ13፥31-33*

18ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
"የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች?
ከምንስ ጋር ላመሳስላት? 19አንድ ሰው ወስዶ
በዕርሻው ውስጥ የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት
ትመስላለች፤ አድጋ ዛፍ ሆነች፤ የሰማይ
ወፎችም በቅርንጫፎቿ ላይ ሰፈሩ።"
20ደግሞም እንዲህ አለ፤ "የእግዚአብሔርን
መንግሥት ከምን ጋር ላመሳስላት?

**13፥6-7 የበለስ ተክል ... ቍረጣት፤** ከቍ 6-9 ይመልከቱ:: የበለስ ተክሉ ምሳሌ በይበልጥ የሚያመለክተው እስራኤልን ነው (ከ3፥9፤ ከሆሴ 9፥10፤ ከኢዩ 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ):: ይሁን እንጂ ምሳሌው የሚጠቅሰው እውነት፣ በክርስቶስ እናምናለን በሚሉ ነገር ግን ከኀጢአት መለየት ባልቻሉት ሁሉ ላይ ይፈጸማል:: እግዚአብሔር ለማንኛውም ሰው ከኀጢአቱ ንስሓ ይገባ ዘንድ ብዙ ዕድል ቢሰጥም፣ ለዘላለም ኀጢአትን አይታገሥም:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚወሰድበትና ንስሓ ያልገቡት ያለምሕረት የሚቀጡበት ጊዜ ይመጣል (ከ20፥16፤ 21፥20-24 ያነጻጽሩ)::

**13፥11 የድካም መንፈስ ... አካለ ስንኩል ያደረጋት፤** አንዳንድ በአካል ላይ የሚታዩ ሕመሞች በቀጥታ የኢጋንንት ሥራና ተጽዕኖ ውጤት እንደ ሆኑ ኢየሱስ ያውቃል:: ይህች ሴት አካለ ስንኩል ልትሆን የቻለችው የሰይጣን ወኪል በሆነው "መንፈስ" ነው (ቍ 16 ይመ፤ ከማቴ 9፥32-33፣ 12፥22፣ ከማር 5፥1-5፤ 9፥17-18፤ ከሐሥ 10፥38 ጋር ያነጻጽሩ)::

**13፥16 ይህች ሴት ... በሰይጣን ታስራ ስትኖር፤** በመከራ ውስጥ ያለ ሰው በሐዘንና በጭንቀት ሲቃትት ሰምቶ እንዳልሰማ ችል ማለት በክርስቶስ ዘንድ አስጸያፊ ኀጢአት ነው (ቍ 11-14):: ሰዎች በኀጢአት፣ በሕመምና በሞት የታሰሩ እንደሆኑ፣ የልብ ሐዘንና ከፍተኛ ችግር እንዳላቸው ኢየሱስ ያስተምራል (ቍ 11፥16፤ ማቴ 4፥23፤ ሐሥ 26፥18):: ዛሬ በዓለም ላይ ለሚደርሰው ሥቃይና መከራ ግዴለሾች በመሆን በአደገኛ ሁኔታ ላይ እንገኛለን፤ ይህም ሊሆን የቻለው ሥጋዊ ደስታን ለማግኘት ኢግብረገባዊነትንና ዐመፀኛነትን ወደ ሕይወታችን በመጋበዝ እንድንጨፍርና እንድንደሰት የሚያደርጉንን በመገናኛ ብዙኀን የሚተላለፉ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በመቀበላችን ነው:: እውነተኛ ደቀ መዛሙርት የሕይወትን ሐዘን ለማየትና የፍጥረትን መቃተት ለመስማት በመቻላቸው አምላካቸውን ይመስላሉ (10፥33-37፤ ሮሜ 8፥22 ይመ፤ በገጽ 1327 ላይ፣ "ድኾችንና ችግረኞችን መርዳት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**13፥19 የሰናፍጭ ቅንጣት፤** የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌና የእርሾው ምሳሌ ስለ መንግሥተ ሰማይ የሚገልጹ ጥንድ ምሳሌዎች ናቸው፤ የእርሾው ምሳሌ በሚታየው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ክፉ ነገር ገብቶ እንዴት እያደገ እንደሚሄድ የሚገልጽ ነው:: የሰናፍጩ ቅንጣት ምሳሌ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በትንሹ ጀምሮ በዘመናት ሁሉ እያደገ እንደሚሄድ ይገልጻል:: ይህ የተጀመረው በጌታ ኢየሱስና ራሳቸውን ለእርሱ አሳልፈው በሰጡ ጥቂት ደቀ መዛሙርት ነው (ዮሐ 20፥22፤ ሐሥ 2፥4 ይመ):: ይሁን እንጂ ተገልጾ የሚታየው የእግዚአብሔር መንግሥት እስከሚሰፋ፣ እስከሚጠነክርና ምንም ነገር ሊቋቋመው የማይችል ኀይለኛ እስከሚሆን ድረስ ያድጋል:: የሰማይ ወፎችም በቅርንጫፎቹ ላይ ያርፋሉ:: በሌላ ስፍራ ግን ወፎች የተዘራውን የእውነት ዘር የሚለቅሙ የክፉው ምሳሌዎች ናቸው:: በማቴ 13፥4፡19 ላይ ክርስቶስ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ ወፎች የክፉውን ሥራ የሚፈጽሙ ናቸው፤ በራእ 18፥2 ላይ እምነትዋን የጣለችው ቤተ ክርስቲያንን የምታመለክተው ባቢሎን የአጋንንት መኖሪያ፣ "የርኵስና የአስጸያፊ ወፎች ሁሉ መጠለያ" እንደሆነች ተገልጾአል:: (ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ብዙዎቹ ላይ መንፈሳዊ ውድቀት እንዴት ሊደርስ እንደቻለ በራእ 2—3 ላይ ክርስቶስ የተናገረውን ይመልከቱ፤ በራእ 18፥4 ላይ የሳተች ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ)::

21 አን ዱት ሴት ወስዳ በሙሉ እስኪቦካ
ድረስ በዛ ካለ[a] ዱቄት ጋር የደባለቀችውን
እርሾ ትመስላለች።"

## ጠባቧ በር

22 ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም
እያመራ ሳለ፣ በሚያልፍባቸው ከተሞችና
መንደሮች እያስተማረ ያልፍ ነበር። 23 አንድ
ሰውም ቀርቦ፣ "ጌታ ሆይ፤ የሚድኑት
ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸውን?" አለው።
እርሱም እንዲህ አላቸው፤ 24 "በጠባቧ
በር ለመግባት ተጣጣሩ፤ እላችኋለሁ፤
ብዙዎች ለመግባት ይፈልጋሉ ነገር ግን
አይሆንላቸ ውም፤ 25 የቤቱ ባለቤት ተነሥቶ
በሩን ከቈለፈ በኋላ በውጭ ቆማችሁ፣ ጌታ
ሆይ፤ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ማንኳኳት
ትጀምራ ላችሁ።
"እርሱ ግን፣ 'ማን እንደ ሆናችሁና
ከየት እንደ መጣችሁ አላውቅም' ብሎ
ይመልስላችኋል።
26 "እናንተም፣ ከአንተ ጋር አብረን
በልተናል፤ ጠጥተናል፤ በአደባባዮችንም
አስተምረሃል ትላላችሁ።
27 "እርሱም፣ እላችኋለሁ፤ 'ማን
እንደሆናች ሁና ከየት እንደመጣችሁ
አላውቅም፤ እናንት ዐመፀኞች ሁሉ ከእኔ
ራቁ' ይላል።
28 "አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን፣
ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት
ውስጥ ስታዩ፣ እናንተ ግን ወደ ውጭ
ተጥላ ችሁ ስትቀሩ በዚያን ጊዜ ልቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። 29 ሰዎች
ከምሥራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ
መጥተው በእግዚአብሔር መንግሥት በማእድ
ይቀመጣሉ። 30 እነሆ፤ ከኋለኞች መካከል
ፊተኞች የሚሆኑ፣ ከፊተኞች መካከልም
ኋለኞች የሚሆኑ አሉ።"

## ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ዐዘነ

*13፥34፡35 ተዛ ምብ — ማቴ 23፥37-39*
*13፥34፡35 ማመ — ሉቃ 19፥41*

31 በዚያን ጊዜ ከፈሪሳውያን አንዳንዶች
መጥተው፣ "ሄሮድስ ሊገድልህ ስለሚፈልግ
ተነሥተህ ከዚህ ሂድ" አሉት።
32 እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ሄዳችሁ
ለዚያ ቀበሮ፣ እነሆ፤ ዛሬና ነገ አጋንንትን
አወጣለሁ፤ ሕመምተኞችን እፈውሳለሁ፤
በሦስተኛውም ቀን ከግቤ እደርሳለሁ ብሎአል
በሉት፤ 33 ይሁን እንጂ ነቢይ ከኢየሩሳሌም
ውጭ ይሞት ዘንድ አይገባምና ዛሬና ነገ፣ ከነገ
ወዲያም ወደዚያው ጕዞዬን እቀጥላለሁ።
34 "ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፤
ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ አንቺ

13፥21 1ቆሮ5፥6
13፥22 ሉቃ9፥51
13፥24 ማቴ7፥13
13፥25 ማቴ7፥23፤ 25፥10-12
13፥27 ማቴ7፥23
13፥28 ማቴ8፥12
13፥29 ማቴ8፥11
13፥30 ማቴ19፥30
13፥31 ማቴ14፥1
13፥32 ዕብ2፥10
13፥33 ማቴ21፥11
13፥34 ማቴ23፥27

*[a]13፥21 ግሪኩ ሦስት መስፈሪያ (22 ሊትር የሚያህል) ይላል*

**13፥21 እርሾ፤** በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙውን ጊዜ እርሾ ክፉ ነገርን ወይም እድፈት መኖሩን የሚያመለክት ትእምርት ነው። እርሾ የማፍላት (የማቡካት)፣ የመፈረካከስ ወይም የመበከል ባሕርይ አለው (ዘፀ 12፥19፤ 13፥6-8፤ ዘሌ 2፥11፤ 6፥17፤ ዘዳ 16፥3-4፤ አሞ 4፥4-5 ይመ፤ ዘፀ 13፥7 እና ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እርሾ የፈሪሳውያንን፣ የሰዱቃውያንን (16፥2) እና የሄሮድስን (ማር 8፥15 እና ማብራሪያውን ይመ) የሐሰት ትምህርትንና ክፉ አስተምህሮን ያመለክታል። በ1ቆሮ 5፥6-8 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እርሾ ያለበት ነገር፣ «ግፍንና ክፉትን» እንደሚያመለክት፣ ከእርሾ ነጻ የሆነ ነገር ደግሞ፣ «ቅንነትንና እውነትን» እንደሚያሳይ ይገልጻል (ከገላ 5፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ይህ ምሳሌ ክፉት፣ የሐሰት አስትምህሮና ርኵሰት በሚታየው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሊገባና ሊስፋፋ እንደሚችል የሚያመለክት እንደሆነ ብዙዎች ይረዳሉ።

(1) ይህ የክፉት እርሾ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ሁሉ ይሰራጫል፤ ቀጥሎ ያሉትም ይህ ሁኔታ የሚገልጽባቸው መንገዶች ናቸው፤ (ሀ) ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ይልቅ ለሰው ሐሳብ ከፍተኛ ግምትንና ጉልህ ስፍራን የሚሰጡ በሞደርኒዝም፣ በሊብራሊዝምና በሊበሬሽን ሐሳብ ላይ ያተኮሩ የሥነ መለኮት ትምህርቶች (ከማቴ 22፥23፡29 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (ለ) ዓለማዊነትና ኢግብረገባዊነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየጨመረ መሄዱ (ከ1ቆሮ 5፥1-2፤ ከራእ 2—3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (ሐ) እግዚአብሔርን ከማክበር ይልቅ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ዕቅድ ያላቸው ሰዎች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣንና የክብር ስፍራን ለመያዝ የሚያደርጉት ሩጫ (ከማቴ 23 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (መ) የሐሰት አስተምህሮ (ከገላ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (ሠ) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች (ከማቴ 24፥11፡24 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ረ) ራሳቸውን ክርስቲያን አድርገው የሚቈጥሩ ነገር ግን ዳግመኛ ያልተወለዱ ሰዎች (ከማቴ 23፤ ከይሁ 1፥12-19 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ዘመን መጨረሻ አካባቢ፣ እነዚህ የክፉት ድርጊቶች የአዲስ ኪዳንን የሐዋርያት የወንጌል ትምህርትንና የጽድቅ ኑሮን በከፍተኛ ደረጃ እስከሚበርዙና እስከሚያበላሹ ድረስ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት፣ ቤተ እምነቶች፣ ኮሌጆችና ሴሚናሪዎች ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ሰርገው ይገባሉ (18፥8፤ ማቴ 24፥10-12፤ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ 2ተሰ 2፥3፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ ራእ 2—3 ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ «ታላቁ መከራ» በሚል ርእስና በገጽ 1716 ላይ፣ «*የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው*» በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)።

(2) እያንዳንዱ ክርስቲያን በክፉት እርሾ ሕይወቱ እንዳይበከል መጠንቀቅ ይገባዋል። ድል የመቀዳጀት ምስጢሩ የዓለምን ነገር በመናቅ (ያዕ 1፥27፤ 1ዮሐ 2፥15-17)፣ በእግዚአብሔር ቃል ጸንቶ በመኖር (ዮሐ 15፥7፤ ያዕ 1፥21)፣ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ተስፋ በማድረግ (12፥35-40)፣ ሁልጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ በመስማትና በእርሱም በመመራት (ሮሜ 8፥12-14፤ ገላ 5፥16-18)፣ መከራን ለመቀበል ፈቃደኛ በመሆን (1ጴጥ 4፥1-2)፤ ከክፉ በመራቅ (1ቆሮ 10፥6፤ 1ተሰ 5፥15፤ 1ጴጥ 3፥11)፣ ስለ ወንጌል በመቆም (ፊል 1፥17) እና የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ በመልበስ (ኤፌ 6፥11-18) ዓይናችንን በእምነት በኢየሱስ ላይ ማድረግ ነው (ቲቶ 2፥13፤ ዕብ 12፥2፡15)።

**13፥24 በጠባቧ በር፤** ማቴ 7፥14 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥30 ከኋለኞች ... ፊተኞች የሚሆኑ፤** ማቴ 19፥30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥34 ይህ ጥቅስ የጌታን ታላቅ ሐዘን**

የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ!
ዶሮ ጫጩቶ ቿን በክንፎቿ ሥር
እንደምትሰበስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ
ስንት ጊዜ ፈለግሁ፤ እናንተ ግን እምቢ
አላችሁ፤ 35እነሆ፤ ቤታችሁ ወና ሆኖ
ቀርቶአል። እላችኋለሁ፤ በጌታ ስም
የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ
ከእንግዲህ አታዩኝም።"

## ኢየሱስ በአንድ ፈሪሳዊ ቤት

*14፥8-10 ማመ — ምሳ 25፥6፡7*

**14** አንድ ሰንበት ቀን፣ ኢየሱስ ምግብ
ሊበላ ከፈሪሳውያን አለቆች አንዱ
ወደ ነበረ ሰው ቤት በገባ ጊዜ፣ ሰዎች
በዐይን ይከታተሉት ነበር። 2በዚያም
በአካል እብጠት የሚሠቃይ አንድ ሰው
ከፊት ለፊቱ ነበር። 3ኢየሱስም ሕግ
ዐዋቂዎችንና ፈሪሳውያንን፣ "በሰንበት ቀን
ሕመምተኞችን መፈወስ ተገቢ ነው ወይስ
አይደለም?" ሲል ጠየቃቸው። 4እነርሱ ግን
ዝም አሉ። እርሱም ሰውየውን ይዞ ፈወሰውና
አሰናበተው።
5ደግሞም፣ "ከእናንተ አንዱ፣ ልጁ[ሀ]
ወይም በሬው በሰንበት ቀን ጕድጓድ
ቢገባበት ፈጥኖ የማያወጣው ማን ነው?"
አላ ቸው። 6እነርሱም ለዚህ አንዳች መልስ
ሊያገኙ አልቻሉም።
7ኢየሱስ ተጋባዦቹ የክብር ስፍራ
ሲመርጡ ተመልክቶ፣ እንዲህ ሲል ይህን
ምሳሌ ለእነርሱ ነገራቸው፤ 8"አንድ ሰው
ሰርግ ቢጠራህ፣ በክብር ስፍራ አትቀመጥ፤
በክብር ከአንተ የሚበልጥ ሰው ተጠርቶ
ከሆነ፣ 9ሁለታችሁንም የጋበዘው መጥቶ፣
ስፍራ ውን 'ለዚህ ሰው ልቀቅለት' ይልሃል፤
አን ተም እያፈርህ ወደ ዝቅተኛው ስፍራ
ትሄዳለህ። 10ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ
ዝቅተኛውን ስፍራ አይተህ ተቀመጥ፤
ጋባዥህም ሲመጣ፣ ወዳጄ ሆይ፤ ወደ ላይ
ከፍ በል ይልሃል፤ አንተም በዚያን ጊዜ
አብረውህ በማእድ በተቀመጡ ሰዎች ሁሉ
ፊት ትከበራለህ። 11ምክንያቱም ራሱን ከፍ
ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ራሱንም
ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ሁሉ ከፍ ይላል።"
12ኢየሱስም የጋበዘውን ሰው
ደግሞ እንዲህ አለው፤ "የምሳ ወይም
የእራት ግብዣ በምታደርግበት ጊዜ፣
በአጸፋው እንዳይጋ ብዙህና ብድራትን
እንዳይመልሱልህ፣ ወዳጆችህን ወይም
ወንድሞችህን ወይም ዘመዶችህን ወይም
ከበርቴ ጐረቤቶችህን አት ጋብዝ። 13ነገር
ግን ግብዣ ባዘጋጀህ ጊዜ ድኾችን፣ አካለ
ስንኩሎችን፣ ሽባዎችንና ዐይነ ስውሮችን
ጥራ፤ 14ትባረካለህም። እነ ዚህ ብድር
ሊመልሱልህ ስለማይችሉ፣ በጻድቃንም
ትንሣኤ ብድራትህ ይመለስልሃል።"

## የትልቅ ግብዣ ምሳሌነት

*14፥16-24 ማመ — ማቴ 22፥2-14*

15ከኢየሱስ ጋር በማእድ ከተቀመጡት
መካከል አንዱ ይህን ሰምቶ "በእግዚአብሔር
መንግሥት ቀርቦ ከማእድ የሚበላ ብፁዕ
ነው" አለው።
16ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "አንድ
ሰው ትልቅ ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ ሰው
ጠራ፤ 17የግብዣውም ሰዓት በደረሰ ጊዜ
የተጋበ ዙትን እንግዶች፣ እነሆ፤ ሁሉም
ነገር ተዘጋጅቶአልና ኑ ብሎ እንዲጠራ
አገልጋዩን ላከባቸው።
18"ነገር ግን ሁሉም የየራሳቸውን
ምክንያት ይፈጥሩ ጀመር፤ አንደኛው፣ 'ገና

13፥35 መዝ118፥26፤ ኤጥ12፥17፤ 22፥5፤ ሉቃ19፥38
14፥1 ማቴ12፥10፤ ሉቃ7፥36፤ 11፥37
14፥3 ማቴ12፥2፤ 22፥35
14፥5 ሉቃ13፥15
14፥7 ሉቃ11፥43
14፥11 ማቴ23፥12
14፥13 ቍ21
14፥14 ሐሥ24፥15
14፥15 ኢሳ25፥6፤ ማቴ3፥2፤ 26፥29፤ ሉቃ13፥29፤ ራእ19፥9

[ሀ] 14፥5 አንዳንድ ቅጆች አህያው ይላሉ

**ይገልጻል፡፡** ጌታችን ስለ ኢየሩሳሌም ልበ ደንዳናነት ማልቀሱ (ከሉቃ 19፥41 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሰው ካልፈለገ የእግዚአብሔርን ጸጋና ፈቃድ ላለመቀበልም ነጻነት እንዳለው ያመለክታል (19፥41 እና ማብ፤ ሐሥ 7፥51፤ ሮሜ 1፥18-32፤ 2፥5 ይመ)::

**14፥11 ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤** በዚህ ዓለም ራሳቸውን ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ሰዎች በሚመጣው ሰማያዊ መንግሥት ኀፍረት እንደሚጠብቃቸው አዳኙ ጌታ ያስጠነቅቃል:: ከምድራዊ ክብር እጅግ የሚበልጠው በእግዚአብሔር ዘንድ ያለን የክብር ስፍራ ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ክብር ትሑትና ቅን አገልጋይ በመሆን (ቍ 12-14) እንዲሁም “ከአንዱ አምላክ የሚመጣውን ክብር” (ዮሐ 5፥44) በመፈለግ እንጂ በራስ ጥረት ማግኘት አይቻልም::

**14፥15-24 በዚህ ክፍል የትልቁ ግብዣ ምሳሌነት ተጠቅሶአል::** ይህ ምሳሌ በመጀመሪያ እስራኤል የወንጌል የምሥራች ቀርቦላት አለመቀበሏን የሚገልጽ ቢሆንም፣ ዛሬ ያሉትንም አብያተ ክርስቲያናትንና እያንዳንዱን አማኝ የሚመለከት ነው፤ (1) የዚህ ምሳሌ ዋና ሐሳብ ለድነት የሚደረገው የወንጌል ጥሪና ወደፊት በታላቅ ሰማያዊ ክብር የሚከሰተውን የሙታን ትንሣኤን ቀንየሚመለከት ነው (ቍ 14-15 ይመ፤ ከ22፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም ክርስቶስ ሕዝቡን ወደ ሰማያዊ መንግሥት ለማስገባት ተመልሶ የሚመጣበት ነው::

(2) በመጀመሪያ የግብዣውን ጥሪ ተቀብለው በኋላ ለመምጣት ፈቃደኛ ያልሆኑት፣ ወደ ድነት ይመጡ ዘንድ የኢየሱስን ጥሪ የተቀበሉ ወይም የመቀበል አዝማሚያ ያሳዩ ነገር ግን ለክርስቶስና ለሰማያዊው መንግሥት ያላቸው ፍቅር የቀዘቀዘባቸውን ሰዎች ያመለክታል (ቍ 17-20)::

(3) እንደዚህ ዐይነት ሰዎች ዐላማቸው በሰማያዊ ሕግ ላይ ያተኰረ አይደለም (ቍ 18-20):: የክርስቶስን መምጣት ሲጠባበቁ፣ “አሳባችሁም በላይ ባለው እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን” (ቈላ 3፥1-4) የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር አይቀበሉም፤ ተስፋ የሚያደርጉትና በሕይወታቸው ትኩረት የሚሰጡት የዚህን ዓለም ነገር ነው፤ የሚበልጠውንም ሰማያዊ አገር አይናፍቁም (ዕብ 11፥16)::

(4) ልባቸው በዚህ ምድር ይሆናል ብለው በሚጠብቁት ነገር ላይ ሳይሆን፣ ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ያደረጉ ሰዎች እንደሚኖሩ ቍ 21-23 ያመለክታል፤ ከመንፈሱና ከሙሽራዪቱ ጋር እየጸለዩ፣ “አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና” ይላሉ (ራእ 22፥20)::

አሁን መሬት ስለ ገዛሁ ሄጄ ማየት አለብኝ፤
እባክህ፣ ይቅርታ አድርግልኝ' አለው።
19"ሌላኛውም፣ 'አምስት ጥማድ በሬዎች
ገዝቻለሁ፤ እነርሱን ልፈትናቸው ስለሆነ
እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ' አለ።
20"ሌላው ደግሞ፣ 'ገና ሙሽራ ስለሆንሁ
ልመጣ አልችልም' አለ።
21"አገልጋዩም ተመልሶ መጥቶ ይህንኑ
ለጌታው ነገረው። በዚህን ጊዜ የቤቱ ጌታ
ተቈጥቶ አገልጋዩን፣ 'ቶሎ ብለህ ወደ
ከተ ማው አውራ ጐዳናዎችና መተላለፊያ
መንገዶች ውጣ፤ ድኾችንና አካለ
ስንኩሎችን፣ ዐይነ ስውሮችንና ዐንካሶችን
ወደዚህ አስገ ባቸው' አለው።
22"አገልጋዩም፣ 'ጌታዬ፤ ያዘዝኸው ሁሉ
ተፈጽሟል፤ ገና አሁንም ቦታ አለ' አለው።
23"ጌታውም አገልጋዩን፣ 'ወደ
ጐዳናዎችና ወደ ገጠር መንገዶች ውጣ፤
ቤቴም እን ዲሞላ ያገኘኸውን ሁሉ በግድ አም
ጥተህ አስገባ፤ 24እላችኋለሁና ከተጋበዙት
ከእነዚያ ሰዎች መካከል አንድ ሰው እንኳ
ግብዣዬን አይቀምስም አለው።'"

## ደቀ መዝሙር መሆን የሚያስከፍለው ዋጋ

25ብዙ ሕዝብ አብሮት እየተጓዘ ሳለ፣
ኢየሱስ ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው፤
26"ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና
እናቱን ሚስቱ ንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና
እኅቶቹን፣ የራሱንም ሕይወት እንኳ ሳይቀር
ባይጠላ፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም፤
27የራሱንም መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ
ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
28"ከእናንተ አንድ ሰው ሕንጻ ለመሥራት
ቢፈልግ፣ መደምደም መቻል አለመቻሉን
በመጀመሪያ ተቀምጦ ዋጋውን የማይተምን
ማን ነው? 29መሠረቱን ጥሎ መደምደም
ቢያቅተው፣ ያዩት ሁሉ ይዘባበቱበታል፤

14፥21 ቈላ4፥3
14፥24 ማቴ21፥43፤ ሐሥ13፥46
14፥26 ማቴ10፥37፤ ዮሐ12፥25
14፥27 ማቴ10፥38፤ ሉቃ9፥23
14፥33 ፊል3፥7፡8
14፥34 ማር9፥50
14፥35 ማቴ5፥13፤ ማቴ11፥15
15፥1 ሉቃ5፥29
15፥2 ማቴ9፥11
15፥3 ማቴ13፥3
15፥4 መዝ23፤ 119፥176፤ ኤፀ31፥10፤ ሕዝ34፥11-16፤ ሉቃ5፥32፤ 19፥10
15፥6 ቍ9
15፥7 ቍ10

30እንዲህም ይላሉ፤ 'ይህ ሰው ማነጽ ጀምሮ
ነበር፤ መደምደም ግን አቃተው።'
31"ወይም አንድ ንጉሥ ከሌላው ንጉሥ
ጋር ጦርነት ሊገጥም በሚነሣበት ጊዜ፣
ሃያ ሺህ ሰራዊት አስከትቶ የሚመጣበትን
ንጉሥ፣ በዐሥር ሺህ ሰራዊት መመከት
እንደሚችል ተቀምጦ የማይመክር ማን
ነው? 32መቋቋም የማይችል ከሆነ፣ ሌላው
ንጉሥ ገና ሩቅ ሳለ፣ መልእክተኞች
ልኮ ዕርቅ ይጠ ይቃል። 33እንደዚሁም፣
ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው፣
ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
34"ጨው መልካም ነው፤ ጨው ጣዕሙን
ካጣ ግን እንዴት ተመልሶ የጨውነት ጣዕም
ሊኖረው ይችላል?
35ለመሬትም ሆነ ለማዳበሪያነት የማይጠ
ቅም በመሆኑ ወደ ውጭ ይጣላል።
"ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።"

## የጠፋው በግ ምሳሌ

*15፥4-7 ተጓ ምብ — ማቴ 18፥12-14*

15 አንድ ቀን፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና
"ኀጢአተኞች" ሁሉ ሊሰሙት በዙሪ
ያው ተሰበሰቡ። 2ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣
"ይህ ሰው ኀጢአተኞችን ይቀበላል፤ ከእነ
ርሱም ጋር ይበላል" እያሉ አጕረመረሙ።
3ኢየሱስም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
ነገራቸው፤ 4"ከእናንተ መካከል አንዱ መቶ
በጎች ቢኖሩትና ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋ
በት፣ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ላይ ጥሎ የጠፋ
ውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ
ማን ነው? 5ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫ
ንቃው ተሸክሞ፣ 6ወደ ቤቱ ይመለሳል፤ ወዳ
ጆቹንና ጎረቤቶቹንም በአንድነት ጠርቶ፣
'የጠፋውን በጌን አግኝቻለሁና ከእኔ ጋር
ደስይበላችሁ' ይላቸዋል። 7እላችኋለሁ፤ እን
ደዚሁም ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና

---

**14፥26 አባቱን ... ባይጠላ፤** በዚህ ክፍል፣ "መጥላት" የሚለው ቃል "ፍቅር የሌለው" ማለት ነው (ይህን ጥቅስ በማቴ 10፥37 ላይ ካለው ጋር ያነጻጽሩ፤ ዘፍ 29፥31 እና ማብ፤ ሚል 1፥3 እና ማብ ይመ):: ለእርሱ ያለን ታማኝነትና ፍቅር ለቤተ ሰቦቻችንና ለሌሎች ነገሮች ካለን ፍቅር ሁሉ የላቀ መሆን እንደሚገባው ኢየሱስ ያስገነዝባል::

**14፥27 የራሱንም መስቀል ተሸክሞ፤** 9፥23 እና ማብራሪያውን፤ ማር 8፥34 እና ማብራሪውን ይመልከቱ::

**14፥28-33 በዚህ ክፍል ደቀ መዝሙርነት ስለሚያስከፍለው ዋጋ ተገልጾአል::** ኢየሱስ፣ ሊከተለውና ደቀ መዝሙሩ ሊሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በመጀመሪያ ደቀ መዝሙርነት የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል መወሰን እንዳለበት ያስተምራል:: የእውነተኛ ደቀ መዝሙርነት ዋጋ ወዳጆቻችንንና ያለንን ነገር ሁሉ እንድንተው የሚጠይቅ ነው (ቍ 33):: ይህም ሲባል ያለንን ነገር ሁሉ እርግፍ አድርገን መጣል ማለት ሳይሆን፣ ባለን ነገር ሁሉ ክርስቶስን ለማገልገልና በእርሱ ለመመራት ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን የሚያመለክት ነው (13፥24፤ ማቴ 7፥14 ይመ፤ ከዮሐ 16፥33፤ ከ2ጢሞ 3፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::

**15፥1-7 በዚህ ክፍል ስለ ጠፋው በግ ተጠቅሶአል::** በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ዋና የሆነው ጥቅስ፣ "የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው" የሚለው ነው (19፥10):: በምዕራፍ 15 ላይ የተጠቀሱት ሦስት ምሳሌዎች ይህንን የኢየሱስ ምድራዊ ተልእኮ ዐላማና እግዚአብሔር የጠፉትን ለዘላለም ይድኑ ዘንድ ለማድረግ ያለውን ምኞት የሚገልጽ ነው፤ ከዚህም የሚከተለውን ነገር እንማራለን፤ (1) ይድኑ ዘንድ በኀጢአት የጠፉትን መፈለግ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ አስፈላጊ ነገር እንደ ሆነ (ቍ 4:8:20:24)፤ (2) አንድ ኀጢአተኛ እንኳ ንስሓ ቢገባ በእግዚአብሔር ዘንድና በሰማይ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን (ቍ 7:10) እንደዚሁም (3) የጠፋውን ፈልጎ ወደ ኢየሱስ ለማምጣት ማንኛውም መሥዋዕትነት ቢከፈልና ማንኛውም መከራ ቢገጥም ብዙ እንዳልሆነ (ቍ 4:8)::

**15፥7 በሰማይ ደስታ ይሆናል፤** በሰማይ እግዚአብሔርና መላእክቱ በኀጢአት ለወደቁትና

ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፣ ንስሓ በሚገባ በአንድ
ኀጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።

## የጠፋው ሳንቲም ምሳሌ

8"ወይም ዐሥር የብር ሳንቲሞች ያላት
ሴት ከዐሥሩ አንዱ ቢጠፋባት፣ እስክታገ
ኘው ድረስ መብራት አብርታ፣ ቤቷን
ጠርጋ፣ አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን
ናት? 9ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆቿንና ጐረቤ
ቶቿን፣ በአንድነት ጠርታ፣ 'የጠፋብኝን
የብር ሳንቲም አግኝቻለሁና ከእኔ ጋር ደስ
ይበላችሁ' ትላቸዋለች። 10እላችኋለሁ፤ እን
ደዚሁም ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ
በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።

## ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌነት

11ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
"አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት።
12ከእነርሱም ታናሹ ልጅ አባቱን፣ 'አባቴ
ሆይ፤ ከሀብትህ ድርሻዬን ስጠኝ' አለው፤
አባትየውም ሀብቱን ለልጆቹ አካፈላቸው።
13"ብዙም ቀን ሳይቈይ፣ ታናሹ ልጅ
ድርሻ ውን ሁሉ ጠቅልሎ ወደ ሩቅ አገር
ሄደ፤ በዚያም በማጋጣነት ንብረቱን አባከነ
። 14እርሱም ያለውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ፣
በዚያ አገር ሁሉ ጽኑ ራብ ሆነ፤ ይቸገርም
ጀመር። 15ስለዚህ ከዚያ አገር ነዋሪዎች
አንዱን ተጠጋ፤ ሰውየውም ዐሣማ እንዲቀ

15፥9 ቍ6
15፥10 ቍ7
15፥11
ማቴ21፥28
15፥12 ቍ30፤
ዘዳ21፥17
15፥13 ቍ30፤
ሉቃ16፥1
15፥15 ዘሌ11፥7

15፥18
ዘሌ26፥40፤
ማቴ3፥2
15፥20
ዘፍ45፥14:15፤
46፥29፤
ሐሥ20፥37
15፥21 መዝ51፥4
15፥22
ዘፍ41፥42፤
ዘካ3፥4፤ ራእ6፥11
15፥24 ቍ32፤
ኤፌ 2፥1:5፤
5፥14፤ 1ጢ.5፥6

ልብለት ወደ ዕርሻው ላከው። 16ዐሣማዎቹ
የሚመገቡትን ዐሠር እንኳ ለመብላት
ይመኝ ነበር፤ ኾነር ግን ይህን እንኳ
የሚሰጠው ሰው አልነበረም።
17"ልብ በገዛ ጊዜ ግን እንዲህ አለ፤
'ስንቱ የአባቴ ሠራተኛ ምግብ ተርፎታል፤
እኔ ግን እዚህ በራብ ልሞት ተቃርቤአለሁ
18ተነሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና፣ እንዲህ
ልበለው፤ "አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በአንተ
ፊት በድያለሁ፤ 19ከእንግዲህ ልጅህ
ተብዬ ልጠራ አይገባኝም፤ ከተቀጠሩት
አገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቍጠረኝ።'
20ስለዚህም ተነሥቶ ወደ አባቱ ሄደ።
"ነገር ግን፣ እርሱ ገና ሩቅ ሳለ፣ አባቱ
አይቶት ራራለት፤ ወደ እርሱም እየሮጠ
ሄዶ ዐቅፎ ሳመው።
21"ልጁም፣ 'አባቴ ሆይ፤ በሰማይና
በአንተ ፊት በድያለሁ፤ ከእንግዲህ ልጅህ
ተብዬ ልጠራ አይገባኝም' አለው።+
22"አባቱ ግን አገልጋዮቹን እንዲህ
አላቸው፤ 'ፈጥናችሁ ከሁሉ ምርጥ የሆነውን
ልብስ አምጡና አልብሱት፤ ለጣቱ ቀለበት፣
ለእግሩም ጫማ አድርጉለት፤ 23የሰባውንም
ፍሪዳ አምጡና ዕረዱ፤ እንብላ፤ እንደሰት፤
24ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፤ አሁን ግን ሕያው

*+15፥21 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንኳ እንደ አንዱ ቍጥረህ ተቀበለኝ የሚል አላቸው*

በመንፈሳዊ ሞት ውስጥ ለሚገኙት እንደዚህ ዐይነት ፍቅር፣ ርኅራኄና አዘኔታ ስላላቸው፣ አንድ ኀጢአተኛ ንስሓ በሚገባበት ጊዜ በግልጽ ሐሤት ያደርጋሉ። እግዚአብሔር ለኀጢአተኛ ያለውን ፍቅር ለመረዳት ኢሳ 62፥5፤ ኤር 32፥41፤ ሕዝ 18፥23:32፤ ሆሴ 11፥8፤ ዮሐ 3፥16፤ ሮሜ 5፥6-11፤ 2ጴጥ 3፥9 ይመልከቱ።

**15፥8 እስክታገኘው ድረስ ... አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት?** ኀጢአተኞች ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱና እንዲድኑ ለማድረግ እጅግ የሚቀና ልብ መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጠን አጥብቀን መጸለይ ይገባናል።

**15፥13 ወደ ሩቅ አገር ሄደ፤** ኀጢአትና ራስ ወዳድነት የሞላበት ሕይወት በጥልቀት ሲታሰብ ከእግዚአብሔር ፍቅር፣ ኅብረትና ሥልጣን መለየት ነው። ኀጢአት የሚሠራ ወይም ከእምነቱ ወደ ኋላ የሚመለስ ሰው፣ ለጊዜው በኀጢአት ከሚገኝ ደስታ ተታሎ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን አካላዊ፣ አእምሮአዊና መንፈሳዊ ስጦታውን እንዳበላሸው መጣቱ ልጅ ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ስሕተት ተስፋ መቍረጥን፣ ሐዘንን፣ ውርደትንና ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ኅብረት በመመሥረት የሚገኘውን እውነተኛ ሕይወት ማጣትን ያስከትላል።

**15፥17 ልብ በገዛ ጊዜ፤** የጠፉት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ከመምጣታቸው በፊት በኀጢአት ባርነት ሥር እንዳሉና ከእግዚአብሔር የተለዩ እንደሆኑ በትክክል ያሉበትን ሁኔታ መረዳት አለባቸው (ቍ 14-17)። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆንና ኀጢአታቸውን በመናዘዝ በትሕትና ወደ አባታቸው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለባቸው (ቍ 17-19)። የጠፉት ወደዚህ ግንዛቤ እንዲመጡ ማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው (ዮሐ 16፥7-11)።

**15፥20 እርሱ ገና ሩቅ ሳለ፤** ማንኛቸውም ክርስቲያን አባትና እናት እግዚአብሔር እየባዘነ ያለውን ልጃቸውን እንደሚወድና እነርሱ ይድን ዘንድ እንደሚፈልጉ ሁሉ እግዚአብሔርም ለዚያ ልጅ ያለው ምኞት ያ እንደሆነ መረዳት አለባቸው። ልጁ ወደ ሰማያዊ አባቱ እስከሚመለስ ድረስ ወላጆቹ ስለ እርሱ በማሰብ መጸለይና እግዚአብሔርን ታምኖ መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል።

**15፥20 አባቱ አይቶት ራራለት፤** ልጁ በመመለሱ የአባትየው ምላሽ ምን እንደሚመስል ኢየሱስ ከሰጠው ገለጻ ብዙ አስፈላጊ እውነቶችን እንማራለን፤ (1) ካሉበት አሳዛኝ ሁኔታ የተነሣ እግዚአብሔር ለጠፉት ይራራል፤ (2) እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለው ፍቅር ታላቅ በመሆኑ፣ ስለ እነርሱ ማዘኑንና ይመለሳሉ ብሎ ተስፋ ማድረጉን አይተውም፤ (3) ኀጢአተኞች ከልብ ንስሓ ገብተው በሚመለሱበት ጊዜ እግዚአብሔር በይቅርታ፣ በፍቅር፣ በርኅራኄ፣ በጸጋውና ሙሉ የልጅነት መብት በመስጠት በበለጠ ሁኔታ ሊቀበላቸው ዝግጁ ነው (ከዮሐ 1፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ከክርስቶስ ሞት የተገኘው ጥቅም፣ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትና እርዳታ እንዲሁም ባለ ጸጋ የሆነው የእግዚአብሔር ጸጋ እግዚአብሔርን ለሚፈልጉ ሁሉ ይሆኑ ዘንድ የተሰጡ ናቸው፤ (4) በኀጢአተኞች መመለስ እግዚአብሔር የሚሰማው ደስታ እጅግ ታላቅ ነው (ቍ 6-7:10:22-24)።

**15፥24 ይህ ልጄ ... ጠፍቶም ነበር፤** "ጠፋ" የሚለው ቃል ልክ "እንደ ጠፉ በጎች" (1ጴጥ 2፥25 ይመ፤ ከኢሳ 53፥6 ጋር ያነጻጽሩ) ከእግዚአብሔር መራቁን ለመግለጽ የገባ ነው። ከእግዚአብሔር ኅብረት የተለየ ሕይወት የሚጠብቀው መንፈሳዊ ሞት ነው (ኤፌ 2፥1፤ 1ዮሐ 3፥14)። ወደ እግዚአብሔር መመለስ ዘላለማዊ ሕይወትን ያስገኛል (ዮሐ 11፥26)።

ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር፤ ተገኝቶአል።”
ከዚያም ይደሰቱ ጀመር።
25 “በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጅ በዕርሻ ቦታ
ነበረ፤ ከዚያም ተመልሶ ወደ ቤት በተቃረበ
ጊዜ፣ የሙዚቃና የጭፈራ ድምፅ ሰማ፤
26 እርሱም ከአገልጋዮቹ አንዱን ጠርቶ ነገሩ
ምን እንደ ሆነ ጠየቀው። 27 አገልጋዩም፣
‘ወንድምህ መጥቶአል፤ በሰላም በጤና ስለ
መጣም አባትህ የሰባውን ፍሪዳ ዐርዶለ
ታል’ አለው።
28 “ታላቅ ወንድሙም ተቈጣ፤ ወደ
ቤትም መግባት አልፈለገም፤ አባቱም
ወደ ውጭ ወጥቶ እንዲገባ ለመነው።
29 እርሱ ግን መልሶ አባቱን እንዲህ አለው፤
‘እነሆ፤ ይህን ያህል ዘመን እንደ ባሪያ
አገለግዬሃለሁ፤ ከትእዛዝህም አንዱን እንኳ
አላጓደልሁም፤ አንተ ግን ከባልንጀሮቼ ጋር
እንድደሰት አንዲት የፍየል ግልገል እንኳ
አልሰጠኸኝም፤ 30 ነገር ግን ይህ ልጅህ
ንብረትህን ከጋለሞቶች ጋር አውድሞ
ሲመጣ፣ የሰባውን ፍሪዳ አረድህለት።’
31 “አባቱም እንዲህ አለው፤ ‘ልጄ ሆይ፤
አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤ የእኔ የሆነው
ሁሉ የአንተ ነው፤ 32 ይህ ወንድምህ ግን ሞቶ
ነበር፤ ሕያው ሆነ፤ ጠፍቶ ነበር ተገኘ፤ ስለዚህ
ደስ ሊለንና ፍሥሐ ልናደርግ ይገባናል።” ’

## የብልጉ መጋቢ ምሳሌነት

16 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አለ፤ “አንድ ሀብታም ሰው አንድ
መጋቢ ነበረው፤ ይኸው መጋቢ የሀብታ
ሙን ሰው ንብረት እንደሚያባክን ለዚሁ
ሀብታም ሰው ወሬ ደረሰው። 2 ስለዚህ አስጠ
ራውና፣ ‘ይህ የምሰማብህ ምንድን ነው?
ከእንግዲህ አንተ መጋቢ ልትሆነኝ ስለ
ማትችል፣ የምታስተዳድረውን ንብረት
መቈጣጠሪያ ሒሳብ አስረክበኝ’ አለው።
3 “መጋቢውም በልቡ እንዲህ አለ፤ ‘ጌታዬ
ከመጋቢነት ሊሽረኝ ነው፤ ለማረስ ጕልበት
የለኝም፤ መለመን ደግሞ ዐፍራለሁ፤ ስለዚህ
ምን ላድርግ? 4 ከመጋቢነት የተሻርሁ
እንደ ሆነ ሰዎች በቤታቸው እንዲቀበሉኝ
የማደርገውን ዐውቃለሁ።’
5 “ስለዚህ የጌታው ዕዳ ያለባቸውን ሰዎች
እያንዳንዳቸውን ጠራ፤ የመጀመሪያውንም
ሰው ‘የጌታዬ ዕዳ ምን ያህል አለብህ?’
አለው።
6 “እርሱም፣ ‘አንድ መቶ ማድጋ[a] ዘይት
አለብኝ’ አለ።
“መጋቢውም፣ ‘የውል ወረቀትህን እንካ፤
ቶሎ ተቀምጠህ “አምሳ ማድጋ” ብለህ ጻፍ’
አለው።
7 “ከዚያም ሌላውን፣ ‘አንተስ ስንት
አለብህ?’ አለው።
“እርሱም፣ ‘አምሳ ዳውላ[+] ስንዴ’
አለው።
“መጋቢውም፣ ‘የብድር ደብዳቤህን
እንካ፤ “አርባ ዳውላ” ብለህ ጻፍ’ አለው።
8 ጌታውም አጭበርባሪውን መጋቢ
በብልኀነቱ አደነቀው፤ የዚህ ዓለም ልጆች
ከመሰሎቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት
ከብርሃን ልጆች ይልቅ ብልኆች ናቸውና።
9 ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የዚህ ዓለም ገንዘብ
ባለቀ ጊዜ በዘላለም ቤት ተቀባይነት
እንዲኖራ ችሁ፣ በዚሁ ገንዘብ ወዳጆችን
ለራሳችሁ አፍሩበት።
10 “በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም
ይታመናል፤ በትንሽ ነገር ያልታመነበት
ልቁም አይታመንም። 11 እንግዲህ፣
በዚህ ዓለም ሀብት ካልታመናችሁ፣
እውነተኛውንማ ሀብት ማን ዐደራ ብሎ
ይሰጣችኋል? 12 በሌላው ሰው ሀብት
ካልታመናችሁ፣ የራሳ ችሁ የሆነውን ሀብት
ማን ይሰጣችኋል?
13 “በአንድ ጊዜ ሁለት ጌቶችን ማገልገል
የሚችል ማንም ባሪያ የለም፤ አንዱን
ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን
ይጠጋል፤ ሌላውን ይንቃል። የእግዚአብሔርም
የገንዘብም ባሪያ መሆን አትችሉም።”
14 ገንዘብ የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ

15፥28 ዮና4፥1
15፥30 ቍ12፡13፤ ምሳ29፥3
15፥32 ቍ24፤ ሚል3፥17
16፥1 ሉቃ15፥30:30
16፥8 መዝ17፥14፤ መዝ18፥26፤ ዮሐ12፥36፤ ኤፌ5፥8፤ 1ተሰ5፥5
16፥9 ቍ11:13፤ ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33
16፥10 ማቴ25፥21:23፤ ሉቃ19፥17
16፥11 ቍ9:13
16፥13 ቍ9:11፤ ማቴ6፥24
16፥14 ሉቃ23፥35፤ 1ጢሞ3፥3

[a]16፥6 ምናልባት 3 ሺህ ሊትር ይሆናል
[+]16፥7 ምናልባት 35 ሺህ ሊትር ይሆናል

15፥28 **ተቈጣ፤** “ታላቅ ወንድሙ”፣ የኃይማኖተኝነት መልክ ያላቸውና በውጪ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁ የሚመስሉ ነገር ግን በውስጣቸው ከእግዚአብሔርና ከመንግሥቱ ዐላማ የተለዩትን ሰዎች የሚያመለክት ነው (ቍ 28-30)።

16፥8 **አጭበርባሪውን መጋቢ … አደነቀው፤** ኢየሱስ ይህን ገለጻ የሰጠበት ዋና ዐላማ ያላመኑ ሰዎች ምድራዊ ፍላጎታቸውንና እድገታቸውን ከፍ ለማድረግ ምን ያህል እንደሚተጉ ለማሳየት ነው። በሌላ አንጻር አማኞች ምድራዊ ሀብታቸውን፣ መንፈሳዊና ሰማያዊ ፍላጎታቸውን ለማሳደግ ያውሉ ዘንድ ሁል ጊዜ ለመንፈሳዊው ነገር በማሰብ የሚተጉ አይደሉም።

16፥9 **የዚህ ዓለም ገንዘብ፤** “ምድራዊ ሀብትን” ከማከማቸትና ከመጠቀም በስተጀርባ ሁልጊዜ የፍትሕ መጓደል፣ ስግብግብነትና ኀይል አለ (በገጽ 1577 ላይ፣ “ብልጽግናና ድህነት” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ያለን ሀብትና ገንዘብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ሌሎች ይድኑ ዘንድ ወንጌልን ለማሰራጨት ማዋል ይገባናል።

16፥11 **ካልታመናችሁ፤** የዚህን ዓለም ሀብት በማግኘትና በመጠቀም አንጻር ታማኝ ሊሆኑ ያልቻሉ ሰዎች፣ ለመንፈሳዊም ነገር ታማኝ ሊሆኑ አይችሉም። አማኞች በተለይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብን ከመውደድ ነጻ መሆን ያለባቸው ለዚህ ነው (1ጢሞ 3፥1-3)።

16፥13 **የእግዚአብሔርም የገንዘብም ባሪያ መሆን አትችሉም፤** እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲነግሥ ለማድረግ የዓለም ሀብት ትልቅ ዕንቅፋት ይሆናል፤ ይህን ጉዳይ ይበልጥ ለመረዳት፣ በገጽ 1577 ላይ፣ “*ብልጽግናና ድህነት*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

16፥14 **ገንዘብ የሚወዱ ፈሪሳውያን፤** ፈሪሳውያን ሀብትን የሚቈጥሩት ሕጉን በታማኝነት በመፈጸማቸው ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት በረከት እንደ ሆነ ነው። ድኽነቱን እግዚአብሔር እንዳላከበረው

ሰምተው በኢየሱስ አፌዙበት። 15እርሱም
እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ በሰዎች ፊት ራሳ
ችሁን የምታጸድቁ ናችሁ፤ እግዚአብሔር ግን
ልባችሁን ያውቃል፤ በሰዎች ዘንድ የከበረ፣
በእግዚአብሔር ፊት የረከሰ ነውና።
16"ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ
ሲነገሩ ኖረዋል፤ ከዚያ በኋላ ግን የእግዚአብሔር
መንግሥት የምሥራች ተሰብኮአል፤ ሰውም
ሁሉ ወደዚያ ለመግባት ይሻማል። 17ነገር
ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ
ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀ ላል።
18"ሚስቱን ፈቶ ሌላይቱን የሚያገባ
ሁሉ ያመነዝራል፤ ከባሏ የተፋታችውንም
ሴት የሚያገባ ያመነዝራል።"

## ሀብታሙ ሰውና አልዓዛር

19ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
"ሐምራዊና ቀጭን በፍታ የለበሰ፣ በየቀኑም
በተድላ ደስታ የሚኖር አንድ ሀብታም ሰው
ነበረ። 20በእንጻሩም፣ መላ ሰውነቱ በቍስል
የተወረረ አንድ አልዓዛር የሚባል ድኻ
በዚህ ሀብታም ሰው ደጃፍ ይተኛ ነበር፤
21ከሀብታሙ ሰው ማእድ የወደቀውን ፍርፋሪ
እንኳ ሊመገብ ይመኝ ነበር፤ ውሾችም
ሳይቀሩ መጥተው ቍስሉን ይልሱ ነበር።
22"ይህም ድኻ ሞተ፤ መላእክትም
ወደ አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት።
ሀብታሙም ሰው ደግሞ ሞቶ ተቀበረ።
23በሲኦልም እየተሠ ቃየ ሳለ ቀና ብሎ
ከሩቅ አብርሃምን አየ፤ አልዓዛርንም
በዕቅፉ ይዞት አየ። 24እርሱም፣ 'አብርሃም
አባት ሆይ፤ ራራልኝ፤ በዚህ ነበልባል
እየተሠቃየሁ ስለ ሆነ፣ አልዓዛር የጣቱን
ጫፍ ውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያቀዘቅዝልኝ
እባክህ ላክልኝ' እያለ ጮኸ።

16፥15
ሉቃ10፥29፤
ራእ2፥23
16፥16
ማቴ4፥23፤ 5፥17፤
11፥12፡13
16፥17 ማቴ5፥18
16፥18
ማቴ5፥31፡32፤
19፥9፤
ማር10፥11፤
ሮሜ7፥2፡3፤
1ቆሮ7፥10፡11
16፥19 ሕዝ16፥49
16፥20 ሐሥ3፥2
16፥21
ማቴ15፥27፤
ሉቃ15፥16
16፥24 ቍ30፤
ማቴ5፥22፤
ሉቃ3፥8
16፥25
መዝ17፥14፤
ሉቃ6፥21፡24፡25
16፥28
ሐሥ2፥40፤
20፥23፤ 1ተሰ4፥6
16፥29
ሉቃ4፥17፤
24፥27፡44፤
ዮሐ1፥45፤ 5፥45-
47፤ ሐሥ15፥21
16፥30 ቍ24፤
ሉቃ3፥8
17፥1 ማቴ5፥29፤
ማቴ18፥7
17፥2 ማቴ5፥29፤
ማር10፥24፤
ሉቃ10፥21
17፥3
ማቴ18፥15፤
ኤፌ4፥32፤
ቈላ3፥13

25"አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ 'ልጄ
ሆይ፤ አንተ በምድራዊ ሕይወትህ ዘመን
መልካም ነገሮችን እንደ ተቀበልህ፣ አል
ዓዛርም ደግሞ ክፉ ነገሮችን እንደ ተቀበለ
አስታውስ፤ አሁን ግን እርሱ እዚህ ሲጽናና፣
አንተ በሥቃይ ላይ ትገኛለህ። 26ከሁሉም
በላይ ከዚህ ወደ እናንተ ለማለፍ የሚፈልጉ
እንደማይችሉ፣ እዚያ ያሉትም ደግሞ ወደ
እኛ እንዳይሻገሩ፣ በእኛና በእናንተ መካከል
ትልቅ ገደል ተደርጎአል።'
27"እርሱም እንዲህ አለ፤ 'አባት
ሆይ፤ እንግዲያውስ አልዓዛርን ወደ
አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤
28አምስት ወንድ ሞች ስላሉኝ፣ እነርሱም
ወደዚህ የሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ
ያስጠንቅቃቸው።'
29"አብርሃም ግን፣ 'ሙሴና ነቢያት
አሏቸው፤ እነርሱን ይስሙ' አለው።
30"እርሱም፣ 'አብርሃም አባት ሆይ፤ እን
ደዚህ አይደለም፤ አንድ ሰው ከሙታን ተነ
ሥቶ ቢሄድላቸው ንስሓ ይገባሉ' አለ።
31አብርሃምም፣ 'ሙሴንና ነቢያትን
የማይሰሙ ከሆነ፣ አንድ ሰው ከሙታን
ቢነሣ እንኳ አያምኑም' አለው።

## ኀጢአት፣ እምነት፣ ኀላፊነት

17 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ
አላቸው፤ "ሰዎችን የሚያሰናክል
መምጣቱ አይቀርም፤ ነገር ግን ለመሰናከሉ
መምጣት ምክንያት ለሚሆን ለዚያ ሰው
ወዮለት። 2ይህ ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች
አንዱን ከሚያሰናክል፣ የወፍጮ ድንጋይ
በዐንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው
ነበር። 3ስለዚህ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።

ምልክት አድርገው ስለቈጠሩት ፈሪሳውያን ድኻ በነበረው በኢየሱስ ላይ አፌዙበት (በገጽ 1577 ላይ፣ *«ብልጽግናና ድህነት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**16፥18 *ያመነዝራል፤*** *መጽሐፍ ቅዱሳዊ* ባልሆነ ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዋን የሚያገባ ሰው (*ማቴ* 19፥9 እና *ማብ ይመ*) *«ያመነዝራል»*። *«ያመነዝራል»* የሚለው ቃል በግሪክ በመሆን ላይ ያለ ድርጊትን የሚያመለክት የአሁን ጊዜ ግቢር ግሥ ነው። ይህም ንጹሕ ሆና እያለች የተፈታችው ሴት፣ ለመታረቅ እየፈለገች፣ በዳዩ ባል ሌላ ሴት ቢያገባ፣ ጋብቻው በዝሙት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ጋብቻ እንደፈረሰ ስለማይቈጥረው፣ ሌላ ጋብቻ መመሥረቱ ማመንዘር ነው፤ (1) እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ግብረገባዊ ጉዳይ ጥፋተኛ የሆነው ወገን እንደገና የሚፈጽመው ጋብቻ ከፍጻሜ መድረስ ላለባቸው ለመጀመሪያው ጋብቻ ኪዳናዊ ሕጎችና የወላጅነት ኀላፊነቶች ዋጋ ያለመስጠቱ ነው። ንጹሕ የሆነው የትዳር ጓደኛ ዕርቅ የሚፈልግ ከሆነ፣ ጉዳዩ ወሳኝ ነገር ነው፤ በደለኛው ወገን ጋብቻ ቢፈጽም ያመነዝራል (ከማር 10፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ይሁን እንጂ ጥፋተኛው ወገን (ሀ) የመጀመሪያውን ጋብቻ ለማደስ የማይችልበት ሁኔታ ካጋጠመው፣ (ለ) ኢየሱስ ማመንዘር እንደ ሆነ ከገለጸው ዐይነት ጋብቻ ውስጥ ከገባ፣ (ሐ) በእግዚአብሔር ፊት ከልብ የሆነ ንስሓ ከገባና በአሁኑ ጋብቻው እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ለመኖር እውነተኛ ውሳኔ ካደረገ፣ ጋብቻው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያገኝ ይሆናል።

**16፥19-20 አንድ ሀብታም ሰው ... አልዓዛር፤** ከቍ 19-31 ይመልከቱ። ሀብታሙ ሰው ዕድሜውን የጨረሰው፣ በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት በመኖር ነው። ትክክለኛ ምርጫ ባለማድረጉ፣ መጨረሻው የዘላለም ሥቃይ ሆነ (ቍ 22-23)። አልዓዛር በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በድኽነት ቢኖርም እግዚአብሔርን የሚፈራና የቀና ልብ የነበረው ሰው ነው። የስሙ ትርጕምም፣ «እግዚአብሔር ረዳቴ ነው» የሚል ነው። አልዓዛር ተስፋ ሳይቈርጥ በእግዚአብሔር ያለውን እምነት ጠብቆአል፤ በሞተም ጊዜ ከአብርሃም ጋር ይሆን ዘንድ ወዲያው ወደ ገነት ተወሰደ (ቍ 22፤ 23፥43፤ ሐሥ 7፥59፤ 2ቆሮ 5፥8፤ ፊል 1፥23)፤ ሁለቱም ሰዎች ከሞት በኋላ የሚጠብቃቸው ዕጣ ፈንታ የማይለወጥ ነበር (ቍ 24-26)።

**17፥2 የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ፤** ጥሩ ምሳሌ ባለመሆንና ጥሩ ባሕርይ ባለማሳየት ወይም ችላ በማለት ለአንድ ሰው ኀጢአት ያደርግ ዘንድ ምክንያት መሆን፣ እንደዚህ ዐይነቱን የከፋ ቅጣት ያስከትላል፤ ቅጣቱም 'ምነው ይህን ኀጢአት ከመፈጸሜ በፊት በሞትኩ' የሚያሰኝ ነው (*ማቴ* 18፥6 እና *ማብ ይመ*)።

"ወንድምህ ቢበድል ገሥጸው፤ ቢጸጸት
ይቅር በለው። 4በቀን ሰባት ጊዜ ቢበድል ህና
ሰባት ጊዜ፣ 'ተጸጽቻለሁ' እያለ ወደ አንተ
ቢመለስ ይቅር በለው።"
5ሐዋርያትም ጌታን፣ "እምነታችንን
ጨምርልን" አሉት።
6ጌታም፣ "የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል
እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህን ሾላ፣ 'ተነቅለህ
ባሕር ውስጥ ተተከል' ብትሉት ይታዘዝላ
ችኋል" አላቸው። ዮሐ 12
7ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "ከእናንተ
መካከል አንድ ሰው ዐራሽ ወይም በግ
ጠባቂ የሆነ አገልጋይ ቢኖረው፣ ከዕርሻ የተ
መለሰውን አገልጋዩን፣ 'ቶሎ ወደ ማእድ
ቅረብ' ይለዋልን? 8ከዚህ ይልቅ፣ 'እራቴን
እንድበላ አዘጋጅልኝ፣ እኔ እስክበላና እስክ
ጠጣ ድረስ ታጥቀህ አገልግለኝ፤ ከዚያ በኋላ
አንተ ደግሞ ትበላለህ፤ ትጠጣለህ' አይለው
ምን? 9እንግዲህ ይህ ሰው፣ አገልጋዩ የታዘዘ
ውን በመፈጸሙ መልሶ ያመሰግነዋልን?
10ስለዚህ እናንተም የታዘዛችሁትን ሁሉ
ባደረጋችሁ ጊዜ፣ 'ከቍጥር የማንገባ
አገልጋዮች ነን፤ ልናደርገው የሚገባንን
ተግባር ፈጽ መናል በሉ።"

## ከለምጽ የነጹ ዐሥር ሰዎች

11ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም
ሲሄድ፣ በሰማርያና በገሊላ ድንበር በኩል
ዐለፈ፤ 12ወደ አንድ መንደር እንደ ገባም
ለምጽ* የያዛቸው ዐሥር ሰዎች አገኙት፤
እነርሱም በርቀት ቆመው፣ 13በታላቅ
ድምፅ፣ "ኢየሱስ፤ ጌታ ሆይ፤ ራራልን!"
አሉት።
14እርሱም ባያቸው ጊዜ፣ "ሂዱና ራሳች
ሁን ለካህናት አሳዩ" አላቸው። እነርሱም
ወደዚያው በመሄድ ላይ ሳሉ ነጹ።

17፥4
ማቴ18፥21፡22
17፥5 ማር6፥30፤
ሉቃ7፥13
17፥6
ማቴ13፥31፤
17፥20፤ 21፥21፤
ማር9፥23፤
ሉቃ13፥19
17፥8 ሉቃ12፥37
17፥10 1ቆሮ9፥16
17፥11
ሉቃ9፥51፡52፤
ዮሐ4፥3፡4
17፥12
ዘሌ13፥45፡46፤
ማቴ8፥2
17፥13 ሉቃ5፥5
17፥14 ዘሌ14፥2፤
ማቴ8፥4
17፥15 ማቴ9፥8
17፥16 ማቴ10፥5
17፥19 ማቴ9፥22
17፥20 ማቴ3፥2
17፥21 ቍ23
17፥22
ማቴ8፥20፤
ሉቃ5፥35
17፥23
ማቴ24፥23፤
ሉቃ21፥8
17፥24
ማቴ24፥27
17፥25
ማቴ16፥21፤
ማር13፥30፤
ሉቃ9፥22፤
18፥32፤ 21፥32

15ከእነርሱም አንዱ መፈወሱን ባየ
ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ
ተመለሰ፤ 16በኢየሱስም እግር ላይ በፊቱ
ተደፍቶ አመሰገነው፤ ይህም ሰው ሳምራዊ
ነበረ።
17ኢየሱስም እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ "የነ
ጹት ዐሥር ሰዎች አልነበሩምን? ታዲያ፣
ዘጠኙ የት ደረሱ? 18ከዚህ ከባዕድ ሰው
በስተቀር ተመልሰው እግዚአብሔርን የሚያ
መሰግኑ የሉም ማለት ነውን?"። 19ሰው
የውንም፣ "ተነሥተህ ሂድ፤ እምነትህ አድኖ
ሃል" አለው። ዮሐ 4፥46-53

## የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት

*17፥26፡27 ተጓ ምብ — ማቴ 24፥37-39*

20ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት
መቼ እንደምትመጣ ኢየሱስን በጠየቁት
ጊዜ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ "የእግዚአብ ሔር
መንግሥት በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም፤
21ሰዎችም፣ 'እዚህ ነው' ወይም 'እዚያ ነው'
ማለት አይችሉም፤ እነሆ፤ የእ ግዚአብሔር
መንግሥት በመካከላችሁ† ናትና።"
22ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አላቸው፤
"ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ለማየት
የምትመኙበት ጊዜ ይመጣል፤ ደግሞም
አታዩ ትም። 23ሰዎች፣ 'እዚያ ነው' ወይም
'እዚህ ነው' ይሏችኋል፤ ተከትላችኋቸውም
አትሂዱ፤ 24ምክንያቱም መብረቅ በርቆ
ሰማዩን ከዳር እስከ ዳር እንደሚያበራ፣
የሰው ልጅም በሚመጣበት ቀን ልክ
እንደዚሁ ይሆናል። 25ነገር ግን ይህ ከመሆኑ
በፊት የሰው ልጅ ብዙ መሠቃየትና በዚህም

*17፥12 የግሪኩ ቃል ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቈዳ በሽታዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል።

†17፥21 ወይም በውስጣችሁ

**17፥3 ቢጸጸት ይቅር በለው፤** ኢየሱስ ስለ ይቅርታ የተናገረውን ነገር ለመረዳት ቀጥሎ ያለውን ይመልከቱ፤ (1) የኢየሱስ ዐላማ በበደሉን ላይ የጥላቻና የበቀል መንፈስ ከሚኖረን ይልቅ እነርሱን ይቅር ለማለትና ለመርዳት የሚፈልግ ልብ እንዲኖረን ነው፤ (2) የበደለው ሰው ስሕተቱን አምኖ ከልቡ ንስሓ እስካልገባ ድረስ እውነተኛ ይቅርታና ዕርቅ ሊኖር አይችልም። እዚህ ላይ ኢየሱስ የተናገረው ሁልጊዜ ተደጋግሞ የሚፈጸም ተመሳሳይ በደልን በሚመለከት አይደለም፤ (3) በደለኛው ከልቡ ንስሓ ከገባ፣ እኛም ሁልጊዜ ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኞች መሆን አለብን። ኢየሱስ ይቅርታን አስመልክቶ «በቀን ሰባት ጊዜ» በማለት የተናገረው፣ በማዘውተር የሚደረግ ኀጢአትን ይቅር ስለማለት አይደለም፤ ወይም አንድ ሰው ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ በአማኙ ላይ አብዝቶ የከፋ በደል ሲፈጽም ዝም ብሎ ይቀበለው ማለቱም አይደለም። ነገር ግን ይህን የተናገረው ሁልጊዜ በደለኛውን ለመርዳትና ይቅር ለማለት የተዘጋጀ ልብ እንዲኖረን ለማስተማር ነው።

**17፥6 እምነት፤** ማቴ 17፥20 እና ማብራሪያውን፤ 21፥21 እና ማብራሪያውን፤ ማር 11፥24 እና ማብራሪያውን ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ «*እምነትና ጸጋ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**17፥16 አመሰገነው፤** ከእግዚአብሔር ፍቅርን፣ ጸጋን፣ ድነትንና መንፈሳዊ በረከቱን ሁሉ የተቀበልን እኛ እርሱን ማመስገን እንደሚገባን መዘንጋት የለብንም። እርሱ ያደረገልን ነገር፣ የሚያመሰግን ልብ ይዘን በፊቱ እንድንቀርብ ሊያደርገን ይገባል። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን» (1ዮሐ 4፥19)።

**17፥21 የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና፤** ኢየሱስ እንደተናገረው፣ አሁን የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕርይ መንፈሳዊ እንጂ በጉልህ የምትታይ ወይም ምድራዊ መንግሥት አይደለችም። «የእግዚአብሔር መንግሥት በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም» (ቍ 20)፤ ማለትም እንደ ምድራዊ የፖለቲካ ሥልጣን የምትመጣ አይደለችም። ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ በሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብና በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የምትገለጥ ናት (ሮሜ 14፥17)። ነገሥታትንና ሕዝቦችን በማሸነፍ ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የኀጢአትን፣ የደዌንና የሰይጣንን ኀይል ድል በማድረግ የምናሳየው ነው (በገጽ 1443 ላይ፣ «*የእግዚአብሔር መንግሥት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ምድር ተመልሶ ሲመጣ፣ መንግሥቱ ነገሥታትንና ሕዝቦችን ሁሉ ድል ነሥቶ (ራእ 11፥15-18፤ 19፥11-21) በሙሉ ሥልጣኑና ክብሩ ይታያል (ቍ 24 ይመ፤ ከማቴ 24፥30 ጋር ያነጻጽሩ)።

ትውልድ መናቅ ይኖርበታል።
[26]"በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው ሁሉ፣ በሰው
ልጅ ዘመንም እንደዚሁ ይሆናል። [27]ኖኅ
ወደ መርከቡ እስከ ገባበት ቀን ድረስ ሰዎች
ይበሉና ይጠጡ፣ ያገቡና ይጋቡ ነበር፤ የጥ
ፋትም ውሃ መጥቶ ሁሉንም አጠፋቸው።
[28]"በሎጥ ዘመንም እንዲሁ ነበር፤ ሰዎች
ይበሉና ይጠጡ፣ ይገዙና ይሸጡ፣ ተክል
ይተክሉና ቤት ይሠሩ ነበር፤ [29]ሎጥ ከሰ
ዶም በወጣበት ዕለት ግን እሳትና ዲን
ከሰማይ ዘንቦ በሙሉ አጠፋቸው።
[30]"የሰው ልጅ በሚገለጥበትም ቀን
እንደዚሁ ይሆናል። [31]በዚያን ቀን በቤቱ
ጣራ ላይ ያለ ማንም ሰው በቤቱ ውስጥ
ያለውን ንብረት ለመውሰድ አይውረድ፤
እንዲሁም በዕርሻ ቦታ ያለ ሰው ወደ ኋላው
አይመለስ። [32]የሎጥን ሚስት አስታውሱ።
[33]ሕይ ወቱን ለማሰንበት የሚፈልግ ሁሉ
ያጣታል፤ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን
ያቈያታል። [34]እላችኋለሁ፤ በዚያች ሌሊት
ሁለት ሰዎች በአንድ ዐልጋ ይተኛሉ፤ አንዱ
ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል። [35]ሁለት ሴቶች
አብረው ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰዳለች፤
ሌላዋ ትቀራለች። [36]ሁለት ሰዎች በዕርሻ
ቦታ አብረው ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል፤
ሌላው ይቀራል።"[1]
[37]እነርሱም መልሰው፣ "ጌታ ሆይ፤
የሚወሰዱት ወዴት ነው?" አሉት።
እርሱም፣ "ጥንብ ባለበት አሞሮች
ይሰበሰባሉ" አላቸው።

ዮሐ 14፥

17፥26 ዘፍ6፥5-8፤ 7፥6-24
17፥28 ዘፍ19፥1-28
17፥30 ማቴ10፥23፤ 16፥27፤ 24፥3፡27፡37፡39፤ 25፥31፤ 1ቆሮ1፥7፤ 1ተሰ 2፥19፤ 2ተሰ1፥7፤ 2፥8፤ 2ጴጥ3፥4፤ ራእ1፥7
17፥31 ማቴ24፥17፡18
17፥32 ዘፍ19፥26
17፥33 ዮሐ12፥25
17፥35 ማቴ24፥41
17፥37 ማቴ24፥28
18፥1 ኢሳ40፥31፤ ሉቃ11፥5-8፤ ሐሥ1፥14፤ ሮሜ1፥10፤ 12፥12፤ ኤፌ6፥18፤ ቆላ4፥2፤ 1ተሰ5፥17
18፥3 ኢሳ1፥17
18፥5 ሉቃ11፥8
18፥6 ሉቃ7፥13
18፥7 ዘዐ22፥23፤ መዝ88፥1፤ ራእ6፥10
18፥8 ማቴ8፥20፤ 16፥27

## ተግታ የለመነችው መበለት ምሳሌነት

18 ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ ሁል ጊዜ
መጸለይ እንደሚገባቸው ለማሳየት
ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ [2]እንዲህም
አላቸው፤ "በአንዲት ከተማ የሚኖር
እግዚአብሔርን የማይፈራና ሰውን የማያከብር
አንድ ዳኛ ነበረ። [3]በዚያችው ከተማ
የምትኖር አንዲት መበለት ነበረች፤ እርሷ፣
'ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ ፍረድልኝ'
እያለች ወደ እርሱ ትመላለስ ነበር።
[4]"ዳኛውም ለተወሰነ ጊዜ አልተቀበላትም
ነበር፤ በኋላ ግን በልቡ እንዲህ አለ፤ 'ምንም
እግዚአብሔርን ባልፈራ፣ ሰውንም ባላከብር፣
[5]ይህች መበለት ስለምትጨቀጭቀኝ
እፈርድላታለሁ፤ አለበለዚያ ዘወትር
እየተመላለሰች ታሰለቸኛለች።"
[6]ጌታም እንዲህ አለ፤ "ዐመፀኛው
ዳኛ ያለ ውን ስሙ። [7]እግዚአብሔር ቀንና
ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ
አይፈርድላቸውምን? ከመጠን በላይስ
ችላ ይላቸዋልን? [8]እላችኋለሁ፤ ፈጥኖ
ይፈርድላቸዋል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ

[1]17፥35 አንዳንድ ቅጆች ቍ 36 የላቸውም

17፥26 **በኖኅ ዘመን፤** ማቴ 24፥37 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

17፥31 **በዚያን ቀን፤** ማር 13፥14 እንዲሁም ጥፋት በሚያመጣው አስጸያፊ ርኩሰት ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ ይመልከቱ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

17፥32 **የሎጥን ሚስት አስታውሱ፤** የሎጥ ሚስት የፈጸመችው ከባድ ስሕተት፣ ከሰማያዊው ይልቅ ምድራዊ የሆነውን ንብረት መውደድዋ ነው (ከዕብ 11፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። ልብዋ አሁንም ሰዶም ላይ ስለነበር፣ ወደኋላዋ ተመለሰች (ዘፍ 19፥17፡26፤ 19፥26 እና ማብ ይመ)። እያንዳንዱ አማኝ፣ "ልቤ ስለ ኢየሱስና ስለ መመለሱ ተስፋ ከማሰብ ይልቅ በዓለም ካለው ነገር ጋር የተቈራኘ ነውን?" ብሎ መጠየቅ አለበት።

17፥37 **ጥንብ ባለበት አሞሮች፤** በመንፈሳቸው ሙታን በሆኑት ላይ ፍርድ መምጣቱ አይቀሬ እንደ ሆነ ይህ ጥቅስ ያመለክታል (ከማቴ 24፥28፤ ከራእ 19፥17-18 ጋር ያነጻጽሩ)። ጥንብ ባለበት የአሞሮች መሰብሰብ እርግጠኛ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በኀጢአተኞች ላይ እንደሚፈርድ ጥርጥር የለውም።

18፥1 **ሁል ጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው፤** የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታቸው እንዲፈጸም፣ ተከታዮቹ ሳያቋርጡ ይጸልዩ ዘንድ ኢየሱስ ግድ ይለዋል (በገጽ 528 ላይ፣ "*መልስ የሚያስገኝ ጸሎት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህችን ትጉህ መበለት በሚመለከት የተሰጠው ምሳሌ ብዙ ነገር ያስተምረናል፤ (1) ኢየሱስ ተመልሶ እስከሚመጣ ድረስ ስለ ሁሉ ነገር በመጸለይ መትጋት እንዳለብን (ቍ 7-8፤ ሮሜ 12፥12፤ ኤፌ 6፥18፤ ቈላ 4፥2፤ 1ተሰ 5፥17)፣ (2) በዚህ ሕይወት እስካለን ጠላት እንዳለብን (ቍ 3)፣ እርሱም ሰይጣን እንደ ሆነ (1ጴጥ 5፥8)፤ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ ከክፉው እንደምንጠበቅ (ማቴ 6፥13)፣ (3) ኀጢአትን መቃወምና ስለ ፍትሕ መስፈን መጸለይ እንዳለብን (ቍ 7)፣ (4) ያለማቋረጥ መጸለይ የእምነትን ጽናት እንደሚያመለክት (ቍ 8)፣ (5) ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ባሉት የመጨረሻዎቹ ቀናት፣ በታማኝ ክርስቲያኖች ጸሎት ላይ የሚነሳው የዲያብሎስ ተቃውሞ እየጨመረ እንደሚሄድ (1ጢሞ 4፥1)። ሰይጣን ከሚፈጥረው ጫናና ዓለምን ከመውደድ የተነሣ ብዙ ክርስቲያኖች በጸሎት ከመትጋት ወደኋላ ይላሉ (8፥14፤ ማቴ 13፥22፤ ማር 4፥19)።

18፥7 **ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ፤** በእምነትና በቅድስና ጸንተው የቆሙ እውነተኛ የእግዚአብሔር ምርጦች፣ የሰይጣንን ኀይልና የዓለምን ክፉ ሥርዐት ለማስወገድ ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መጮኻቸውን አያቋርጡም። እግዚአብሔር ፈጥኖ ይፈርድላቸው ዘንድ (ቍ 8)፣ ለዚህ ዓለም ብቸኛ እውነተኛ ተስፋ የክርስቶስ መመለስ እንደ ሆነ በመገንዘብ (ከዮሐ 14፥2፤ ከ1ተሰ 5፥2-3፤ ከ2ተሰ 2፥8፤ ከራእ 19፥11-21 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ክርስቶስ በጽድቅ ለመግዛት ይመጣ ዘንድ በጸሎት ይተጋሉ።

18፥8 **ይፈርድላቸዋል፤** ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ የሚጮኹትን የምርጦቹን ጸሎት ሰምቶ በሚመለስበት ጊዜ (ቍ 7) ከጠላትና ክፉ ከሆነው ዓለም እጅ የሚደርስባቸው ሐዘንና መከራ እንዲያበቃ ያደርጋል፤ እርሱ ወዳለበትም ይወስዳቸዋል (ዮሐ 14፥2-3 እና ማብ ይመ)። በሚመጣበትም ጊዜ በቤቱ ውስጥ በታማኝነት እርሱን የምንጠብቅ፣ "ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን" (1ተሰ 4፥17)። እግዚአብሔር በዐመፀኞች ላይ ፍርዱንና ቍጣውን ይገልጻል (1ተሰ 5፥2-3፡9)።

18፥8 **በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?**

በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን
ያገኝ ይሆንን?"

### የፈሪሳዊውና የቀረጥ ሰብሳቢው ምሳሌነት

9ራሳቸውን እንደ ጻድቃን በመቍጠር
ለሚመኩና ሌሎቹን በንቀት ዐይን
ለሚመለከቱ ሰዎች እንዲህ ሲል ይህን
ምሳሌ ነገራቸው፤ 10"ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ
ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ፤ አንዱ ፈሪሳዊ፣
ሌላው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበሩ። 11ፈሪሳዊውም
ቆሞ ስለ[ǂ] ራሱ እንዲህ ይጸልይ ነበር፤
'እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ እንደ ሌላው ሰው
ሁሉ ቀማኛ፣ ዐመፀኛ፣ አመንዝራ፣
ይልቁንም እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ
ባለመሆኔ አመሰግንሃለሁ፤ 12በሳምንት
ሁለት ጊዜ እጾማለሁ፤ ከማገኘውም ሁሉ
ዐሥራት አወጣለሁ።'
13"ቀረጥ ሰብሳቢው ግን በርቀት
ቆሞ፣ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ማየት እንኳ
አልፈለገም፤ ነገር ግን ደረቱን እየደቃ፣
'እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ኀጢአተኛውን
ማረኝ' ይል ነበር።
14"እላችኋለሁ፤ ከፈሪሳዊው ይልቅ
ይኸኛው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጻድቅ
ተቈጥሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ
ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል።"

### ኢየሱስ ከሕፃናት ጋር

*18፥15-17 ተጓ ምብ — ማቴ 19፥13-15፤ ማር 10፥13-16*

15ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች
ሕፃናትን ወደ እርሱ ያመጡ ነበር፤ ደቀ
መዛሙርቱም ይህን ባዩ ጊዜ ገሠጿቸው።
16ኢየሱስ ግን ሕፃናቱን ወደ ራሱ ጠርቶ
እንዲህ አለ፤ "ሕፃናት ወደ እኔ እንዲመጡ

18፥9 ኢሳ65፥5፤ ሉቃ16፥15
18፥10 ሐሥ3፥1
18፥11 ማቴ6፥5፤ ማር11፥25
18፥12 ኢሳ58፥3፤ ሚል3፥8፤ ማቴ9፥14፤ ሉቃ11፥42
18፥13 ኢሳ66፥2፤ ኤፕ31፥19፤ ሉቃ5፥32፤ 23፥48፤ 1ጢሞ1፥15
18፥14 ማቴ23፥12
18፥17 ማቴ11፥25፤ 18፥3
18፥18 ሉቃ10፥25
18፥20 ዘፀ20፥12-16፤ ዘዳ5፥16-20፤ ሮሜ13፥9
18፥22 ማቴ19፥26፤ ሐሥ2፥45
18፥24 ምሳ11፥28
18፥27 ማቴ19፥26

ፍቀዱላቸው፤ አትከልክሏቸው፤
የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት
ናትና። 17እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን
መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበል ሁሉ
ከቶ አይገባባትም።"

### ሀብታሙ የአይሁድ አለቃ

*18፥18-30 ተጓ ምብ — ማቴ 19፥16-29፤ ማር 10፥17-30*

18ከአይሁድ አለቆች አንዱ፣ "ቸር
መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት
ለመውረስ ምን ላድርግ?" ሲል ጠየቀው።
19ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ "ስለ
ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር
በቀር ቸር ማንም የለም፤ 20'አታመንዝር፣
አትግደል፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣
አባትህንና እናትህን አክብር' የሚለውን
ትእዛዝ ታውቃለህ።"
21ሰውየውም፣ "እነዚህንማ ከልጅነቴ
ጀምሬ ጠብቄአለሁ" አለው።
22ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ፣
"እንግዲያውስ አንድ ነገር ይቀርሃል፤
ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድኾች ስጥ፤ በሰማይ
መዝገብ ይኖርሃል፤ ከዚያም መጥተህ
ተከተለኝ" አለው።
23ሰውየው ግን ይህን ሲሰማ፣ ብዙ ሀብት
ስለ ነበረው በጣም ዐዘነ። 24ኢየሱስም
ሰውየውን ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ "ብዙ
ሀብት ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
መግባት እንዴት ጭንቅ ነው? 25ሀብታም
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።"
26ይህን የሰሙ ሰዎችም፣ "ታዲያ፣ ማን
ሊድን ይችላል?" አሉ።
27ኢየሱስም፣ "በሰው ዘንድ የማይቻል
በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል" አለ።

[ǂ]18፥11 ወይም ለራሱ

---

የኢየሱስ ጥያቄ ምናልባት የመምጫው ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች ከእውነተኛው እምነት ወደ ኋላ እስከሚሉ ድረስ ክፋት እያየለ እንደሚሄድ ያመለክታል (ማቴ 24፥11-13:24፤ 1ጢሞ 4፥1 ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ፣ በገጽ 1913 ላይ፣ *"የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን"* በሚል ርእስና፣ በገጽ 1962 ላይ ደግሞ፣ *"ክሕደት"* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ):: ወደ ታሪክ መጨረሻ እየተቃረብን ስንመጣ፣ እያንዳንዱ አማኝ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ አለበት፤ "እምነቴ ጽኑ ነውን፣ ፍትሕ እንዲሰፍንና የእርሱ ጽድቅ ሙሉ በሙሉ ለዘላለም እንዲያሸንፍ፣ በመጸለይና ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ እየተጋሁ ነኝን? ወይስ ስለ ክርስቶስ መመለስና ስለ ዘላለማዊ መንግሥቱ ናፍቆትና ጥማት እስከማይኖረኝ ድረስ ሐሳቤ በዚህ ዓለም የኑሮ ጉዳይ ተይዞአል?" (ራእ 19—22)::

**18፥9-14 በዚህ ክፍል የፈሪሳዊውና የቀረጥ ሰብሳቢው ምሳሌነት ተጠቅሶአል፤** (1) ፈሪሳዊው ራሱን ጻድቅ አድርጎ የሚቈጥር ሰው ነበር:: ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው የሚቈጥሩ ሰዎች በራሳቸው ጥረት ከሚያደርጉት መልካም ሥራ የተነሣ ጻድቅ የሆኑ ይመስላቸዋል፤ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ እንዳላቸው፣ በራሳቸው ምንም ዋጋ እንደሌላቸውና ከዚህም የተነሣ ሁልጊዜ የእግዚአብሔር እርዳታ፣ ምሕረትና ጸጋ እንደሚያስፈልጋቸው አያስተውሉም:: እነዚህ ሰዎች ለሃይማኖታቸው የተለየ ቅናትና መልካም ምግባር ስላላቸው፣ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያስፈልጋቸው አይመስላቸውም፤ (2) በሌላ አንጻር ቀረጥ ሰብሳቢው በኀጢአቱና በጥፋቱ እጅግ አዝኖ እውነተኛ ንስሓ በመግባት፣ ከእግዚአብሔር ይቅርታንና ምሕረትን ይለምናል:: ይህም እውነተኛ የእግዚአብሔርን ልጅ ምሳሌነት የሚያሳይ ነው::

**18፥22 ያለህን ሁሉ ሽጠህ፤** ማቴ 19፥21 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**18፥25 ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት፤** ኢየሱስ ስለ ሀብታም የተናገረውን ነገር ደቀ መዛሙርቱ በአይሁድ ዘንድ ካለው አመለካከት ጋር ሲያነጻጽሩ፣ በጣም አስደንቆአቸዋል (ቍ 24-26):: ስለዚህ ጉዳይ ይበልጥ ለመረዳት (በገጽ 1577 ላይ፣ *"ብልጽግናና ድህነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

28ጴጥሮስም፣ "እነሆ፤ እኛ ያለንን ሁሉ
ትተን ተከትለንሃል" አለው።
29ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ብሎ
ቤቱን ወይም ሚስቱን ወይም ወንድሞቹን
ወይም ወላጆቹን ወይም ልጆቹን የተወ፣
30በዚህ ዘመን ብዙ ዕጥፍ፣ በሚመጣውም
ዘመን የዘላለምን ሕይወት የማይቀበል
ማንም የለም።"

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ ዳግመኛ ተናገረ

*18፥31-33 ተጓ ምብ — ማቴ 20፥17-19፤ ማር 10፥32-34*

31ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ደቀ
መዛሙርት ለብቻ ወስዶ እንዲህ አላቸው፤
"እንግዲህ ወደ ኢየሩሳሌም ልንወጣ ነው፤
ነቢያት ስለ ሰው ልጅ የጻፉትም
ሁሉ ይፈጸማል። 32ለአሕዛብ አሳልፈው
ይሰጡታል፤ እነርሱም ያፌዙበታል፤
ያንገላቱታል፤ ይተ ፉበታል፤ ይገርፉታል፤
ከዚያም ይገድሉታል።33እርሱም በሦስተኛው
ቀን ከሙታን ይነሣል።" 34ደቀ መዛሙርቱ
ግን ከዚህ ሁሉ የተረዱት አንድም ነገር
አልነበረም፤ አባባሉም ተሰውሮባቸው ነበር፤
ስለምን እንደ ተናገረም አላወቁም።

## የዐይነ ስውሩ መፈወስ

*18፥35-43 ተጓ ምብ — ማቴ 20፥29-34፤ ማር 10፥46-52*

35ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ በቀረበ ጊዜ፣
አንድ ዐይነ ስውር መንገድ ዳር ተቀምጦ
ይለምን ነበር። 36ዐይነ ስውሩም ሕዝቡ በዚያ
ሲያ ልፍ ሰምቶ ስለ ሁኔታው ጠየቃቸው።
37እነርሱም፣ "የናዝሬቱ ኢየሱስ በዚህ
እያለፈ ነው" ብለው ነገሩት።
38እርሱም፣ "የዳዊት ልጅ፣ ኢየሱስ
ሆይ፤ ማረኝ!" እያለ ጮኸ።
39ከፊት የሚሄዱ ሰዎችም ዝም እንዲል
ገሠጹት፤ እርሱ ግን፣ "የዳዊት ልጅ ሆይ፤
ማረኝ!" እያለ አብዝቶ ጮኸ።
40ኢየሱስም ቆም ብሎ ሰውየውን ወደ
እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ፤ ወደ እርሱም
በቀረበ ጊዜ፣ 41"ምን እንዳደርግልህ
ትፈልጋ ለህ?" ብሎ ጠየቀው።
ዐይነ ስውሩም፣ "ጌታ ሆይ፤ ማየት

18፥28 ማቴ4፥19
18፥30 ማቴ12፥32፤ 25፥46
18፥31 መዝ22፤ ኢሳ53፤ ማቴ8፥20፤ ሉቃ9፥51
18፥32 ማቴ16፥21፤ ሉቃ23፥1፤ ሐሥ2፥23
18፥33 ማቴ16፥21
18፥34 ማር9፥32
18፥35 ሉቃ19፥1
18፥37 ሉቃ19፥4
18፥38 ቍ39፤ ማቴ9፥27፤ 17፥15፤ ሉቃ18፥13
18፥39 ቍ38
18፥42 ማቴ9፥22
18፥43 ማቴ9፥8፤ ሉቃ13፥17
19፥1 ሉቃ18፥35
19፥4 1ነገ10፥27፤ 1ዜና27፥28፤ ኢሳ9፥10፤ ሉቃ18፥37
19፥7 ማቴ9፥11
19፥8 ዘፀ22፥1፤ ዘሌ 6፥4፡5፤ ዘኍ5፥7፤ 2ሳሙ12፥6፤ ሕዝ33፥14፡15፤ ሉቃ3፥12፡13
19፥9 ሉቃ3፥8
19፥10 ሕዝ34፥12፡16፤ ዮሐ3፥17
19፥11 ማቴ3፥2፤ ሉቃ17፥20፤ ሐሥ1፥6
19፥13 ማር13፥34

እፈልጋለሁ" አለው።
42ኢየሱስም፣ "እይ፤ እምነትህ አድኖሃል"
አለው። 43ሰውየውም ወዲያውኑ ማየት ቻለ፤
እግዚአብሔርንም እያከበረ ኢየሱስን ተከተለው።
ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ እግዚአብሔርን
አመሰገኑ።

## ቀረጥ ሰብሳቢው ዘኬዎስ

19ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ገብቶ በዚያ
አልፎ ይሄድ ነበር። 2ስሙ ዘኬ ዎስ
የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤ ዋና ቀረጥ
ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ። 3እርሱም ኢየሱስ
የተባለው ዮትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ
ነበር፤ ቁመቱ አጭር ነበረና ከሕዝቡ ብዛት
የተነሣ ሊያየው አልቻለም። 4ኢየሱስ በዚያ
መንገድ ያልፍ ስለ ነበርም፣ ሊያ የው ወደ
ፊት ሮጦ አንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ።
5ኢየሱስም እዚያ ቦታ ሲደርስ፣ ቀና
ብሎ፣ "ዘኬዎስ ሆይ፤ ዛሬ አንተ ቤት
መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ" አለው።
6እርሱም ፈጥኖ ወርዶ በደስታ ተቀበለው።
7በዚያ የነበሩ ሰዎችም ይህንን አይተው፣
"ከኀጢአተኛ ቤት ገብቶ ሊስተናገድ ነው።"
በማለት ሁሉም ማጕረምረም ጀመሩ።
8ዘኬዎስ ግን ቆመና ጌታን፣ "ጌታ ሆይ፤
እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ ግማሹን ለድኾች
እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ቀምቼ ከሆነ፤
አራት ዕጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ" አለው።
9ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "ይህ ሰው
ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለ ሆነ፣ ዛሬ መዳን
ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤
10ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው
የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው።"

## የዐሥሩ ምናን ምሳሌ

*19፥12-27 ማመ — ማቴ 25፥14-30*

11ሕዝቡ ይህን እየሰሙ ሳሉ፣ በምሳሌ
መናገሩን ቀጠለ፤ ምክንያቱም ወደ
ኢየሩሳሌም በመቃረቡና ሰዎቹም
የእግዚአብሔር መንግሥት የሚገለጥ ስለ
መሰላቸው ነው። 12ስለዚህም እንዲህ አለ፤
"አንድ መስፍን የንጉሥነትን ማዕረግ
ተቀብሎ ለመመለስ ወደ ሩቅ አገር ሄደ።
13ከአገልጋዮቹም መካከል ዐሥሩን ጠርቶ
ዐሥር ምናን ሰጣቸውና "ተመልሼ እስክመጣ

**18፥30 ብዙ ዕጥፍ ... የማይቀበል፤** ማር 10፥30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥1-10 በዚህ ክፍል የዘኬዎስ መለወጥ ተገልጾአል፤** ከስቅለቱ በፊት ባሉት ጥቂት ቀናት እንኳ ኢየሱስ የጠፉትን ለማዳን ይፈልግ ነበር (ቍ 10)፤ ይህም ወደዚህ ምድር የመጣበት ዋና ዐላማ ነበር (ከ15፥3-7፣ ከሕዝ 34፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። ቀረጥ ሰብሳቢው ዘኬ ዎስ ይተዳደር የነበረው ሕዝቡን ከተገቢው በላይ ቀረጥ በማስከፈል ትርፉን ለራሱ በማድረግ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ቀረጥ ሰብሳቢዎች በሕዝቡ ዘንድ የተናቁና የተጠሉ ነበሩ። ኢየሱስ ስለ ዘኬዎስ ግድ ብሎት ያደረገው ነገር፣ የወንጌልን ምሥራች ለተናቀውም ኅብረተ ሰብ እንድናደርስ ያስጠነቅቀናል፤ ምክንያቱም ሰው ሁሉ የጠፋ በመሆኑ ድነት ያስፈልገዋል።

**19፥8 ለድኾች እሰጣለሁ፤** ከልብ የሆነ የኀጢአት ኑዛዜና በክርስቶስ ያለን ለድነት የሚያበቃ እውነተኛ እምነት፣ ከውጭም የሚታይ የሕይወት ለውጥ እንዲኖረን ለመወሰን ያስችለናል። ማንም ሰው ኀጢአትን በማድረግ፣ በማታለልና ለሌሎች ክፉ በመሆን እየኖረ፣ ክርስቶስን ሊያውቅና እርሱ የሚሰጠውን ድነት ሊቀበል አይችልም።

**19፥13 ተመልሼ እስክመጣ ድረስ፤** የዐሥሩ ምናን ምሳሌ፣ እያንዳንዱ ቤዛነትን ያገኘ አማኝ እግዚአብሔር የሰጠውን ነገር በታማኝነት የመጠቀምና አገልግሎት ላይ የማዋል ኀላፊነት እንዳለበት የሚገልጽ ነው። እያንዳንዳችን ቸርነት በማድረግ፣ በመጸለይ፣

# ብልጽግናና ድህነት

*ሉቃ 18፥24-25 "ኢየሱስም ሰውየውን ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ 'ብዙ ሀብት ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው? ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።"*

---

ጌታ ከተናገራቸው እጅግ አስደንጋጭ ንግግሮች አንዱ ለሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት በጣም ከባድ እንደ ሆነ የተናገረው ነው። ነገር ግን ይህ ሐዋርያት በብዙ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ለተናገሩት ነገር አስተያየት የሚሰጥ ሲሆን፣ ብልጽግናና ድኽነትን በተመለከተ ጌታ ከተናገራቸው ብዙ ንግግሮች ውስጥ አንዱ ነው።

**ብልጽግና፤** (1) ሀብታም መሆን ከእግዚአብሔር የተለየ ሞገስ የማግኘት ምልክት እንደ ሆነ፣ ድኻ መሆን ደግሞ የእምነት ቢስነትና እግዚአብሔርን ደስ ያለማሰኘት ምልክት እንደ ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን በነበሩት አይሁድ ዘንድ በስፋት የሚሰጥ አስተያየት ነበር (ምሳ 10፥15 እና ማብ ይመ)። ለምሳሌ ፈሪሳዊያን እንዲህ ዐይነት አስተሳሰብ ነበራቸው፣ ኢየሱስም ድኻ በመሆኑ አፌዙበት (ሉቃ 16፥14)። ይህ የተሳሳተ ሐሳብ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ቢነገርም ክርስቶስ ግን ሙሉ በሙሉ አልተቀበለውም (ሉቃ 6፥20፤ 16፥13፤ 18፥24-25 ይመ)።

(2) መጽሐፍ ቅዱስ ስግብግብነትንና ገንዘብን መውደድ ጣዖትን እንደ ማምለክና ከአጋንንት ጋር እንደ መተባበር ይቈጥረዋል (ከ1ቆሮ 10፥19-20 ከቈላ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (በገጽ 428 ላይ፣ "የጣዖት አምልኮ ባሕርይ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ሀብት ከማግኘት በስተጀርባ የአጋንንት ኀይል ስለሚሠራ፣ ሀብታም ለመሆን መፈለግና ገንዘብ መውደድ የዚያ ባሪያ እንድንሆን ያደርገናል (ከማቴ 6፥24 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) በኢየሱስ አመለካከት ሀብት፣ ለድነትም ሆነ ለደቀመዝሙርነት ዕንቅፋት ነው (ማቴ 19፥24፤ 13፥22)። ሀብት የተሳሳተ የደኅንነት ስሜት ይሰጣል (ሉቃ 12፥15)፤ ያታልላል (ማቴ 13፥22)፤ የሰውን ልብ ሙሉ በሙሉ መቈጣጠር ይችላል (ማቴ 6፥21)። ሀብታሞች በውስጣቸው እግዚአብሔርን የመሻት ስሜት የሌላቸው መስለው ይኖራሉ፤ ሀብትን በመፈለግ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ይታነቃል (ሉቃ 8፥14)፤ በፈተናና በክፉ ምኞት ውስጥ ይወድቃሉ (1ጢሞ 6፥9)፤ ውጤቱም የሚያድነውን እምነት መተው ይሆናል (1ጢሞ 6፥10)። ብዙውን ጊዜ ሀብታሞች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ድኾችን ይበድላሉ (ያዕ 2፥5-6)። ስለዚህ ማንም ክርስቲያን ባለጠጋ ለመሆን መፈለግ የለበትም (1ጢሞ 6፥9-11)።

(4) ምድራዊ ሀብትን በስግብግብነት መሰብሰብ ሕይወትን ከዘላለማዊ እይታ አንጻር መረዳት አለመቻልን ያመለክታል ቈላ 3፥1)። ራስ ወዳድና ስግብግብ ሰዎች ዐላማቸውና ተግባራቸው የሚያተኵረው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ላይ ሳይሆን፣ የራሳቸውን ፈቃድ በማድረግና ሀብትን በመሰብሰብ ላይ ነው። ለምሳሌ የሎጥ ሚስት እንደዚያ ዐይነት አሳዛኝ ነገር ሊደርስባት የቻለው ከሰማያዊ ይልቅ ምድራዊውን ከተማ አብልጣ በመውደድዋ ነው (ዘፍ 19፥16፡26፤ ሉቃ 17፥28-33፤ ዕብ 11፥8-10)። በሌላ አነጋገር ሀብታም ለመሆን መጓጓት፣ ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር መለየትን ያስከትላል (1ጢሞ 6፥10)።

(5) ለክርስቲያን እውነተኛው ሀብት ራስን በመካድና ክርስቶስን በመከተል የሚገለጽ እምነትና ፍቅር ዋና ነገር አድርጎ የያዘ ነው (1ቆሮ 13፥4-7፤ ፊል 2፥3-5)። እውነተኛ ሀብታሞች እግዚአብሔር አባታቸው ስለሆነና ፈጽሞ ስለማይጥላቸው (2ቆሮ 9፥8፤ ፊል 4፥19፤ ዕብ 13፥5-6)፣ በእርሱ በመታመን በዓለም ላለው ነገር ለመገዛት ልባቸውን ያልሰጡና ነጻነት ያላቸው ናቸው።

(6) ያለንን ሀብት ከመጠቀምና ለዚያም ተገቢ የሆነውን አመለካከት ከመያዝ አንጻር ጻድቃን ታማኞች ይሆኑ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል (ሉቃ 16፥11)። አማኞች ያላቸውን ሀብትና ንብረት ሙጭጭ አድርገው መያዝ የለባቸውም፤ ነገር ግን ያላቸውን ሀብትና ገንዘብ ለመንግሥቱ አገልግሎት፣ በምድር ላይ የክርስቶስን ሥራ ለማስፋፋት፣ ለሌሎች መዳንና ችግር ይውል ዘንድ በክርስቶስ እጅ መተው አለባቸው (በገጽ 1406 ላይ፣ "ዐሥራትና መባ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ስለዚህ ምድራዊ ሀብትና ንብረት ያላቸው አማኞች ራሳቸውን እንደ ሀብታም ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ሀብት ባለ አደራዎች እንደ ሆኑ መቍጠር አለባቸው (ሉቃ 12፥31-48)፤ እንደዚሁም ቸሮች፣ ለተቸገሩት የሚያካፍሉና መልካም ነገር በማድረግ ሀብታሞች ሊሆኑ ይገባል (ኤፌ 4፥28፤ 1ጢሞ 6፥17-19)።

(7) እያንዳንዱ ክርስቲያን ልቡንና ምኞቱን በመርመር፣ "ስግብግብና ራስ ወዳድ ነኝን? ለመበልጸግ ከፍተኛ ናፍቆት አለኝን? ሀብታም በመሆን ዝናን፣ ክብርንና ሥልጣንን ለማግኘት ከፍተኛ ምኞት አለኝን?" በማለት ራሱን መጠየቅ አለበት።


ድኽነት፤ ኢየሱስ ከሚሠራቸው ሥራዎች አንዱ የሆነውና ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ተልእኮ እንደ ሆነ የሚረዳው ለድኾች ወንጌልን መስበክ ነበር (ሉቃ 4፥18 ይመ፤ ከኢሳ 61፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። በሌላ አባባል የክርስቶስ ወንጌል "የድኾች ወንጌል ነው" ብሎ መናገር ይቻላል (ማቴ 5፥3፣ 11፥5፣ ሉቃ 7፥22፤ ያዕ 2፥5)።

(1) ድኾች ዝቅ ያሉና በዓለም ውስጥ ብዙ የተጐዱ ስለሆኑ፣ ወደ እግዚአብሔር በቀላሉ ለመመለስ የሚፈልጉና የእርሱን እርዳታ የሚሹ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እንደዚሁም ለእግዚብሔር ታማኝ በመሆን፣ እርሱ ሕዝቡን በዚህ ምድር ካለው ኀጢአት፣ ሥቃይ፣ ራብና ጥላቻ ነጻ የሚያወጣበትን ጊዜ በናፍቆት ሊጠብቁ ይችላሉ። በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብልጽግናንና ሕይወትን ምድራዊ ከሆነው ነገር ለማግኘት አይፈልጉም (መዝ 18፥27፣ 22፥26፤ 25፥9፤ 37፥11፣ 72፥2፡12-13፣ 74፥19፣ 147፥6፣ ኢሳ 11፥4፣ 29፥19፤ ሉቃ 6፥20፤ 16፥25፣ ዮሐ 14፥3-እና ማብ ይመ)።

(2) በእርግጥ ከመከራ፣ ከጭቆና፣ ፍትሕ ከማጣትና ከድኽነት ነጻ የሚወጡት በእግዚአብሔር ፊት ድኾች የሆኑት ናቸው (ሉቃ 6፥20-23፤ 18፥1-8) በከፊልም ቢሆን እነዚህ ሰዎች የሚያገኙት ርዳታ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በምድራዊ ሀብት የተባረኩ ክርስቲያኖች በለጋስነት ከሚያደርጉት ስጦታ መምጣት አለበት (በገጽ 1327 ላይ፣ "ድኾችንና ችግረኞችን መርዳት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) እግዚአብሔር የሕዝቡን ድኽነት ከተመለከተ በኋላ፣ "ሀብታም ነህ" ብሎ ይናገራል (ራእ 2፥9)። በምንም ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመንፈሳዊ ወይም ከግብረገባዊ ነገር አንጻር ዝቅተኛ አይደለም (ራእ 2፥9 እና ማብ ይመ)።

## ኢየሱስ በገሊላ




© 1989 The Zondervan Corporation

ድረስ በዚህ ገንዘብ ነግዱበት" አላቸው።
14"የአገሩ ሰዎች ግን ስለ ጠሉት፣ 'ይህ
ሰው በላያችን እንዲነግሥ አንፈልግም'
ብለው ከኋላው መልእክተኞችን ላኩበት።
15"ይሁን እንጂ ይህ መስፍን ንጉሥ ሆኖ
ወደ አገሩ ተመለሰ፤ እነዚያ አገልጋዮቹም
እርሱ በሰጣቸው ገንዘብ ነግደው ምን ያህል
እንዳተረፉ ለማወቅ አስጠራቸው።
16"የመጀመሪያው አገልጋይ ቀርቦ፣
'ጌታ ሆይ፤ የሰጠኸኝ ምናን ዐሥር ምናን
ትርፍ አስገኝቶአል' አለው።
17"ጌታውም፣ 'አንተ ታማኝ አገልጋይ፣
መልካም አድርገሃል፤ በትንሽ ነገር ታማኝ
ሆነህ ስለ ተገኘህ፣ በዐሥር ከተሞች ላይ
ሥልጣን ተሰጥቶሃል' አለው።
18"ሁለተኛውም ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤
የሰጠኸኝ ምናን አምስት ምናን ትርፍ
አስገኝቶአል' አለው።
19"ጌታውም፣ 'አንተ ደግሞ በአምስት
ከተሞች ላይ ሥልጣን ተሰጥቶሃል' አለው።
20"ሌላውም አገልጋይ ቀርቦ እንዲህ
አለው፤ 'ጌታ ሆይ፤ በጨርቅ ጠቅልዬ
ያቈየሁት ምናንህ ይኸው፤ 21አንተ
ያላስቀመጥ ኸውን የምትወስድ፣
ያልዘራኸውን የምታጭድ ጨካኝ ሰው ስለ
ሆንህ ፈራሁህ።'
22"ጌታውም እንዲህ አለው፤ 'አንተ ክፉ
አገልጋይ! በራስህ ቃል እፈርድብሃለሁ፤
ያላስቀመጥሁትን የምወስድ፣ ያልዘራሁትን
የማጭድ፣ ጨካኝ ሰው መሆኔን ካወቅህ፣
23መጥቼ ገንዘቤን ከነትርፉ እንድወስድ፣
ለምን ለሚሠሩበት ሰዎች አልሰጠህም?'
24"ጌታውም እዚያ የቆሙትን፣ 'ምናኑን
ውሰዱበትና ዐሥር ምናን ላለው ስጡት'
አላቸው።
25"እነርሱም፣ 'ጌታ ሆይ፤ እርሱ እኮ
ዐሥር ምናን አለው' አሉት።
26"እርሱም እንዲህ አለ፤ 'እላችኋለሁ፤
ላለው ሁሉ ይጨመርለታል፤ የሌለው ግን
ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። 27ነገር
ግን እኔ በላያቸው እንዳልነግሥ የፈለጉትን
እነዚያን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡና በፊቴ
ዕረዱአቸው።' "

19፥17 ምሳ27፥18፤ ሉቃ6፥10
19፥21 ማቴ25፥24
19፥22 2ሳሙ1፥16፤ ኢዮ15፥6፤ ማቴ25፥26
19፥26 ማቴ25፥29
19፥28 ማር10፥32፤ ሉቃ9፥51
19፥29 ማቴ21፥1፤ 21፥17
19፥32 ሉቃ22፥13
19፥36 2ነገ9፥13
19፥37 ማቴ21፥1
19፥38 መዝ118፥26፤ ሉቃ2፥14፤ 13፥35
19፥39 ማቴ21፥15፡16
19፥40 ዕን2፥11
19፥41 ኢሳ22፥4፤ ሉቃ13፥34፡35

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

*19፥29-38 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥1-9፤ ማር 11፥1-10*
*19፥35-38 ተጓ ምብ — ዮሐ 12፥12-15*

28ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ወደ
ኢየሩሳሌም ሊወጣ ቀድሞአቸው ይሄድ
ነበር። 29ደብረ ዘይት በተባለው ተራራ
ወደሚገኙት፣ ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ
ከተሞች በቀረበ ጊዜ፣ ከደቀ መዛሙርቱ
ሁለቱን እንዲህ ሲል ላካቸው፤ 30"በፊታችሁ
ወዳለችው መንደር ሂዱ፤ ወደዚያም ስትገቡ
ማንም ገና ያልተቀመጠበት ውርንጫ ታስሮ
ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ ወደዚህ አምጡት።
31ማንም፣ 'ለምን ትፈቱታላችሁ?' ብሎ ቢጠ
ይቃችሁ፣ 'ለጌታ ያስፈልገዋል' በሉት።"
32የተላኩትም ሄደው ልክ እንደ ነገራቸው
ሆኖ አገኙት። 33ባለቤቶቹም ውርንጫውን
ሲፈቱ አይተው፣ "ውርንጫውን ለምን ትፈ
ታላችሁ?" አሏቸው።
34እነርሱም፣ "ለጌታ ያስፈልገዋል"
አሉ።
35ከዚያም ውርንጫውን ወደ ኢየሱስ
አመጡት፤ ልብሳቸውንም በላዩ ጣል
አድርገው ኢየሱስን በውርንጫው ላይ
አስቀመጡት። 36ሰዎችም እርሱ በሚሄድበት
መንገድ ላይ ልብሳቸውን ያነጥፉ ነበር።
37በደብረ ዘይት ተራራ ቍልቍል
ወደ ሚወስደው መንገድ በተቃረቡ ጊዜ፣
ቍጥራቸው እጅግ ብዙ የሆነ ደቀ መዛሙርት
ስላዩት ታምራት ሁሉ ደስ እያላቸው
ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ እንዲህ እያሉ
እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ጀመር፤

38"በጌታ ስም የሚመጣው ንጉሥ
የተባረከ ነው!"
"በሰማይ ሰላም፣ በአርያምም ክብር
ይሁን!"

39በሕዝቡ መካከል የነበሩ አንዳንድ
ፈሪሳውያንም ኢየሱስን፣ "መምህር ሆይ፤
ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው እንጂ"
አሉት።
40እርሱም፣ እላችኋለሁ፤ "እነርሱ ዝም
ቢሉ፣ ድንጋዮች ይጮኻሉ" አላቸው።
41ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረብ

---

መባ በመስጠትና በሌሎችም መንገዶች ለክርስቶስ ለመኖር ዕድሉ፣ ጊዜውና ችሎታው ተሰጥቶናል።

**19፥17 ታማኝ ሆነህ ስለ ተገኘህ፤** እዚህ ምድር ላይ ጌታን በማገልገልና እርሱ ስለ ሌሎች ያለውን ሸክም በመካፈል በታማኝነት የኖረ ማንኛውም አማኝ በሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት በብዙ ይሸለማል፣ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድርም የበለጠ ኀላፊነት ይሰጠዋል (ራእ 21፥1)። ታማኝነታቸው አነስተኛ የሆነ ሰዎች ዝቅተኛ ቦታ ኀላፊነት ይቀበላሉ።

**19፥26 ያለው እንኳ ይወሰድበታል፤** ማቴ 25፥29 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥28 ይህ ጥቅስ ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን ያመለክታል፤** ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት፣ በትንቢት የተነገረው የእስራኤል ንጉሥና መሲሕ እርሱ እንደ ሆነ በግልጽ ይመሰክራል (ዘካ 9፥9 እና ማብ ይመ)፤ (1) ኢየሱስ በዚህ ሁኔታ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ ነቢዩ ዘካርያስ ትንቢት ተናግሮ ነበር፤ (2) ኢየሱስ ተሑት ሆኖ መግባቱ፣ መንግሥቱ ከዚህ ዓለም እንዳልሆነና ዓለምንም በኀይል ወይም በጕልበት ለመግዛት እንዳልመጣ ለማሳየት ታስቦ የተፈጸመ ትእምርታዊ ድርጊት ነው። ኢየሱስ እንደ ድል አድራጊ ጀኔራል ራሱ ለመግለጽ ያለመፈለጉ፣ መንግሥቱ መንፈሳዊ መንግሥት እንደ ሆነ ያመለክታል።

**19፥41 ከተማዋን አይቶ አለቀሰላት፤** ሕዝቡና መሪዎቻቸው የሚፈልጉት ምድራዊ መንግሥትን የሚያቋቁም መሲሕ እንደሆነና እርሱ እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል የመጣ መሲሕ መሆኑን

ከተማዋን አይቶ አለቀሰላት፤ [42]እንዲህም
አለ፤ "ሰላምሽ የሚሆነውን ምነው አንቺ
ዛሬ በተረዳሽ ኖሮ! አሁን ግን ከዐይንሽ
ተሰውሮአል፤ [43]ጠላቶችሽ ዙሪያሽን ቅጥር
ሠርተው፣ ከየአቅጣጫውም ከበው አንቺን
የሚ ያስጨንቁበት ጊዜ ይመጣልና፤
[44]አንቺንና በቅጥርሽ ውስጥ የሚኖሩትንም
ልጆችሽን ከዐፈር ይደባልቃሉ፤ ድንጋይም
በድንጋይ ላይ አይተዉም፤ የመጐብኛሽን
ጊዜ አላ ወቅሽምና።"

## ኢየሱስ በቤተ መቅደስ

*19፥45፡46 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥12-16፤*
*ማር 11፥15-18፤ ዮሐ 2፥13-16*

[45]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ
ገብቶ፣ ሻጮችን ከዚያ አስወጣ፤ [46]ደግሞም
"'ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል' ተብሎ
ተጽፎአል፤ እናንተ ግን 'የወንበዴዎች ዋሻ'
አደረጋችሁት" አላቸው።
[47]በየቀኑም በቤተ መቅደስ ያስተምር
ነበር፤ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና
የሕዝብ መሪዎችም ሊገድሉት ይፈልጉ
ነበር፤ [48]ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉ ከእርሱ ጋር
ተቈራኝተው ትምህርቱን ይከታተሉ ስለ
ነበር፣ የሚያደርጉት ግራ ገባቸው።

19፥43 ኢሳ29፥3፤ ኤዞ6፥6፤ ሕዝ4፥2፤ 26፥8፤ ሉቃ21፥20
19፥44 መዝ137፥9፤ ሉቃ21፥6፤ 1ጴጥ2፥12
19፥46 ኢሳ56፥7፤ ኤዞ7፥11
19፥47 ማቴ12፥14፤ 26፥55፤ ማር11፥18
20፥1 ማቴ26፥55፤ ሉቃ8፥1
20፥2 ዮሐ2፥18፤ ሐሥ4፥7፤ 7፥27
20፥4 ማር1፥4
20፥6 ማቴ11፥9፤ ሉቃ7፥29

## የኢየሱስ ሥልጣን ለአይሁድ አጠያያቂ ሆነባቸው

*20፥1-8 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥23-27፤*
*ማር 11፥27-33*

**20** አንድ ቀን ኢየሱስ ሕዝቡን በቤተ
መቅደስ ሲያስተምርና ወንጌልን
ሲሰብክ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና ሽማ
ግሌዎች ተሰብስበው ወደ እርሱ መጡ፤
[2]እነርሱም፣ "እነዚህን ነገሮች የምታደርገው
በምን ሥልጣን እንደ ሆነ ንገረን፤ ሥልጣንስ
የሰጠህ ለመሆኑ እርሱ ማን ነው?" ብለው
ጠየቁት።
[3]እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ እስቲ
መልሱልኝ፤ [4]የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ
ነበር ወይስ ከሰው?"
[5]እነርሱም እንዲህ ብለው እርስ በርስ
ተመካከሩ፤ "'ከሰማይ' ብንል፣ 'ታዲያ፣
ለምን አላመናችሁበትም?' ይለናል፤ [6]'ከሰው'
ብንል ሕዝቡ ሁሉ ዮሐንስ ነቢይ መሆኑን
ስለሚያምኑ በድንጋይ ይወግሩናል።"

---

እንደማይቀበሉት ኢየሱስ ስላወቀ፣ ፈጥነው በከባድ ፍርድ ላይ ስለሚወድቁት ስለ እነዚህ ሰዎች በማዘን አለቀሰ። በግሪኩ "አለቀሰ" የሚለው ቃል ትርጒም እንባን ከማፍሰስ በላይ ነው፤ ሰቆቃን፣ ዋይታንና ስቅስቅ ብሎ ማልቀስን ያመለክታል፤ ይህም የነፍስን መሪር ሐዘን ይገልጻል። ኢየሱስ አምላክ እንደመሆኑ ይህን ያደረገው ስሜቱን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን የሰው ዘር የጠፋ ሆኖ እያለ ለድነት የሚያበቃውን ንስሓ ለመግባት ፈቃደኛ ያለመሆኑ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ልብ እንደሚያሳዝን ለመግለጽም ጭምር ነው (ማር 11፥9 እና ማብ ይመ)።

**19፥43 ጠላቶችሽ ዙሪያሽን ... ከበው፤** ኢየሱስ የተናገረው ትንቢት የተፈጸመው ከአርባ ዓመት በኋላ በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በሮማ ወታደሮች ተወርራ በጠፋችና በሺህ የሚቈጠሩ አይሁድ በተገደሉ ጊዜ ነው።

**19፥45 ሻጮችን ከዚያ አስወጣ፤** ቤተ መቅደሱን የማንጻቱ ተግባር ኢየሱስ በይፋ የገለጸው የመጀመሪያውና የመጨረሻው ታላቅ አገልግሎት ነው (ዮሐ 2፥13-22 ይመ፤ ከማቴ 21፥12-17፤ ከማር 11፥15-17 ጋር ያነጻጽሩ)። ኢየሱስ ቍጣው ነድዶ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸውን፣ ስግብግቦችንና የቤተ መቅደሱን እውነተኛ መንፈሳዊ ዐላማ የሚያበላሹትን ሰዎች ከቤተ መቅደሱ አስወጣ። በኢየሱስ የሦስት ዓመት አገልግሎት ሁለት ጊዜ የተፈጸመው ቤተ መቅደሱን የማንጻት ተግባር የሚከተሉትን አስፈላጊ ትምህርቶች የያዘ ነው፤

(1) ክርስቶስ ቅድስና፣ ንጽሕናና እውነተኛነት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዲታይ አጥብቆ ግድ ይለዋል (ከዮሐ 17፥17፡19 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለ እርሷ የሞተውም፣ « ... በማንጻት እንድትቀደስ ... ቅድስትና ነውር አልባ ... አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው» (ኤፌ 5፥25-27)፤

(2) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው አምልኮ በመንፈስና በእውነት መሆን አለበት (ዮሐ 4፥24)። ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር የሚጸለይበትና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚደረግበት ቦታ መሆን አለበት (ከማቴ 21፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) ቤተ ክርስቲያንን፣ ወንጌሉን ወይም መንግሥቱን የግል ጥቅም፣ ክብርና እድገት ለመገንባት የሚያውሉትን ሰዎች ሁሉ ክርስቶስ ያወግዛል።

(4) ለእግዚአብሔርና ለማዳን ዐላማው እውነተኛ ፍቅር ካለን፣ በእግዚአብሔር ቤትና በመንግሥቱ ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው ቅድስና በልባችን የሚቃጠል ቅናት እንዲኖረን ያደርጋል (ዮሐ 2፥17)። በእውነት ክርስቶስን መምሰል፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታየውን ቅድስና የጐደለውን ነገር ለመታገሥ አያስችለንም (ከራእ 2—3 ጋር ያነጻጽሩ)።

(5) እውነተኛ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያረክሱትንና የሚንቁትን ሰዎች መቃወም ይገባዋል (ከ1ቆሮ 6፥9-11፤ ከገላ 1፥6-10፤ ከራእ 2—3 ጋር ያነጻጽሩ)።

(6) ክርስቶስ አታላይነትን፣ ኢግብረገባዊነትን፣ ዓለማዊነትንና ርኵሰትን ሁሉ ያስወግድ ዘንድ በጉባኤያችን እንዲገኝ ልባችን ፈቃደኛ መሆን አለበት (ራእ 2—3)፤ ይህ ካልሆነ፣ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ በመለኮታዊ ፍርድ ቤተ ክርስቲያኑን ፈጽሞ ያነጻል (ሚል 3፥2)።

**19፥46 የጸሎት ቤት፤** ማር 11፥17 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**20፥2 በምን ሥልጣን፤** የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ለማንጻትና ሕዝቡን ለማስተማር ማን ሥልጣን እንደሰጠው ጠየቁት (19፥45-48)። እነዚህ መሪዎች በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚደረገውን አስጸያፊ ነገር ዝም ብለው ከመቀበላቸውም በላይ የድርጊቱ ተካፋዮች ስለነበሩ፣ ኢየሱስ ይህን ክፉ ሥራ በማውገዙ እጅግ ተቈጡ። እንደዚህ ዐይነቱ ድርጊት እነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ መሪዎች ለመሆን ምን ያህል ብቁ እንዳልሆኑ ይገልጻል። ኢየሱስ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ እንደመሆኑ፣ ሕይወቱን እስከ መስጠት ዋጋ የሚያስከፍለው ቢሆንም እንኳ እውነትንና ጽድቅን ይገልጽ ዘንድ ሥልጣኑን ከመጠቀም ወደ ኋላ አላለም።

7ስለዚህ፣ "ከየት እንደ ሆነ አናውቅም"
ብለው መለሱለት።
8ኢየሱስም፣ "እንግዲያውስ እኔም
እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ
አልነግራችሁም" አላቸው።

## የጭሰኞቹ ምሳሌ

*20፥9-19 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥33-46፤
ማር 12፥1-12*

9ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ይህን
ምሳሌ ለሕዝቡ ይነግራቸው ጀመር፤ "አንድ
ሰው የወይን ተክል ተከለ፤ ለገበሬዎችም
አከራየና ወደ ሌላ አገር ሄዶ ብዙ ጊዜ
ቈየ። 10በመከርም ወራት፣ ከወይኑ ፍሬ
እንዲ ልኩለት አገልጋዩን ወደ እነዚህ
ገበሬዎች ላከ፤ ገበሬዎቹ ግን አገልጋዩን
ደብድበው ባዶ እጁን ሰደዱት። 11ቀጥሎም
ሌላ አገልጋዩን ላከ፤ ገበሬዎቹም እርሱንም
ደግሞ ደበደቡት፤ አዋርደውም ባዶ እጁን
ሰደዱት። 12አሁንም ቀጥሎ ሦስተኛ
አገልጋዩን ላከ፤ ገበሬዎቹም እርሱንም
ደግሞ አቍስለው ወደ ውጭ ጣሉት።
13"የወይኑ ተክል ባለቤትም፣ 'እንግዲህ
ምን ላድርግ? እስቲ ደግሞ የምወደውን
ልጄን እልካለሁ፤ ምናልባት እርሱን ያከ
ብሩት ይሆናል' አለ።
14"ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩት ጊዜ፣ ይህ
እኮ ወራሹ ነው፣ 'ኑና እንግደለው፤ በዚህም
ርስቱ የእኛ ይሆናል' እየተባባሉ ተመካ
ከሩ፤ 15ከወይኑም ተክል ቦታ ወደ ውጭ
አውጥተው ገደሉት።
"እንግዲህ የወይኑ ተክል ባለቤት ምን
ያደርጋቸዋል? 16መጥቶ እነዚያን ገበሬዎች
ያጠፋቸዋል፤ የወይኑንም ተክል ቦታ
ለሌሎች ይሰጣል።"
ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ፣ "እንዲህ
ያለውንስ አያምጣው" አሉ።
17ኢየሱስም ወደ እነርሱ ተመልክቶ
እንዲህ አላቸው፤
" 'ታዲያ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
'እርሱ የማእዘን ራስ^ ሆነ' ተብሎ
የተጻፈው ትርጕሙ ምንድን
ነው?
18በዚህ ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ
ይቀጠቀጣል፤ ድንጋዩም በላዩ የሚወድቅበት
ሁሉ ይደቃል።"

20፥9 ኢሳ5፥1-7፤
ማቴ25፥14
20፥13 ማቴ3፥17
20፥16
ሉቃ19፥27
20፥17
መዝ118፥22፤
ሐሥ4፥11
20፥18
ኢሳ8፥14፡15
20፥19
ማር11፥18፤
ሉቃ19፥47
20፥20
ማቴ12፥10፤
27፥2
20፥21 ዮሐ3፥2
20፥25
ሉቃ23፥2፤
ሮሜ13፥7
20፥27
ሐሥ4፥1፤ 23፥8፤
1ቆሮ15፥12
20፥28 ዘዳ25፥5

19ጸሐፍትና የካህናት አለቆችም ይህንን
ምሳሌ የተናገረው በእነርሱ ላይ መሆኑን
ስላወቁ፣ በዚያኑ ሰዓት ሊይዙት ፈልገው
ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ።

## ለቄሣር ግብር መክፈል

*20፥20-26 ተጓ ምብ — ማቴ 22፥15-22፤
ማር 12፥13-17*

20ኢየሱስን አሳልፈው ለገዢው ኀይልና
ሥልጣን ለመስጠት፣ ከአፉ በሚወጣ ቃል
ለማጥመድ ይከታተሉት ነበር፤ ስለዚህም
ጻድቃን መስለው የሚቀርቡ ሰላዮችን
ላኩበት። 21ሰላዮቹም እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፤
"መምህር ሆይ፤ አንተ ትክክለኛውን
ነገር እንደምትናገርና እንደምታስተምር
እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንገድ በእውነት
እንደ ምታስተምርና ለማንም እንደማታደላ
እና ውቃለን። 22ለመሆኑ ለቄሳር ግብር
መክፈል ይገባል ወይስ አይገባም?"
23እርሱ ግን ተንኰላቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ 24"እስቲ አንድ ዲናር አሳዩኝ፤
በላዩ ያለው የማን መልክና ጽሕፈት ነው?"
25እነርሱም፣ "የቄሳር ነው" ብለው መለ
ሱለት።
እርሱም፣ "እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄ
ሳር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ"
አላቸው።
26ስለዚህ በተናገረው ቃል በሕዝቡ ፊት
ሊያጠምዱት አልቻሉም፤ በመልሱም ተገር
መው ዝም አሉ።

## ትንሣኤ ሙታንና ጋብቻ

*20፥27-40 ተጓ ምብ — ማቴ 22፥23-33፤
ማር 12፥18-27*

27ትንሣኤ ሙታን የለም ከሚሉት
ሰዱቃውያን አንዳንዶቹ ወደ ኢየሱስ
መጥተው ጥያቄ አቀረቡለት፤ 28እንዲህም
አሉት፤ "መምህር ሆይ፤ አንድ ሰው
ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣
ወንድሙ መበለቲቱን አግብቶ ልጆች
በመውለድ ለወንድሙ ዘር እንዲተካ ሙሴ
ጽፎልናል። 29ታዲያ፣ ሰባት ወንድማማቾች
ነበሩ፤ የመጀመሪያው ሚስት አግብቶ ልጅ
ሳይወልድ ሞተ፤ 30ሁለተኛውም እንደዚሁ፤
31ሦስተኛው ደግሞ አገባት፤ ሰባቱም እንዲሁ

^20፥17 ወይም የማእዘን ድንጋይ

**20፥9-16 በዚህ ክፍል ስለ ጭሰኞች ምሳሌ ተጠቅሶአል፤** ማቴ 21፥33 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**20፥16 የወይኑንም ተክል ቦታ ለሌሎች ይሰጣል፤** ማቴ 21፥43 እና "የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ" በሚለው ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**20፥18 በዚህ ድንጋይ፤** ጌታ ኢየሱስን የማይቀበሉ ይሰበራሉ፤ በፍርዱም ሥር የሚወድቁ ሙሉ በሙሉ ይደቃሉ:: ክርስቶስ ለብዙዎች የሚያደናቅፍ ድንጋይ፣ የሚያሰናክልም ዐለት እንደ ሆነ የተጠቀሰበትን ክፍል ኢሳ 8፥14 እና ሉቃ 2፥34 እንደዚሁም መሲሑ መንግሥታትን ሁሉ እንደሚያደቅ የተገለጸበትን ክፍል ዳን 2፥34-35፡44-45 ይመልከቱ::

**20፥25 እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄሳር … ስጡ፤** አማኞች ከሁሉም በላይ ለእግዚአብሔር ታማኞች መሆን የሚጠበቅባቸው ቢሆንም በተለመደው አሠራርና ተገቢ በሆነው መንገድ ግብር መክፈልና ለመንግሥት ባለሥልጣናት መታዘዝ ይገባቸዋል (ሮሜ 13፥1-7):: ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የማይቃረን እስከ ሆነ ድረስ፣ የምድራዊውን መንግሥት ትእዛዝ ማክበር ይገባናል:: "የቄሳርን ለቄሳር" ባለመስጠት፣ ጌታ ኢየሱስ ያዘዘን ትእዛዝ ከማድረግ በፍጹም ወደ ኋላ ማለት የለብንም::

እያሉ አግብተዋት ልጆች ሳይወልዱ ሞቱ።
32በመጨረሻም ሴትዮዋ ሞተች። 33እንግዲህ
ሰባቱም ስላገቧት፣ በትንሣኤ ጊዜ የማን
ሚስት ትሆናለች?"
34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ፤ ይጋባሉም፤
35የሚመጣውን ዓለምና የሙታንን ትንሣኤ
ማግኘት የሚገባቸው ግን አያገቡም፤
አይጋቡም፤ 36እንደ መላእክትም ስለሆኑ
ከዚያ በኋላ አይሞቱም፤ የትንሣኤ ልጆች
ስለ ሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።
37ሙሴ ስለ ቍጥቋጦ በተጻፈው ታሪክ
ውስጥ ጌታን፣ 'የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ
አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ' በማለቱ ሙታን
እንደሚነሡ ያሳያል፤ 38ሁሉም ለእርሱ
ሕያዋን ስለሆኑ፣ እርሱ የሕያዋን አምላክ
እንጂ የሙታን አይደለም።"
39አንዳንድ ጸሐፍትም፣ "መምህር ሆይ፤
መልካም ተናገርህ" አሉት። 40ከዚህ በኋላ
አንድ ሰው እንኳ ሊጠይቀው አልደፈረም።

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

*20፥41-47 ተጓ ምብ — ማቴ 22፥41—23፥7፤ ማር 12፥35-40*

41ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
"ሰዎች ክርስቶስን[a] እንዴት የዳዊት ልጅ
ነው ይሉታል? 42ምክንያቱም ራሱ ዳዊት
በመዝሙራት መጽሐፉ እንዲህ ብሏል፤

" 'ጌታ ጌታዬን፣
"በቀኜ ተቀመጥ፤
43እኔ ጠላቶችህን፣
ለእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ
ድረስ።' "
44እንግዲህ ዳዊት እርሱን፣ 'ጌታ' ብሎ
ሲጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል?"
45ሕዝቡ ሁሉ እየሰሙትም ለደቀ
መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ 46"ዘርፋፋ
ቀሚስ ለብሰው መዞር ከሚወዱ፣ በገበያ
ቦታ ሰላምታ ከሚሹና በምኵራብ
የከበሬታ መቀመጫ፣ በግብዣ ቦታም
የክብር ስፍራ ከሚ ፈልጉ፣ ከጸሐፍት
ተጠንቀቁ፤ 47እነርሱም የመበለቶችን ቤት
የሚያራቍቱ ናቸው፤ ለታይታ ብለውም
ጸሎታቸውን ያስረዝማሉ፤ እነዚህ የከፋ
ፍርድ ይጠብቃቸዋል።"

## መበለቷ የሰጠችው መባ

*21፥1-4 ተጓ ምብ — ማር 12፥41-44*

21 ኢየሱስ ቀና ብሎ ሲመለከት
ሀብታሞች በቤተ መቅደሱ መባ
መሰብሰቢያ ውስጥ መባቸውን ሲጨምሩ
አየ። 2ደግሞም አንዲት ድኻ መበለት ሁለት
ትናንሽ የናስ ሳንቲሞች በዚያ ስትጨምር
ተመለከተ፤ 3እንዲህም አለ፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ከሁሉም ይልቅ ይህች ድኻ
መበለት የበለጠ ሰጥታለች፤ 4እነዚህ ሰዎች
የሰጡት ከትርፋቸው ላይ ሲሆን፣ እርሷ ግን
የሰጠችው በድኽ ህቅሟ ያላትን መተዳደሪያ
በሙሉ ነው።"

## የዘመኑ መጨረሻ ምልክቶች

*21፥5-36 ተጓ ምብ — ማቴ 24፤ ማር 13፤*
*21፥12-17 ተጓ ምብ — ማቴ 10፥17-22*

5ከደቀ መዛሙርት አንዳንዶች ቤተ
መቅደሱ በውብ ድንጋዮችና በስእለት
ስጦታዎች እንዳማረ ሲነጋገሩ፣ ኢየሱስ
እንዲህ አለ፤ 6"ይህ የምታዩት ሁሉ

20፥35 ማቴ12፥32
20፥36 ዮሐ1፥12
20፥37 ዘፀ3፥6
20፥40 ማቴ12፥34፤ 22፥46
20፥41 ማቴ1፥1
20፥43 መዝ110፥1፤ ማቴ22፥44
20፥46 ሉቃ11፥43
21፥1 ማቴ27፥6፤ ዮሐ8፥20
21፥4 2ቆሮ8፥12
21፥6 ሉቃ19፥44

[a]20፥41 ወይም መሲሕ

---

**20፥36 እንደ መላእክትም፤** ጌታ ኢየሱስ በወዲያኛው ዓለም የአማኞች ሕይወት ምን እንደሚመስል ሲገልጽ ከሙታን ትንሣኤ እንደሚጀምር፣ ፈጽሞ የማይሞት የከበረ አካል እንደሚኖራቸው፣ ጋብቻን የመሳሰሉ ምድራዊ ትስስሮችና ሥርዐቶች ከእንግዲህ እንደማይኖሩ ተናግሮአል። በምድር ያለው ግንኙነትና ትስስር በዚያ አይኖርም ሲባል፣ እርስ በርስ አንተዋወቅም ማለት አይደለም። ጌታ ኢየሱስን ከትንሣኤው በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ እንደ ሆነ አውቀውታል (ሉቃ 24፥31፡39፤ ማቴ 28፥9)።

**20፥44 ዳዊት እርሱን፣ 'ጌታ' ብሎ ሲጠራው፤** አይሁድ መሲሑ ከዳዊት ዘር እንደ ሆነ፣ ስለዚህም ሰብዓዊ ፍጡር የሆነ ገዥ እንጂ አምላክ እንዳልሆነ ያስቡ ነበር። ዳዊት በመዝ 110፥1 ላይ የእግዚአብሔርን ልጅ፣ ፎጌታዬ ብሎ ሲጠራው፣ መሲሑ ሰብዓዊ ፍጡር ከሆነ ገዥ የላቀና አምላክም መሆኑን እንደሚያመለክት ኢየሱስ ይገልጻል፤ ደግሞም እርሱ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ ነው (መዝ 110፥1-7 እና ማብ ይመ)።

**20፥46 ከጸሐፍት ተጠንቀቁ፤** ማቴ 23፥13 እና ማብራሪያውን ይመ፤ (በገጽ 1519 ላይ፣ "***የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ)።

**21፥1-4 ይህ ክፍል መበለቷ የሰጠችውን ያመለክታል፤** ሰው የሚያቀርበውን ስጦታ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመዝን፣ ኢየሱስ የሚከተለውን ትምህርት ይሰጣል፤ (1) የሰው ስጦታ ዋጋ እንዲኖረው የሚያደርገው፣ የስጦታው ብዛት ሳይሆን፣ ፍጹምና እውነተኛ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡ ነው። ሀብታሞች የሚሰጡት ከትርፋቸው በመሆኑ፣ ስጦታቸው ፍጹም የሆነ መሥዋዕት አይደለም። መበለትዋ ግን ያላትን ሁሉ መሥዋዕት አድርጋ አቅርባለች፤ የሰጠችውም ያላትን ሁሉ ነው፤ (2) ይህ መርሕ ለኢየሱስ በምንሰጠው አገልግሎት ሁሉ ተግባራዊ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ሥራችንንና አገልግሎታችንን በመመዘን ዋጋ የሚሰጠው በብዛት፣ በሰዎች ዘንድ በሚኖረን ተቀባይነት ወይም በምናገኘው ድል ሳይሆን በምናሳየው እውነተኛ መሰጠት፣ መሥዋዕትነት፣ እምነትና ፍቅር ነው (22፥24-30 እና ማብ፤ ማቴ 20፥26 እና ማብ ይመ)።

**21፥6 ድንጋይ በድንጋይ ላይ እንደተካበ የማይቀርበት፤** ይህ ትንቢት የተፈጸመው፣ በ70 ዓ.ም. የሮማ ጄኔራል ቲቶና ወታደሮቹ ከመቶ ሰላሣ አራት ቀን ከበባ በኋላ ኢየሩሳሌምን ባጠፉና ቤተ መቅደሱን ባቃጠሉ ጊዜ ነው። ቤተ መቅደሱ የተቃጠለው፣ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ልጅ በመናቃቸውና በእርሱም በኩል የተደረገውን የማዳን ሥራ ስላልተቀበሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ተፈጽሞባቸው ነው።

# የሕማማት ሳምንት

**1. ቢታንያ መድረሱ** ዐርብ ዮሐ 12፥1

ኢየሱስ ከወዳጆቹ ከማርያም፣ ማርታና አልዓዛር ጋር ለመሆን ከፋሲካ ስድስት ቀን ቀደም ብሎ ቢታንያ ደረሰ። ኢየሱስ እዚያው ቢታንያ እያለ ማርያም ትሕትናን ለማሳየት፣ እጅግ ውድ በሆነ ሽቱ የኢየሱስን እግር ቀባች። ይህ ድርጊት ማርያም ለኢየሱስ ራሷን መስጠቷንና ልታገለግለውም ሙሉ ፈቃደኝነቷን ያመለክታል።

**2. ሰንበት፣ የእረፍት ቀን** ቅዳሜ በወንጌላት ውስጥ አልተጠቀሰም

የሚቀጥለው ቀን ሰንበት ስለሆነ፣ በባሕሉ እንደተለመደው ጌታ ከወዳጆቹ ጋር ቀኑን አሳለፈ።

**3. በክብር መግባት** እሁድ ማቴ 21፥1-11፤ ማር 11፥1-11፤ ሉቃ 19፥28-44፤ ዮሐ 12፥12-19

በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ኢየሱስ የተነገረለትን ትንቢት ለመፈጸም፣ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ (ዘካ 9፥9)። ሕዝቡ "ሆሳዕና" በማለት በመዝ 118፥25-26 ባለው ቃል መሠረት ተቀበለው፤ ይህም መሲሑ እንደ ሆነና የሚመጣው የእስራኤል ንጉሥ እርሱ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው።

**4. ቤተ መቅደሱን ማንጻት** ሰኞ ማቴ 21፥10-17፤ ማር 11፥15-18፤ ሉቃ 19፥45-48

በሚቀጥለው ቀን ወደ ቤተ መቅደሱ ሄደ፤ በዚያም በአሕዛብ አደባባይ በነጋዴዎችና የአሕዛብን ገንዘብ በአይሁድ ገንዘብ በመለወጥ ብዙ ትርፍ በሚያገኙ ገንዘብ ለዋጮች ተሞልቶ አገኘ። ኢየሱስም እነዚህን ሰዎች አባረረ፤ ጠረጴዛዎቻቸውንም ገለበጠ።

**5. የክርክርና የምሳሌዎች ቀን በኢየሩሳሌም በካህናት የተዘጋጀበትን ወጥመድ አመለጠ።** ማክሰኞ ማቴ 21፥23—24፥51፤ ማር 11፥27—13፥37፤ ሉቃ 20፥1—21፥36

ከደብረ ዘይት ላይ ሆኖ ኢየሩሳሌምን ተመለከተ። በምሳሌ አስተማራቸው፤ ሕዝቡንም ከፈሪሳውያን እንዲጠበቁ አስጠነቀቃቸው። የሄሮድስ ቤተ መቅደስ እንደሚፈርስ አስቀድሞ ተናገረ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮችና ስለ ዳግም ምጽአቱ ነገራቸው።

**6. የእረፍት ቀን** ረቡዕ በወንጌላት ውስጥ አልተጠቀሰም

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ቀን ምንም አልጠቀሱም፤ ሆኖም የቀናት አቈጣጠር (ማር 14፥1፤ ዮሐ 12፥1) በወንጌላት ውስጥ ያልተጠቀሰ ሌላ ቀን እንዳለ የሚያመለክት ይመስላል።

**7. ፋሲካ የመጨረሻ እራት** ሐሙስ ማቴ 26፥17-30፤ ማር 14፥12-26፤ ሉቃ 22፥7-23፤ ዮሐ 13፥1-30

በላይኛው ክፍል ኢየሱስ ራሱንና ደቀ መዛሙርቱን ለሞቱ አዘጋጀ። የፋሲካ መብል የተለየ ትርጉም እንዲኖረው አደረገ። የቈረሰው እንጀራና በጽዋ ያለው ወይን በቅርብ የሚሠዋውን ሥጋውንና የሚፈሰውን ደሙን እንደሚወክሉ አሳየ። በዚህም፣ "የጌታ እራት" ሥርዐት መሠረተ። ከዘመሩ በኋላ ከፊቱ ያለውን በማወቅ በጣር ወደ ጸለየበት ስፍራ ወደ ጌቴሴማኒ ሄዱ።

**8. ስቅለት** ዐርብ ማቴ 27፥1-66፤ ማር 15፥1-47፤ ሉቃ 22፥66—23፥56፤ ዮሐ 18፥28—19፥37

አልፎ ከተሰጠ፣ ከታሰረ፣ ደቀ መዛሙርቱ ከተለዩት፣ በሐሰት ከተከሰሰ፣ ከተካደ፣ ወታደሮች ከመቱትና ካፌዙበት በኋላ ኢየሱስ "የራስ ቅል" ወደ ተባለ ስፍራ መስቀሉን ተሸክሞ እንዲሄድ ተደረገ፤ በዚያም ከሌሎች ሁለት እስረኞች ጋር ሰቀሉት።

**9. መቃብሩ** ዐርብ ማቴ 27፥57-61፤ ማር 15፥42-47፤ ሉቃ 23፥50-56፤ ዮሐ 19፥38-42

የኢየሱስ ሥጋ ከምሽቱ 12:00 በፊት በመቃብሩ ውስጥ እንዲሆን ተደረገ። ዐርብ ማታ ሰንበት ጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በመቃብር ውስጥ ነበረ።

© 1989 The Zondervan Corporation

ማቴ 28፥1-13፤ ማር 16፥1-20፤

**10. ትንሳኤ** እሑድ ሉቃ 24፥1-49፤ ዮሐ 20፥1-31

ጠዋት በማለዳ ወደ መቃብሩ የሄዱት ሴቶች የመቃብሩ መዝጊያ የነበረው ድንጋይ ተንከባሎ አገኙት። አንድ መልአክም ኢየሱስ ሕያው እንደ ሆነ ነግሮአቸው መልእክት ላካቸው። ኢየሱስ በአትክልት ስፍራ ለመግደላዊት ማርያም፣ ከዚያም ለጴጥሮስ፣ በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ ለነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙርትና በኋላም ከቶማስ በስተቀር ለሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ታየ። የትንሣኤው እውነተኛነት የተረጋገጠ ነው።

ሳይፈርስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ እንደ
ተከበ የማይቀርበት ጊዜ ይመጣል።"
7እነርሱም፣ "መምህር ሆይ፤ እንግዲህ
ይህ ሁሉ የሚሆነው መቼ ነው? ደግሞም
ይህ እንደሚሆን ምልክቱ ምንድን ነው?"
ብለው ጠየቁት።
8እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እንዳትስቱ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች፣ 'እኔ
እርሱ ነኝ' በማለት፣ ደግሞም፣ 'ጊዜው
ቀርቦአል' እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ እናንተ
ግን እነርሱን አትከተሏቸው። 9ስለ ጦርነትና
ስለ ሕዝብ ዐመፅ ስትሰሙ አትደንግጡ፤
ይህ አስቀድሞ መሆን የሚገባው ነውና፤
መጨረሻው ግን ወዲያውኑ አይሆንም።"
10ቀጥሎም እንዲህ አላቸው፤ "ሕዝብ
በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት
ላይ ይነሣል፤ 11ታላቅ የመሬት መናወጥ
ይሆ ናል፤ ራብና ቸነፈር በተለያየ ስፍራ
ይከሠ ታል፤ አስፈሪ ነገር እንዲሁም
ከሰማይ ታላቅ ምልክት ይሆናል።
12"ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት ግን ሰዎች
ይይዟችኋል፤ ያሳድዱችኋል፤ ወደ ምኵራ
ብና ወደ ወህኒ ቤት ያስገቧችኋል፤ በነገ
ሥታትና በገዥዎች ፊት ያቀርቧችኋል፤
ይህም ሁሉ በስሜ ምክንያት ይደርስባችኋል።
13ይህም ለመመስከር ጥሩ ዕድል
ይሆንላችኋል። 14ስለዚህ ምን መልስ
እንሰጣለን በማለት አስቀድማችሁ
እንዳትጨነቁ ይህን ልብ በሉ፤
15ተቃዋሚዎቻችሁ ሁሉ ሊቋቋሙትና
ሊያስተባብሉት የማይችሉትን ቃልና
ጥበብ እሰጣችኋለሁና። 16ወላጆቻችሁ፣
ወንድሞቻችሁ፣ዘመዶቻችሁና ጓደኞቻችሁ
እንኳ ሳይቀሩ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፤
ከእናንተም አንዳንዶቹን ይገድ ላሉ፤ 17ስለ
ስሜም በሰዎች ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ
ትሆናላችሁ። 18ነገር ግን ከራሳችሁ ጠጕር
አንዲ እንኳ አትጠፋም፤ 19ጽንታችሁም
በመቆም ነፍሳችሁን ታተርፋላችሁ።
20"ኢየሩሳሌም በጦር ሰራዊት ተከባ
በምታዩበት ጊዜ፣ ጥፋቷ መቃረቡን ዕወቁ።
21በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች
ይሽሹ፤ በከተማ ያሉትም ከዚያ ይውጡ፤
በገጠር ያሉትም ወደ ከተማዪቱ አይግቡ፤
22የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይህ
የበቀል ጊዜ ነውና። 23በምድሪቱ ላይ ታላቅ
መከራ ይሆናል፤ በዚህም ሕዝብ ላይ ቍጣ
ይመጣል፤ ስለዚህ በዚያን ወቅት ለነፍሰጡ
ሮችና ለሚያጠቡ እናቶች ወዮላቸው!
24በሰይፍ ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛብም ሁሉ
በምርኮ ይወሰዳሉ፤ ኢየሩሳሌምም የአሕዛብ
ዘመን እስኪፈጸም ድረስ፣ በአሕዛብ የተረ
ገጠች ትሆናለች።
25"በፀሓይ፣ በጨረቃና በከዋክብት

21፥8 ሉቃ17፥23
21፥10 2ዜና15፥6፤ ኢሳ19፥2
21፥11 ኢሳ29፥6፤ ኢል2፥30
21፥13 ፊል1፥12
21፥14 ሉቃ12፥11
21፥15 ሉቃ12፥12
21፥16 ሉቃ12፥52:53
21፥17 ዮሐ15፥21
21፥18 ማቴ10፥30
21፥19 ማቴ10፥22
21፥20 ሉቃ19፥43
21፥21 ሉቃ17፥31
21፥22 ኢሳ63፥4፤ ዳን9፥24-27፤ ሆሴ9፥7፤ ማቴ1፥22
21፥24 ኢሳ5፥5፤ 63፥18፤ ዳን8፥13፤ ራእ11፥2
21፥25 2ጴጥ3፥10፡12

**21፥7 ይህ ሁሉ የሚሆነው መቼ ነው?** ከቍ 7-19 ይመልከቱ:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ለጠየቁት ጥያቄ የሰጠው መልስ፣ የኢየሩሳሌምን መጥፋት ከታላቁ መከራ በኋላ እውን ከሚሆነው ከዳግም ምጽአቱ ጋር እጅግ የተቀራረበ ያደርገዋል፤ በመሆኑም ኢየሩሳሌምን ብቻ የሚመለከተውንና ዳግም ምጽአቱ የሚመለከተውን ክፍል መለየት አስቸጋሪ ይሆናል:: ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋት ሲጠቅስ፣ በዓለም ላይ ለመፍረድ እንደሚመጣ የሚያመለክት መሆኑን መናገሩ ነው::

**21፥8 እንዳትስቱ ተጠንቀቁ፤** ማቴ 24፥5 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**21፥9 ስለ ጦርነትና ስለ ሕዝብ ዐመፅ፤** ማቴ 24፥4 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**21፥16 ከእናንተም አንዳንዶቹን ይገድላሉ፤** ከዮሐንስ በስተቀር ሐዋርያት ሁሉ በአሳዳጆቻቸው እጅ በሰማዕትነት እንደሞቱ የጥንት ጸሐፊዎች ይናገራሉ:: ጥንት በነበረው ክርስትና ብዙ አማኞች ተሠቃይተዋል፤ ተገድለዋልም (ማቴ 24፥9 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ)::

**21፥18 ከራሳችሁ ጠጕር አንዷ እንኳ አትጠፋም፤** ይህ ተስፋ፣ ስለ ሥጋዊ ሰውነታችን በደኅና ሁኔታ መጠበቅ ሳይሆን፣ ስለ መንፈሳዊ ደኅንነታችን ዋስትና የሚሰጥ ነው (በቍ 16 ላይ ስለ ሞት ከተጠቀሰው ጋር ያነጻጽሩ):: ክርስቲያኖች እስከ መጨረሻ ድረስ ታማኞች ሆነው ከቆሙ፣ እግዚአብሔር ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲሆንላቸው ያደርጋል (ከሮሜ 8፥28 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ምንም ነገር ከእርሱ ፍቅር ሊለያቸው አይችልም (ሮሜ 8፥35-39)::

**21፥19 ጽንታችሁም በመቆም፤** በጸጋው አማካይነት ሙሉ በሙሉ ራሳችንን ለክርስቶስ ለማስገዛት በጸሎት፣ ስለ እርሱ በመመስከር፣ ቃሉን በማጥናት፣ እርሱን በማምለክ፣ ከክርስቲያኖች ጋር ኅብረት በማድረግና በየዕለቱ ኀጢአትን አጥብቀን በመቃወም ተግባር የተጠመድን መሆን ይገባናል (ዮሐ 15፥6 እና ማብ ይመ):: በእውነተኛው እምነት በመጽናት፣ አማኞች የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ፤ በሁሉም ነገር አሸናፊዎች ይሆናሉ::

**21፥20 ኢየሩሳሌም በጦር ሰራዊት ተከባ፤** ጌታ ኢየሱስ አሁንም በ70 ዓ.ም. ስለሚከሰተው ነገር ይናገራል (የቍ 6 ማብ ይመ):: እነዚህ ሁኔታዎች በተፈጸሙ ጊዜ፣ ጌታ ኢየሱስ መሲሑን ባለመቀበላቸውና ከኀጢአታቸው ንስሓ ባለመግባታቸው፣ "በዚህ ትውልድ ላይ" መለኮታዊ ፍርድ እንደሚሆን የተናገረው ትንቢት እውን ሆኖአል (ማቴ 23፥36 ይመ፤ ከሉቃ 23፥27-30 ጋር ያነጻጽሩ):: በመጀመሪያ የጦር ሰራዊቱን በሚያዩበት ጊዜ ከከተማዋ እንዲሸሹ ጌታ ኢየሱስ ተከታዮቹን ያስጠነቅቃል (ቍ 21)::

**21፥24 የአሕዛብ ዘመን፤** "የአሕዛብ ዘመን" የሚለው ሐረግ እስራኤል አይሁድ ባልሆኑ ሕዝቦች ሥልጣን ወይም የጭቈና አገዛዝ ሥር የምትሆንበትን ጊዜ ያመለክታል:: ይህ የጀመረው ከእስራኤል ሕዝብ የተወሰነው በ586 ዓ.ቅ.ክ ተማርኮ ወደ ባቢሎን በሄደ ጊዜ ነው (2ዜና 36፥1-21፤ ዳን 1፥1-2)፤ ዘመኑም እስከሚፈጸም ድረስ ይቀጥላል:: ይህም ክርስቶስ በሕዝቦች ሁሉ ላይ ለመግዛት በክብርና በሥልጣን የሚመጣበት ጊዜ ማለት ነው (1፥32-33፤ ኤር 23፥5-6፤ ዘካ 6፥13፤ 9፥10፤ ሮሜ 11፥25-26፤ ራእ 20፥4)::

**21፥25 በፀሓይ፣ በጨረቃና በከዋክብት ላይ ምልክት፤** ከጌታ ኢየሱስ መምጣት በፊት በሰማይ ላይ ምልክቶች ይታያሉ፤ ከታላቁ መከራ የተነሣ ዓለም በከባድ ጭንቅና ሐዘን ውስጥ ትሆናለች (ማቴ 24፥29 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: ከኀጢአታቸው በንስሓ የማይመለሱ ሰዎች በታላቅ ፍርሀትና ተስፋ መቍረጥ ውስጥ ይወድቃሉ::

ላይ ምልክት ይሆናል፤ ከባሕሩና ከሞገድ
ድምፅ የተነሣ፣ በምድር ላይ ያሉ ሕዝቦች
ይጨነ ቃሉ፤ ይታወካሉም፤ [26]የሰማያት
ኀይላት ስለሚናወጡ፣ ሰዎች በፍርሀትና
በዓለም ላይ ምን ይመጣ ይሆን እያሉ
በመጠባበቅ ይዝ ላሉ። [27]በዚያን ጊዜ የሰው
ልጅ በኀይልና በታላቅ ክብር በደመና
ሲመጣ ያዩታል። [28]እናንተም እነዚህ
ነገሮች መፈጸም ሲጀ ምሩ፣ መዳናችሁ ስለ
ተቃረበ፣ ቀጥ ብላችሁ ቁሙ፤ ራሳችሁንም
ወደ ላይ ቀና አድርጉ።"
[29]ቀጥሎም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
ነገራቸው፤ "በለስንና ዛፎችን ሁሉ
ተመልከቱ፤ [30]ቅጠሎቻቸው አቈጥቍጠው
ስታዩ፣ በዚያን ጊዜ በጋ መቃረቡን ራሳችሁ
ታውቃላችሁ። [31]እንዲሁ ደግሞ እነዚህ
ነገሮች መፈጸማቸውን ስታዩ፣ የእግዚአብሔር
መንግሥት እንደ ቀረበች ዕወቁ።
[32]"እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ
እስኪፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ[a] አያልፍም።
[33]ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያ
ልፍም።"
[34]"እንግዲህ በገደብ የለሽ ሕይወት፣
በመጠጥ ብዛትና ስለ ኑሮ በመጨነቅ

21፥26 ማቴ24፥29
21፥27 ማቴ8፥20፤ ራእ1፥7
21፥28 ሉቃ18፥7
21፥31 ማቴ3፥2
21፥32 ሉቃ11፥50፤ 17፥25
21፥33 ማቴ5፥18
21፥34 ማር4፥19፤ ሉቃ12፥40፡46፤ 1ተሰ5፥2-7
21፥36 ማቴ26፥41
21፥37 ማቴ21፥1፤ 26፥55፤ ማር11፥19
21፥38 ዮሐ8፥2
22፥1 ዮሐ11፥55
22፥2 ማቴ12፥14
22፥3 ማቴ4፥10፤ ማቴ10፥4

ልባችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ
ድንገት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ፤
[35]ይህ በመላው ምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ
ይደርሳልና። [36]ስለዚህ ከሚመጣው ሁሉ
እንድ ታመልጡና በሰው ልጅ ፊት መቆም
እንድ ትችሉ ሁልጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ።"
[37]ኢየሱስም ቀን ቀን በቤተ መቅደስ
እያስተማረ፣ ሌሊት ግን ደብረ ዘይት ወደ
ተባለ ተራራ ወጥቶ ያድር ነበር። [38]ሕዝቡም
ሁሉ ሊሰሙት ማልደው ወደ ቤተ መቅደስ
ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

### ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ

*22፥1፡2 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥2-5፤ ማር 14፥1፡2፡10፡11*

22 በዚህ ጊዜ ፋሲካ የተባለው የቂጣ
በዓል ተቃርቦ ነበር። [2]የካህናት
አለቆችና ጸሐፍትም ሕዝቡን ይፈሩ
ስለ ነበር፣ እንዴት አድርገው ኢየሱስን
እንደ ሚያስወግዱት መንገድ ይፈልጉ
ነበር። [3]ሰይጣንም ከዐሥራ ሁለቱ ጋር

[a]21፥32 ወይም ዘር

21፥27 **የሰው ልጅ ... ሲመጣ፤** "የሰው ልጅ" የሚለው አነጋገር ኢየሱስ ራሱን ለማመልከት ብዙውን ጊዜ የተጠቀመበት ቃል ነው (ማቴ 24፥30 እና ከታላቀው መከራ በኋላ በሚሆነው በክርስቶስ መምጣት ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)።

24፥31 **እነዚህ ነገሮች መፈጸማቸውን ስታዩ፤** አንድ አማኝ የምልክቶችን መፈጸም በሚያይበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ መንግሥቱን ለመመሥረት በታላቅ ክብር ዳግመኛ ወደዚህ ምድር የሚመጣበት ጊዜ ቅርብ እንደ ሆነ መናገር ይችላል (ማቴ 24፥33 እና ማብ ይመ)። በሌላ በኩል ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ታማኝ የሆኑትን ክርስቲያኖች ለመውሰድ ባልታወቀና ባልታሰበ ሰዓት የሚገለጥበትን ማለትም እውነተኛ አማኞች ሁሉ የሚነጠቁበትን ጊዜ (ከዮሐ 14፥1-4፤ ከ1ተሰ 4፥13-18 ጋር ያነጻጽሩ) የሚያመለክተው በቍ 34-36 የተጠቀሰው ሐሳብ ሊሆን ይችላል (ማቴ 24፥44 እና ማብ ይመ)።

21፥31 **የእግዚአብሔር መንግሥት እንደቀረበች፤** ማቴ 24፥33 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

21፥32 **ይህ ትውልድ፤** ማቴ 24፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

21፥34 **ያ ቀን ... ድንገት እንዳይደርስባችሁ፤** ኢየሱስ ትንቢታዊ መልእክቱን የሚደመድመው በዓለም ደስታና ኑሮ ጉዳይ ተጠምደው ለዳግም ምጽአቱ ከመዘጋጀት እንዳይዘናጉ ተከታዮቹን በማስጠንቀቅ ነው፤ (1) ይህ ማስጠንቀቂያ ታላቁ መከራ ሊመጣ በተቃረበበት ጊዜ የሚኖሩትን ብቻ ሳይሆን፣ በሁሉም ዘመን የሚኖሩትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ የሚመለከት ነው። ጌታ ኢየሱስ ታማኝ የሆኑትን ክርስቲያኖች ለመውሰድ ድንገት ተመልሶ እንደሚመጣ ካስተማረው ትምህርት አንጻር፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ታማኝ ሆኖ የመገኘቱ ጉዳይ ወሳኝ ነገር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመንጠቅ ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜ በትክክል ስለማይታወቅ፣ አማኞች ሁል ጊዜ ተዘጋጅተው መጠበቅ አለባቸው (ማቴ 24፥40፡42 እና ማብ፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)፤ (2) ክርስቶስ ታማኝ ለሆኑት የሚያደርገው ንጥቀት (1ተሰ 4፥16-17)፣ በመላው ምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ ሊደርስ ካለው (ቍ 35-36 ይመ፤ ከቍ 25-26 ጋር ያነጻጽሩ፤ ከዚያም ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ይመ፤ ራእ 3፥10 እና ማብ ይመ) "ከሚመጣው ቍጣ" ያድነናል (1ተሰ 1፥10)።

21፥36 **ከሚመጣው ሁሉ እንድታመልጡ፤** የክርስቶስ ተከታዮች፣ በእምነትና በጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸንተው ለመቆም ኀይልን ይቀበሉ ዘንድ፣ ኀጢአትን በመቃወምና ለክርስቶስ ያላቸው ፍቅር እያነሰ እንዳይሄድ በመጸለይ ተግተው መጠበቅ አለባቸው። በመጨረሻዎቹ ቀናት በዓለም ላይ ሊደርስ ካለው አስፈሪ ነገር "ማምለጥ" የሚችሉት፣ እንደዚህ ዐይነት ጽናትና ትጋት ካሳዩ ብቻ ነው (1ተሰ 1፥10 እና ማብ፤ ራእ 3፥10 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ ፥ ጽ 39)። በታማኝነት እየጸለዩ ለሚጠብቁት "የማምለጫው" መንገድ መነጠቅ እንደ ሆነ ብዙዎች ያምናሉ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንጥቀት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

22፥1 **ፋሲካ፤** ማቴ 26፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

22፥3 **ሰይጣንም ... የአስቆሮቱ ይሁዳ በተባለው ገባበት፤** ከኢየሱስ ጋር የቅርብ ግንኙነት በነበረው (መዝ 41፥9 ይመ፤ ከዮሐ 13፥18 ጋር ያነጻጽሩ) ነገር ግን ጌታውን አሳልፎ በመስጠት እርሱን በተወው (6፥64 እና ማብ ይመ) በይሁዳ የተፈጸመው አሳዛኝ ታሪክ፣ ክርስቶስን ለሚከተሉ ሁሉ እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ምድር በምንኖርበት ጊዜ ለክርስቶስ ያለን ፍቅር ሊቀዘቅዝ፣ ቀስ በቀስ ለሰይጣን በር በመክፈት ከዓለም ጋር እንድንስማማ ሊያደርገን፣ በመጨረሻም ጌታን ክደን ከእርሱ ዐላማ ውጭ እንድንሆን የሚያደርግ ሁኔታ ሊገጥመን ይችላል።

በተቈጠረው የአስቆሮቱ ይሁዳ በተባለው
ገባበት፤ 4ይሁዳም ወደ ካህናት አለቆችና
ወደ ቤተ መቅደሱ ሹሞች ሄዶ ኢየሱስን
እንዴት አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ተነጋገረ፡
፡ 5እነርሱም በዚህ ደስ ተሰኝተው፣ ገንዘብ
ሊሰጡት ተዋዋሉ። 6እርሱም በነገሩ
ተስማማ፤ አሳልፎ ሊሰጣቸውም ሕዝብ
የማይገኝበትን ምቹ ጊዜ ይጠብቅ ጀመር።

## የመጨረሻው እራት

*22፥7-13 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥17-19፤*
*ማር 14፥12-16*
*22፥17-20 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥26-29*
*ማር 14፥22 —25፥1 ቆሮ 11፥23-25*
*22፥21-23 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥21-24፤*
*ማር 14፥18-21፤ ዮሐ 13፥21-30*
*22፥25-27 ተጓ ምብ — ማቴ 20፥25-28፤*
*ማር 10፥42-45*
*22፥33:34 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥33-35፤*
*ማር 14፥29-31፤ ዮሐ 13፥37:38*

7ከዚህ በኋላ የፋሲካ በግ የሚታረድበት
የቂጣ በዓል ደረሰ። 8ኢየሱስም፣ "የፋሲካን
እራት እንድንበላ ሄዳችሁ አዘጋጁልን" ብሎ
ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላካቸው።
9እነርሱም፣ "የት እንድናሰናዳ
ትፈልጋለህ?" አሉት።
10እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እነሆ፤
ወደ ከተማ ስትገቡ የውሃ እንስራ የተሸከመ
ሰው ያገኛችኋል፤ እርሱ ወደሚገባበት ቤት
ድረስ ተከተሉት፤ 11ለቤቱም ባለቤት፣
'መምህሩ፣ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲካን
እራት የምበላበት የእንግዳ ክፍል ወዴት
ነው? ይልሃል' በሉት። 12እርሱም በሰገነት
ላይ ያለውን ተነጥፎ የተዘጋጀ ሰፊ አዳራሽ
ያሳያችኋል፤ በዚያም አሰናዱልን።"
13እነርሱም ሄደው ልክ ኢየሱስ እንደ
ነገራቸው ሆኖ አገኙት፤ ፋሲካንም በዚያ
አዘጋጁ።
14ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ኢየሱስ ከሐዋር
ያቱ ጋር በማእድ ተቀመጠ፤ 15እንዲህም
አላቸው፤ "መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን
ፋሲካ አብሬያችሁ ለመብላት በጣም
ስመኝ ነበር፤ 16እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር
መንግሥት የዚህ ትርጒም እስኪፈጸም
ድረስ ይህን ፋሲካ ዳግመኛ አልበላም።"
17ጽዋውን ተቀብሎ ካመሰገነ በኋላ
እንዲህ አላቸው፤ "እንካችሁ፤ ሁላችሁ ከዚህ
ተካ ፈሉ፤ 18እላችኋለሁና፤ ከአሁን ጀምሮ
የእግዚአብሔር መንግሥት እስክምትመጣ
ድረስ፣ ከዚህ ወይን ፍሬ አልጠጣም።"
19እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ፤
ቈርሶም ሰጣቸውና፣ "ይህ ስለ እናንተ
የሚሰጥ ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ
አድርጉት" አለ።
20እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን
አንሥቶ እንዲህ አለ፤ "ይህ ጽዋ ስለ እናንተ
በሚፈሰው ደሜ የሚመሠረት አዲስ ኪዳን
ነው። 21ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው
እጅ በማእድ ከእኔ ጋር ናት። 22የሰው ልጅስ
አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ይሄ ዳል፤
ነገር ግን እርሱን አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ
ሰው ወዮለት።" 23እነርሱም ከመካከላቸው
ይህን የሚያደርግ ማን ሊሆን እንደሚ ችል
እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ ጀመር።
24ደግሞም ከመካከላቸው ማን
እንደሚበልጥ በእነርሱ ዘንድ ክርክር

22፥4 ቍ52፤ ሐሥ4፥1፤ 5፥24
22፥5 ዘካ11፥12
22፥7 ዘፀ12፥18-20፤ ዘዳ16፥5-8፤ ማር14፥12
22፥8 ሐሥ3፥1:11፤ 4፥13:19፤ 8፥14
22፥13 ሉቃ19፥52
22፥14 ማቴ26፥20፤ ማር6፥30፤ 14፥17:18
22፥15 ማቴ16፥21
22፥16 ሉቃ14፥15
22፥19 ማቴ14፥19
22፥20 ዘፀ24፥8፤ ኢሳ42፥6፤ ኤ.ፕ31፥31-34፤ ዘካ9፥11፤ 2ቆሮ3፥6፤ ዕብ8፥6፤9፥15
22፥21 መዝ41፥9
22፥22 ማቴ8፥20፤ ሐሥ2፥23፤ 4፥28
22፥24 ማር9፥34፤ ሉቃ9፥46

**22፥18 ይህ ጥቅስ ስለ ጌታ እራት ይናገራል፤** 1ቆሮ 11፥24-25 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**22፥18 ከዚህ ወይን ፍሬ፤** በፋሲካ እራት ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የጠጡት፣ «ጽዋው» ወይም የምስጋና ጽዋ (22፥17፤ ማቴ 26፥27፤ ማር 14፥23፤ 1ቆሮ 10፥16፤ 11፥25) እንደዚሁም «የወይኑ ፍሬ» (22፥18፤ ማቴ 26፥29፤ ማር 14፥25) ተብሎ ይጠራል። በጌታ እራት ጊዜ የቀረበው የወይን ፍሬ ጭማቂ ያልፈላ ነበር የሚለው አስተያየት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የሚደግፈው ነው (በገጽ 1547 ላይ፣ *«የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1»* በሚል ርእስ ላይ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**22፥20 ደሜ … አዲስ ኪዳን፤** ኢየሱስ በእርሱ የመሥዋዕትነት ሞት የተመሠረተውን የአዲስ ኪዳን ሥርዐት መጀመሩን አስታወቀ (ከማቴ 26፥28፤ ከ1ቆሮ 11፥25 ጋር ያነጻጽሩ፤ ኤር 31፥31 እና ማብ ይመ)። አዲሱ ኪዳን ሕጋዊ ሊሆን የሚችለው በክርስቶስ ሞት ብቻ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ዕብ 9፥15-18)።

**22፥20 ስለ እናንተ በሚፈሰው ደሜ፤** ማቴ 26፥28 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**22፥24-30 በዚህ ክፍል ስለ እውነተኛ ታላቅነት ማብራሪያ ተሰጥቶአል፤** እውነተኛ ታላቅነት ከሰው ውስጣዊ መንፈስና ልብ ጋር የተያያዘ ነው፤ ይህም በፍጹም ትሕትና ፍቅሩን ለክርስቶስ በሚገልጽ፣ እግዚአብሔርንና አብረውት ያሉትን በቅንነት ማገልገል በሚፈልግና በዚህ ዓለም ከሁሉም ያነሰ ሆኖ ለመታየት ፈቃደኛ በሆነ ሰው ሕይወት ውስጥ ይታያል (ፊል 2፥3)።

(1) ታላቅነት ሥልጣንን፣ የመሪነት ሥፍራን፣ ተደማጭነትን፣ ዲግሪንና ዝናን ማግኘት ወይም ታላቅን ሥራ ማከናወን መቻል አይደለም። ታላቅነት በምናደርገው ሳይሆን፣ በመንፈስ በእግዚአብሔር ፊት በምንሆነው መሆን የሚገኝ ነው (ቍ 25-27፤ ማቴ 18፥3-4፤ 20፥25-28)።

(2) እውነተኛ ታላቅነት በትክክለኛው ቦታ ትልቅ ሆነን እንድንገኝ የሚጠይቅ ነው። በእምነት፣ በትሕትና፣ በመልካም ባሕርይ፣ በጥበብ፣ ራስን በመግዛት፣ በትዕግሥትና በፍቅር ታላቅ ሆነን ለመገኘት መትጋት አለብን (ገላ 5፥22-23)። ታላቅነት ጽድቅን የወደደው፣ ዐመፃን የጠላው (ዕብ 1፥9) የክርስቶስ ታላቅነት በእኛ ውስጥ የመገኘቱ ጉዳይ ነው።

(3) እውነተኛ ታላቅነት፣ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ መውደድንና ለእርሱም ሙሉ በሙሉ መሰጠትን የሚመለከት ነው፤ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በሚያስቀምጠን ስፍራ ሁሉ ለእርሱ የተቀደሰንና ታማኝ ሆኖ መገኘትን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር በመንግሥቱ ታላቅ የሚባለው ለእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር ያለውና ለተገለጠው ቃሉ ልቡን ሙሉ በሙሉ የሰጠ ሰው ነው (21፥3፤ ሮሜ 12፥1-2)።

(4) መቀደስ በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ፍሬህ የበለጠ እንዲያምር ያደርጋል፤ ይህም የሚሆነው ባስቀመጠህ ስፍራ ስትገኝና በሰጠህ ስጦታ ስታገለግል ብቻ ነው (ሮሜ 12፥3-8፤ 1ቆሮ 12)።

ተነግ። 25ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤
"የአሕዛብ ነገሥታት ሕዝቦቻቸውን
በኀይል ይገዛሉ፤ በእነርሱ ላይ ሥልጣን
ያላቸውም በጎ አድራጊዎች ተብለው
ይጠራሉ። 26በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ
አይሁን፤ ይልቁን ከእናንተ ታላቅ የሆነ
እንደ ታናሽ፣ ገዥ የሆነም እንደ አገልጋይ
ይሁን። 27ለመሆኑ፣ በማእድ ከተቀመጠና
ቆሞ ከሚያስተናግድ ማን ይበልጣል?
በማእድ የተቀመጠው አይደለምን? እኔ
ግን በመካከላችሁ ያለሁት እንደ አንድ
አገልጋይ ነው። 28እናንተም ሳትለዩኝ በመ
ከራዬ ጊዜ በአጠገቤ የቆማችሁ ናችሁ፤
29አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ እኔም ደግሞ
በመንግሥቴ እሾማችኋለሁ፤ 30ይኸውም
በመ ንግሥቴ ከማእዴ እንድትበሉና
እንድት ጠጡ ደግሞም በዙፋን ላይ
ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል
ነገድ ላይ እንድ ትፈርዱ ነው።"
31ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "ስምዖን፣
ስምዖን ሆይ፤ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ
ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ 32እኔ ግን እምነትህ
እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም
በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ።"
33ስምዖንም፣ "ጌታ ሆይ፤ እኔ ከአንተ
ጋር ወህኒ ለመውረድም፣ ለመሞትም ዝግጁ
ነኝ" አለው።
34ኢየሱስም፣ 'ጴጥሮስ ሆይ፤ ዛሬ ዶሮ
ሳይ ጮኽ፣ አላውቀውም ብለህ ሦስት ጊዜ
ትክ ደኛለህ እልሃለሁ" አለው።
35ከዚያም ኢየሱስ፣ "ያለ ኰረጆ፣ ያለ ከረ
ጢትና ያለ ጫማ በላክኋችሁ ጊዜ የጐደለ
ባችሁ ነገር ነበርን? ብሎ ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ "ምንም አልጐደለብንም"
አሉ።
36እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "አሁን
ግን ኰረጆም፣ ከረጢትም ያለው ሰው
ይያዝ፤ ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሽጦ
ይግዛ። 37እላችኋለሁና፤ 'ከዐመፀኞች ጋር
ተቈጠረ' ተብሎ የተጻፈው በእኔ መፈጸም
አለበት፤ ስለ እኔ የተጻፈው ፍጻሜው
በርግጥ ደርሶ አል።"
38ደቀ መዛሙርቱም፣ "ጌታ ሆይ፤ እነሆ፤
ሁለት ሰይፎች እዚህ አሉ" አሉት።
እርሱም፣ "ይበቃል" አላቸው።

22፥26 ማር9፥35፤ 1ጴጥ5፥5
22፥27 ማቴ20፥28
22፥29 ማቴ25፥34፤ 2ጢሞ2፥12
22፥30 ማቴ19፥28፤ ሉቃ14፥15
22፥31 ኢዮ1፥6-12፤ አሞ9፥9
22፥32 ዮሐ17፥9፡15፤ ዮሐ21፥15-17
22፥33 ዮሐ11፥16
22፥35 ማቴ10፥9፡10፤ ሉቃ9፥3፤ 10፥4
22፥37 ኢሳ53፥12
22፥39 ማቴ21፥1፤ ሉቃ21፥37
22፥40 ማቴ6፥13
22፥41 ሉቃ18፥11
22፥42 ማቴ20፥22፤ 26፥39
22፥43 ማቴ4፥11፤ ማር1፥13

## ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ጸለየ

*22፥40-46 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥36-46፤ ማር 14፥32-42*

39ኢየሱስ እንደ ልማዱ ወጥቶ ወደ
ደብረ ዘይት ተራራ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ተከተሉት። 40እዚያም በደረሱ ጊዜ፣
"ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ" አላቸው።
41ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ ያህል ርቆ
ተንበርክኮ ጸለየ፤ 42እንዲህም አለ፤ አባት
ሆይ፤ ፈቃድህ ከሆነ፣ ይህችን ጽዋ ከእኔ
ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን
የአንተ ፈቃድ ይፈጸም።" 43መልአክም
ከሰማይ ተገልጦለት አበረታታው።
44እጅግ ተጨንቆም በብርቱ ይጸልይ
ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ

[a]22፥44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ቍጥር 43 እና 44 የላቸውም

22፥27 **ቆሞ ከሚያስተናግድ፤** በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይመሩ ዘንድ የተመረጡትን በሚመለከት (1ጢሞ 3፥1-7)፣ በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽሙ ዘንድ ሌሎችን በመርዳት፣ የአገልጋይነት መንፈስ ያላቸው መሪዎች ሆነው መምራት እንዳለባቸው ክርስቶስ ተናግሮአል:: ዝናን፣ ሥልጣንን፣ ሀብትን ወይም የተለየ ጥቅምን በመፈለግ የተሰጣቸውን ኀላፊነት ያለአግባብ መጠቀም ወይም ያለቦታው ማዋል የለባቸውም::

22፥28 **በአጠገቤ የቆማችሁ፤** ኢየሱስ በዚህ ምድር እያለ፣ በሕይወቱ ፈታኝ ሁኔታዎች በገጠሙት ጊዜ ለእርሱ ያሳዩትን ታማኝነት በማሰብ፣ ደቀ መዛሙርቱን ያመሰግናል:: የእርሱን ዐላማና የጽድቅ መንገድ በምትቃወም ዓለም ውስጥ ዋነኛ ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው የእርሱን ዐላማ ደግፎ መቆም ነው::

22፥29 **በመንግሥቴ እሾማችኋለሁ፤** ኢየሱስ ታማኝ የሆኑትን ተከታዮቹን በመሠረተው መንግሥት (ቍ 30) ውስጥ ይሾማቸዋል:: በዚህ ዘመን ደቀ መዛሙርቱ ምድራዊ ክብርና ሥልጣን መፈለግ የለባቸውም::

22፥31-32 **ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ፤** ኢየሱስ ጴጥሮስን በሚመለከት የተናገረው ነገር አስፈላጊ የሆኑ ሁለት እውነቶችን ይገልጻል፤ (1) ሰይጣን በእግዚአብሔር ፈቃድና በተወሰነ ደረጃ ይፈትነን ዘንድ እግዚአብሔር ሊፈቅድ ይችላል (ኢዮ 1፥10፡12 እና ማብ ይመ):: ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ሥልጣን የለውም፤ (2) ኢየሱስ የሕዝቡ እምነት እንዳይጠፋ ይጸልያል:: ሰማያዊ አማላጃችን እንደመሆኑና፣ "ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር ለሚመጡት" (ዕብ 7፥25) ሁሉ ይጸልያል:: በፈተናችን ሁሉ መውጫ መንገድ ያዘጋጅልን ዘንድ እግዚአብሔር ታማኝ ነው (1ቆሮ 10፥13):: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ የጸለየው ጸሎት ለመፈጸሙ በሁኔታዎች የሚወሰን ነው፤ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋና የክርስቶስን መማለድ የማይቀበልና የሚነቅፍ ከሆነ፣ ጸሎቱ ውጤት የለውም (19፥41 እና ማብ ይመ)::

22፥36 **ሰይፍ ... ይግዛ፤** እዚህ ላይ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሰይፍ መግዛት እንዳለባቸው ሲናገር፣ የምጸት ቃል መጠቀሙ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የዓለም መንገድ ከመምረጥ ይልቅ የመስቀል ሕይወት እንዲኖሩ አጥብቆ ሲናገራቸው ነበር:: በመቀጠልም ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን መከራና የመስቀል ሞት ለመቀበል ፈቃደኛነቱን ይናገራል (ቍ 37):: በቍ 38 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ፣ ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ነገር ምን ማለት እንደ ሆነ ደቀ መዛሙርቱ እንዳልተረዱ ያመለክታል::

22፥42 **ይህችን ጽዋ፤** ማቴ 26፥39 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

22፥44 **ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ፤** ክርስቶስ ለሰው ቤዛ ይሆን ዘንድ ያለፈባቸውን ዐሥር የሥቃይ ደረጃዎች በሚመለከት ማቴ 26፥37 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

ምድርᵐ ይፈስ ነበር።
45ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
መጣ፤ እነርሱም ከሐዘን የተነሣ ተኝተው
አገኛቸውና፣ 46"ለምን ትተኛላችሁ? ወደ
ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ"
አላቸው።

## ኢየሱስ ተያዘ

*22፥47-53 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥47-56፤ ማር 14፥43-50፤ ዮሐ 18፥3-11*

47እርሱም ገና እየተነጋገረ ሳለ፣ ብዙ
ሰዎች መጡ፤ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ
ይሁዳ የተባለውም ሰው ይመራቸው ነበር፤
ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ተጠጋ። 48ኢየሱስ
ግን፣ "ይሁዳ ሆይ፤ የሰውን ልጅ በመሳም
አሳልፈህ ትሰጣለህን?" አለው።
49በኢየሱስ ዙሪያ የነበሩ ሰዎችም
ሁኔታውን ተመልክተው "ጌታ ሆይ፤ በሰይፍ
እንምታቸውን?" አሉት። 50ከእነርሱም
አንዱ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ
ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው።
51ኢየሱስ ግን፣ "ተው! እዚህ ድረስም
ፍቀዱ" አለ፤ የሰውየውንም ጆሮ ዳሰ
ፈወሰው።
52ከዚያም ኢየሱስ ሊይዙት የመጡትን
የካህናት አለቆች፣ የቤተ መቅደስ ሹሞችና
ሽማግሌዎችን እንዲህ አላቸው፤ "ወንበዴ
እንደሚይዝ ሰው፣ ሰይፍና ቈመጥ ይዛችሁ
ወጣችሁን? 53በየዕለቱ በቤተ መቅደስ
ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ እጃችሁን
አላነሣችሁብኝም፤ ይህ ግን ጨለማ
የነገሠበት ጊዜያችሁ ነው።"

## ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ

*22፥55-62 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥69-75፤ ማር 14፥66-72፤ ዮሐ 18፥16-18፡25-27*

54ከዚህ በኋላ ኢየሱስን ይዘው ወሰዱት፤
ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ አስገቡት፤ ጴጥሮ
ስም በርቀት ይከተለው ነበር። 55ሰዎቹ በሊቀ
ካህናቱ ግቢ ውስጥ እሳት አንድደው በአን
ድነት ተቀምጠው ሳለ፣ ጴጥሮስም ከእነርሱ
ጋር ተቀምጦ ነበር። 56አንዲት የቤት ሠራ
ተኛም ጴጥሮስ እሳቱ አጠገብ ተቀምጦ
አየችውና ትኵር ብላ በመመልከት፣ "ይህ
ሰው ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ" አለች።
57እርሱ ግን፣ "አንቺ ሴት፤ እኔ ሀላውቀ
ውም" ብሎ ካደ።
58ከጥቂት ጊዜ በኋላም አንድ ሌላ ሰው
አይቶት፣ "አንተም ደግሞ ከእነርሱ አንዱ
ነህ" አለው።
ጴጥሮስ ግን፣ "አንተ ሰው፤ እኔ
አይደለሁም" አለ።
59አንድ ሰዓት ያህል ቈይቶም፣ ሌላ ሰው
በርግጠኝነት፣ "ይህ ሰው ገሊላዊ ስለ ሆነ
ያለ ጥርጥር ከእርሱ ጋር ነበረ" አለ።
60ጴጥሮስ ግን፣ "አንተ ሰው፤ የምትለውን
እኔ አላውቅም" አለ፤ ይህንም ተናግሮ ገና
ሳይጨርስ ዶሮ ጮኸ። 61ጌታም መለስ ብሎ
ጴጥሮስን ተመለከተው፤ ጴጥሮስም፣ "ዛሬ
ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ብሎ
ጌታ የተናገረው ቃል ትዝ አለው። 62ጴጥሮ
ስም ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።

## ወታደሮች በኢየሱስ ላይ አፌዙበት

*22፥63-65 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥67፡68፤ ማር 14፥65፤ ዮሐ 18፥22፡23*

63ኢየሱስን አስረው ይጠብቁት የነበሩት
ሰዎችም ያፌዙበትና ይመቱት ጀመር፤
64ዐይኑንም ሸፍነው፣ "እስቲ ትንቢት ተና
ገር፤ የመታህ ማነው? እያሉ ይጠይቁት
ነበር። 65ሌላም ብዙ የስድብ ቃል እየተናገሩ
ያቃልሉት ነበር።

## ኢየሱስ በጲላጦስና በሄሮድስ ፊት

*22፥67-71 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥63-66፤ ማር 14፥61-63፤ ዮሐ 18፥19-21*
*23፥2፡3 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥11-14፤ ማር15፥2-5፤ ዮሐ 18፥29-37*
*23፥18-25 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥15-26፤ ማር 15፥6-15፤ ዮሐ 18፥39—19፥16*

66በነጋም ጊዜ፣ የሕዝብ ሽማግሌዎች፣
የካ ህናት አለቆችና ጸሐፍት ተሰበሰቡ፤
ኢየሱስንም በሸንጎአቸው ፊት አቀረቡት።
67እነርሱም፣ "አንተ ክርስቶስᵒ ነህን? እስቲ
ንገረን" አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ብነግራችሁ
አታምኑኝም፤ 68ብጠይቃችሁም
አትመልሱም። 69ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ
የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ኀይል ቀኝ
ይቀመጣል።"
70በዚህ ጊዜ ሁሉም፣ "ታዲያ፣ አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህን?" አሉት።
እርሱም፣ "መሆኔን እኮ እናንተው
ተናገራችሁት" አላቸው።
71እነርሱም፣ "ከእንግዲህ ሌላ ምስክር
ምን ያስፈልገናል? ራሳችን ከገዛ አንደበቱ

22፥46 ቍ40
22፥49 ቍ38
22፥52 ቍ4
22፥53 ማቴ8፥12፤ 26፥55፤ ዮሐ1፥5፤ 3፥20፤ 12፥27
22፥54 ማቴ26፥57፡58፤ ማር14፥53፡54፤ ዮሐ18፥15
22፥59 ሉቃ23፥6
22፥61 ቍ34፤ ሉቃ7፥13
22፥65 ማቴ16፥21
22፥66 ማቴ5፥22፤ 27፥1፤ ማር15፥1
22፥68 ሉቃ20-8
22፥69 ማር16፥19
22፥70 ማቴ4፥3፤ 27፥11፤ ሉቃ23፥3

ᵒ22፥67 ወይም መሲሕ

22፥54 **ከዚህ በኋላ ኢየሱስን ይዘው፤** ከክርስቶስ መያዝ ጀምሮ እስከ ስቅለቱ ድረስ በቅደም ተከተል የተፈጸሙትን ነገሮች ለመረዳት ማቴ 26፥57 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

22፥62 **ምርር ብሎ አለቀሰ፤** ጴጥሮስ ጌታውን ከመውደድና በእርሱም ከማመን ጨርሶ ወደ ኋላ የማይል ሰው ነበር፤ ስለዚህ በዐመፅ ምክንያት ሳይሆን፣ ከድካም የተነሣ ጌታውን ካደ። ሌሎችን ደቀ መዛሙርት ጨምሮ ጴጥሮስ በዚህን ጊዜ ገና በመንፈስ ቅዱስ ስላልተሞላ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ደካማና ከባድ ፈተና መቋቋም የማይችል ሰው ነበር።

22፥63 **ያፌዙበትና ይመቱት ጀመር፤** ማቴ 26፥67 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

22፥71 **ጲላጦስ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘበት የፋሲካ በዓል ጊዜ ኢየሩሳሌምን ይገዛ የነበረው ሮማዊ ባለሥልጣን ጲላጦስ ነበር። በሮም ሕግ መሠረት፣ አይሁድ በሰው ላይ የሞት ፍርድ መፍረድ ስለማይችሉ፣ ኢየሱስን ይዘው ወደ እርሱ አመጡት። ጲላጦስ፣ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ከእውነትና ከፍትሕ አንጻር ሳይሆን፣ ፖለቲካዊ ጥቅምን ከማስጠበቅ አንጻር ውሳኔና ፍርድ

ሰምተናልና" አሉ።
23 በዚያ የተሰበሰቡት በሙሉ ተነሥ
ተው ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ ወሰ
ዱት፤ 2እንዲህም እያሉ ይከሱት ጀመር፤
"ይህ ሰው ሕዝባችንን ሲያስት፣ ለቄሳር
ግብር እንዳይከፈል ሲከለክል፣ ደግሞም፣
'እኔ ክርስቶስ″ ንጉሥ ነኝ' ሲል አገኘነው።"
3ጲላጦስም፣ "አንተ የአይሁድ ንጉሥ
ነህን?" ብሎ ጠየቀው።
ኢየሱስም፣ "አንተው እልህ" አለው።
4ጲላጦስም ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ፣
"እኔ በዚህ ሰው ላይ ምንም ወንጀል አላገኘ
ሁበትም" አለ።
5እነርሱ ግን፣ "ይህ ሰው ከገሊላ ጀምሮ
እዚህ ድረስ መላውን ይሁዳ ሳይቀር‴ እያ
ወከ ነው" እያሉ አጽንተው ተናገሩ።
6ጲላጦስም ይህን ሲሰማ፣ ሰውየው
የገሊላ ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ጠየቀ፤
7ኢየሱስ ከሄድሮስ ግዛት የመጣ መሆኑን
ጲላጦስ ባወቀ ጊዜ፣ ሄሮድስ በዚያን ወቅት
በኢየሩሳሌም ስለ ነበረ ወደ እርሱ ላከው።
8ሄሮድስም ኢየሱስን ብዙ ጊዜ ሊያየው
ይፈልግ ስለ ነበር፣ ባየው ጊዜ እጅግ
ደስ አለው፤ ስለ እርሱ ሰምቶ ስለ ነበር፣
ታምራት ሲሠራ ለማየት ተስፋ ያደርግ
ነበር። 9ብዙ ጥያቄዎችንም አቀረበለት፤
እርሱ ግን ምንም አልመለሰለትም።
10የካህናት አለቆችና ጸሐፍትም እዚያው
ቆመው በብርቱ ይወነጅሉት ነበር።
11ሄሮድስም ከወታደ ሮቹ ጋር ናቀው፤
አፌዙበትም፤ የክብር ልብስ አልብሶም
ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደ ደው። 12ሄሮድስና
ጲላጦስም በዚሁ ዕለት ተወዳጁ፤ ቀደም ሲል
ግን በመካከላቸው ጥል ነበረ።
13ጲላጦስም የካህናት አለቆችን፣
ገዥዎችንና ሕዝቡን በአንድነት ሰብስቦ፣
14እንዲህ አላቸው፤ "ይህ ሰው ሕዝቡን ለዐመፅ
ያነሣሣል ብላችሁ ወደ እኔ አምጥታችሁት
ነበር፤ እኔም በእናንተው ፊት መርምሬው፣
ባቀረባችሁበት ክስ አንዳች ወንጀል አላገኘ
ሁበትም። 15ደግሞም ሄሮድስ እንዲሁ
ምንም ስላላገኘበት ወደ እኛ መልሶታል፤
እንደምታዩት ይህ ሰው ለሞት የሚያበቃ
ምንም ነገር አልፈጸመም፤ 16ስለዚህ ቀጥቼ
እፈታዋለሁ።" 17ይህን ያለው በበዓሉ አንድ

23፥1 ማቴ27፥2
23፥2 ቍ14፤
ሉቃ20፥22፤
ዮሐ119፥12
23፥4
ቍ14፡22፡41፤
ማቴ27፥23፤
ዮሐ18፥38፤
2ቆሮ5፥21፤
1ጢሞ6፥13
23፥5 ማር1፥14
23፥6 ሉቃ22፥59
23፥7 ማቴ14፥1
23፥8 ሉቃ9፥9
23፥9 ማር14፥61
23፥11
ማር15፥17-19፤
ዮሐ19፥2፡3
23፥12 ሐሥ4፥27
23፥14 ቍ4
23፥16 ቍ22፤
ማቴ27፥26፤
ዮሐ19፥1፤
ሐሥ16፥37፤
2ቆሮ11፥23፡24
23፥18
ሐሥ3፥13፡14
23፥22 ቍ16
23፥26
ማቴ27፥32፤
ማር15፥21፤
ዮሐ19፥17
23፥27 ሉቃ8፥52
23፥28
ሉቃ19፥41-44፤
21፥23፡24
23፥29
ማቴ24፥19
23፥30 ኢሳ2፥19፤
ሆሴ10፥8፤
ራእ6፥16

እስረኛ እንዲፈታላቸው የግድ ያስፈልግ ስለ
ነበረ ነው።′
18ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ላይ፣ "ይህን
ሰው ወዲያ አስወግደው! በርባንን ፍታልን!"
እያሉ ጮኹ፤ 19በርባንም በከተማ ውስጥ
የሕዝብ ዐመፅ በማነሣሣትና በነፍስ ግድያ
የታሰረ ሰው ነበር።
20ጲላጦስም ኢየሱስን ሊፈታው ስለ
ፈለገ፣ እንደ ገና ተናገራቸው፤ 21እነርሱ ግን፣
"ስቀ ለው! ስቀለው!" እያሉ ይጮኹ ነበር።
22ጲላጦስም ሦስተኛ ጊዜ፣ "ለምን? ይህ
ሰው ምን የፈጸመው ወንጀል አለ? እኔ ለሞት
የሚያበቃ ምንም በደል አላገኘሁበትም፤
ስለዚህ ቀጥቼ እፈታዋለሁ" አላቸው።
23እነርሱ ግን ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ
እንዲሰቀል አጥብቀው ለመኑት፤ ጩኸታ
ቸውም በረታ። 24ስለዚህ ጲላጦስ የጠየቁት
እንዲፈጸም ውሳኔ አስተላለፈ። 25የሕዝብ
ዐመፅ በማነሣሣትና በነፍስ ግድያ ታስሮ
የነበረውን፣ እንዲፈታላቸውም የለመኑትን
ያን ሰው ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን እንዳሻ
ቸው እንዲያደርጉት አሳልፎ ሰጣቸው።

## የኢየሱስ መስቀል

*23፥33-43 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥33-44፤ ማር 15፥22-32፤ ዮሐ 19፥17-24*

26ኢየሱስንም ይዘው ሲወስዱት፣ ስምዖን
የተባለውን የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ
አግኝተው መስቀሉን አሸከመው ኢየሱስን
ተከትሎ እንዲሄድ አስገደዱት። 27ብዙ ሕዝ
ብና ደረታቸውን እየደቁ የሚያለቅሱለት
ሴቶችም ከኋላው ይከተሉት ነበር። 28ኢየ
ሱስ ግን ወደ እነርሱ ዞሮ ብሎ እንዲህ
አላቸው፤ "እናንት የኢየሩሳሌም ሴቶች፤
ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ
ለእኔ አታልቅሱ፤ 29እነሆ፤ 'መካኖችና ያል
ወለዱ ማሕፀኖች፣ ያላጠቡ ጡቶችም ብፁ
ዓን ናቸው' የምትሉበት ጊዜ ይመጣልና።
30በዚያን ጊዜም፣
" 'ተራሮችን፣ "ውደቁብን"

*″23፥2 ወይም መሲሕ፤ እንዲሁም ቍ 35 እና 39 ይመ*
*‴23፥5 ወይም በመላው የአይሁድ ምድር*
*′23፥17 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ይህን ቍጥር ይጨምራሉ*

ለሚሰጡ ባለ ሥልጣኖች እንደ ምሳሌ ሆኖ ይጠቀሳል:: አማኞች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ፈጽሞ መደራደር የለባቸውም፤ የግል ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሳይሆን፣ እውነተኛ ለሆነው ነገር ጸንተው መቆም ይገባቸዋል::

23፥3 **አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?** ማቴ 27፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

23፥8-11 **ይህ ክፍል ኢየሱስ በንጉሥ ሄሮድስ ፊት መቅረቡን ያመለክታል፤** ይህ የመጥምቁ ዮሐንስ ራስ እንዲሰየፍ ያደረገው ሄሮድስ ነው:: ሄሮድስ ልቡን እጅግ ያደነደነ በመሆኑ፣ ኢየሱስ ያነጋግረው ዘንድ አልወደደም:: ሄሮድስና አብረውት የነበሩ ሰዎች በቍጣ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን በመናቅ አፌዙበት::

23፥11 **አፌዙበትም፤ የክብር ልብስ አልብሶም፤** ማቴ 27፥28-29 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

23፥14 **ባቀረባችሁበት ክስ አንዳች ወንጀል አላገኘሁበትም፤** ኢየሱስ በሮም መንግሥት ላይ ዐመፅ ያነሣሣል ተብሎ ክስ ቀርቦበት ነበር:: ጲላጦስ ግን ኢየሱስ በሮም መንግሥት ላይ ዐመፅን ከማነሣሣት ወንጀል ንጹሕ እንደ ሆነ አረጋገጠ:: ኢየሱስ መንግሥቱ መንፈሳዊ መንግሥት እንጂ በዚህ ዓለም ያለ ፖለቲካዊ መንግሥት እንዳልሆነ ተናግሮአል (ዮሐ 18፥36):

23፥22 **ቀጥቼ፤** ማቴ 27፥26 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

23፥25 **ኢየሱስን ግን እንዳሻቸው እንዲያደርጉት አሳልፎ ሰጣቸው፤** ጲላጦስ ፖለቲካዊ ጥቅሙን ለማስጠበቅ ሲል ኢየሱስን ለአይሁድ ሕግ አሳልፎ ሰጠው (ቍ 1 እና ማብ ይመ)::

ኰረብቶችንም፣ "ሰውሩን" ይላሉ።'
[31]እንግዲህ በእርጥብ ዕንጨት እንዲህ
ካደረጉ፣ በደረቁ ምን ያደርጉ ይሆን?"
[32]ከእርሱ ጋር እንዲገደሉ ሌሎች ሁለት
ወንጀለኞችን ወሰዱቸው። [33]ቀራንዮ[፩] የተ
ባለ ቦታ በደረሱ ጊዜ ሰቀሉት፤ ወንጀለኞ
ቹንም አንዱን በቀኙ፣ ሌላውን በግራው ሰቀ
ሏቸው። [34]ኢየሱስም፣ "አባት ሆይ፤ የሚያ
ደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"[፪]
አለ። እነርሱም ልብሱን በዕጣ ተከፋፈ
ሉት።
[35]ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር።
ገዦችም፣ "ሌሎችን አዳነ፤ በእግዚአብሔር
የተመረጠው ክርስቶስ እርሱ ከሆነ፣ እስቲ
ራሱን ያድን" እያሉ አፌዙበት።
[36]ወታደሮችም ቀርበው ያፌዙበት ነበር፤
የሆመጠጠ የወይን ጠጅ እየሰጡትም፣
[37]"አንተ የአይሁድ ንጉሥ ከሆንህ፣ ራስህን
አድን" ይሉት ነበር።
[38]ከራሱም በላይ፣ "ይህ የአይሁድ ንጉሥ

23፥31 ሕዝ20፥47
23፥32 ኢሳ53፥12፤ ማቴ27፥38፤ ማር15፥27፤ ዮሐ19፥18
23፥34 መዝ22፥18፤ ማቴ5፥44፤ 11፥25
23፥35 መዝ22፥17፤ ኢሳ42፥1
23፥36 መዝ22፥7፤ 69፥21፤ ማቴ27፥48
23፥37 ሉቃ4፥3፡9
23፥38 ማቴ2፥2
23፥39 ቊ35፡37
23፥41 ቊ4
23፥42 ማቴ16፥27
23፥43 2ቆሮ12፥3፡4፤ ራእ2፥7

ነው" የሚል ጽሑፍ ነበር።
[39]ከተሰቀሉት ወንጀለኞችም አንዱ
የስድብ ናዳ እያወረደበት፣ "አንተ ክርስቶስ
አይደለህምን? እስቲ፣ ራስህንም እኛንም፣
አድን" ይለው ነበር።
[40]ሌላኛው ወንጀለኛ ግን እንዲህ ሲል
ገሥ ጸው፤ "ተመሳሳይ ፍርድ እየተቀበልህ
ሳለህ፣ ከቶ እግዚአብሔርን አትፈራምን? [41]እኛ
ላደረ ግነው ነገር ቅጣት እየተቀበልን ስለ
ሆነ፣ ተገቢ ፍርድ ላይ ነን፤ ይህ ሰው ግን
አንዳች ክፉ ነገር አላደረገም።"
[42]ደግሞም፣ "ኢየሱስ ሆይ፤ በመንግሥ
ትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ"[፫] አለው።
[43]ኢየሱስም፣ "እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ
ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" አለው።

[፩]*23፥33 በግሪክ ቋንቋ የራስ ቅል ማለት ነው፤ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ይባላል*
[፪]*23፥34 አንዳንድ የጥንት ቅጆች፣ ይህ ዐረፍተ ነገር የላቸውም*
[፫]*23፥42 አንዳንድ ቅጆች በንጉሥነት ሥልጣንህ ስትመጣ ይላሉ*

**23፥31 በእርጥብ ዕንጨት ... በደረቁ፤** ንጹሕና እንከን የሌለው ኢየሱስ እንዲህ ከተደረገበት፣ በደለኛ የሆነችው ኢየሩሳሌም ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን?

**23፥33 ቀራንዮ፤** በግሪክ ቋንቋ የራስ ቅል ማለት ነው፤ ኢየሱስን ከከተማው ውጭ ወስደው ሰቀሉት (ከዕብ 13፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ቦታ "የራስ ቅል" ተብሎ ቢጠራም፣ ምክንያቶቹ እስካሁንም አከራካሪዎች ናቸው። በግሪክ "የራስ ቅል" የሚለው ቃል በላቲኑ ቅጂ "ካልቫሪያ" ተብሎአል፤ "ካልቫሪ" የሚለውም የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው ከዚሁ ነው።

**23፥33 ሰቀሉት፤** የኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀልና መሞት፣ በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ዋና እና መሠረታዊ ነገር ነው (1ቆሮ 1፥23-24)። ፈጽሞ ኀጢአት የሌለበት ኢየሱስ በኀጢአተኛ ሰው ፈንታ ሞተ። በእርሱም ስቅለት የኀጢአታችን ዕዳ ተከፈለ፤ የሰይጣንም ሥራ ፈረሰ (ከሮሜ 3፥25 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)። አሁን ሰው ሁሉ በንስሓና በእምነት ወደ እግዚአብሔር በመመለስ፣ ምሕረትንና የዘላለም ሕይወትን ሊቀበል ይችላል።

**23፥34-46 ይህ ክፍል ከክርስቶስ ሰባት የመጨረሻ ንግግሮች ውስጥ ሦስቱን ያካተተ ነው።** ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ከተናገራቸው ሰባት የመጨረሻ ንግግሮች ውስጥ፣ በቍ 34 ላይ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል የሚለው ግምት ከፍተኛ ነው። ሰባቱ የክርስቶስ ንግግሮች ቅደም ተከተል ቀጥሎ እንዳለው ነው፤

(1) ከ3 ሰዓት እስከ እኩለ ቀን ድረስ የተናገረው፤ (ሀ) "አባት ሆይ ... ይቅር በላቸው" የሚለው (ቍ 34) የይቅርታ ቃል፣ (ለ) "ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" የሚለው (ቍ 43) የድነት ቃል፣ (ሐ) "አንቺ ሴት ሆይ፤ ልጅሽ ይኸው ... እናትህ ይህችው" የሚለው (ዮሐ 19፥26-27) የፍቅር ቃል ነው።

(2) ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው የሦስት ሰዓት የጨለማ ጊዜ ኢየሱስ ምን እንደተናገረ የተጻፈ ነገር የለም።

(3) ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ የተናገረው፣ (ሀ) "አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?" የሚለው (ማር 15፥34) መንፈሳዊ ሥቃዩን የሚያመለክት ቃል፣ (ለ) "ተጠማሁ" የሚለው (ዮሐ 19፥28) ሥጋዊ ሥቃዩን የሚያመለክት ቃል፣ (ሐ) "ተፈጸመ" የሚለው (ዮሐ 19፥30) ድል ማድረጉን የሚገልጽ ቃል፣ (መ) "አባት ሆይ፤ መንፈሴን በእጅህ እሰጣለሁ" የሚለው (ቍ 46) ራሱን አሳልፎ መስጠቱን የሚያመለክት ቃል ነው።

**23፥35 ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር፤** የሰውን ልብ ኢግብረገባዊነትና ብልሹነት ከሚያመለክቱት ታጨባጭ ማስረጃዎች አንዱ፣ ሰዎች ዐመፅ ሲካሄድ፣ ደም ሲፈስና ሰው ሲገደል ደስ መሰኘታቸው ነው፤ (1) በሮምና በግሪክ ስፖርት በሚካሄድባቸው ስፍራዎች ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲዋጉና ሲገዳደሉ፣ ተመልካቾች ግን በደስታ ሲጮኹና ሲፈነድቁ ስንመለከት፣ ኢየሱስ አሰቃቂ ሞት ሲሞት ሕዝቡ ቆመው መመልከታቸውን ስናይ (ቍ 35-37)፣ በአማኞች ላይ የደረሰውን የስደት ታሪክ ስንመረምር፣ ከላይ የተቀጠሰው ነገር እውን ሆኖ እናገኘዋለን፤ (2) አሁን ባለው ኅብረተ ሰብ ውስጥ ያሉ በሚሊዮን የሚቈጠሩ ጐልማሶችና ልጆች በቴሌቭዥንና በሌሎችም መገናኛ ብዙኀን በሚተላለፉና የሰውን ሥቃይ፣ ደም መፋሰስን፣ ዐመፅንና ግድያን በሚገልጹ ሁኔታዎች መደሰታቸውና መዝናናታቸው (ሮሜ 1፥32 እና ማብ ይመ) ሌላው ማረጋገጫችን ነው፤ (3) ኢየሱስ የሞተው ይህን አስተሳሰብ ለመለወጥ፣ በሰዎችም ዘንድ ፍቅርና መተሳሰብ እንዲኖር ለማድረግ ነው። ኢየሱስ፣ ኀጢአት በሰው ሕይወት ላይ ያመጣውን አስከፊ ውጤት በርኅራኄ ዐይን እንድንመለከትና የሰውን የሥቃይ ጩኸት ሰምተን ምላሽ እንድንሰጥ ይፈልጋል (13፥16 እና ማብ ይመ)። (4) ለሰው ሥቃይና ሐዘን ስሜት እንዳይኖራቸው ከሚያደርጉ ሁኔታዎች ራሳቸውንና ቤተ ሰቦቻቸውን መጠበቅ የወላጆች ኀላፊነት ነው (ማቴ 18፥6 እና ማብ ይመ)።

**23፥35 አፌዙበት፤** ማቴ 27፥39 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**23፥43 በገነት፤** "ገነት" የሚለው ቃል አገባብ፣ ሰማይን ወይም የእግዚአብሔርን ህልዎት የሚያመለክት ነው፤ "ሰማይ" እና "ገነት" አንድ ዐይነት ቦታን እንደሚያመለክቱ፣ በ2ቆሮ 12፥2፡4 ላይ በግልጽ መረዳት ይቻላል። የጻኑት ከሞት በኋላ ወደ ሰማይ ወደ ኢየሱስ ህልዎት እንደሚሄዱ፣ ኢየሱስ የተናገረው ቃል ያስተምረናል።

## የኢየሱስ መሞት

*23፥44-49 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥45-56፤
ማር 15፥33-41*

44ጊዜው ስድስት ሰዓት ያህል ነበር፤
እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስም በምድር ሁሉ ላይ
ጨለማ ሆነ፤ 45የፀሐይ ብርሃን ተከልክሎአ
ልና። የቤተ መቅደሱም መጋረጃ ተቀዶ
ለሁለት ተከፈለ። 46ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ
ጮኸ፣ "አባት ሆይ፤ መንፈሴን በእጅህ
እሰጣለሁ" አለ፤ ይህንም ብሎ ሞተ።
47የመቶ አለቃውም የሆነውን ነገር ባየ
ጊዜ፣ "ይህ ሰው በርግጥ ጻድቅ ነበር" ብሎ
እግዚአብሔርን አመሰገነ። 48ይህንን ለማየት
በስፍራው ተሰብስበው የነበሩ ሰዎችም ሁሉ
የሆነውን ነገር በተመለከቱ ጊዜ ደረታቸውን
እየደቁ ተመለሱ። 49ነገር ግን ኢየሱስን
በቅርብ የሚያውቁት ሁሉ እንዲሁም
ከገሊላ ጀምሮ የተከተሉት ሴቶች ይህን
እየተመለከቱ ከሩቅ ቆመው ነበር።

## የየኢየሱስ መቀበር

*23፥50-56 ተጓ ምብ — ማቴ27፥57-61፤
ማር 15፥42-47፤ ዮሐ 19፥38-42*

50የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነ፣ አንድ ዮሴፍ
የሚባል በጎና ጻድቅ ሰው ነበር። 51ይህ ሰው
በሸንጎው ምክርና ድርጊት አልተባበረም ነበረ፣
እርሱም አርማትያስ የም ትባል የአይሁድ
ከተማ ሰው ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት
መምጣት ይጠባበቅ ነበር። 52ይህም ሰው
ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው፤
53በተፈቀደለትም ጊዜ፣ ሥጋውን አውርዶ፣
በበፍታ ገነ ዘው፤ ከድንጋይ ተፈልፍሎ
በተሠራና ገና ማንም ባልተቀበረበት
መቃብር ውስጥ አስቀመጠው። 54ዕለቱ
የመዘጋጃ ቀን ነበረ፤ ሰንበትም ሊገባ ነበር።
55ከገሊላ ጀምሮ ከኢየሱስ ጋር የመጡት
ሴቶችም ተከትለው መቃብሩን አዩ፤
ሥጋውንም እንዴት እንዳስቀመጡት
ተመለከቱ። 56ከዚያም ተመልሰው ሽቱና
ቅባት አዘጋጁ፤ ሕጉ በሚያዘው መሠረት
በሰንበት ቀን ዐረፉ።

## የኢየሱስ ትንሣኤ

*24፥1-10 ተጓ ምብ — ማቴ 28፥1-8፤
ማር 16፥1-8፤ ዮሐ 20፥1-8*

24 በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ሴቶቹ
ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው እጅግ
ማለዳ ሳለ ወደ መቃብሩ ሄዱ። 2ድንጋዩም
ከመቃብሩ ደጃፍ ተንከባሎ አገኙት፤ 3ወደ
ውስጥ ዘልቀው በገቡ ጊዜ ግን የጌታ ኢየሱስን
ሥጋ አላገኙም። 4በሁኔታው ግራ ተጋብተው
ሳሉ፣ እነሆ፤ እጅግ የሚያንጸባርቅ ልብስ
የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠገባቸው
ቆሙ። 5ሴቶቹም ከመፍራታቸው የተነሣ
ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፣ ሰዎቹ እንዲህ
አሏቸው፤ "ሕያው የሆነውን እርሱን ለምን
ከሙታን መካከል ትፈልጋላችሁ? 6እርሱ
ተነሥቶአል! እዚህ የለም፤ ደግሞም በገሊላ
በነበረ ጊዜ ምን እንዳላችሁ አስታውሱ፤
7'የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ አልፎ
ሊሰጥ፣ ሊሰቀልና በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ
ይገባል' ብሎ ነበርና።" 8ሴቶቹም በዚህ ጊዜ
ቃሉን አስታወሱ።
9ሴቶቹ ከመቃብሩ ስፍራ ተመልሰው
ይህን ሁሉ ነገር ለዐሥራ አንዱና ለተቀሩት
ሁሉ ነገሯቸው። 10ይህን ለሐዋርያት
የነገሯቸው ፦ መግደላዊት ማርያም፣
ዮሐና፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ከእነርሱ
ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። 11እነርሱ
ግን ሴቶቹ የተናገሩት ቃል መቀባጠር ስለ
መሰላቸው አላመኗቸውም። 12ጴጥሮስ ግን
ተነሥቶ ወደ መቃብሩ ሮጠ፤ እዚያ ደርሶም
ጐንበስ ብሎ ወደ ውስጥ ሲመለከት፣ በፍታው
እንዳለ ለብቻው ተቀምጦ አየ፤ በሆነውም
ነገር እየተገረመ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

23፥44 አሞ8፥9
23፥45 ዘፀ26፥31-33፤ ዕብ9፥3፡8፤ 10፥9፡20
23፥46 መዝ31፥5፤ ማቴ27፥50፤ ዮሐ19፥30፤ 1ጴጥ2፥23
23፥47 ማቴ9፥8
23፥48 ሉቃ18፥13
23፥49 መዝ38፥11፤ ሉቃ8፥2
23፥51 ሉቃ2፥25፡38
23፥54 ማቴ27፥62
23፥55 ቁ40
23፥56 ዘፀ12፥16፤ 20፥10፤ ማር16፥1፤ ሉቃ24፥1
24፥1 ሉቃ23፥56
24፥3 ቁ23፡24
24፥4 ዮሐ20፥12፤
24፥6 ማቴ17፥22፡23፤ ሉቃ9፥22፤ 24፥24
24፥7 ማቴ8፥20፤ 16፥21
24፥8 ዮሐ2፥22
24፥10 ማር6፥30፤ ሉቃ8፥1-3
24፥11 ማር16፥11
24፥12 ዮሐ20፥3-7፡10

**23፥46 አባት ሆይ ... በእጅህ እሰጣለሁ፤** ኢየሱስ በፈቃዱ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ፤ በዚያን ጊዜ በመንፈስ በሰማይ ወዳለው አባቱ ሄደ (*መዝ* 31፥5 *እና ማብ ይመ*)።

**23፥46 መንፈሴን በእጅህ እሰጣለሁ፤** *ማቴ* 27፥50 *እና ማብራሪያውን ይመልከቱ*።

**24፥6 እርሱ ተነሥቶአል፤** ቀጥሎ ያሉት ማስረጃዎች የኢየሱስን ትንሣኤ (*ማቴ* 28፥6 *እና ማብ ይመ*) ያረጋግጣሉ፤ (1) ባዶው መቃብር፤ የኢየሱስ ጠላቶች የእርሱን ሥጋ ወስደውት ቢሆን ኖሮ፣ እንዳልተነሣ ለማረጋገጥ እንዲታይ ያደርጉ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ሥጋ ወስደውት ቢሆን ኖሮ መነሣቱ ውሸት መሆኑን ስለሚያውቁ፣ ሕይወታቸውንና ያላቸውን ነገር ውሸት ለሆነ ነገር መሥዋዕት አድርገው ባልሰጡም ነበር። ባዶው መቃብር ኢየሱስ መነሣቱንና በእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይገልጻል።

(2) የጥንት ቤተ ክርስቲያን መኖር፣ የነበራት ኀይል፣ ደስታና መሰጠት፤ ኢየሱስ ከሞት ባይነሣና ለደቀ መዛሙርቱም ባይታይ ኖሮ፣ ሐዘናቸውና ትካዜአቸው እጅግ ድንቅ ወደ ሆነ ደስታ፣ ድፍረትና ተስፋ ባልተለወጠ ነበር (ቊ 52-53)።

(3) የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ መጻፍ፤ አዲስ ኪዳን የተጻፈው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ላስተማረው እውነትና ጽድቅ ሕይወታቸውን አሳልፈው በሰጡ ሰዎች ነው። የእርሱ አገልግሎት በሞት ያበቃና ከንቱ ሆኖ የቀረ ቢሆን ኖሮ፣ ደቀ መዛሙርቱ ስለ መሲሑና ስለ ትምህርቱ ለመጻፍ ያን ሁሉ መከራ ባልተቀበሉም ነበር (1ቆሮ 15፥12-19)።

(4) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና እርሱንም ተከትሎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታየው ነገር፤ በተግባር በሚታይ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ቀን መውረዱ፣ ኢየሱስ እንደተነሣና በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ እንዳለ የሚያረጋግጥ ነው (ከሐሥ 1፥3-5፤ 2፥33 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ ከሞት ባይነሣ ኖሮ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ የተነገረው ቃል እውን አይሆንም ነበር (ከዮሐ 16፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

(5) ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ሁሉ በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች፣ የኢየሱስን በልባቸው ውስጥ መኖሩንና የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት በሚገባ አይተዋል።

## በኤማሁስ መንገድ ላይ

[13]በዚሁ ቀን ከደቀ መዛሙርት ሁለቱ፣
ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር[ሀ]
ያህል ወደሚርቅ፣ ኤማሁስ ወደሚባል
መንደር ይሄዱ ነበር፤ [14]እነርሱም ስለ ሆነው
ነገር ሁሉ እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር።
[15]እየተነጋገሩና እየተወያዩ ሳሉም ኢየሱስ
ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ጀመር፤ [16]ነገር
ግን እንዳያውቁት ዐይናቸው ተይዞ ነበር።
[17]እርሱም፣ "እየሄዳችሁ፣ መንገድ ላይ
እርስ በርስ እንዲህ የምትወያዩት ምንድን
ነው?" አላቸው።
እነርሱም በሐዘን ክው ብለው ቆሙ።
[18]ከእነርሱም አንዱ፣ ቀለዮጳ የተባለው፣
"በእነዚህ ቀናት እዚህ በኢየሩሳሌም
የሆነውን ነገር የማታውቅ፣ አንተ ብቻ
ለአገሩ እንግዳ ነህን?" ሲል መለሰለት።
[19]እርሱም፣ "የሆነው ነገር ምንድን ነው?"
አላቸው።
እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "በእግዚአብሔርና
በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ
ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፤
[20]እርሱን የካህናት አለቆችና ገዦቻችን
ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሰጡት፤ ሰቀሉትም።
[21]እኛ ግን እስራኤልን ይቤዥል
ብለን ተስፋ ያደረግነው እርሱን ነበር፤
ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተ
ኛው ቀን ነው። [22]ደግሞም ከእኛው መካከል
አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤ እነርሱም
ማልደው ወደ መቃብሩ ሄደው ነበር፤
[23]ሥጋውንም ባጡ ጊዜ መጥተው እርሱ
በሕይወት እንዳለ የነገሯቸውን መላእክት
በራእይ እንዳዩ አወሩልን። [24]ከእኛም
መካከል አንዳንዶች ወደ መቃብሩ ሄደው፣
ልክ ሴቶቹ እንዳሉት ሆኖ አገኙት፤ እርሱን
ግን አላዩትም።"
[25]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ
የማታስተውሉ ሰዎች፣ ልባችሁም ነቢያት
የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ፣
[26]ክርስቶስ[ለ] ይህን መከራ መቀበልና ወደ
ክብሩም መግባት አይገባውምን?" [27]ከሙሴና
ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት
ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው።
[28]ወደሚሄዱበትም መንደር በተቃረቡ
ጊዜ፣ ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ።
[29]እነርሱ ግን፣ "ምሽት እየተቃረበ፣ ቀኑም
እየመሸ ስለ ሆነ ከእኛ ጋር እደር" ብለው

24፥13 ማር16፥12
24፥15 ቍ36
24፥16 ዮሐ20፥14፤ 21፥4
24፥18 ዮሐ19፥25
24፥19 ማቴ21፥11፤ ማር1፥24
24፥20 ሉቃ23፥13
24፥21 ማቴ16፥21፤ ሉቃ1፥68፤ 2፥38፤ 21፥28
24፥22 ቍ1-10
24፥24 ቍ12
24፥26 ዕብ2፥10፤ 1ጴጥ1፥11
24፥27 ዘፍ3፥15፤ ዘኍ21፥9፤ ዘዳ18፥15፤ ኢሳ7፥14፤ 9፥6፤ 40፥10:11:53፤ ሕዝ34፥23፤ ዳን9፥24፤ ሚክ7፥20፤ ሚል3፥1፤ ዮሐ1፥45
24፥30 ማቴ14፥19
24፥31 ቍ16
24፥32 ቍ27:45፤ መዝ39፥3
24፥34 ሉቃ7፥13፤ 1ቆሮ15፥5
24፥35 ቍ30:31
24፥36 ዮሐ20፥19:21፤ 26፤ 14፥27
24፥37 ማር6፥49
24፥39 ዮሐ20፥27፤ 1ዮሐ20፥27፤ 1ዮሐ1፥1
24፥43 ሐሥ10፥41
24፥44 ቍ27፤ መዝ2፥16፤ 22፤ 69፤ 72፤ 110፤ 118፤ ማቴ1፥22፤ 16፥21፤ ሉቃ9፥22:44:45፤ 18፥31-34፤ 22፥37
24፥46 ማቴ16፥21

አጥብቀው ለመኑት፤ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር
ለማደር ገባ።
[30]አብሮአቸውም በማእድ በተቀመጠ
ጊዜ እንጀራውን አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም
ሰጣቸው። [31]በዚህ ጊዜ ዐይናቸው ተከፈተ፤
ዐወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ።
[32]እነርሱም፣ "በመንገድ ሳለን፣ እያነጋገረን
ቅዱሳት መጻሕፍትንም ገልጦ ሲያስረዳን፣
ልባችን እንደ እሳት ይቃጠልብን
አልነበረምን?" ተባባሉ።
[33]በዚያኑም ሰዓት ተነሥተው ወደ
ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ዐሥራ አንዱና
ከእነርሱ ጋር የነበሩትም በዚያ በአንድነት
ተሰብ ስበው አገኟቸው፤ [34]"እነርሱም
ጌታ በእርግጥ ተነሥቶአል! ለስምዖንም
ታይቶአል" ይባባሉ ነበር። [35]ሁለቱ ደቀ
መዛሙርትም በመንገድ ላይ የሆነውንና
ኢየሱስ እንጀራውን በቈረሰ ጊዜ እንዴት
እንዳወቁት ተረ ኩላቸው።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ተገለጠ

[36]ይህን እየተነጋገሩ ሳሉ፣ ኢየሱስ
ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፣ "ሰላም ለእናንተ
ይሁን" አላቸው።
[37]እነርሱ ግን ደንግጠው በፍርሀት
ተዋጡ፤ መንፈስም ያዩ መሰላቸው።
[38]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ለምን
ትጨነቃላችሁ? ለምንስ ጥርጣሬ በልባችሁ
ይገባል? [39]እጆቼንና እግሮቼን ተመልከቱ፤
እኔው ራሴ ነኝ። ደግሞም ንኩኝና እዩ፤
በእኔ እን ደምታዩት መንፈስ ሥጋና ዐጥንት
የለው ምና።"
[40]ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳ
ያቸው። [41]እነርሱም ከመደሰትና ከመገረም
የተነሣ ገና ሳያምኑ፣ "በዚያ ቦታ እን ዳች
የሚበላነገር አላችሁን?"አላቸው። [42]እነርሱም
ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራሽ ሰጡት፤
[43]እርሱም ተቀብሎ በፊታቸው በላ።
[44]እርሱም፣ "ከእናንተ ጋር በነበርሁበት
ጊዜ፣ 'በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙር
መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም
ዘንድ ይገባል' ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ
ነው" አላቸው።
[45]በዚህ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን
እንዲያስተውሉ አእምሮአቸውን
ከፈተላቸው፤ [46]እንዲህም አላቸው፤

*[ሀ]24፥13 ግሪኩ ሥልሳ ምስራፍ ይላል*
*[ለ]24፥26 ወይም መሲሕ እንዲሁም ቍ 46 ይመ*

**24፥15 ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ፤** ከትንሣኤው በኋላ የክርስቶስን መታየት በተመለከተ ማቴ 28፥9 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**24፥19 ነቢይ ... ኢየሱስ፤** የወንጌል ጸሐፊዎች ኢየሱስን የተረዱት ከእግዚአብሔር የተላከ «ነቢይ» እንደ ሆነ ነው (ከዘዳ 18፥15-16:19፤ ከማር 6፥4፤ ከሐሥ 3፥22 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 6፥23 እና ማብ ይመ)::

**24፥27 በቅዱሳት መጻሕፍት ... አስረዳቸው፤** መሲሑ እንዲሁም በመከራ ውስጥ አልፎ የፈጸመው የማዳን ሥራው የብሉይ ኪዳን ማእከላዊና ዋና ሐሳብ ነው:: ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ቀጥሎ ያሉትን ክፍሎች ጠቅሶ ይሆናል፡ ዘፍ 3፥15፣ 22፥18፤ 49፥10፤ ዘኍ 24፥17፤ መዝ 22፥1:18፤ 110፥1፤ ኢሳ 25፥8፤ 52፥14፤ 53፤ ኤር 23፥5፤ ዳን 2፥24:35:44፤ ሚክ 5፥2፤ ዘካ 3፥8፤ 9፥9፤ 13፥7፤ ሚል 3፥1፤ (በገጽ 552 ላይ፣ *«ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**24፥39 መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና፤** በሰማይ ያሉት ቅዱሳን ክቡርና መንፈሳዊ አካል እንዳላቸው ሁሉ (1ቆሮ 15፥40) ኢየሱስም ክቡርና መንፈሳዊ አካል አለው (ፊል 3፥20-21)::

**24፥46 ይህ ጥቅስ የትንሣኤውን አስፈላጊነት ያመለክታል፤** ማቴ 28፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

"'እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ ክርስቶስ
መከራን ይቀበላል፤ በሦተኛውም ቀን
ከሙታን ይነሣል፤ 47ከኢየሩሳሌም ጀምሮ
ለሕዝቦች ሁሉ ንስሐና የኀጢአት ስርየት
ዮሐ በስሙ ይሰበካል፤' 48እናንተም ለዚህ
1፥7 ምስክሮች ናችሁ። 49እኔም አባቴ የሰጠውን
ተስፋ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ
ዮሐ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም
1፥32-33 ከተማ ቈዩ።"

24፥47 ኢሳ2፥3፤ ማቴ28፥19፤ ማር13፥10፤ ሐሥ5፥31፤ 10፥43፤ 13፥38
24፥48 ዮሐ15፥27፤ ሐሥ1፥8፤ 2፥32፤ 4፥20፤ 5፥32፤ 13፥31፤ 1ጴጥ5፥1
24፥49 ዮሐ14፥16፤ ሐሥ1፥4

## የኢየሱስ ዕርገት

50ከዚህ በኋላ እስከ ቢታንያ ይዞአቸው
ወጣ፤ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው። 51እየ
ባረካቸውም ሳለ፣ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ
ሰማይ ዐረገ። 52እነርሱም ሰገዱለት፤ በታላቅ
ደስታም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤
53እግዚአብሔርንም እየመሰገኑ ዘወትር
በቤተ መቅደስ ነበሩ።

24፥50 ማቴ21፥17 24፥51 2ነገ2፥11
24፥53 ሐሥ2፥46

**24፥47 ንስሐና የኀጢአት ስርየት፤** ደቀ መዛሙርቱ ሰዎች ንስሐ መግባት እዳለባቸው ሳይናገሩ፣ ስለ ኀጢአት ስርየት ቢሰብኩ አድራጎቱ ትክክል አይደለም። ልል በሆነ እምነት ላይ ተመሥርተው ድነትን ለሰዎች የሚሰብኩ ወይም ክርስቶስንና ቃሉን በፍጹም ልብ መታዘዝ አስፈላጊ እንደሆነ ሳይገልጹ ድነትን ስለመቀበል ብቻ የሚሰብኩ ካሉ፣ ስብከታቸው የሐሰት ወንጌል ነው። ንስሓ መግባት ኀጢአትን መተው ያካትታል። ይህ በአዲስ ኪዳን እውነተኛ ወንጌል ውስጥ እስከ አሁንም በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው (ማቴ 3፥2 እና ንስሐን በሚመለከት የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ)።

**24፥47 ይሰበካል፤** ታላቁን ተልእኮ በሚመለከት ስለ ተሰጠው አስተያየት ማቴ 28፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**24፥47 ለሕዝቦች ሁሉ፤** ክርስቶስ ይህን ክርስቲያናዊ ተልእኮ ቅዱስ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ልትፈጽመው የሚገባት ሥራና ኀላፊነት አድርጐ መሥርቶታል። ተልእኮ፣ በብሉይ ኪዳን (ዘፍ 22፥18፤ 1ነገ 8፥41-43፤ መዝ 72፥8-11፤ ኢሳ 2፥3፤ 45፥22-25) እና በአዲስ ኪዳን (ማቴ 28፥19፤ ሐሥ 1፥8፤ 28፥28፤ ኤፌ 2፥14-18) በሁለቱም ላይ ዋና ሐሳብ ነው።

**24፥49 አባቴ የሰጠውን ተስፋ፤** "ከላይ ኀይል" እንዲመጣ የሚያደርገው "አባቴ የሰጠው ተስፋ" የሚለው ሐሳብ፣ በበዓለ ኀምሳ ቀን የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ያመለክታል (ሐሥ 1፥4 እና ማብ፤ 2፥4 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም (በገጽ 1664 ላይ፣ *"በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህ ተስፋ በብሉይ ኪዳን (ኢሳ 32፥15፤ 44፥3፤ ሕዝ 39፥29፤ ኢል 2፥28) እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ (ዮሐ 14፥16-17፡26፤ 15፥26፤ 16፥7፤ ሐሥ 1፥4-8፤ 2፥33፡38-39) ተጽፎ እናገኘዋለን። ደቀ መዛሙርት በጸሎት እየተጉ የዚህን ተስፋ መፈጸም ይጠባበቁ ነበር (ሐሥ 1፥14 እና ማብ ይመ)። ዛሬም በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የሚፈልጉ አማኞች እንዲሁ ማድረግ አለባቸው።

**24፥50 ባረካቸው፤** የእግዚአብሔር በረከት በተከታዮቹ ላይ መሆኑ እጅግ አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔርን በረከት በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ብዙ ነገሮች ያስተምረናል።

(1) "በረከት" (በግሪክ "ዩሎጂያ") የሚለው ቃል ትርጕም የሚከተለው ነው፤ (ሀ) ሥራችንን እንድናከናውንና ከግብ እንድናደርስ የሚያደርግ መለኮታዊ ስጦታ (ዘዳ 28፥12)፣ (ለ) የእግዚአብሔር ህልዎት ከእኛ ጋር መሆን (ዘፍ 26፥3)፣ (ሐ) እግዚአብሔር ብርታትን፣ ኀይልንና እርዳታን ለእኛ መስጠቱ (ኤፌ 3፥16፤ ቈላ 1፥11) እንዲሁም (መ) መልካምን ነገር ለማድረግ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥና በእኛ በኩል መሥራቱ (ፊል 2፥13)።

(2) በብሉይ ኪዳን ውስጥ "ከበረከት" ጋር የሚዛመዱ ከአራት መቶ በላይ የሚሆኑ ቃላት ተጠቅሰዋል። የሰውን ልጅ በሚመለከት እግዚአብሔር በመጀመሪያ ያደረገው ነገር እርሱን መባረክ ነው (ዘፍ 1፥28)፤ ደግሞም እግዚአብሔር ሥራውን ቀጣይነት እንዲኖረው ያደረገው በመባረክ ነው (ሕዝ 34፥26)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወትና ታሪክ በረከትና ርግም ያለበት ነው (ዘዳ 11፥26)።

(3) በአዲስ ኪዳን ውስጥ የክርስቶስ አገልግሎት (ሥራ) ሁሉ፣ እግዚአብሔር፣ "ይባርካችሁ ዘንድ አስቀድሞ ወደ እናንተ ላከው" በሚለው (ሐሥ 3፥26) ንግግር ሊጠቃለል ይችላል። በረከቱ ለሕፃናት እንደተሰጠ (ማር 10፥13-16) እንደዚሁም ከእነርሱ ተለይቶ በሚሄድበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይህን በረከት እንደተቀበሉ (ቍ 50-51) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። እንደዚሁም በረከት ከሐዋርያት አገልግሎት ተነጥሎ የማይታይ ነው (ሮሜ 15፥29)።

(4) የእግዚአብሔር በረከት በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመታዘዝ በረከትን ለመቀበል፣ ባለመታዘዝ ደግሞ ለእርግማን ለመዳረግ ምርጫው የእርሱ ነው (ዘዳ 30፥15-18፤ ኤር 17፥5፡7)።

(5) የጌታን በረከት የምንቀበለው እንዴት ነው? በረከቱን ለመቀበል የሚከተሉትን ሦስት ነገሮች ማድረግ ይገባናል፤ (ሀ) በአገልግሎታችን፣ በሥራችንና በቤተ ሰባችን ውስጥ በረከቱን ለማግኘት ሁል ጊዜ ኢየሱስን በተስፋ መጠበቅ አለብን (ዕብ 12፥2)፤ (ለ) በእርሱ ማመን፣ እርሱን መውደድና መታዘዝ አለብን (ከማቴ 5፥3-11፤ 24፥45-46፤ ከራእ 1፥3፤ 16፥15፤ 22፥7 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ሐ) በረከቱን እንዳንቀበል የሚያግድ ማንኛውንም ነገር ከሕይወታችን ማስወገድ ይኖርብናል (ሮሜ 13፥12፤ ኤፌ 4፥22፤ ዕብ 12፥1)።

(6) የእግዚአብሔርን "በረከት"፣ ካለን ምድራዊ ሀብት ወይም በሕይወታችን መከራን ካለመቀበል ጋር አንድ አድርገን ማየት የለብንም (ዕብ 11፥37-39፤ ራእ 2፥8-10 ይመ)።